# ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ

በአስቴር ሙሉ

በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ
ለማግኘት ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት
የቀረበ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር

የካቲት፣ 2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ

በአስቴር ሙሉ

አማካሪ፣
ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር)

በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ
ለማግኘት ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት
የቀረበ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር

የካቲት፣ 2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ

በአስቴር ሙሉ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

________________ ________________

አማካሪ

________________ ________________

ፈታኝ

________________ ________________

ፈታኝ

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........................................................................iv
የቃላት መፍቻ ...............................................................v
የሰንጠረዥ ማውጫ ..........................................................vi
የስዕል ማውጫ ...............................................................vii
ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ (ካርታ) ...........................................viii
ዘጌ ባህረሰላጤ (ካርታ) ..................................................ix
አጠቃሎ ........................................................................x
1.መግቢያ ........................................................................1
1.1 የጥናቱ መነሻ ሃሳብ ......................................................1
1.2 የጥናቱ ዓላማ ...............................................................4
1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት .......................................................4
1.4 የጥናቱ ወሰን ...............................................................5
1.5 የጥናቱ ውስንነት .........................................................5
1.6 የአጠናን ዘዴ ..............................................................6
2. ክለሳ ድርሳን፣የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..........................10
3. ትውራዊ ዳራ .............................................................18
3.1 ቁሳዊ ባህል ምንድን ነው? .........................................18
3.2 የቁሳዊ ባህል ዘርፎች ...............................................20
3.2.1 ሀገረሰባዊ ምህንድስና (Folk architecture) ....................21
3.2.1.1 ባህላዊ ቤቶች .........................................................22
3.2.1.2 ባህላዊ ቤቶች በተገኙበት ቦታ እንዲገኙ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ....23
3.2.1.3 ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ እቃዎች ....................28
3.2.2 ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ (Folk Crafts) ................................30
3.2.2.1 ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች ..........31
3.2.2..2 በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ነገሮች ....32
3.3 የቁሳዊ ባህል ሰሪዎች (የቁሳዊ ባህል ባለሙያዎች) ..............34
3.4 የቁሳዊ ባህል ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ ........................35

3.5 ቁሳዊ ባህልን ለበለጠ ጥቅም ማዋል ........................................37
4. የዘጌ ባህረሰላጤና የማህበረሰቧ አጠቃላይ ገጽታ........................................39
4.1 የዘጌ ባህረ ሰላጤ የመሬት አቀማመጥና የአየር ፀባይና ስያሜ...............39
4.2 የዘጌ ባህረ ሰላጤ ማህበረሰብ ታሪክ ........................................41
4.3 የዘጌ ባህረ ሰላጤ ማህበረሰብ ማህበራዊ ግንኙነት..............................42
4.4 የዘጌ ሰላጤ ማህበረሰብ የኢኮኖሚ ተግባራት........................................44
4.5 የዘጌ ባህረሰላጤ የተፈጥሮ ሃብቶች ........................................46
4.5.1 መሬት ........................................46
4.5.2 ጣና ሃይቅ........................................47
4.5.3 ደን........................................48
5. የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ በዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች ላይ ...............50
5.1 የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች አይነትና ተግባራቸው..........................50
5.2 ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች ........................................60
5.3 የባህላዊ ቤቶች የአሰራር ሂደትና ዘዴ........................................63
5.3.1 ጥሬ እቃ ስብሰባ ........................................63
5.3.2 ድግስ ........................................64
5.3.3 ቁሶችን ለግንባታ ማመቻቸት........................................65
5.3.4 ግድግዳ መገንባት (ማቆም)........................................66
5.3.5 ጣሪያ ማዋቀር ........................................69
5.3.6 ሳር መክደን........................................70
5.3.7 ግድግዳ መምረግ........................................71
5.3.8 ቤት ማስዋብ ........................................72
5.3.9 ቤት ማሰናዳት
(እቃዎችን በቦታቸው ማስቀመጥ) ........................................73
5.4 የዘጌ ባህረ ሰላጤ ቤት ሰሪዎች ........................................74
5.5 የቤት ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃ........................................77
5.6 የዘጌ ባህረ ሰላጤ ባህላዊ ቤቶች በማህበራዊ፣ ባህላዊና
ኢኮኖሚያዊ አውዶች ........................................78
5.7 ከባህላዊ ቤቶች ጋር የተያያዙ እምነቶች፣ትረካዎችና
ስነቃሎች በቤቶች ህልውና ላይ ያላቸው ተፅዕኖ........................................81
5.8 በዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች ላይ ተፅዕኖ ያደረጉ ነገሮች ...............84
5.9.ባህላዊ ቤቶችን እንዴት ለበለጠ ጥቅም ማዋል ይቻላል ?.....................88
6. የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ በዘጌ ባህረሰላጤ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች..........90

6.1 የሸክላ ቁሳቁስ ዓይነቶችና ተግባራቸው ....................................96

6.2 በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሸክላ ቁሶች መስሪያ

ጥሬ ዕቃና መገኛው....................................................111

6.3 የሸክላ ቁሶች አሰራር ..................................................113

6.3.1 የሸክላ አፈርን መቆፈርና ለመስራት ማዘጋጀት ...... ........113

6.3.2 የሸክላ ቁሶች ቅርጽ እንዲይዙ ማድረግ.............................114

6.3.3 የሸክላ ቁሶችን ማስጌጥ................................................120

6.3.4 የሸክላ ቁሶችን ማድረቅና ማቃጠል ..................................121

6.4 የሸክላ ስራ ባለሙያዎች .................................................124

6.5 የሸክላ ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃ.........................................127

6.6 ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በማህበራዊ፣ ባህላዊና

ኢኮኖሚያዊ አውዶች ......................................................131

6.7 ከሸክላ ስራና ስራተኞች ጋር የተያያዙ እምነቶችና አመለካከቶች.... 135

6.8 በሸክላ ቁሶችና በሸክላ ስራ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች............137

6.9. የሸክላ ቁሶችን እንዴት ለበለጠ ጥቅም ማዋል ይቻላል ?...............139

7. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ...................................141

7.1 ማጠቃለያና መደምደሚያ ..................................................141

7.2 አስተያየት ......................................................................144

ዋቢዎች..............................................................................146

አባሪ 1፣ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች...............................150

አባሪ 2. የመረጃ አቀባዮች

ዝርዝር መግለጫ ..........................................................151

አባሪ 3. ፎቶዎች................................................................157

# ምስጋና

በመጀመሪያ አማካሪዬን ዶር.ፈቃደ አዘዘን አመሰግናለሁ፡፡

በመቀጠል በዚህ የትምህርት መርሃ ክፍል እንድሳተፍ ለላከኝ ብሎም ስማር የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ያለኝ ምስጋና ከፍተኛ ነው፡፡ በመርሃ ግብሩ እንድማር እድሉን የሰጠኝን እንዲሁም ለጥናታዊ ጽሁፉ ማካሄጃ መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲንም አመሰግናለሁ፡፡

በመስክ ቆይታዬ መረጃ በመስጠት ጥናቱ እንዲሳካ ቀና ትብብር ያደረጉልኝን በአባሪው ክፍል ስማቸው የተጠቀሰውን መረጃ አቀባዮቼን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ለጥናታዊ ጽሁፉ አርትኦት (ኤዲቲንግ) ስራ እንድጠቀምበት «ላፕቶፕ» ኮምፒውተር በማዋስ የተባበረችኝን ሰብለ ትርፌን አመሰግናለሁ፡፡

ይህንን ጥናት በማደርግበት ጊዜ ከጎኔ ሆነው ሲያበረታቱኝ የነበሩትንና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን አቅማቸው በፈቀደ መጠን የረዱኝን ቤተሰቦቼን፣ቀናህ ምክራቸውን ይለግሱኝ የነበሩ መምህሮቼንና ጓደኞቼን ምን ብዬ ባመሰግናቸው የልቤ ይደርስ ይሆን?

# የቃላት መፍቻ

መረቀ - አመሰገነ
መንፈቅ - ስድስት ወር
ሙግድ - አክንባሎ
ማውገዝ - መርገም
ማዱጋ - እንስራ
ምዕመናን - የቤተክርስቲያን አባላት
ሰበዝ - ለስፌት መስሪያ የሚያገለግል የሳር ዘር
ሰደቃ - የቡና ስኒ ማቅረቢያ ( ረከቦት)
ቁንጮ - ጫፍ
ቅንቡርስ - ጣሪያ ላይ የለበሰን ሳር የሚበላ የትል አይነት
ቆረንጮ - ቆዳ
ባህረሰላጤ - ሾጠጥ ብሎ ወደ ባህር አካል መካከል የተዘረጋ መሬት
ባጥ - ጣሪያ
ቦሀሮ - መጠኑ ተለቅ ያለ የሎሚ ዘር
ተርቲም - በዙር የሚደርስ የቡና ማህበር
ተቆረቆረ - የሰውን ስራ ልክ እንደራሱ አድርጎ ሰራ
ታንኳ - ከደንገል የሚሰራ የውሃ ላይ መንኅገር
ትዝቢ - የማይመስል ግን የሆነ( አስገራሚ )
ችሃል - መሬት ላይ የሚተከል ምልክት
አላቆጠ - አጨማለቀ
አሰናዳ - አስተካከለ
አበልጅ - አንዱ የሌላውን ሰው ልጅ ክርስትና በማንሳቱ ምክንያት በመካከላቸው የሚፈጠር የዝምድና አይነት
አንዱር - ፈሳሹ የሚቀዳበት የጀበና አካል
አዘቦት - የስራ ቀን
ወንፈል - ብድር
የአባት ነው - ከዘር የተወረሰ ነው
ደበል አንሳ - ማህበረሰቡ ለእጅ ስራ ባለሙያዎች በተለይም ለቆዳ ስራ ባለሙያዎች የሰጣቸው ነቃፊ ስም
ዳስ - እንደ አጣና ጨፈቃና ሳር ባሉ ነገሮች የሚሰራ ጊዜያዊ መጠለያ
ድግስ - ለግብገቦ የሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ
ጂኒ - ውሃ ውስጥ ይኖራል ተብሎ የሚታመን ርኩስ መንፈስ
ጀበና - ጀበና
ገል - የሸክላ እቃ ስባሪ
ገበያ መዋል ያዘ - ለገበያ ቀረበ
ጉባ - የቡና ጀንፈል
ግራምጣ - ለስፌት መስሪያ የሚውል የሳር ዘር
ጥሪት - ለረጅም ጊዜ የተጠራቀመ ሃብት
ፍንጃል - ስኒ


## የሠንጠረዥ ማውጫ


ሠንጠረዥ 1. የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች አማካይ መጠን....................................59
ሠንጠረዥ 2. የሸክላ ቁሶች አማካይ መጠን....................................................110
ሠንጠረዥ 3. ሸክላ ሰሪዎች የሚኖሩባቸው ጎጦችና አፈር ለማግኘት
የሚጓዙት ሰዓት...................................................................................112

# የሥዕል ማውጫ


ገጽ

ሥዕል 1. እሳተከላ ቤት ............................................................51
ሥዕል 2 ደርብና ምድር ቤት ..................................................55
ሥዕል 3 ክፍክፍ ጎጆ ቤት..........................................................58
ሥዕል 4 አልባሶ ጎጆ ቤት ........................................................59
ሥዕል 5 ድስት ......................................................................97
ሥዕል 6 ወጨ.ትና ክዳኑ ...........................................................99
ሥዕል 7 ትዝቢ. በተጋፍቼ ላይ ተቀምጦ..................................101
ሥዕል 8 የማዲጋ ዘሮች..........................................................102
ሥዕል 9 ገንቦ ....................................................................102
ሥዕል 10 ጎራሽ...................................................................103
ሥዕል 11 ጀበና...................................................................106
ሥዕል 12 (የእጣን) ማጤሻ...................................................107
ሥዕል 13 ( የከሰል) ምድጃ ....................................................108
ሥዕል 14 ምጣድ.................................................................108
ሥዕል 15 ቤተ ሞገስ............................................................. 119


N
E
S
BAHIR DAR ZURIA WOREDA
BY KEBELE
Dike Deset
Lijomi
Sikelit Duri Banita
Yiganda Mahal
Aura K/Mihiret
Lata Amiba
Wenjata
Zege Town
Robit Bata
Yigodi Tintila
Dihna Misinta
Zinzilima
Wigelisana Niche Dini
Weramit
Bhir Dar Town
Chenita Sositu
Yibabina Chinchir
Werib Kota Slewan
Yimishet
Dishit Abaraji
Sibatamit
Yigoma Hulitu
Windata
Maji Dibre Nigst
Meshenti Town
Mishenit Werkimila
Yisala Dir Dir
Kimibaba
Yigind Lomi
Makol Kifilom
Fires Woga
Ginb Sositu
Scale:- 1:300000
Source: GIS Team of ANRS BoFED




Source: Rahel Mesfin (1999) MA Thesis

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የቁሳዊ ባህል ጥናት ነው፡፡ ዋና አላማ አድርጎ የተነሣው በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ከባህር ዳር ከተማ በስተሰሜን በየብስ 30፣በባህር ትራንስፖርት ደግሞ 11 ኪ.ሜ. ርቃ በምትገኝ ዘጌ በተባለች ባህረ ሰላጤ(Peninsula) ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችንና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በሳይንሳዊ አጠናን መንገድ መግለጽ ፣መቅረጽናመሰነድና እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ህልውናቸው ፈጽሞ ከመጥፋት ተቆጥቦ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚያበረክቱበትን መንገድ መጠቆም ሲሆን ከዚህ ዋና አላማ ስር ጥናቱ የሚመልሳቸው ስምንት ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡

የጥናቱ አላማ ግቡን እንዲመታና በጥናቱ የተነሱ ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ሲባል ከቤተመጽሃፍት፣ከመረጃ መረብ (internet) እና ከመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በመስክ ስራ ከቤት ባለቤቶች፣ከቤትሰሪዎች፣ከሸክላስራ ባለሙያዎች ፣ከተጠቃሚዎችና ከተለያዩ ዕውቀቱ ካላቸው የሰላጤዋ ነዋሪዎች በቪዲዮና በፎቶ ካሜራ እንዲሁም በቴፕሪከርደር ታግዘው መረጃዎች በምልከታና በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ ሲሆን የተገኙ መረጃዎች በሚገባ ከተመረመሩ በኋላ ባህላዊ ቤቶች፣ማህበረሰቡ ቅርጽን ተከትሎ በሰጣቸው ስያሜ መሰረት፣ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ደግሞ በተግባራቸው ተመድበው የመስክ መረጃዎች ከትውራዊ ዳራዎች ጋር እየተገናዘቡ ተተንትነዋል፡፡

ከትንተናውም የዘጌ ባህረሰላጤ ማህበረሰብ በባህላዊ ቤቶቹና ከሸክላ በተሰሩ የቤት ቁሶች አማካይነት ኪነቱን፣ ዕውቀቱን ፣አሰተሳሰቡን ፣እምነቱንና ፍልስፍናውን ሲገልፅ የቆየ ቢሆንም አሁን ግን እነዚህ ቁሳዊ ሃብቶቹ በማህበረሰቡ አመለካከትና ሃገረሰባዊ እምነት፣ በደን ሃብት መጨፍጨፍና በኢንዱስትሪ አብዮት የተነሳ ህልውናቸው በመውደም ላይ ነው ከሚል ውጤት ላይ ተደርሷል፡፡

ይህን የጥናት ውጤት መሠረት በማድረግ አንድን ማህበረሰብ ካለበት ችግር ለማላቀቅም ሆነ ኑሮው እንዲሻሻል የተለያዩ ክፍሎች ትብብር አስፈላጊ ነውና የአማራ ክልል መንግስት፣የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ፣የቅርስና ባህል ጥበቃ ቢሮ፣የቤቶች ባለቤቶችና የሸክላ ስራ ባለሙያዎች፣የሰላጤዋ ነዋሪዎች፣ወጣቶችና የተማሩ የማህበረሰቡ ተወላጆች በየደረጃቸው የባህላዊ ቤቶችንና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን ህልውና ለመጠበቅ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ማድረግ ይገባቸዋል የሚል አስተያየት በመስጠት ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

# 1. መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ «ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረሰላጤ» በሚል ርዕስ የተደረገው ጥናት የተካሄደባቸውን ምክንያቶች የሚገልፁ፣የጥናቱን አካሄድ የሚጠቁሙና የጥናቱን ዓላማ ለአንባቢ ግልፅ የሚያደርጉ ሃሳቦች የቀረቡ ሲሆን ምዕራፉ፤የጥናቱ መነሻ ሃሳብ፣የጥናቱዓላማ፣የጥናቱ አስፈላጊነት፣የጥናቱ ወሰን ፣የጥናቱ ውስንነትና የቃላት መፍቻ የሚሉ ርዕሶችን ይዟል፡፡

## 1.1 የጥናቱ መነሻ ሃሳብ

ዘጌ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የምትገኝ ስፍራ ናት፡፡ ከባህር ዳር ወደ ዘጌ በጀልባና በመኪና መጓዝ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከባህር ዳር ወደ ዘጌ ለመድረስ በጀልባ የአንድ ሰዓት ተኩል፣ በመኪና ደግሞ የሁለት ሰዓት ጉዞ ነው፡፡

ዘጌ አያሌ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች የሚገኙባት ቦታ ናት፡፡ መሃልዘጌ ጊዮርጊስ፣ አቡነ በትረማርያም፣አዘዋ ማርያም፣ ስላሴ፣ ይጋንዳ ተክለሃይማኖት፣ ፉሬ ማርያም፣ ዑራ ኪዳነምህረት የተባሉ ከ14ኛው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ እስከ 17ኛው ምዕተ አመት ድረስ የታነፁ ሰባት አብያተ ክርስትያናትና ገዳማት በዘጌ ባህረሰላጤ ይገኛሉ፡፡ በእያንዳንዱ ገዳምም ረጅም ዕድሜ ያላቸው ንዋየ ቅድሳት፣ የብራና መፃህፍትና መዛግብት፣ የነገስታት አልባሳት፣ ዘውዶች፣ ጌጣጌጦች፣ የገበታና የግድግዳ ላይ ቅቦች /ስዕሎች/ ባህላዊ የጦር መሳሪዎች /ጋሻ፣ ጦር፣ ጎራዴ/ ወዘተ ይገኛሉ፡፡

ሰባቱ ጥንታዊ ገዳማትና በእነርሱም ውስጥ የሚገኙ አያሌ የኪነጥበብ ቅርሶችና የመገልገያ ቁሶች ስለመንፈሳዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ጥበባዊ ፋይዳቸው የአያሌ ጎብኝዎችን ቀልብ (ስሜት) ይስባሉ፡፡ ስለዚህም በየጊዜው ብዙ ሺህ የኦርቶዶክስ ክርስትና ዕምነት ተከታዮች ወደ ገዳማቱ መንፈሳዊ ጉዞ (Pilgrimage) ያካሂዳሉ፡፡ ቁጥራቸው እጅግ በርካታ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና የውጭ ሃገር ሰዎችም በቡድንና በግል ጥንታዊ የታሪክ፣ የባህልና የኪነጥበብ ቅርሶችን ለማየት ወደ ገዳማቱ እንደሚመጡ አካባቢውን ለረጅም ጊዜ የሚያውቁ ሰዎች ይናገራሉ (ወጋየሁ ፣1996[1])፡፡ የዘጌ ባህረ ሰላጤና በውስጡ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶች የመንፈሳዊ ተጓዦችንና ጎብኝዎችን ስሜትና ፍላጎት የመማረካቸውን ያህል የባህልና የፎክሎር ተመራማሪዎችን ስሜትና ትኩረት አግኝተዋል ለማለት የሚያስደፍሩ መረጃዎች የሉም፡፡ ስለዚህም በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙት

---

[1]. በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የተጠቀሱ ዓመተ ምህረቶች የፀሃፊዎች ስም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈ ከሆነ እንደ አውሮፓውያን፣ የፀሃፊዎች ስም በአማርኛ የተፃፉ ከሆነ ደግሞ በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

ቅርሶችና ያሉ መረጃዎች ከቁሳዊ ባህል አንፃር፣ በሳይንሳዊ አጠናን ዘዴ አልተሰበሰቡም፣ አልተተነተኑም::

ቁሳዊ ባህል ከአራቱ የፎክሎር ጥናት መስኮች አንዱ ነውDorson (1972)፣ ፈቃደ (1991):: ቁሳዊ ባህል ከቅድመ ታሪክ ዘመን እስከ ዘመናዊው ዘመን የሰው ልጅ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሰራቸውን በአይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ በአንድ ስፍራ የተተከሉና ከስፍራ ወደ ስፍራ ሊዘዋወሩ የሚችሉ ቁሶችን የሚጠቀልል እሳቤ (Concept) ነው:: Ralf and Harry (1959, 229) የቁሳዊ ባህልን ምንነት ሲገልጹ:- «ቁሳዊ ባህል ባጠቃላይ የእጅ ጥበብ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚመለከት ነው:: እነዚህ እደ-ጥበቦች መገልገያ መሳሪያዎችንና መያዣዎችን፣ የምግብ ዝግጅቶችን፣ከደሳሳ ጎጆ እስከ ከፍተኛ ቤተ መቅደስ ያሉ መጠለያዎችን፣ አልባሳትንና ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን ማንኛ ውንም ቁሳቁሶች የሚያጠቃልል ነው» ይላሉ::

ከፍ ብለን በተመለከትነውና በሌሎችም (ለምሳሌ ፈቃደ (1991)) ብያኔዎች በተካተቱት ሀሳቦች መሰረት ቁሳዊ ባህል፣ በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙትን ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም በውስጣቸው ያከማቹዋቸውን ቀለም ቅቦች፣ ጥንታዊ የወግ ዕቃዎችና አልባሳት የጦር መሳሪዎችና የብራና መፃህፍት ወዘተ ጠቅልሎ ሊገልጽ የሚችል ስያሜ (Terminology) ነው ማለት እንችላለን:: በሌላ አገላለፅ የዘጌ ባህረ ሰላጤ የአያሌ ባህላዊ ቁሶች/ ቁሳዊ ባህሎች ቤተ መዘክር ወይም ሙዚየም ነው ማለት ይቻላል::

ቁሳዊ ባህል በዓይነታቸው ልዩ ልዩ የሆኑ አያሌ ነገሮችን የሚያጠቃልል በመሆኑ በአንድ አነስተኛ ጥናት ውስጥ የአንድን ማህበረሰብ ይዞታዎች ሙሉ ለሙሉ መርምሮ መግለፅ አይቻልም:: ስለዚህም ትኩረትን በጥቂትና የተወሰኑ የቁሳዊ ባህል ገፅታዎች ላይ ማሳረፍ የተሻለ ይሆናል ብዬ አምናለሁ:: በዘጌ ባህረ ሰላጤ ከሚገኙት አያሌ ቅርሶች መካከል ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ይገኙበታል:: እነዚህን ቁሳዊ ባህሎች ማጥናት ደግሞ የማህበረሰቡን ማንነት አውቆ እንዴት ኑሮውን ሊያሻሽል እንደሚችል ለመጠቆም ያስችላል የሚለው የዚህ ጥናት ባለቤት እምነት ነው:: በመሆኑም በሚከተሉት ምክንያቶች አነሳሽነት ጥናቱ ተካሂዷል::

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት በፎክሎር ዘርፍ በቁሳዊ ባህል ላይ ነው:: ፈቃደ (1991) እንደሚገልፁት በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል በፎክሎር ዘርፍ ከተሰሩ ጥናቶች ውስጥ ብዙዎቹ በስነ ቃል ላይ የተሰሩ ሲሆን በቁሳዊ ባህል ላይ የተሰሩት ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ ነው:: ይህ እውነት ደግሞ በቁሳዊ ባህል ጥናት ዙሪያ ያለውን ክፍተት ከመሙላት አንፃር የዚህን ጥናት ትኩረት በቁሳዊ ባህል ላይ እንዲያርፍ አድርጎታል:: ከዚህ ውጭ ለጥናት የመረጥኩት ቦታ ዘጌ (ባህረሰላጤ)ን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ለጉብኝት ሄጄ በነበረበት በ1998ዓ.ም ነው:: በዚህ ጉብኝት

ወቅትም ቀደም ብዬ ስለቁሳዊ ባህል ምንነትና ጠቀሜታ ከትምህርቴ ያገኘሁት ግንዛቤ በመኖሩ በዘጌ ባህረ ሰላጤ የተመለከትኳቸው ባህላዊ ቁሶች ከፎክሎር አንፃር ቢጠኑ ምን ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ በአእምሮዬ አደረ:: በተለይ ደግሞ በጉብኝቴ ጊዜ በሰላጤው ውስጥ የሚገኙ ለየት ያሉ ባህላዊ ቤቶች እንዳሉና አሁን ግን ህልውናቸው አደጋ ላይ መሆኑን በአጋጣሚ መስማቴ ቤቶች ፈርሰው ከመጥፋታቸው በፊት ተሽቀዳድሞ መቅረስ የግድ አስፈላጊ ነው ብዬ እንዳምን አደረገኝ:: የማህበረሰቡ መግባቢያ ቋንቋ አማርኛ መሆኑ ደግሞ በመረጃ መሰብሰብ ሂደት ብዙ እንቅፋት እንደማይገጥመኝ ስለገመትኩ በፎክሎርና ስነ ፅሁፍ ዘርፍ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚከናወነውን መለስተኛ ጥናት በዘጌ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ ባህላዊ የቤት ቁሶች ላይ ለማካሄድ ወሰንኩ:: የቤት አሰራር፣ የሃገረሰባዊ ምህንድስና፣ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ደግሞ የሃገረሰባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች ናቸው:: እነዚህም ጠቅለል ተደርገው በቁሳዊ ባህል ስር ይታያሉ:: ይህንን ሃሳብ Dorson (1972፣ 282) «ማንኛውም ሃገረሰባዊ ምህንድስና ቅርፅን፣ መጠንንና አይነትን ማለትም መኖሪያ ቤቶችን፣ የእቃ መሸጫ ሱቆችን፣ ታላላቅ ቤተ መቅደሶችን፣ ሐውልቶችን፣ በረቶችን፣ አጥሮችን፣ ጎተራዎችንና መቃብሮችን አካቶ ይይዛል» በማለት ይገልፁታል:: ባህላዊ ምህንድስና ደግሞ እንደማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በየዘመኑ የቴክኖሎጂን ዕድገት ተከትለው ወደ አንድ ህብረተሰብ በሚገቡ የአዳዲስ ቁሶች አሰራር መንገዶች ተፅዕኖ ይደርስበታል:: ይህ ከሆነ ደግሞ ቀደም ሲል የተሰሩት ቤቶች ፈርሰው ከመጥፋቸው በፊት ተሽቀዳድሞ መቅረስ አስፈላጊ ነው ብዬ በማመኔ ጥናቱን እንድጀምር ከገፋፉኝ ምክንያቶች ቀዳሚው ነው:: ከሸክላ የተሰሩ ባህላዊ የቤት ቁሶችን ማጥናት ያስፈለገበት ምክንያት ግን ባህላዊ ቤቶች ሲነሱ ባህላዊ የሆኑ የቤት ቁሶችም ቢነሱ መልካም ነው ከሚል ሀሳብ የመነጨ ሲሆን ነገር ግን ባህላዊ የቤት እቃዎችን ለማጥናት በተከናወነው የመስክ ስራ ወቅት በሰላጤዋ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ የቤት እቃዎች ከሸክላ እቃዎች በስተቀር እክሌ የተባለ ሰሪ የሌላቸው ከመሆኑ ባሻገር አብዛኞቹ ባለቤቶቻቸው ከወላጆቻቸውና ከአያቶቻቸው የወረሷቸው አሁን ግን የማይሰሩ በመሆናቸው ባለቤቶቻቸው ስለ እቃዎች አሰራርም ሆነ ታሪክ የሚሰጡት በቂ መረጃ እንደሌለና የተገኘው መረጃ ደግሞ ይህንን የቁሳዊ ባህል ጥናት የተሟላ ሊያደርገው እንደማይችል ስለተረጋገጠና በሌላ በኩል ደግሞ አሁን በመሰራት ላይ ያልሆኑ ቁሶችን ማጥናቱ ምናልባት ፎክሎርን ካረጀ ነገር ጋር ብቻ የሚያያይዝን ሃሳብ የሚያንፀባርቅ እንዳይሆን ስለተሰጋ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የግድ ከአሮጌና የጥንት እቃዎች ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች አይደሉምና (Dorson (1972፣ 234), Oring (1986፣ 216):: ጥናቱ ከባህላዊ ቤቶች በተጨማሪ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በሰላጤዋ ውስጥ እየተሰሩ ያሉትንና ታሪካቸውን ከተጠቃሚዎች እንዲሁም ከሰሪዎች አንፃር ሊጠና የሚችሉትን ስለ አሰራር ሂደታቸውም በፎቶግራፍና በቪዲዮ የተደገፈ መረጃ

ሊሰበሰብባቸው በሚችሉት፣ በአጠቃላይ «የተሟላ» መረጃ ሊገኝባቸው በሚችሉት ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ላይ ትኩረቱን አድርጓል።

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችንና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በሳይንሳዊ አጠናን መንገድ ከመግለፅ፣ ከመቅረስና ከመሰነድ በተጨማሪ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚያበረክቱበትን መንገድ መጠቆም ነው።

በመሆኑም ጥናቱ፡-

1. የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች አይነታቸውና አገልግሎታቸው ምን ይመስላል?
2. በዘጌ ባህረሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች አሰራር ምን ምን ገፅታዎች አሏቸው?
3 በዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ የሚገኙ ቤቶች ከሃገረሰባዊ ምህንድስና አንፃር ምን ልዩ ሁኔታ ይታይባቸዋል?
4. ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች የማህበረሰቡን ባህላዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገፅታ ምን ያህል ያንፀባርቃሉ?
5. በዘጌ ባህረ ሰላጤ በባህላዊ ቤቶችና በሸክላ ስራ ባለቤትነት ተለይተው የሚታወቁ ወገኖች አሉ? ካሉ በየትኛው ማህበራዊ ደረጃ (Social status) ይመደባሉ? የማህበረሰቡ አባላትስ ለእነዚህ ወገኖች ምን አመለካከት አለው?
6. ከቤት አሰራር ዲዛይን እንዲሁም ከሸክላ ቁሶችና ማምረቻ መሳሪያዎች ጋር የተሳሰሩ እምነቶች ትረካዎችና አመለካከቶች አሉ? ካሉስ በቤቶችና የቤት ቁሶች ህልውና ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ምንድን ነው?
7. በባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ህልውና ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ ነገሮች አሉ ወይ? ካሉስ እንደምን ይገለፃሉ?
8. ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በምን መንገድ አሁን ካሉበት የተሻለ ለማህበረሰቡ ጥቅም ሊሰጡ ይችላሉ? ለሚሉት የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘ ት ይሞክራል።

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

የፎክሎር ጥናት በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። ፈቃደ(1991፣44 ) Putting Folklore to use (1994) የተባለን መፅሃፍ ጠቅሰው እንደገፁት ፎክሎር የማስተማር ዘዴን በማበልፀግ፣ ማህበራዊ ችግሮችን በመፍታት፣ ባህላዊ ቅርስን በመጠበቅ፣ የአኗኗር

ሁኔታን በማሻሻል (ለምሳሌ በጤና፣ ማህበረሰባዊ ማንነትን በመግለፅ፣ የባህሉን ባለቤቶችና ፈጣሪዎችን በማነቃቃትና በማበረታታት ረገድ ሊጠቅም ይችላል:: ይህ ጥናትም የፎክሎር ጥናት እንደመሆኑ:-

- በጠቅላላው ስለ ቁሳዊ ሃብቶች፣ በተለይ ደግሞ ስለ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች አመራረትና አጠቃቀም መረጃ ይሰጣል::
- የጥናቱ ውጤትና ትንታኔ ወደፊት በተመሳሳይ የፎክሎር ገፅታዎች ላይ ንፅፅራዊ ጥናት ለሚያካሂዱ ተመራማሪዎች መረጃ ይሰጣል::
- በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የቤት አሰራርና ቁሳቁስ አይነቶችን እንደዚሁም ከእነርሱ ጋር የተያያዙ ሃገረሰባዊ እውቀቶችን (Indigenous Knowledge) ቀርሶና ሰንዶ በማቆየት ረገድ ጥናቱ የራሱ ፋይዳዎች ይኖሩታል::
- ጥናቱ ቁሳዊ ሃብቶችና ከእነርሱ ጋር የተሳሰሩ ዕምነቶችና አተያዮች ለማህበረሰቡ እድገት የተሻለ ፋይዳ ሊያበረክቱ የሚችሉባቸውም ሁኔታዎች ይጠቁማል፣ ይገልፃል::

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

በDorson (1972) አከፋፈል መሰረት ፎክሎር በአራት ሰፋፊ ክፍሎች ተመድቦ ወይም ተዋግኖ ሊጠና የሚችል የሙያ መስክ ነው:: ከእነዚህ ታላላቅ የፎክሎር የጥናት መስኮች የዚህ ጥናት ትኩረት በቁሳዊ ባህል ዘርፍ ላይ ነው:: ቁሳዊ ባህል አያሌ ጉዳዮችን ስለሚያካትት ከእነዚህ ውስጥ በተለይ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዚህ ጥናት ይተኮርባቸዋል:: ከማህበረ ባህላዊ መቼት አንፃር ጥናቱ በተለይ በአንድ ማህበረሰባዊ አውድ፣ ይኸውም በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን በባህር ዳር ከተማ አካባቢ በምትገኝ ዘጌ በተባለች ባህረ ሰላጤ ላይ ያተኩራል::

## 1.5 የጥናቱ ውስንነት

በተለያዩ ጥናቶች እንደሚታየውና እኔም እንደምገምተው ኢትዮጵያ ሊጠኑ የሚችሉ በርካታ የፎክሎር ሃብቶች ያሏት ሃገር ናት:: በመሆኑም እነዚህን ሃብቶች በማጥናት ለህዝብ ልማት ፋይዳ ያላቸው ጥናቶች ማድረግ ለነገ የማይባል ስራ ነው:: ይሁን እንጂ በፎክሎር የጥናት ዘርፍ አንዱ የሆነው ቁሳዊ ባህል በአይነታቸው ልዩ ልዩ የሆኑ አያሌ ነገሮችን የሚያጠቃልል በመሆኑ በአንድ አነስተኛ ጥናት ውስጥ የአንድን ሃገር ይቅርና የአንድ ማህበረሰብ ይዞታዎች እንኳን ሙሉ በሙሉ ለመግለፅ መሞከር ትልቅ የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት አቅምን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ የጥናቱን ውጤት ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚጥል በመሆኑ የዚህ ጥናት ድንበር በአማራ ክልል

በምዕራብ ጐጃም ዞን በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ከባህር ዳር ከተማ በአማካይ 20 ኪ.ሜ ያህል ርቃ በምትገኝ ዘጌ በተባለች ባህረ ሰላጤ ውስጥ በሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች ላይ ብቻ ሆኗል፡፡

ጥናቱ ድንበሩን በሁለቱ ቁሳዊ ባህሎች (ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች) ላይ ያደረገውና ሁለቱን በአቻነት ለማጥናት ዋናው ምክንያት በጥናቱ መነሻ ሃሳብ እንደተገለፀው ቤቶችን ማጥናት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነውና ቤቶች ከተጠኑ የቤት ዕቃዎችም ቢጠኑ መልካም ይሆናል ከሚል ሃሳብ ሲሆን በተለይ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን ከቤቶች ጋር ማጥናት ያስፈለገበት ምክንያት ግን በሌላ በኩል ደግሞ አሁን በመሰራት ላይ ያልሆኑ የጥንት እቃዎችን ማጥናቱ ምናልባት ፎክሎርን ካረጀና ከጥንታዊ እቃዎች ጋር የማያያዝን ሃሳብ እንዳያንፀባርቅ ያሰጋል፡፡ ስለዚህ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በሰላጤዋ ውስጥ እየተሰሩ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ቁሶች በመሆናቸው ከቃለ መጠይቅ ሌላ በፎቶና ቪዲዮ ካሜራዎች የተደገፈና ጥናቱን የተሟላ የሚያደርግ መረጃ ሊገኝባቸው የሚችሉ በመሆናቸው የጥናቱ ድንበር ፣ጨርሰው ሳይጠፉ የግድ ሊቀረሱ ይገባል ባላቸው በባህላዊ ቤቶች በተጨማሪ ከሌሎች ባህላዊ የቤት ቁሶች ይልቅ የተሻለ መረጃ ይገኝባቸዋል ብሎ ባመነባቸው ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ላይ ተወስኗል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ ምክንያት የተነሳ ሁለቱ የቁሳዊ ባህል ዘርፎችን በአንድ የጥናት ወረቀት ላይ «አመጣጥኖ» ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 1.6 የአጠናን ዘዴ

የፎክሎር ጥናት የመስክ ምርምር የሚጠይቅ የጥናት አይነት እንደመሆኑ ይህ ጥናት ከመስክ በተሰበሰቡ መረጃዎች የተሰራ ነው፡፡ ነገር ግን ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ከመሰብሰባቸው በፊት በጥናቱ ርዕስ ዙሪያ ተቀራራቢነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶችና ርዕሱን የሚመለከቱ ትወራዎች ከቤተመፃህፍትና «Wikipedia»ን የመሳሰሉ ታማኝ የመረጃ ምንጮች ከመረጃ መረብ (ኢንተርኔት) ተፈልገው ክለሳ ተደርጓል ፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ቀዳማይና ካልአይ መረጃዎችን (Primary and secondary data) በማሰባሰብ፣ በመሰነድና በመተንተን ወደ ግቡ ለመድረስ ጥረት አድርጓል፡፡

ጥናቱ ስለተደረገበት ቦታ በቂ እውቀት ለመጨበጥ ደግሞ ወደ ተለያዩ መስሪያ ቤቶች መሄድ ከቱሪዝም፣ ግብርናና የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ፤ስለ ማህበረሰቡ ጠቅላላ መልክ ስለ አካባቢው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሃብቶችና በአጠቃላይ ጥናቱ በሚደረግበት አካባቢ ስለሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በቂ ዳራ ሊሆኑ ስለሚችሉ የአካባቢው ሁኔታዎች የሚገልፁ ፅሁፎችን በመዳሰስ የፅሁፍ መረጃ በሌለበት በዘጌ

ማዘጋጃ ቤት፣ ደግሞ በማዘጋጃ ቤቱ ውስጥ ሃላፊነት ላላቸው ሰዎች ቃለመጠይቅ በማድረግ የተሟላ መረጃ ለማግኘት ጥረት ተደርጓል::

ከዚህ በኋላ ደግሞ Williams (1967:65) «የመስክ አጥኚዎች በምልከታ ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃ በማደራጀት፣ በመተንተንና የተገኘውን መረጃ በአግባቡ በመጠቀም ረገድ በጥናት መስካቸውና በሌሎች የማህበራዊ ሳይንስ መስኮች የሚያውቋቸውን ዕውቀቶች ሁሉ መጠቀም አለባቸው» እንደሚሉትና ፈቃደ (1991) ና Macdonald (1972) ስለፎክሎር የመረጃ አሰባሰብ ካቀረቧቸው ሃሳቦች በመነሳት በዘጌ ባህረ ሰላጤ ስለሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በቂና ጥልቅ መረጃዎችን ለማግኘት ምልከታና ቃለመጠይቅ በመረጃ ዘዴነት ውለዋል::

ምልከታው የተደረገው በባህረሰላጤው ውስጥ ከሚገኙ አምስት ደብሮች ውስጥ ባህላዊ ቤቶች በሚገኙባቸው ይጋንዳ ተክለሃይማኖት፣ ኡራ ኪዳነምህረት፣ በትረማርያም፣ መሃል ዘጌ ጊዮርጊስና የሸክላ ስራ ከሚከናወንባቸው ጋሚ፣ አፋፍ 01 ቀበሌ፣ በተባሉ ቦታዎች ውስጥ ሲሆን በተጠቀሱት ደብሮች ከሚገኙ በጠቅላላው ይሆናሉ ተብለው በመረጃ አቀባዮችከሚገመቱ 80 ባህላዊቤቶች ውስጥ ከኡራ ኪዳነምህረት7፣ከይጋንዳ ተክለሃይማኖት 7፣ ከበትረማርያም 7፣ ከመሃል ዘጌ ጊዮርጊስ 7፣ አፋፍ 01ቀበሌ 6፣ጋሚ 6 ባህላዊ ቤቶች የናሙና ምልከታ ተደርጎባቸዋል:: የናሙናዎችን ቁጥር የወሰነውም የባለቤቶችና የመረጃ ሰጪዎች ፈቃድ ነው:: የዚህም ምክንያቱ አካባቢው በቱሪስት መስህብነቱ የታወቀ በመሆኑ ብዙ ነዋሪዎች ቤቶቻቸውን እንዲታዩ ሲጠይቁ የሚጠይቁት ገንዘብ እጅግ ከአቅም በላይ መሆኑ አንድ ምክንያት ሲሆን ሌላው ደግሞ ብዙ የቤት ባለቤቶች ቤታቸው እንዲታይና እንዲመረመር አይፈልጉም:: «ቤትን ያህል ነገር ለማንኛውም ሰው ማሳየት ይከብዳቸዋል:: ሆኖም ይህንን ችግር ባለቤቶችን በሚያውቋቸው ሰዎች አማካይነት በማነጋገርና መረጃ ሰጪዎችን ጋብዞ የጓደኝነት ስሜት በመፍጠርና« በወሬን ወሬ ያነሳዋል» ስሜት መረጃ ሰጭዎች ተጎትጉተው ሣይሆን በራሳቸው ፈቃድ እንዲናገሩ በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ተሞክሯል:: በአንፃሩ ከሸክላ ስለተሰሩ የቤት ቁሶች መረጃ ለመሰበሰብ የሸክላ ስራ ከሚከናወኑባቸው ጋሚና አፋፍ 01 ቀበሌ ውስጥ በሚገኙ የ14 የሸክላ ስራ ባለሙያ ቤቶች ሁሉ በመገኘት ምልከታ ተደርጓል::

ቃለመጠይቅ ከምልከታ በተጨማሪ ለዚህ ጥናት ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው:: የቃለ መጠይቁ አይነትም መረጃ አቀባዮች ያለምንም መጨነቅ ነፃ ሆነው መረጃ እንዲሰጡ ሲባል ቀድሞ ባልተዘጋጁ ነገር ግን ሁነት የሚጠራቸው ጥያቄዎች (Unstructured interview) የተደረገ ሲሆን በተለይ አስፈላጊ መረጃ ለማግኘት ሲባል ደግሞ ውስን ቃለመጠይቅ (Structured interview) ተደርጓል:: በመሆኑም ስለአካባቢው ባህላዊ ቤቶች አሰራር የት መጤነት፣ ስለ ባህላዊ ቤቶች የአሰራር ሂደት፣ ስለቤት

ቁሳቁሶች አሰራርና አገልግሎት እንዲሁም የመስሪያ ቁስ ለማወቅ ለ16 ባህላዊ ቤት ሰሪዎችና የቤት ባለቤቶች ፣ለ 14 የሸክላ ቁሳቁስ ሰሪዎችና ተጠቃሚዎች ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡ በተለይ የጥንታዊ ቤቶችን አሰራር በተመለከተ የተገኘው መረጃ ሙሉ በሙሉ በቃለመጠይቅ የተገኘ ነው፡፡ ለዚህም በማህበራዊ ተቋሞችና በሌሎች አጋጣሚዎች ዕውቀቱ ያላቸው ሰዎች መረጃ በመስጠት ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ ስለቤቶችና የቤት ቁሶች አገልግሎት ለመረዳት ሲባል ተገልጋዮች ተጠይቀዋል፡፡ በቤትና በቤት ቁሶች ዙሪያ ስለሚታዩ ተምሳሌታዊ ትርጉሞች «ያውቃሉ» የተባሉ የአካባቢው ነዋሪዎች በቃለመጠይቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የባህላዊ ቤቶችንና የቤት ቁሳቁስ ሰሪዎችን ማህበራዊ ደረጃ ለመገንዘብ ደግሞ በአካባቢው የሚኖሩ የተለያዩ የማህበረሰቡ ክፍሎችና ራሳቸው ባለሙያዎች መልስ እንዲሰጡ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡

በመሆኑም ከጥናቱ አላማ አንፃር በታቀደ ሁኔታ ከተመረጡ የተለያየ ዕድሜና ፆታ ካላቸው 30 የሰላጤ ነዋሪዎች ጋር ቃለመጠይቅ ተካሂዷል፡፡ የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ ይሁነኝ ተብሎ በተጠና መልኩ ከመሆኑም በላይ አብዛኞቹ የማህበሰቡን ባህልና ህይወት ሊገልፁ እንደሚችሉ ነዋሪዎች የመሰከሩላቸው ናቸው፡፡ በፆታ ረገድ 17ቱ ሴቶች ሲሆኑ ቀሪዎች ወንዶች ናቸው፡፡ በዕድሜ አኳያ ሲታይ አብዛኞቹ ከ30 ዓመት በላይ ናቸው፡፡ እንደተጠያቂዎች መረጃ የመስጠት ብቃትም ርዕሰ ጉዳዩን በመወሰን መረጃ ተሰብስበዋል፡፡ (የመረጃውን አይነት፣የተሰበሰበበትን ጊዜ፣ የመረጃ አቀባዮችን ስምና አድራሻ በአባሪ ክፍል ይመልከቱ)፡፡

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቴፕ፣ፅሁፍ፣የፎቶና የቪዲዮ ካሜራዎች ናቸው፡፡ ቴፕ አገልግሎት ላይ የዋለው ስለባህላዊ ቤቶችም ሆነ የቤት ቁሶች መረጃ ለማግኘት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ከመረጃ አቀባዮች መልሶችን በመቅረፅ ሲሆን ይህም ሰዎች በሚናገሩበት ጊዜ በመዘናጋትም ይሁን በሌላ ምክንያት መረጃዎች እንዳይጓደሉ ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም 10 ሰዎች የሰጡት መረጃ በቴፕ ካሴት ተቀርጿል፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ መረጃ አቀባዮች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ሊዘሏቸው የሚችሉና ሊጠቅሙ ይችላሉ የተባሉ መረጃዎች ማስታወሻ በመያዝ በፅሁፍ ተሰብስበዋል፡፡

ፎቶ ግራፍና የቪዲዮ ካሜራዎች ምልከታውን በማገዝ ያገለገሉ ሲሆን ፎቶግራፍ የቤቶችና የሸክላ ቁሶችን ቅርፅ ለማሳየት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ቪዲዮ ካሜራው ደግሞ የቤቶችን የአሰራር ሂደትና ቤቶች አሁን ያሉበትን ሁኔታ ለማሳየት መረጃዎች ተሰብስበውበታል፡፡

ለጥናት በተመረጠው የዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ ስለባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በምልከታና በቃለመጠይቅ የመረጃ መሠብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች በሚገባ ከተመረመሩ በኋላ Kenneth (1978፡ 20) «ቁሶችን መልክ ባለው ምድብ ውስጥ አስገብቶ ለመመደብ ከቅርፃቸው፣ ከተግባራቸው ፣ቁሶች ከተሰሩበት ጊዜ ፣ከሰሪዎቻቸው

ወይም ከይትባህላቸው አንፃር መመደብ ይቻላል:: ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ለወቅቱ የተሻለና ተመራጭ የሆነው አገልግሎት ላይ ይውላል::» እንደሚሉትና ሌሎችም ለምሳሌ Glassie (1991) ቁሶች በተግባራቸው ሊመደቡ ይችላሉ ሲሉ እንደሚገልፁት በዚህ ጥናትም ባህላዊ ቤቶች ማህበረሰቡ ቅርፃቸውን ተከትሎ ለመለያ ሲል በሰጣቸው ስያሜ መሰረት፤ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ደግሞ ከተግባራቸው አንፃር ተዋግነዋል::ከዚያም ጥሬ መረጃዎች በምዕራፍ ሦሥት ከቀረቡ ትውራዊ ዳራዎች ጋር እየተገናዘቡ ትንተና ተደርጎባቸዋል:: የትንተናው አይነትም አይነታዊ የትንተና ዘዴ ነው::

## 2. ክለሳ ድርሳን፣ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በበርካታ ምሁራን እንደሚገለፀው ፎክሎር በአንድ በኩል እንደ ጥናት መስክ በሌላ በኩል ደግሞ በጥናት መስኩ ስር የሚጠኑ ጉዳዮች መጠሪያ ሆኖ የሚያገለግል ቃል ነው:: ይህ ቃል እንደጥናት መስክ፤የመስኩ ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት ስነቃል (Oral literature) ሀገረሰባዊ ልማድ (Social folk customs) ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት (Social performance) እና ቁሳዊ ባህል (material culture) የሚባሉ ንዑሳን ክፍሎች ቢኖሩትም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ግን በርካታ ቁጥር ያላቸው ጥናቶች የተሰሩት በስነቃል ላይ እንደሆነ ፈቃደ(1991፣140)፣ የስነቃል መምሪያ በተባለ መፅሃፋቸው ገልፀዋል::

ይህ ማለት ግን« በሌሎች ዘርፎች የተሰሩት ጥናቶች ቁጥራቸው አናሳ ነው::» ለማለት እንጂ ጨርሶ አልተሰራም ለማለት አይደለም:: ከዚህም አንፃር በትምህርት ክፍሉ ውስጥ በቁሳዊ ባህል ላይ የተሰሩ ጥናቶችን ስመረምር ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ በሚል ርዕስ የተሠራ ጥናት አላገኘሁም::ይህ የእኔን ጥናት የመጀመሪያ ያደርገዋል ብዬ አስባለሁ::

ነገር ግን በቁሳዊ ባህል ዙሪያ ከዚህ ርዕስ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውና ለጥናቴም እንደመንደንደሪያ ሊያገለግሉ የሚችሉ ጥቂት ስራዎች በትምህርት ክፍሉ አሉ:: ከእነዚህ ስራዎች ውስጥ ከእኔ ጥናት ጋር የተሻለ ቅርበት አላቸው ያልኳቸውን ብቻ ቃኝቻቸዋለሁ::

የተቃኙት ጥናቶች በጠቅላላው ቁጥራቸው 8 ነው:: ሰባቱ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ትኩረት አንጻር በባህላዊ ቤቶችና በባህላዊ የቤት ቁሶች ላይ የተሰሩ በሚል በሁለት ምድቦች ተከፍለው ተቃኝተዋል:: በዚህም መሰረት በባህላዊ ምህንድስና ላይ የተሰሩት በመጀመሪያ፣ በቤት ቁሳቁስ ላይ የተሰሩት ደግሞ ቀጥለው በተሰሩበት ጊዜ ቅደም ተከተል ቀጥሎ ቀርበዋል:: አንዱና በመጨረሻ የተዳሰሰው ጥናት ደግሞ በቁሳዊ ባህል ላይ የተሰራ በመሆኑ ምክንያት በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተተ ነው::

የመጀመሪያ ሆኖ የቀረበው ስራ የJudit Olmstead,« The Dorze House: A Bamboo Basket.» 1972. የሚል ነው:: ይህ ስራ በደቡብ ኢትዮጵያ ከጨንቻ ከተማ አጠገብ አባያና ጫሞ ከተባሉ የስምጥ ሸለቆ ሃይቆች በላይ በጋሞ ከፍተኛ ቦታዎች በሚገኙት እንግዳና ቆንጆ የዶርዜ ቤቶች ላይ ያተኩራል:: አጥኝዋ በአካባቢው ለአንትሮፖሎጂካል የመስክ ስራ ሲሉ ለሁለት ዓመታት ያህል እንደቆዩ ይገልፃሉ::

ቦታውን በተመለከተ የገብስ እርሻ የእንሰት ተክልና የቀርከሃ ደን እንዳለ ይጠቁማሉ:: ባህላዊ ቤቶችም ከቀርከሃ የሚሰሩና ቅርፃቸው የቻይናውያንን ባርኔጣ

የመሰለ ቱቦ አይነት (Cylindrical) ቅርፅ ያለው ግድግዳ ያላቸው ናቸው፡፡ የቤቶች ማገኛ ውም ክፍል እንዲሁም ክፍፍሉ ከቀርከሃ እንደሚሰራ የገለፁት አጥኝዋ የቤቶችን አገልግሎት በተመለከተ ለሰዎችና ለእንስሳት መኖሪያ፣ ባህላዊ ቢራ(ጠላ) ማስቀመጫና ዶርዜዎች ጥሩ ቤት ሰሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሸማ ሰሪዎችም ናቸውና የሚሰሩ ልብሶችን ከዝናብ ለመጠለል ያገለግላሉ ይላሉ፡፡

የቤቶችን መጠን አስመልክቶ በሰዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ትልቅ ቤት ለፈለገ ትልቅ፣ ትንሽ ቤት ለፈለገ ደግሞ ትንህ ቤት ይሰራለታል፡፡የቤቶች ዋጋ እንደመጠናቸው ይለያያል፡፡ወደ ቤት ሰሪዎች ሲመጣ ደግሞ በዶርዜ ቤት ሰሪ ይመሰገናል፡፡ እንደ ስጋ፣ ቅቤ ወተት፣ ገብስና የስንዴ ጠላ የመሳሰሉትን ጥሩ ምግቦች ይቀርቡለታል፡፡ ቤት ማሰራት ብዙ ወጪ የሚጠይቅ ስለሆነ አንድ ሰው ቤት ማሰራት ከፈለገ ለዓመታት ገንዘብ መቆጠብ አለበት፡፡

የዶርዜ ቀርከሃ ቤቶች ተሰርተው ካለቁ በኋላ ነው በእንጨት ተገፍተው እንዲቆሙ የሚደረጉት፡፡ እነዚህ ቤቶች አናታቸው ላይ ቀጥ ያለ እንጨት ይኖራል፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ርኩስ መንፈስ ይከላከላል ተብሎ ይታመናል፡፡ አዲስ ቤት ተሰርቶ ካለቀና በእንጨት ተገፍቶ ከቆመ በኋላ ባለቤቶች በቤቱ ውስጥ መኖር ከመጀመራቸው በፊት የቅርብ ዘመዶችና ጓደኞች ገንዘብ አዋጥተው ድግስ ይደገሳል፡፡ መዋጮው “Waitto” ይባላል፡፡ በዚህ ጊዜ የሚዋጣ ገንዘብ ወደፊት በቤተሰብ ውስጥ በሚደረግ ጋብቻና በመሳሰሉ ዝግጅቶች ብድሩ ይመለሳል፡፡ በድግሱ ወቅት እንግዶች ባለቤቱን ሃብታም ሁን ልጆችህ ፣ንብረቶችህ፣ ገንዘብህ ይብዛልህ ብለው ይመርቁታል፡፡ የዶርዜ የቀርከሃ ቤቶች ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ቤቶችን ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ሲወስዷቸው ሰዎች ተሰብስበው እየዘፈኑና እየጨፈሩ ነው በማለት አጥኝዋ ይገልፃሉ፡፡ሌላው በባህላዊ ቤት ላይ ተሰርቶ ያገኘሁትንና በሁለተኛነት የቃኘሁት ጥናት Elisabeth Dorothea Hecht “The city of Harar and the Traditional Harar House”.( የሐረር ከተማና የሐረር ከተማ ባህላዊ ቤቶች) 1982 የሚል ነው፡፡

አጥኝዋ በዚህ ስራቸው በአብዛኛው Burton /1856/ Paulitschee /1888/ የተባሉ ሰዎችን ዋቢ በማድረግ ስለ ሐረር ከተማና ባህላዊ ቤቶች ፅፈዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከተማዋን አስመልክቶ ጥናቱ በተደረገበት ጊዜ ሃረር 4500 የሚደርስ የህዝብ ቁጥር ያላት የተለያዩ ጎሳዎች፣ ባህሎች፣ ሐይማኖቶችና ቋንቋዎች ያላቸው ቡድኖች ያሉባት፤ የአረብ፣ የህንድ የግሪክና የጣሊያን ነጋዴዎች የነበሩባት በዚህም የረጅም ዘመን የንግድ ባህል ያላት ባለ አምስት በር ከተማ ናት ሲሉ ይገልፃሉ፡፡የአምስቱን በሮች ስሞች ዘርዝረዋል፡፡

ቤቶችን በተመለከተ ደግሞ የተሰሩባቸውን ቁሶች ሀኪም ከተባለ ተራራ የሚመጡ የሸክላ አፈርና ድንጋይ እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ የግድግዳዎቹ ቁመት ከ 3-4

ሜትር በአብዛኛው ደግሞ 1.50 ሜትር አካባቢ እንደሆነ፣ በአንድ አካባቢ በአንድ አጥር ውስጥ በርካታ ቤቶች እንደሚኖሩ፣ በእነዚህ ቤቶች የሚኖሩ ቤተሰቦች ደግሞ በአንድ ማዕድ ቤት እንደሚጠቀሙ ይገልፃሉ፡፡

የቤቶችን የውስጥ አደረጃጀት በተመለከተ ሳሎን የተባለ ሰፊ ክፍል እንዳለና በዚህ ክፍልም አምስት ምንጣፎች ሲኖሩ አንዱ ትልቅ ነው፡፡ ሁሉም ምንጣፎች የማህበረሰቡን ልማድ መሰረት ባደረገ መልኩ የሚነጠፉበት የየራሳቸው ቦታ አላቸው፡፡ ቤቶች ለረመዳንና ለአረፋ በዓል በአመት ሁለት ጊዜ ነጭ ቀለም ይቀባሉ፡፡ በግድግዳው ላይ የሚሰቀሉ ስፌቶችም በእነዚህ ጊዜያት ይታጠባሉ፡፡ ቤቶችን በቁሶች ማሳመር የሴቶች ድርሻ ሲሆን ግድግዳው ላይ የሚሰቀሉትንም ሆነ ለዳቦ ወይም ለኬክ ማቅረቢያ የሚያገለግሉትን ስፌቶች የሚሰሩዋቸው ሴቶች ናቸው ይላሉ፡፡

ከዚህ በተረፈ አጥኚዋ በቤቶች ውስጥ ስለሚከወኑ አንዳንድ ባህላዊ ድርጊያዎች፣ ለምሳሌ ስለጫት መቃምና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች በቤቱ በየትኛው ክፍል እንደሚደረጉና ስለቤቶች የቀለም አቀባብ ቅርፅ ተምሳሌታዊ ትርጉም ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም ፅሁፋቸውን ሲያጠናቅቁ ዋልድሮን (1975) ጠቅሰው ሃረሪዎች ከቤታቸው ጋር እጅግ የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡ ቤታቸውን ለመልቀቅ ወይም ለመሸጥ የግድ እጅግ ከባድ ነገር ሊገጥማቸው ይገባል በማለት ፅሁፋቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡ በሦስተኛነት የቃኘሁት ስራ ደግሞ Girma Kidane፣ «The Traditional ways of Building Houses with in Wolayta Society»1994 ነው፡፡

ፀሐፊው በዚህ ጥናታቸው የወላይታን ማህበረሰብ ባህላዊ ቤት አሰራር መንገዶች ያቀረቡ ሲሆን ፀሁፋቸውን የሚጀምሩት የጥናቱ መነሻ የሆነውን ምክንያት በመጥቀስ ነው፡፡ ፀሃፊው እንዳሉት ወደ ወላይታ ባደረጉት ጉዞ የወላይታዎች ቤቶችና የቤት ቁሶች ውበት ስቧቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ጥናቱን ያደረጉ ሲሆን ለጥናታቸውም የሚረዳቸውን መረጃ በመጠይቅና ለባህላዊ ቤት ሰሪዎች ባደረጉት ቃለ መጠይቅ እንደሰበሰቡ ይገልፃሉ፡፡

በጥናታዊ ፅሁፉ ስለ ወላይታዎች የቤት አሰራር ደንብ ገልፀዋል፡፡ በዚህ ገለፃ ውስጥ ወላይታዎች ቤት ለመስራት ደንብ ያላቸው እንደሆነ፣ ይህ ደንብ ማንኛውም የገንዘብ አቅም ያለውና እድሜው ጉርምስና ላይ የደረሰ ሰው ቤት እንደዲሰራ እንደሚፈቅድ፣ ነገር ግን ሴቶች ይፍጠንም ይዘግይ ባል አግብተው ወደ ባላቸው ቤት መሄዳቸው ስለማይቀር ቤት አይሰሩም ሲሉ ፅፈዋል፡፡

ወላይታዎች ቤት የሚሰሩበት ጊዜ የተወሰነ እንደሆነ የገለፀው ጥናቱ ከምርት ስራ በኋላ ሰዎች ከስራ ነፃ ስለሚሆኑ፣ በክረምት፣ ወንዞች ያለቅጥ ስለሚሞሉና ስለሚፈሱ የመሰሪያ ቁሶችን ማግኘት ከባድ ስለሆነ፣ ቤት ለሚያሳሩ ሰዎች (በቤት ሥራው ለሚተባበሩ ሰዎች) ማስተናገጃ የሚሆን በቂ ጥሬ የማይገኝ በመሆኑና ዛፎችንና

ሳሮችን ለመቁረጥ አስቸጋሪ ስለሆነ በክረምት ቤት መስራት ከባድ ነው:: በመሆኑም በወላይታ ማህበረሰብ ቤት የሚሰራው ከህዳር እስከ ጥር ባለው የበጋ ወር ነው ሲል ይገልፃል::

አጥኚው በጥናታቸው በወላይታ ማህበረሰብ «ሜሽታ» «ጉላንታ» ና «ቡራሪያ» የተሰኙ ቤቶች እንዳሉ የገለፁ ሲሆን በቤቶች መካከል ያለውን ልዩነት አብራርተዋል:: በመሆኑም «ሜሽታ» ሃብታሞች፣«ጉላንታ» መካከለኛ ደረጃ ያላቸው ሰዎች «ቡራሪያ» ደግሞ ድሆች የሚሰሯቸው ቤቶች ናቸው ብለዋል:: እነዚህ ቤቶች ከስማቸው በተጨማሪ በመጠናቸውም«ጋሾ»፣ «ጊጋ»ና «ካራ» የሚል ስያሜ አላቸው የሚለው ጥናቱ ቤቶችሲሰሩ የሚያስወጡትን የገንዘብ መጠንም ይዘረዝራል::

በመጨረሻም «የወላይታ ማህበረሰብ የቤት ግንባታ » በሚል ርዕስ የቤቶች አሰራር ሂደት የቀረበ ሲሆን በሂደቱ አስራ ሁለት ደረጃዎች ተዘርዝረዋል:: ዝርዝሩም ከማቀድና መዘጋጀት ጀምሮ በር በማቆምና ቁልፍ ዘዴ (Fixing Door and locking system) ላይ ያበቃል::

ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በባህላዊ ቤቶች ላይ ተሰርቶ ያገኘሁትና የከለስኩት ጥናታዊ ፅሁፍ ደግሞ Fekadu Gadamu, «The Gurage house: Its construction and Socio-Economic significance» **2003.**የሚል ነው:: ይህ ጥናት ትኩረቱ በጉራጌ ማህበረሰብ ባህላዊ ቤቶች ላይ ሲሆን አጥኚው ፅሁፋቸውን ዕድ፣ ወይራ፣ ዘንባባ ሳር የጉራጌ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች እንደሆኑ፣ እንሰት፣ ማህበረሰቡ የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ የሚያመርተው ምርት እንደሆነና አንድ ሰው ቤት ለመስራት ጥሩ የእጅ ባለሙያ መሆን እንዳለበት በመግለፅ ይጀምራሉ::

በመቀጠልም አጥኚው ማንኛውም ጉራጌ በህይወት ዘመኑ አራት ቤቶችን ይሰራል:: ከእነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው ትዳር ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ዓመታት የሚኖርበት ሲሆን ሌሎች ከዚያ በኋላ የሚሰሩ ናቸው:: ጉራጌዎች ቤታቸውን በህብረት ይሰራሉ:: ወንዶችም ሴቶችም በስራው የሚሳተፉ ሲሆን ቤቶች ከተሰሩ በኋላ ደግሞ ጉረቤት ተሰብስቦ ቡና ይጠጣባቸዋል:: ሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶችም ይደረጉባቸዋል:: ሲሉ ይገልፃሉ::

እንደ ጥናቱ ገለፃ የቤት ስራው የመስሪያ ዕቃዎችን ከመሰብሰብ ይጀምራል:: ከዚያም የሚሰራብትን ቦታ መምረጥና መለካት፣ ግድግዳ ማቆም፣ጣሪያ መስራት ፣ሳር ማልበስ የቤት ዕቃዎችን ማስቀመጥና ቤቱን ማስዋብ የሚባሉ ደረጃዎች አሉ::

አጥኚው ፣ ጉራጌዎች ለቤቶች ውበት ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጡ የገለፁ ሲሆን ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ለቤቶች ውበት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ስለሆነ በእያንዳንዱ ደረጃ የቤቶች ውበት መጠበቅ እንዳለበት ይገልፃሉ:: ሆኖም አሁን በቤቶች

ላይ ለውጥ እየመጣ መሆኑን የጉራጌ ቤቶች የሳር ክዳናቸው በቆርቆሮ እየተለወጠ ነው ሲሉ ገልፀው ፅሁፋቸውን ያበቃሉ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥናቶች በባህላዊ ቤቶች ላይ የተሰሩ መሆናቸው ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ቢሆንም በዶርዜ፣ በሃረሪ፣ በወላይታና በጉራጌ ማህበረሰብ ባህላዊ ቤቶች ላይ ብቻ በማተኮራቸው ትኩረቱን በዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ላይ ካደረገው ከእኔ ጥናት ጋር በዋነኛነት አንደኛ ከተጠኝ ማህበረሰብ ማንነት ሁለተኛ ከትኩረት አቅጣጫ ማነስ አንፃር ይለያሉ።

ከዚህ ቀጥዬ የምመለከታቸው ሶስት ጥናታዊ ፅሁፎች ደግሞ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ዲማፆች ናቸው። ትኩረታቸው ፍፁም በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ላይ ሲሆን ይህ ትኩረታቸውም ከእኔ ስራ ጋር በከፊል የሚገናኝ በመሆኑ ቃኝቻቸዋለሁ።

ብርሃነ ትንሳኤ ወልደ ሰንበት «የሸማኔና የማዕድ ቤት ዕቃዎች» 1963። ይህ ዲማፅ ሁለት ምዕራፎች አሉት። አጥኝው በጥናቱ መግቢያ በዘመኑ የሳይንስና የቴክኖሎጅ ዕድገት ሳቢያ በፊትም ተንቆና ተረግጦ ይኖር የነበረው የሸማኔነትና የሸክላ ሰሪነት ሙያ ይበልጥ ጭቆና በዝቶበት እንደሚገኝ ይገልፃል። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ የሸማኔና የማዕድ ቤት ዕቃዎች አገልግሎታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰና እየተረሳ መሄዱን ያትታል። በመሆኑም የእነዚህን ዕቃዎች ስማቸውን፣ አገልግሎታቸውንና ቅርፃቸውን በጽሁፍ ለማስታወሻነት ለማስቀመጥ፣ በከተማ ተወልደው ላደጉና የአማርኛን ቋንቋ ለሚማሩ የእቃዎችን ምንነት ለማስረዳት፡ በዘመናዊ መልክ ተሰርተው ጥንታዊ ዕቃዎችን የሚተኩትን ለመሰየም ዋና ዋና ዓላማዎቹ እንደሆኑ ጠቁሟል።

ይሁን እንጂ ምንም እንኳን የአጥኚውን ትኩረት የማደንቅና ስጋቱንም የምጋራ ቢሆን አጥኚው ጥናቱን በተለይም ለከተማ ልጆች ማስተማሪያ ሲል ያነሳው ሃሳብ የገጠር ልጆች ሁሉ እነዚህን ዕቃዎች ያውቃሉ ሲል ደምድሞ ይሆን? ሳያስብለኝ አልቀረም። በመሆኑም ጥናቱ በማዕድ ቤት ዕቃዎች ላይ የተሰራ ስለሆነና እነዚህ ዕቃዎች ደግሞ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ናቸውና ከእኔ ጥናት ጋር ዝምድና አለው።

ሌላዋ ትኩረቱ ከእኔ ጥናት ጋር በተሻለ ቅርበት ተገናኝቶ ያገኘሁት ጥናት አስገደች አወቀ «በሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ የሚገኙ ባህላዊ የቤት ዕቃዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎች መዘርዘር ከእነአገልግሎታቸው» 1986 ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ አራት ምዕራፎች አሉት። ምዕራፍ አንድ መግቢያ ሆኖ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች (ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜ፣ መረጃዎች ሲሰበሰቡና መረጃዎች በተሰበሰቡበት ቦታ) ቀርበውበታል።

«ዕቃዎችን ማጥናት» የሚለውን ሃሳብ ዓላማ ያደረገችው አጥኝዋ በምዕራፍ ሁለት፣ የባህላዊ ቤት ዕቃዎች የስም ዝርዝር ከእነአገልግሎታቸው በስድስት ንዑሳን ርዕሶች ክፍፍል በጠቅላለው 87 ያህል ባህላዊ ዕቃዎች አቅርባለች። በምዕራፍ ሶስት ደግሞ የባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎችን መዘርዘር ከእነአገልግሎታቸው በአምስት ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍለው የተዘረዘሩ ሲሆን በአጠቃላይም 35 ባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎች ቀርበዋል። ምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ነው። በማጠቃለያው በአሁኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ሳቢያ ዛሬ የምናውቃቸው ቁሶችና መሳሪያዎች እየተለወጡና እየጠፉ ስለሆነ ይህ አይነት ጥናት በኦሮሞ ማህበረሰብ ብቻ ተወስኖ መቅረት ያለበት ሳይሆን በሌሎች የሃገራችን ህብረተሰቦች ማህበረ ባህላዊ እሴት ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ መቀጠሉ አስፈላጊ ነው ብላ እንደምታምን ትገልፃለች። አስገደች በክለሳ ድርሳኗ የተወሰኑ ስራዎች የቃኘች ሲሆን ይህም የሚያስመሰግናት ነው። ነገር ግን ትውራዊ ዳራዋ በእጅ ስራዎች (Hand crafts) ላይ ከማተኮር ይልቅ በቋንቋ ላይ ያተኮረ ስለሆነ ከትንታኔዋ ጋር ያለው ግንኙነት ጎልቶ የማይታይ ነው። ወሰኑን በተመለከተ ደግሞ አጥኝዋ ለመመልከት የሞከረችው ነገር የሰፋ ይመስለኛል።

ቀጥዬ የቃኘሁት ሌላው ከእኔ ርዕስ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ስራ ደግሞ ተሾመ ፎርሲዶ «የባህላዊ የቤት ዕቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ በሃድያ ብሄረሰብ» 1993 የሚል ነው። ተሾመ ይህንን ጥናት በአራት ምዕራፎች ከፋፍሎታል። ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ ነው። በውስጡ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ አላማ ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣የጥናቱ ወሰንና የጥናቱ ዘዴ ቀርበዋል። የጥናቱ ዓላማ ባህላዊ የቤት ዕቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ጨርሰው ከመጥፋታቸው በፊት በፅሁፍ ቀርሶ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍና የሐድያን ብሔረሰብ ባህልና ቋንቋ ለሚያጠናና የብሔረሰቡ የተግባር መገልገያ መሳሪያዎችን ለማስተዋወቅ ካለው ምኞት የተነሳ መሆኑን ይናገራል። በምዕራፍ ሁለት ቀደምት ጥናቶችን ከቃኘ በኋላ በትውራዊ ዳራ የስሞች ምንነት፣ የአጀማመራቸው ታሪክና ፋይዳቸው የሚሉ ርዕሶች የያዙ ፅሁፎች ቀርበዋል። ነገር ግን እነዚህ በትውራዊ ዳራነት የቀረቡ ርዕሶች ከእቃዎች አሰራርና አገልግሎት ይልቅ ትኩረታቸው ስም ላይ በመሆኑ የጥናቱን ትኩረት ከእኔ ጥናት የተለየ አድርጎታል።

የጥናቱ ሶስተኛ ምዕራፍ ባህላዊ የቤት ዕቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች የሚል ነው። በስሩ የቤት ዕቃዎች፤ ምግብ ማብሰያናመመገቢያ የሚሆኑ የቤት ዕቃዎች ስያሜ፣ ለእህል መስፈሪያና ማስቀመጫ የሚሆኑ የቤት ዕቃዎች፣ የመጠጥ ማዘጋጃና መጠጫ ዕቃዎች፣ ለመቀመጫና ለመኝታ የሚረዱ ዕቃዎች በሚሉ ርዕሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል። ምእራፍ አራት የመጨረሻው የጥናቱ ክፍል ሲሆን ማጠቃለያ አስተያየት የቀረበበት ነው።

አጥኚው በጥናቱ ከአላማው አንፃር የማህበረሰቡን የመገልገያ ዕቃዎችና የሐዲያን ብሔረሰብ አስተዋውቋል፡፡የአካባቢውን መልክዐ ምድር፣የማህበረሰቡን አሰፋፈር ተናግሯል፡፡ የብሄረሰቦች ታሪካዊ አመጣጥ ከአረቢያ እንደሆነና ረጅም ታሪክ ያላቸው መሆኑን አትቷል፡፡ በጀግንነታቸው የታወቁ ኑሮአቸው ጥንት በከብት እርባታ አሁን በእርሻ ላይ የተመሰረተ ቋንቋቸውም ከቤተ ኩሽቲክ ወገን ሐድይኛ መሆኑን ገልጿል፡፡

በመጨረሻም በቁሳዊ ባህል ላይ ስለተሰራ የቃኘሁት ጥናት ሄለን አላምረው «ባህላዊ ሸመናና የቆዳ ስራ በደንበጫና አካባቢዋ »1999 ነው፡፡ሄለን ይህንን ጥናት በአምስት ምዕራፎች ከፋፍላዋለች፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ ነው፡፡ በውስጡ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ አላማ ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ቀርበዋል፡፡ የጥናቱ ዋነኛአላማ በደንበጫና አካባቢዋ የሚገኙት የባህላዊ ሸመናና የቆዳ ስራዎች የአሰራር ሂደት ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው ፡፡

አጥኝዋ ይህ ዓላማ ግቡን እንዲመታ መረጃዎችን ከቤተመፃህፍትና ከመስክ የሰበሰበች ሲሆን ከመስክ የተገኙ መረጃዎችን የቪዲዮና የፎቶ ግራፍ ካሜራዎችን፣ቴፕሪከርደርንና ፅሁፍን በመጠቀም በምልከታና በቃለመጠይቅ እንደሰበሰበች ገልፃለች፡፡በምዕራፍ ሁለት፤የጥናቱ አካባቢ ተገልፆል፣ስለሸመናና ቆዳ ስራ የተፃፉ ድርሳናት ተከልሰዋል ፡፡ በምዕራፍ ሶስት፤ ትውራዊ ዳራዎች ቀርበዋል ፡፡ በምዕራፍ አራትና አምስት ስለሸመናና ቆዳ ስራ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች በየተራ ተተንትነዋል ፡፡ ከትንተናው ሁለቱም ሙያዎች በልምድ የሚገኙ ናቸው፣መስሪያ መሳሪያዎች በቀላሉ የሚዘጋጁ ናቸው፣ በሙያው የሚታዩ ዲዛይኖችና ሌሎች ሙያው ብልሃቶች ምንጭ ልምድ ነው የሚሉ ውጤቶች ተገኝተዋል ፡፡

ከላይ የቀረቡት ጥናቶች በአብዛኛው አላማቸው አንድ ነው፡፡ በአካባቢ ያሉ የመገልገያ መሳሪያዎችን ስያሜዎቻቸውንና አገልግሎታቸውን ቀርሶ ማስቀመጥና መኖራቸውን እንዲታወቅ የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ቅርስን ቀርሶ ማስቀመጥ እጅግ ጠቃሚ ተግባር ቢሆንም ቁሶችን ከመቅረስ ባሻገር ለማህበረሰቡ አንዳች ፋይዳ እንዲያበረክቱ መደረግ አለበት፡፡ ይህም ሲሆን የሚችለው ለምሳሌ ዕቃዎች በክብር ተቀምጠው ለቱሪስት መስህብ እንዲሆኑ ሙዚየሞች የሚሰሩበትን መንገድ ማሳየት፣ እውቀት ከውጭ ሃገር ብቻ የሚመጣ አድርጎ የማሰብን አመለካከት ከማህበረሰቡ አእምሮ እንዲወጣ የሚያደርግ እውነታን መጠቆም፣ ለጥቂት ገንዘብ ሲባል ቅርሶችን ከመሸጥ ይልቅ ባሉበት ሁኔታ ጥቅም የሚያስገኙባቸውን መንገዶች ማሳየት፣ ለምሳሌ የቤቶች ባህላዊነት እንደተጠበቀ የቱሪስት ማረፊያ ማድረግ እንደሚቻል የሚጠቁሙ ጥናቶች ሊሰሩ ይገባል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ይህንን ከማድረግ አንፃር ረብ ያለው ይሆናል የሚል ግምት አለኝና ከሌሎች ጥናቶች የተለየ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

በመቀጠል በጥናቱ ርዕስ ዙሪያ ተዛማጅነት ያላቸው በተለያዩ ምሁራን የተባሉና ከመረጃ መረብ የተገኙ ትውራዊ ዳራዎች ቀርበዋል፡፡

እነዚህ ትውራዊ ዳራዎች በጠቅላላው ስለ ቁሳዊ ባህል በተናጠል ደግሞ ስለ ሃገረሰባዊ ምህንድስናና ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የሚገልፁ ሲሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ ምዕራፍ ተሰጥቷቸው የመቅረባቸው ምክንያት አንድም ጥናቱ ከሌሎች ቀደም ሲል በዘርፉ ከተደረጉ ጥናቶች ጋር ያለውን ተለጣጣቂነት የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለዚህ ጥናት መንደርደሪያ የሆኑ በመሆናቸው ነው፡፡ቀጥሎ ትውራዊ ዳራ ይቀርባል፡፡

## 3. ትውራዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ በቁሳዊ ባህል ጥናት ቅቡልነት ያላቸው ምሁራንና እንደ «Wikipidia» ያሉ ከመረጃ መረብ የሚገኙ ታማኝ ምንጮች ከቁሳዊ ባህል ጋር በተያያዘ ያሏቸው ትወራዎች ቀርበዋል፡፡ትወራዎች ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ሲተነተኑ ማገናዘቢያ በመሆን ያገለገሉ ሲሆን ከዚህ ጥናት አላማ አንፃር ጥናቱ ይመልሳቸዋል ተብው ለተቀረፁ ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት አንፃር ሊበጁ በሚችሉ መልኩ ተመርጠውና ተዋቅረው የቀረቡ ናቸው፡፡

ስለዚህም ምዕራፉ፤ቁሳዊ ባህል ምንድን ነው?፣የቁሳዊ ባህል ዘርፎች፣ባህላዊ ቤቶች በተገኙበት ቦታ እንዲገኙ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ነገሮች፣ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች፣፣በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ነገሮች፣ የቁሳዊ ባህል ሰሪዎች፣የቁሳዊ ባህል ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃና ቁሳዊ ባህልን ለበለጠ ጥቅም ማዋል የሚሉ ዓበይት ርዕሶች በስራቸው ሊሎች ንዑሳን ርዕሶችን ይዘው ቀርበዋል፡፡

### 3.1 ቁሳዊ ባህል ምንድን ነው?

ባህል ተኮር የሆኑ ሃገር በቀል ዕውቀቶች ጥቅል መጠሪያና የእነዚህ ዕውቀቶች የጥናት ወይም የሙያ መስክ የሆነው ፎክሎር ምንነቱን በተመለከተ እስካሁን ድረስ አንድ ወጥ ብያኔ አላገኘም፡፡ ይህ በመሆኑም ምክንያት ለበርካታ የመስኩ ሰዎች የተሻለ ሆኖ የተገኘው ነገር በስሩ የሚጠኑና ሊጠኑ የሚችሉ ነገሮችን መዘርዘርና እነዚህ ዝርዝሮች ደግሞ በክፍል በክፍል ማጥናት ነው፡፡ በዚህ ተመራጭ አካሄድ መሰረት በበርካታ ምሁራን የፎክሎር ዘርፎች ተብለው ከሚጠኑት መካከል ቁሳዊ ባህል አንዱ ነው፡፡

ቁሳዊ ባህል፣ የሰው ልጅ ለመኖር ሲል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ፈጥሮ የተገለገለባቸውንና በአይን የሚታዩ፣ በእጅ የሚጨበጡና የሚዳሰሱ ባህላዊ ቁሶችን እንደሚመለከት የዘርፉ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

ቁሳዊ ባህል፣ የዘመን አሻራን የሚመለከቱ፣ የሚጠቁሙና ራሳቸው ሰዎች ስርተዋቸው ለኑሯቸው ለመዝናኛቸው፣ ለጌጣጌጦቻቸው የሚጠቀሙባቸውን እንዲሁም ህይወታቸውን ከአደጋ ለመከላከል የሚያግዟቸውን መሳሪያዎች የሚያካትት አካዳሚያዊ ስያሜ እንደሆነ Dorson (1972:2) በሚከተለው ሁኔታ ይገልፃሉ፡-

> Material culture responders to technices,skills,recipes,and formulas transmited across the generation and subject to the same forces of conservative tradition and individual varation as verbal art,How men and

women in tradition oriented societys build their home,make their clothes, prepare their food,farm and fish,process the earthes bounty,fashion their tooles and implements, and design their furniture andutensils and questions that concern the student of material culture.

Dorson ከላይ በሰፈረው ሃሳብ ቁሳዊ ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩ ባህላዊ ቁሶችን የሚመለከት ጥንታዊ የሆኑ ቁሶች የሚጠኑበትና እነዚህ ቁሶች ደግሞ በአመዛኙ ከማህበረሰቡ ጋር በማያያዝ ማጥናት የቁሳዊ ባህል ተማሪን የሚመለከት እንደሆነ ይገልፃሉ:: የቁሳዊ ባህልን ምንነት በተመለከተ ከዚህ በተጨማሪ Ralf and Harry, An Introduction to Anthropology በሚል መፅሃፋቸው:- ቁሳዊ ባህል ባጠቃላይ የእደጥበብ (artifacts) ቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚመለከት እንደሆነ ይገልጻሉ :: እነዚህ እደ ጥበቦች መገልገያ መሳሪያዎች መያዣዎች፣ የምግብ ዝግጅት፣ ከደሳሳ ጐጆ እስከ ከፍተኛ ቤተመቅደስ ያሉ መጠለያዎች አልባሳትና ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ማናቸውም ቁሶች ናቸው (1959፣229):: በማለት የሚገልፁት ሲሆን Jones (2000፣9) ደግሞ«Material culture is an abbrivation for the material manifestiations of culture, i.e., objects made by human beings-the tangible things that people make, alter, and use, and to which they often attribute meanings and significance beyond utility or practicality. Artifacts relate to human values, concerns, needs, and desires both past and present. They may reflect the spirit of an age, the belief of a society or a sub group, or the experience of an individual » ሲሉ ቁሳዊ ባህል፣ ባህልን የሚገልፅ ቁስ በአጭር የሚጠራበት ቃል እንደሆነና ቁሳዊ ባህሎች ሰዎች የሚሰሯቸው ፣የሚጠቀሙባቸው ከጥቅማቸውና ከአገልግሎታቸው ባሻገር ትርጉምና ጥቅም ያላቸው ፣ካለፈና ከአሁን የሰዎች እሴቶች አመለካከቶችና ፍላጐቶች ጋር የዘመንን መንፈስ፣ የማህበረሰብን ወይም የተወሰነን ቡድን ወይም የግለሰቦችን የህይወት ልምድ የሚያንፀባርቁ ናቸውን የሚል ትርጓሜ ይሰጣሉ:: Glassie (1991፣22) ደግሞ ቁሳዊ ባህልን ከነአጠናኑ ሲገልፁት «Material culture is culture made matrial. It is the inner wit at work in the world.Beginning nessarly with thinges,dut not ending with them . The study of material culture uses objects to approach human thoughts and actions. » ሲሉ ፈቃደ(1991፣15) በበኩላቸው «ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣ የቅመማቅመም ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወዘተ አሰራርን፣ የሰዎችልዩ ልዩ ስራዎች የሚከወኑባቸውን መሳሪያዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል ማለት ነው» ሲሉ የሰጡት ብያኔ የግላሲን ሃሳብ የሚያብራራ ነው::

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው ቁሳዊ ባህሎች በአንድ አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች (ግለሰብም ሊሆን ይችላል) የአካባቢውን ወግ፣ ልማድ፣ ባህል፣

እምነትና ፍልስፍና ተከትለው የሚሰሩ፣ማህበረሰቦች በአካባቢያቸው የሚያገኟቸውን ነገሮች በመጠቀም የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን የሚፈፅሙባቸውን መሳሪያዎች፣ እንደየባህላቸውን ለመኖሪያነት የሚገለገሉባቸውን ቤቶች፣ ምግቦችን፣ እንዲሁም እርቃናቸውን የሚሸፍኑባቸውን ልብሶችን እንደሚያጠቃልልና የእነዚህን ቁሶችም ከቁስነታቸው ባሻገር የሚያንፀባርቁትን የሰዎች እምነት አስተሳሰብና ፍልስፍና እንደሚያጠና ነው።

ከዚህም ተጨማሪ ቁሳዊ ባህል የአንድን ዘመን አሻራ የሚመለከት እንደሆነ፣ ይህም ማለት በአንድ ወቅት የነበሩ ሰዎች ሲከውኗቸው የነበሩትን ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚናገር እንዲሁም የሰዎች ንቃተ ህሊና የሚያንፀባረቅበት መሆኑን ከላይ ከቀረቡት ምሁራን ሃሳቦች መገንዘብ ይቻላል።

እንግዲህ እነዚህ ምሁራን ለቁሳዊ ባህል ከሰጧቸው ብያኔዎች ሌላው መረዳት የሚቻለው ሃሳብ በቁሳዊ ባህል ስር ሊጠኑ የሚችሉት ጉዳዮች እጅግ ብዙ መሆናቸውን ነው። ለምሳሌ ያህልም የምግብ አሰራር፣ የቅመም አቀማመም፣ ባህላዊ ልብሶች፣ወዘተ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህን ዝርዝር ጉዳዮች እያንዳንዳቸውን ከማጥናት ይልቅ በክፍል መድቦ ማጥናቱ ጉዳዩን በስርዓት ለማሳየት፣ ፅንሰ ሃሳቡንም ለመገንዘብ ያስችላል። በእርግጥ ሙሉ በሙሉ አንዱን ከሌላው በግልፅ ነጥሎ ማሳየት አይቻልም። ይሁን እንጂ በዘርፉ የተለመደውና እየተደረገም ያለው ይኸው በክፍል መድቦ ማጥናት ነው። በመሆኑም ከዚህ እሳቤ ፎክሎር በስሩ ሊጠኑ የሚችሉ ዘርፎች እንዳሉት መገንዘብ ይቻላልና ቀጥሎ እነዚህ ዘርፎች ይቀርባሉ፡-

## 3.2. የቁሳዊ ባህል ዘርፎች

ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ቁሳዊ ባህልንም ሆነ በጠቅላላው ፎክሎርን በማጥናት ሂደት ለእያንዳንዱ ፅንሰ ሃሳብ ብያኔ ከመስጠት ይልቅ የተሻለውና የተለመደው አሰራር በነገሩ ስር የሚጠኑ ጉዳዮችን መዘርዘርና ለእነዚህ ዝርዝሮች ደግሞ ዘርፍ በማበጀት በክፍል ውስጥ አስገብቶ ማጥናት ነው። ስለዚህም ቁሳዊ ባህል በስሩ የሚጠኑ ዘርፎች አሉት፡ Dorson (1972) እነዚህን ዘርፎች ከነምንነታቸው የገለፆቸው ሲሆን፡ዘርፎችም፡-folk art (ሀገረሰባዊ ስዕል), folk custom (ሀገረሰባዊ ልብስ) folk cookery, (ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር), folk crafts (ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ)፣ folk architecture (ሀገረሰባዊ ምህንድስና) [2] ናቸው።

ምንም እንኳን ከላይ እንደተዘረዘረው የፎክሎር ዘርፍ የሚባሉት በአጠቃላይ ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ በአምስት ክፍሎች ተከፍለው የቀረቡ ቢሆንም የዚህ ጥናት

[2] የዘርፎችን የአማርኛ ትርጓሜ የሰጧቸው ፈቃደ (1991) ናቸው።

ዕሁፍ ድንበር ግን በባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ላይ የተገደበ በመሆኑ ለሁሉም የቁሳዊ ባህል ዘርፎች ብያኔና ትንታኔ ከመስጠት ይልቅ በጥናቱ ወሰን ላይ ማተኮሩ የተሻለ ነው።

ከላይ ባህላዊ ቤቶችና የቤት ቁሶች የቁሳዊ ባህል ዘርፎች እንደሆኑ ተገልጿል። እነዚህ ዘርፎች ደግሞ በፎክሎር ሙያዊ ቃል ሲገለፁ ቤቶች በሀገረሰባዊ ምህንድስና (folk architecture)፣ ከሸክላ የተሰሩ ባህላዊ የቤት ቁሶች ደግሞ በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ (folk crafts) ስር የሚመደቡ ናቸው። የፅንሰ ሀሳቦች ምንነታቸውና ሌሎች ባህሪዎቻቸው ቀጥሎ ቀርቧል።

### 3.2.1 ሀገረሰባዊ ምህንድስና (Folk architecture)

> Folk architecture may be said to be traditional architecture.It is concerned with all traditional aspects of building; the shapes,sizes,and layouts of buildings of all kinds,such as dwellings,barns,sheds and craft shopes; the materials used and the tools and techniques of building;the sites chosen and placement of various buildings on the site;and the use to which buildings and various parts of buildings were put. ( Dorson,1972: 28) ።

ይህ ከላይ የተገለፀው ሃሳብ ሃገረሰባዊ ምህንድስና ምን እንደሆነ የገለፀ ከመሆኑም በላይበዚህ ንዑስ የጥናት መስክ ሊጠኑ የሚችሉና ሊጠኑ የሚገባቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑም የጠቆመ ነው።

በዚህም መሰረት ፅንሰ ሃሳቡ የተለያዩ ግንባታዎችን የእነዚህን ግንባታዎች አይነት፣ ቅርፅና መጠን የመስሪያ ቁሶችን፣ የአሰራር ዘዴዎችን፣ ለስራው የሚመረጠው ቦታ፣በተመረጠው ቦታ የግንባታዎችን አቀማመጥ፣የእያንዳንዱ ክፍልና የክፍሎች ጥቅም በሃገረሰባዊ ምህንድስና ስር የሚተኮርባቸው ነጥቦች እንደሆኑ ገልጿል።

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ስለሃገረሰበሳዊ ምህንድስና ገለፃ የሰጡት Glassie (1991:232) «የባህላዊ ግንባታ ጥበብ የነገሮችን ባህላዊ ልዩነትና የግለሰብንና የማህበረሰብን ግንኙነት፣ የባህል ስርፀት፣ የባህል ጠንካራነት፣ በአዲስ አካባቢ የባህልን ተወራራሽነት ለመረዳት ወሳኝ ነገር ነው» ሲሉ ይጠቁማሉ። ከዚህ ጥቆማቸውም ባህል በቤቶች ላይ የሚፈጥረውን ተፅዕኖ፣ ግለሰብ በሚያከናውነው የግንባታ ጥበብ የተነሳ ከማህበረሰብ ጋር የሚፈጥረውን ግንኙነት እንዲሁም ምናልባት በአንድ አካባቢ የሚከወን የቤት አሰራር ዘዴን ከየት መጤነት በማጥናት የባህልን ጉዞ ማጥናት የሚቻልበት መስክ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ ውጭ ግን የባህላዊ ግንባታ ዘርፍ Dorson እንደጠቆሙት በስሩ ሊጠኑ የሚችሉ ነገሮች አያሌ ናቸው። ነገር ግን ምንም እንኳን በሀገረሰብ ምህንድስና ስር የሚጠኑ ጉዳዮች እጅግ ብዙ መሆናቸውን መገንዘብ ቢቻልም የዚህ ጥናት ትኩረት

በተለይ በባህላዊ ቤቶች ላይ በመሆኑ እይታን ጠበብ አድርጎ ስለ ባህላዊ ቤቶች ማየት ተገቢ ነው፡፡

### 3.2.1.1 ባህላዊ ቤቶች

ባህላዊ ቤቶች ቀደም ሲል ከተነሳው የዶርስን ብያኔ መረዳት እንደሚቻለው በሀገረሰባዊ ምህንድስና ውስጥ የሚጠኑ ናቸው፡፡ የቤቶችን አጠናን አስመልክቶም ለጠቅላላው ምህንድስና «ሊተኮርባቸው ይገባል» የተባሉት ሃሳቦች ከጅምላው ወደ ነጠላ በመውረድ ትኩረት የሚያገኙ ነገሮች ናቸው፡፡ መሆኑም ባህላዊ ቤቶች ሲጠኑ፣ የቤቶች ቅርፅና መጠን፣ የመስሪያ ቁሶች፣ የአሰራር ዘዴዎች ለመስሪያ የተመረጠው ቦታ፣ የግንባታዎች አቀማመጥ፣ ቤቶች ያሏቸው ክፍሎች፣ እያንዳንዱ ክፍል የሚሰጠው አገልግሎትና Susan (2002፣2) "ቁሳዊ ባህል ከህዝቦችና ቡድኖች ጥበብና ቴክኖሎጂ የሚመነጨውን እውነትና ትርጉም የያዙ ቁሶች በዘዴ የሚጠኑበት ነው፡፡" ሲሉ እንደሚገልፁት ከቤቶች ባሻገር የቤቶች ትርጉም ምንድን ነው? የሚሉ ሃሳቦች ተተኳሪ ነጥቦች ናቸው፡፡

በመሰረቱ ቤቶች ደሳሳ ጐጆም ይሁኑ አፓርታማ በሳርና በጭቃ ይሰሩ በእምነበረድ ሰዎች እራሳቸውን ከብርድ፣ ከፀሐይና ከዝናብ ብሎም በአውሬ ከመበላት ለመዳን ሲሉ የሚሰሯቸው ናቸው፡፡ በሌላ አባባል የማንኛውም ቤት መሰረታዊ ግልጋሎት መጠለያነት ነው፡፡ይህንንም Foster and L.(1963:375 « The popular idea of the Orign of Vernacular Arctecture is that men in all parts of the world,as their brains and their tools developed, felt the need for shelter aginest the weather and, taking advantage of such materials,wood,clay or stone.as came most conveniently to their hands, made crud structures which they or those of them who remained on the land, gradually improved in to farm houses and peasant dwellings of today »ሲሉ ያረጋግጡታል፡፡ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች በየአካባቢው የሚገኙ ቤቶች የተለያዩ የመስሪያ ቁሶች ሲኖሯቸው፣የተለያየ ቅርጽ ሲይዙና በህብረተሰቡ ውስጥ ለቤቶች የሚሰጠው ትርጉም የተለያየ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ልክ Judith (1972) በጥናታቸው «ሐረሪዎች ከቤቶቻቸው ጋር እጅግ የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡ቤቶቻቸውን ለመልቀቅ ወይም ለመሸጥ እጅግ አስገዳጅ ሁኔታ ሊገጥማቸው ይገባል» እንደሚሉት፡፡ይህ ሁኔታም ባህላዊ ቤቶች በተገኘ ብት ቦታና በተገኙበት መልክ እንዲኖሩ የሚያስገድዷቸው ሁኔታዎች እንዳሉ የሚጠቁም ነው፡፡ ቀጥሎ እነዚህ ሁኔታዎች ይቀርባሉ፡-

### 3.2.1.2 ባህላዊ ቤቶች በተገኙበት ቦታ እንዲገኙ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ቤቶች ምናልባትም አንድ አይነት አለበለዚያም ፍፁም የሆነ የቅርፅና የመጠን አንድነትና ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል:: ይህም የሚሆንበት ምክንያት ሰዎች ቤቶችን ስለፈለጉ ብቻ የፈለጉትን ቅርፅና መጠን አስይዘው ሊሰሯቸው ስለማይችሉ ነው:: ምክንያቱም ቤቶችን እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚነግሯቸውና የሚያስገድዷቸው ከባህላዊ እውቀቶቻቸው የተማሩዋቸውና ከቀደሙ አባቶቻቸው የወረሷቸው ዕውቀቶች አሉ:: በእርግጥ ቤት ሰሪዎች ለሚሰሯቸው ቤቶች እንዴትነት ምክንያት ማቅረብ ይችላሉ:: ለመሆኑ ግን እነዚህ በባህላዊ ባለሙያዎች የሚታወቁና ቤቶች ባሉበት ቦታና ባሉበት መልክ እንዲኖሩ የሚያስገዱዳቸው ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው? በእርግጥ ይህንን ሁኔታ የሚፈጥሩ ጉዳዮች አያሌ ናቸው:: ነገር ግን እነዚህ ጉዳዮች ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ «Metrological»፣ «Geological» ና «Social» ምክንያቶች ተብለው እንደሚከፈሉ Makonnen (1964) ይገልፃሉ:: ከዚሁ አክለውም ጂኦሎጂካሉ ምክንያት በሜትሮሎጂካሉና በማህበረሰቡ ባህል የሚወሰን እንደሆነ ይናገራሉ:: እንግዲህ ከላይ ከቀረበው ገለፃ ለመረዳት እንደሚቻለው በባህላዊ ቤቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ብዙ ቢሆኑም ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ ሦስት ናቸው:: እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ አንዱ በሌላው ላይ የሚደጋገፉ ናቸው:: ለምሳሌ በአንድ አካባቢ የአፈርና የድንጋይ መኖርን ፀባይ እንዲሁም የዕፅዋት አይነትና አበቃቀል በአካባቢው ሙቀት ፣ ነፋስ ፣ ዝናብ የሚወሰን ይሆንና ይህ ደግሞ በተራው በቤቶች አሰራር ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር «ባህል» የተባለን ነገር ይፈጥራል:: ከዚህም የተነሳ በጠቅላላው የባህላዊ ቤቶችን ህልውናና መልክ የሚወስኑ ነገሮች ከሶስት ወደ ሁለት ይወርዱና የአየር ንብረትና የማህበረሰቡ ባህል ይሆናሉ:: ቀጥሎ እያንዳንዳቸው ቀርበዋል:-

#### 3.2.1.2.1 የአየር ንብረት በባህላዊ ቤቶች ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ

የአየር ንብረት ስለ አንድ ሀገር ወይም ቦታ በሚደረግ የስነ ምድር (ጂኦግራፊ)ጥናት ውስጥ አንዱ ተተኳሪ ጉዳይ ሲሆን የፅንሰ ሀሳቡንም ትርጓሜ አስመልክቶ Mulunehe (1986) «የአየር ንብረት ማለት የአንድ ቦታ አማካይ የሙቀት፣ የነፋስ፣ የዝናብ፣ የርጥበት የፀሐይ ወይም የደመና ሁኔታ ነው» በማለት ይበይኑታል:: ታዲያ ይህን ብያኔ የጥናቱን ወሰን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እይታችን ወደሃገራችን አምጥተን ስናየው ኢትዮጵያ ሁሉም አይነት የአየር ንብረት ባለቤት እንደሆነች ነው የተለያዩ ፀሀፎች የሚገልፁ:: ለምሳሌ Atkinss (1970፣31) «በአለም ላይ ካለው አማካይ

ከፍተኛ ሙቀት እስከ ቀዝቃዛው ድረስ ሁሉም አይነት የአየር ንብረት ኢትዮጵያ ውስጥ አለ:: ለዚህ የአየር ንብረት ልዩነት ነፋስ፣ ሙቀት፣ዝናብ፣ ለባህር ያለ ቅርበትና ሃገሪቱ ከምድር ወገብ ያለችበት ርቀት ምክንያት ናቸው:: «አልቲቲውድም» ለዚህ የአየር ንብረት ልዩነት ዋና ምክንያት ነው ሲሉ ይገልፃሉ:: ከጥቅሱ መረዳት የሚቻለው ኢትዮጵያ በአልቲቲውዷ አነስተኛነት የተነሳ በተለያዩ ቦታዎቿ ላይ ተለዋዋጭ የአየር ንብረት ያላት መሆኑን ነው::

ታዲያ እንደጥቅሱ ገለፃ ኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ የአየር ንብረት ካላት ሃገሪቱ ብዙ አይነት መልክዐ ምድሮች ያሏት እንደመሆኑ በእነዚህ የተለያዩ መልክዓ ምድሮች የሚሰሩ ቤቶችም ከአየር ንብረት ጋር አንዳች ንክኪ አላቸው:: ይህንንም Makonnen (1964) እንደሚከተለው ይገልፁታል:-

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ 3.45$^0$ ና 18$^0$ ሰሜን ኬንትሮስ (latitude) 33$^0$ ና 48$^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ(Longitude) የምትገኝ ሃገር ናት:: እንደሚታወቀው አገሪቱ ከላቲቲውዷ አነስተኛነት የተነሳ ለምድር ወገብ የቀረበች ስለሆነ «ቶሪድ» በተባለው ክልል ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ትገባለች:: ይህ ክልል ደግሞ ሞቃቱ አካባቢ ነው:: ይህ ሁኔታም በባህላዊ ምህንድስና ጥናት ውስጥ ባህላዊ ቤቶች ሲጠኑ የሚሰሩባቸውን ቁሶች ተጠኝ ጉዳይ ያደርጋቸዋል:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ሞቃት ሃገር ብትሆንም የአየር ንብረቷ በምንም ምክንያት ፍፁም ሞቃት ነው ተብሎ ሊገለጽ አይችልም:: በከፍታ (Altitude) ልዩነት ምክንያት በአየር ንብረቱ (Climate) ላይ ከፍተኛ ልዩነት አለ:: ይህ ልዩነትም በሚከተለው የከፍታ መጠንና የአየር ንብረት ክልል ይከፈላል::

ሀ. ቆላ /ሞቃትና ደረቅ የአየር ንብረት/ ከባህር ወለል በላይ 500-1500 ሜትር ከፍታ አማካይ የሙቀት መጠን 25$^0$ C::

ለ. ወይና ደጋ /ቀዝቃዛና ሞቃት ርጥበት የአየር ንብረት/ ከባህር ወለል በላይ 1500-2500 ሜትር ከፍታ አማካይ የሙቀት መጠን 22$^0$ C::

ሐ. ደጋ /ቀዝቃዛና እርጥብ የአየር ንብረት/ ከባህር ወለል በላይ 2500-3500 ሜትር አማካይ የሙቀት መጠን 16$^0$ C::

ከ500 ሜትር በታች በጣም ሞቃትና ደረቅ /በረሃ/ የአየር ንብረት ያለው ሲሆን በዚህ አካባቢ የሚሰሩ ቤቶች ከፊል ቋሚዎች (Semi-permanent) ናቸው:: አርብቶ አደሮች የሚሰሯቸው ሊባሉ ይችላሉ:: የሶማሌ ቤቶች የዚህ አይነቶች ናቸው:: በአንፃሩ ከ3500 ሜትር በላይ በጣም ቀዝቃዛና እርጥብ ስለሆነ ሰው ሊኖርበት አይችልምና ቤቶች አይሰሩም:: በመሆኑም ባህላዊ ቤቶች እነዚህን የአየር ንብረቶች መሰረት አድርገው የሚሰሩ ናቸው::

ለእነዚህ የከፍታና የአየር ንብረት ክልሎች በእያንዳንዱ ክልል ውስጥ የባህላዊ ቤቶችን አሰራር የሚወስኑ አያሌ ጉዳዮች ይኖራሉ። ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ ግን ሜትሮሎጂ፣ ጂኦሎጂና ሰሻል ጉዳዮች እንደሆኑ ነው ለማየት የተሞከረው።

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ Glassie (1991) ይህንን በተመለከተ በአንድ የከፍታና የአየር ንብረት ክልል ውስጥ ቤቶችን ከተለያዩ ቁሶች እንዲሰሩ የሚያደርጉ ትልልቅ ምክንያቶች አሉ። ይህ ሁኔታም ቤቶችን ከሚገኙበት ዞን ይልቅ በሚሰሩበት ቁስ እንዲከፈሉ ያደርጋል ሲሉ ይገልፃሉ። እንዲያውም በቤቶች ግንባታ ላይ ጥናት ሲያደርጉ እሳቸው ለቤቶች ቅርጽ ትኩረት መስጠትን ተማርኩ ቢሉም ቤቶቻቸው የሚጠኑት ሰዎች ግን ቤቶችን በተሰሩበት ቁስ በተለይም ጣሪያቸው በተሰሩባቸው ቁሶች ሲመድቧቸው እንዳዩ ይናገራሉ። ለምሳሌ በባንግላዲሽ የአካባቢው ሰዎች የቤቶች ግድግዳ በጭቃ የተመረገ በመሆኑ ወይም በቀርከሃ በመሰራቱ እንዲሁም የቤቶች ጣሪያ በተከደነበት የቆርቆሮ አይነት ይከፍሏቸዋል ይላሉ። በጠቅላላው ግን የአየር ንብረትና የቁሶችን የዋጋ መጠን መሰረት በማድረግ ቁሶች ተመርተው ለቤት መስሪያነት እንደሚውሉና ቤቶችም ከተሰሩባቸው ቁሶች አንጻር እንደሚከፈሉ ይገልፃሉ። እንግዲህ ወደ ተነሳንበት ሃሳብ ስንመለስ እየተገለፀ ያለው የአየር ንብረትና ባህል በባህላዊ ቤቶች ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ እንዳለ ነው። የአየር ንብረት ሁኔታን አስመልክቶ በእፅዋት አበቃቀልና በአፈርና በድንጋይ ፀባይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የቤቶችን አይነት እንዲሁም ለመስሪያ የሚያገለግሉ ቁሶችን የሚወስን መሆኑን ለመግለፅ ተሞክሯል።

በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ባህል ሲመጣ ምሁራኑ ባህል፣ በአንድ ማህበረሰብ ባህላዊ ቤቶች ህልውናና የመስሪያ ቁስ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ትልቅ ጉዳይ መሆኑን ይገልጻሉ። ይህንን ለማየት ባህል በባህላዊ ቤቶች ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ የሚል ርዕስ ቀጥሎ ቀርቧል፡-

### 3.2.1.2.2. ባህል በባህላዊ ቤቶች ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ

ባህል እጅግ ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ በመሆኑ ከተለያዩ እይታዎች፣ ከተለያዩ መስኮችና ከተለያዩ ልምዶች በመነሳት ብያኔ ሊሰጠው የሚችል ጉዳይ ነው። ከዚህም አንጻር የተለያዩ ማህበረሰቦች ወይም የማህበረሰብ ክፍሎች የተለያየ ባህል አላቸው። ወይም አንድ ግለሰብ ከሌላ ግለሰብ የተለየ ባህል ይኖረዋል። ያም ሆኖ Wikipedia (The free Encyclopidia) እንደሚገልጸው ባህል የሰው ልጆችን ተግባራትና በተግባራቱ የሚገኘውን ተምሳሌታዊ ትርጉም ለመግለፅ ይውላል። ሆኖም ማህበረሰብ የሚባለው ነገር ሰፊ እንደመሆኑና ይህ ሰፊ ነገር ደግሞ በተለያዩ መስፈርቶች ማለትም እንደ ጎሳ፣ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ የየራሱ ክፍል ያለው እንደመሆኑ እያንዳንዱ ክፍል ባህል ለሚለው

ፅንሰ ሃሳብ ከየራሱ አመለካከትና ልምድ የተነሳ ብያኔ መስጠቱ የተለመደ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር Beals and Hoijer (1958:210) ባህልን ከአንትሮፖሎጂስቶች አንጻር ሲበይኑት፡-

> "culture" as term is used by the Antorpologist,may be applied(1) to the ways of life or "designs of living" commen at any one time to all mankind,(2) to the ways of living pecular to agroup of Societies between which there is agreater or less degree of interaction,(3) to the patterns of behavior pecular to a given Society,and(4) to special ways of behaving characteristic of the segement of a large and complex Organized Society.

ሲሉ ብያኔውን ያስቀምጣሉ፡፡ ከዚህ ጥቅስም መረዳት የሚቻለው ባህል አንድ ማህበረሰብ አንድ አይነት የሆነ መልክ እንዲኖረው የሚያደርግና ይህን አንድ አይነት መልክ ያለውን ማህበረሰብ ደግሞ ገዝቶ የሚይዘው ስርዓት እንደሆነ ነው፡፡

ባህል ለሚለው ቃል ብያኔ ከመስጠት ጋር በተያያዘ ደግሞ ማህበረሰቡን ገዝቶ የሚይዘውን ነገር (ባህሉን) ማህበረሰቡ እንዴት ሊያገኘው እንደሚችል Encyclopidia of Americana (1983:315) ሲገልጽ « Culture became aterm used to describe the distinictive human mode of adapting to the environment.Molding nature to conferm to man`s desires and goals.There are other meanings.However, all Anthropologists agree that culture consistes of learned ways of behaving and adapting. As contrasted to inherited behavior patterns or instincts. » ይላሉ በማለት ይናገራል፡፡

ጥቅሱ በሁለት ጎራ ያሉ ሃሰቦችን የሚያሳይ ነው፡፡ የመጀመሪያው ወገን ባህል የሚለውን ሃሳብ ከተፈጥሮ ስጦታ ጋር የሚያይዝ ሲሆን በውስጡም ሰው ባህል ይኖረው ዘንድ ወይም አካባቢውን ባህል አድርጎ ይቀበል ዘንድ ይዞት የሚወለደው ተፈጥሮአዊ አቅም ነው የሚል ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ሁለተኛው ሃሳብ ባህል ሰው ከአካባቢው የሚማረው እንጂ ይዞት የሚወለደው አይደለም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን በሁለቱ ሀሳቦች መካከል ምንም እንኳን ልዩነት ያለ ቢመስልም ዞሮዞሮ ሁለቱም ሃሳቦች ሰው ባህልን የሚማረው ነገር እንደሆነ ነው የሚገልጹት፡፡ ይህ አከራካሪ ሃሳብ እንዳለ ሆኖ ግን ባህል የሚለውን ሃሳብ እንዴት መረዳት እንደሚቻል የሚገልፀው Wikipidia (The free Encyclopedia),(2007) ባህልን ለመረዳት ባህል፣ የወል የሆነውን መንገድ በመማር ብቻ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩ እሴቶች (values)፣ ደንቦች (norms)፣ ማህበራዊ ተቋማት (institutions) ጥንታዊ የእጅስራዎች (artificts) የተባሉ መሰረታዊ ነገሮችን የሚይዝ ጽንሰ ሀሳብ እንደሆነ መገንዘብ ይሻላል ይላል፡፡

እነዚህንም ሃሳቦች ሲያብራራ እሴቶች፣በህይወት ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦችን የሚይዙና ሌሎችን የባህል ክፍሎች የሚመሩ ናቸው፡፡ ልምዶች፣ ደግሞ አንድ ህዝብ ሊኖረው ይገባል ተብለው የሚገመቱ ግምቶችን ይይዛሉ፡፡ እነዚህ ግምቶች እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ደንብ እንዲያከብር የማስገደድ ባህርይ አላቸው፡፡ የሚያስገድዱት ልማዶች

ደግሞ ምንም እንኳን ያልተጻፉ ቢሆኑ የህግነት ደረጃ አላቸው:: ማህበራዊ ተቋማት የሚባሉት ደግሞ እሴቶችና ደንቦች የሚፈጥሯቸው የማህበረሰብ መዋቅሮች ናቸው:: ጥንታዊ የእጅ ስራዎች ደግሞ ከእሴቶችና ደንቦች የሚወጡ ነገሮች ወይም ባህላዊ ቁሶች ናቸው የሚለውን ትንታኔ አቅርቧል::

በአጠቃላይ ባህል፣ የሚለው ሃሳብ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከስፋቱ የተነሳ ይህ ነው የሚል አንድ ወጥ ብያኔ መስጠት የሚያስቸግር ቢሆንም ጽንሰ ሀሳቡን ለመረዳት ግን አንድ ትውልድ እለቱን በራሱ ጊዜ የፈጠራቸው ሳይሆኑ ከቀዳሚው ትውልድ የሚማራቸውን እሴቶች፣ ደንቦች፣ ማህበራዊ ተቋማትና፣ ጥንታዊ የእጅ ስራዎችን የያዘ መሆኑን መገንዘብ የተሻለ መሆኑን ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት ይቻላል::

ከእነዚህ ባህልን ለመግለጽ ከቀረቡት አራት መሰረተ ነገሮች እይታን ጠበብ በማድረግ ወደ ቁሳዊ ባህል ሲወረድ ደግሞ (የዚህ ጥናት ትኩረት ቁሳዊ ባህል ላይ ነውና) ቁሳዊ ባህል ሲጠና ቁሱ ብቻ ሳይሆን ከቁሱ ባሻገር የቁሱ አሰራር፣ ቁሱ እንዲፈጠር ያደረጉት የማህበረሰቡ እሴቶች፣ ደንቦችና ማህበራዊ ተቋማቱ ሁሉ ይታያሉ ይህ ሲሆን በቁሱ አማካኝነት የማህበረሰቡን ባህል መገንዘብ ይቻላል:: Wikipedia (2007:213) ይህንን ሀሳብ «. . . "Culture" to refere not only to consumption goods ,dut to the general process which produce such goods and give them meaning ,and to the social relationships and practice in which such objects and processes became embedded. » ሲል ይደግፈዋል::

በአጠቃላይ እስካሁን ከተባለው ሃሳብ ለመረዳት የሚቻለው ባህል የአንድ ማህበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሃብት መሆኑና ይህ ሃብት ደግሞ የማህበረሰቡ እሴቶች፣ ደንቦች፣ ማህበራዊ ተቋማትና የእጅ ስራዎች ህብር ሲሆን እነዚህ መሰረተ ነገሮች ደግሞ አንዱ በአንዱ ላይ ተመስርተው የቆሙ መሆናቸውን ነው:: ከዚህ በመነሳት ከእነዚህ አራት መሰረተ ነገሮች የተገነባው ባህል ከቤቶች ጋር ያለውን ንክኪ ስንመለከት እንደ አየር ንብረት ሁሉ በባህላዊ ቤቶች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ሆኖ እናገኘዋለን::

የተለያዩ ሰዎች ባህል በባህላዊ ቤቶች ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል እንደሆነ ነው የሚናገሩት:: ለምሳሌ Makonnen (1964) የአየር ንብረት በሚፈጥረው ተፅዕኖ የተነሳ የተወሰኑ የግንባታ ቁሶች በተወሰነ ክልል ብቻ እንዲኖሩና ቤት ሰሪዎች የሰሩትን እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል:: ይህ ብቻም ሳይሆን ሰዎች በአካባቢው የሚገኙ የተለያዩ የግንባታ ቁሶች እንዴት በአንድ ላይ ሆነው ቤት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይማራሉ:: ይህንንም ቀስ በቀስ በልምድ እየተመሩ አሰራሩ ይለመድና ባህል ይሆናል:: ከዚህ በኋላ ሁሉም ቤቶች በተጀመረው መንገድና በተጀመረበት ቁስ ብቻ ይሰራሉ:: ምክንያቱም ሌላ መንገድ ስላልተሞከረ አስተማማኙ የተሞከረው ይሆናል በማለት ቤቶች ከአየርንብረት በተጨማሪ

ባህል ተፅዕኖ እንደሚያሳድርባቸው ይገልጻሉ:: ከዚህም የአየር ንብረትና ባህል በባህላዊ ቤቶች ግንባታ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ ነገሮች መሆናቸው ነው መረዳት የሚቻለው:: ማለትም የአንድ አካባቢ የአየርንብረት፤ ዝናቡን፣ ፀሐዩንና ነፋሱን ይወስናል:: እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ በተራቸው በዕፅዋት አበቃቀል፣ በአፈርና በድንጋይ ፀባይ ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ይኖራል:: ይህ ሲሆን ደግሞ የአካባቢው ማህበረሰብ ቤቶችን ለመስራት አካባቢው የሰጠውንና የተሻሉ የሚላቸውን ቁሶች ሃገረሰባዊ ዕውቀቱን ተጠቅሞ ይሰራል:: በአንድ አካባቢ ቤቶችን ለመገንባት አገልግሎት ላይ የዋለው ቁስ ደግሞ ማህበረሰቡ ካልተሞከረው ይልቅ በተሞከረው መስራት የተሻለ ነው ብሎ ስለሚያስብ በዚያው በተጀመረበት ቁስ ቤቶች ይሰራሉ:: ይህም የዚያ አካባቢ ቤቶች መለያና የማህበረሰቡም የቤት አሰራር ባህል ይሆናል::

### 3.2.1.3 ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ እቃዎች

ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎችም ሆኑ ሃገረሰባዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች እነዚህ ናቸው ብሎ መዘርዘሩ ቀላል ጉዳይ አይደለም:: ምክንያቱም ቁሶቹ የሚሰሩባቸውን ጥሬ ዕቃዎች የሚወስኑ አያሌ ጉዳዮች አሉና:: ነገር ግን የግድ ሊያስማማ የሚችለው ነገር የጥሬ ዕቃዎች ሃገርበቀልነት ነው:: ምክንያቱም የቤቶች ወይም የእጅ ስራዎች ሃገረሰባዊነት ምንጩ የሚሰሩበት ጥሬ ዕቃ ጭምር ነውና:: ከዚህ ጋር በተያያዘም የቤቶችም መስሪያ ቁሶች ምርጫ በምን ላይ እንደሚመሰረት Oring (1986፡ 209) «Many objects especially larger objects like houses, tend to have adierct relationship to the place where they are found .They become a built land scape . The constraction and materials of the built land scape show the character of human relation ship to the environment » በማለት ሲገልጹ Glassie. (199፤ ፣237) ደግሞ «The meanings that lie in the selection of materials are socialand economic as well as environmental. But the environment sets the stakes. Living wisely in atight place, people learn the environment. They know how to select from it the right materials for the job. The prime virtue in materials their ability to alter the climate ,shaping alittel environment with in which architecture, which all of them do in bad weather. Their actions often glide out of the pragmatic and into the aesthetic » ሲሉ ለባህላዊ ቤቶች መስሪያ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች ትርጉም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ በተለይም አካባቢያዊ መልክ አላቸው ይላሉ::በመሆኑም ከጥቅሶች መረዳት የሚቻለው ነገር ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ቁሶችና ቁሶችም የሚይዙት ትርጉም አካባቢያዊ /ሃገር በቀል/ መሆናቸውን ነው:: ከዚህም ጋር በተያያዘ Makonnen (1964፣ 110) «የኢትዮጵያ ባህላዊ ቤቶች

መገንቢያ ጥሬ ዕቃዎች» በሚል ንዑስ ርዕስ ስር እንዳሰፈሩት፣ በኢትዮጵያ ለባህላዊ ቤቶች ግንባታ የሚውሉት የግንባታ ቁሶች ድንጋይ፣ ጭቃ፣ እንጨት፣ ሳር፣ ሸንበቆና ቅጠል ናቸው ሲሉ ይዘረዝሩና የቁሶችን አገልግሎት በሚከተለው መልክ ይገልፃሉ፡፡

ድንጋይ፡- በቀላሉ በሚገኝበት አካባቢ ለግድግዳነት ያገለግላል፡፡ በኢትዮጵያ የተለመዱትና ግልጋሎት የሚሰጡት የድንጋይ አይነቶች ባልጩታማ ጥቁር ድንጋይ፣ ደቃቅ (ትንሽ) ድንጋይና ጥቁር (ባርያ) ድንጋይ ናቸው፡፡ በድንጋይ የተገነባ ግድግዳ ድንጋዮች እርስ በእርስ የሚጣበቁት በጭቃ ነው፡፡ ነገር ግን የጭቃው የማጣበቅ አቅም ደካማ ሲሆን በዝናብ ሊታጠብ ይችላል፡፡

ጭቃ፡- አፈርን ከውሃ ጋር ቀላቅሎ በማቡካት ወደ ቤቱ ነፋስ፣ ፀሐይና ሌሎች ነገሮች ወደ ውስጥ እንዳይገቡ ግድግዳው ላይ የሚለጠፍ የቤት መስሪያ ቁስ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ የአፈር አይነቶች ቀይ ወይም የሸክላ አፈርና ጥቁር አፈር ናቸው፡፡ ለጭቃ መስሪያ የሚመረጠው ግን ቀይ አፈር ነው፡፡

እንጨት፡- እንጨት በሚገኝበት አካባቢ በግንባታ ቁስነቱ በጣም የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ እንጨት አካባቢው ሊያበቅለው ከቻለ ርካሽና ለቤቱ ረጅም ዕድሜ የሚሰጥ ቁስ ነው፡፡ እንጨት ለግድግዳና ለጣሪያ መስሪያ የሚያገለግል ሲሆን በእንጨት የተሰራ ግድግዳ ሙቀትና ብርድ ለመከላከል እንዲያስችል በጭቃ ይሸፈናል፤ ዕድ፣ ዝግባ፣ ሞላልካ፣ አዛምር፣ ብሳና፣ ሎል፣ ኮርች፣ ኮሶ፣ በሮራ፣ ወይራ፣ ካሃረት፣ ጥቁር እንጨት፣ አልጊ፣ ዶቅማ በኢትዮጵያ የሚበቅሉና በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች ባህላዊ ቤቶችን ለመስራት የሚያገለግሉ ዛፎች ናቸው፡፡

ሳሮች ሸንበቆዎችና ቅጠሎች፡- ሳር፣ በመሰረቱ ለጣሪያ መክደኛ ያገለግላል፡፡ ጭቃ የማጣበቅ አቅም እንዲኖረው ከጭቃ ጋር አብሮ ይቦካል፡፡ ሸንበቆና ቅጠል ደግሞ ሳር በሌለበት አካባቢ ለጣሪያ መክደኛ ያገለግላሉ፡፡ በሙቀትና ደረቅ የአየር ንብረት ደግሞ እንጨት ስለማይገኝ እነዚህ ቁሶች ለግድግዳነት ያገለግላሉ፡፡

ቀርከሃ፡- በሃገሪቷ ደቡባዊና ምዕራባዊ ድንበሮች የተለመደ የቤት መስሪያና በብዛት የሚገኝ የቤት መስሪያ ቁስ ነው፡፡ ነገር ግን ረጅም ዕድሜ የሌለውና በነፍሳቶች የሚጠቃ ነው፡፡

### 3.2.2 ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ (Folk Crafts)

ሃገረሰባዊ የእጅ ስራ Dorson (1972) በቁሳዊ ባህል ስር ይጠናሉ ሲሉ ከሚዘረዝሯቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው። የዚህን ዘርፍ የፅንሰ ሐሳብ ብያኔ በተመለከተ እንደሚገልጹት ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ባህላዊ የሆኑትንና ማንም ሰው በግልጽ ሊረዳው የሚችለው፣ የአሰራር ዘዴያቸውና ቅርፃቸውም በቅርብ ከተሰሩት ይልቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገሩ የቆዩትን የሚመለከት እንደሆነ ነው የሚናገሩት።

በእርግጥ ይህ ሃሳብ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎችን ከጥንታዊነት ጋር አያይዞ ለመግለጽ የሞከረ ቢመስልም ቁሶችን ባህላዊ ወይም ሃገረሰባዊ ናቸው ለማለት ማርጀታቸውን ወይም አዲስነታቸውን መነሻ ማድረግ አይገባም። ይልቁንስ ከባህሉ መሰረታዊ ነገር አኳያ ማየቱ አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ፣ ምንም እንኳን በጥንታዊ መሳሪያዎችና በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች መካከል ግልጽ የሆነ ጠንካራ ግንኙነት ቢኖርም አንድ ሰው ማንኛውንም አሮጌ ነገር ሀገረሰባዊ ነው ወይም ማንኛውንም አዲስ ነገር ሃገረሰባዊ አይደለም ብሎ አይገምትም ማለት አይደለም ሊገምት ይችላል። ነገር ግን ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ሀገረሰባዊ የሚባሉት የማህበረሰቡ ከፍተኛ አባላትን ትምህርት፣ የቀለም ትምህርት ወይም የተወሳሰበ ሙያዊ ተስተላልፎ ከሌለባቸው ብቻ ነው(Dorson;1972) ሲሉ ጨምረው ይገልፃሉ።

Oring (1986: 216) በበኩላቸው «The designation "folk objects" is not restricted to objects only from thee past. New folk objects are continually emerging. » ሲሉ የሚያቀርቡት ሃሳብ የ«Dorson» ን ሃሳብ የሚደግፍ ነው። በመሆኑም ፀሐፊዎች በዚህ አባባላቸው ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የሚባሉት ማንነታቸው ሊታወቅ የሚችለውና ሃገረሰባዊ ካልሆኑት የእጅ ስራዎች ሊለዩ የሚችሉት በእድሜያቸው አጭርነትና ረጅምነት አለመሆኑን የገለፁ ሲሆን ከዚህ ባሻገር ግን ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የሚባሉት የማህበረሰቡን ማንነት የሚናገሩትን፣ የሰዎችን የፈጠራ ችሎታ የሚያንፀባርቁትን፣ የማህበረሰቡን ባህል ወግና ልማድ ጠብቀው የተሰሩትን፣ ተስተላልፏቸውም ኢመደበኛ በሆነ መልኩ ከቤተሰብ ወደ ቤተሰብ ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሆነውን ቁሶችን እንደሆነ ያስገነዝባሉ።

እንግዲህ ይህንን አባባል ይዘን የሀገራችን ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ስንፈትሽ ሰዎች ለዕለት ተግባራቸው የሚገለገሉባቸው፣ ርቃናቸውን ለመሸፈን የሚሰሯቸውና ለማህበረሰቡ ግልጋሎት የሚሰጡባቸው እንዲሁም የራሳቸው የሰሪዎች ብሎም ሰሪዎች የበቀሉበት የጠቅላላው ማህበረሰብ መገለጫ የሆኑና ሰሪዎችም ኢመደበኛ በሆነ መልኩ ከቀዳሚው ትውልድ በተለይም ከቤተሰቦቻቸው ወርሰው የሰሯቸውና እየሰሯቸው ያሉ

በርካታ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች መኖራቸውን እንገነዘባለን:: እነዚህም የእጅ ስራዎች በተለያዩ አገር በቀል ጥሬ ዕቃዎች ይሰራሉ:: ቀጥለን እንያቸው:-

### 3.2.2.1 ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች

ቀደም ሲል «ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ እቃዎች» በሚለው ንዑስ ርዕስ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎችም ሆኑ ሃገረሰባዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ እቃዎች ሃገር በቀል እንደሆኑ ተገልጧል:: ወደ ሃገራችንም ስንመጣ በርካታ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ያሉ ሲሆን እነርሱም የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች ሃገርበቀል ናቸው:: ለምሳሌ ያህል ብንዘረዝር የሸክላ ስራዎች (ድስት፣ ምጣድ፣ እንስራ) የቆዳ ውጤቶች (ጀንዲ፣ ላምነት፣ መጫኛ) የብረት ስራዎች (ማረሻ፣ መጥረቢያ፣ ማጭድ) የስፌት የቤት ዕቃዎች (ሞሰብ፣ አገልግል፣ ሰፌድ) ጌጣጌጦች (አንባር፣ ጉትቻ፣ ቀለበት) ይገኙበታል:: ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የሚሰሩባቸውን ጥሬ እቃዎች በተለይም በኢትዮጵያ ምን ምን ናቸው የሚለውን ጉዳይ የበለጠ ለመረዳት ኢትዮጵያውያን የእጅ ስራዎች እንዳሏቸው እነዚህን የእጅ ስራዎች ደግሞ ከምን እንደሚሰሯቸው የሚገልጸውን ቀጣዩን ጥቅስ መመልከት ጥሩ ማስረጃ ማግኘት ነው:-

> Like the Europeans before the Industrial revolution, the Ethiopian people at any early date evolved a handi craft industry which met the every day needsof the population.They worked In iron,making knives,swords,spear-heads,plaughshares and other implements. They span and wove both cotton and wool,producing exellent and often beautiful clothing.They preserved and tanning ox hides ,sheep and other skins successfully,and manufactured shields,scabbards and book covers,as well as saddles,bridles and halters for their mules and horses.They also produced good quality pots and jars.Wove attractves wicker baskets,manufactured useful articles of horn,and fashioned exguisite gold, silver and bronze ornaments and crosses,among the handicrafts which caught the eye of visiting authors were articles of apparel made from textiles and skins, carpets of many colours, baskets of various shapes and sizes, illuminated manuscripts and parchments of distinction,beautiful drinking horns,fine jewellery and knives, swords and spears of every description (Richard and Rita, 1964;221).

ይህ ከላይ የቀረበው ጥቅስ በኢትዮጵያ የሚሰሩ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎችን የሚያሳይ ሲሆን እነዚህ የእጅ ስራዎች የሚሰሩባቸውን ጥሬ ዕቃዎችም ይገልጻል:: ጠቅለል ተደርጎ ባህላዊ የእጅ ስራዎች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች ሲታዩ ደግሞ እንጨት፣ ብረት፣ ጥጥና ቆዳ በበርካታ ሃገራት ውስጥ የጋራ የሆኑ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች መስሪያ ጥሬ ዕቃዎች መሆናቸውን Dorson (1972) ይገልጻሉ::

### 3.2.2.2. በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ነገሮች

ይህ ስራ ከባህላዊ ቤቶች በተጨማሪ ከሸክላ በተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች ላይም የሚያተኩር መሆኑ ቀደም ብሎ ተጠቅሷል፡፡ እናም ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ስር የሚመደቡ በመሆኑ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በትኩረት የሚነሣው ነገር በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ጉዳይ ነው፡፡

ሃገረሰባዊ የእጅ ስራ ትናንት ነበር፤ ዛሬም አለ፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ቀደምት ቁሶች ትናንትን አልፈው ዛሬ ላይ ሲደርሱ በነበሩበት መልክ እንዳሉ መጥተዋል ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም አንድም ተለዋዋጭነት የፎክሎር ዋነኛ ባህርይ በመሆኑ ሲሆን እንዲሁም ሌሎች አያሌ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉና ነው፡፡ ከዚህም አንጻር Dorson (1972) ሮበርትን ጠቅሰው በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ላይ ተጽዕኖ አሳድረዋል ሲሉ የሚዘረዝሯቸው ሀሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል፡-

### 3.2.2..2.1 የኢንዱስትሪ አብዮት

ዛሬ ዛሬ የኢንዱስትሪው አብዮት በእጅ ስራዎች ላይ በጠቅላላው ተፅእኖ ያሳደረ ሲሆን ለእጅ ስራ ባለሙያዎች ደግሞ አዋኪ ሆኗል፡፡ በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን የፋብሪካ ዕቃዎች ወደ ገጠሩ ክፍል መጉረፍ ሲጀምሩ በእርግጥም የእጅ ስራ ባለሙያዎች ተጎድተዋል፡፡ የፋብሪካ ውጤት የሆኑትን የፋብሪካ ዕቃዎች መግዛት መጀመራቸው የባህላዊ የእጅ ስራ ባለሙያዎች ስራቸውን እንዲያቆሙና የተበላሹ እቃዎችን ወደ መጠገን እንዲሄዱ አድርጓቸዋል፡፡

### 3.2.2.2.2 የባህላዊ የእጅ ስራ ባለሙያዎች ትኩረት መቀየር

የተጠቃሚን ርካሽ የፋብሪካ ዕቃዎችን የመግዛት ፍላጎት ተከትሎ ባህላዊ የእጅ ስራ ባለሙያዎች የተበላሹ ዕቃዎችን ወደ መጠገን ከመምጣታቸው በላይ ለባህላዊ የእጅ ስራዎች ህልውና መቀጠል ሲሉ የእቃዎችን አሰራር ዘዴ መለወጥም ግድ ብሏቸዋል፡፡ በብዙ አካባቢዎች የቁምሳጥን ስራ አዲስ ነገሮችን ከመስራት ይልቅ እቃዎችን መጠገንና እቃዎች የተሸፈኑባቸውን አሮጌ ልብሶች በአዲስ መቀየር የተለመደ ስራ ሲሆን አንጥረኛ ውም እንዲሁ ብዙ ጊዜውን የሚያጠፋው ዘመናዊ እቃዎችንና መሳሪያዎችን በመበየድ ነው፡፡ ይህም የባለሙያዎች ተግባር መቀየሩን ያሳያል፡፡

### 3.2.2.2.3 የኢኮኖሚና ቴክኖሎጂ ተፅዕኖ

የእጅ ስራ ባለሙያዎች በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ሁኔታዎችን ለእነሱ እንደሚበጁ አድርገው ያመቻቻሉ። ለምሳሌ በደቡብ ህንድ የጨርቅ መስሪያ ጥሬ ዕቃዎች ርካሽ በመሆናቸው ጥቂት ሸማኔዎች በሸማ ዕቃዎች የጨርቅ ስጋጃዎችን ይሰራሉ። ከቴክኖሎጂ አንፃር ዘመናዊ ማሽኖች የእጅ ስራ ባለሙያዎች የሚሰሯቸውን ቁሶች መስራት አለመቻላቸው የእጅ ስራ ባለሙያዎች እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። ለምሳሌ ስፌት (Basket) የሚሰራ ማሽን የለም። በመሆኑም ምንም እንኳን ስፌቶች በፋብሪካ በተሰሩ የወረቀት ወይም የላስቲክ ዕቃዎች ቢተኩ፣ የውጭ ስፌቶች ወደ ሃገር ውስጥ ቢገቡና ከሃገረሰብ የእጅ ስራ ባለሙያዎች ስራዎች ይልቅ በርካሽ ቢሸጡ በተለያዩ አካባቢዎች የእጅ ስራ ባለሙያዎች እየተስፋፉ ነው።

### 3.2.2.2.4 የገበያ ተፅዕኖ

በበርካታ ስፍራዎች ለብዙ ሸማቾች ባህላዊ የእጅ ስራዎች ከፋብሪካ ውጤቶች ይልቅ ክብር ወይም ውበት ናቸው። በዚህም ምክንያት ብዙ ቱሪስቶችና የእጅ ስራ ባለሙያዎች በሚገኙበት አካባቢ የእጅ ስራ መሸጫ ሱቆች ይስፋፋሉ። ነገር ግን በእነዚህ ቦታዎች የሚገኙ ምርቶች ሁልጊዜም ባህላዊ ላይሆኑ ይችላሉ። በአንዳንድ አጋጣሚዎች የእጅ ስራ ባለሙያዎች ስራዎችን ከትምህርት ቤት ወይም በሌላ መደበኛ በሆነ መንገድ ይማሩዋቸውና የእጅ ስራዎች ከገበያ አንፃር የሚዘጋጁ እንጂ ባህላዊውን ቅርጽ ያልተከተሉ ይሆናሉ።

### 3.2.2.2.5 የሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ደረጃ ወደ ዘመናዊ ጥበብ (Modern art) ከፍ ማለት

የሸክላ ስራ፣ ሽመና፣ አንጥረኝነትና ሌሎች በርካታ የእጅ ስራዎች ደረጃቸው «ወደ ዘመናዊ ጥበብ» ያደገ ሲሆን ትምህርታቸውም በኪነጥበብ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኝ ነው። እነዚህ ደግሞ ቴክኒካቸው ባህላዊ ሆኖ ትኩረታቸው ግን ከባህላዊነቱ ይልቅ በፈጠራው ላይ ነው።

### 3.2.2.2.6 በርካታ የእጅ ስራዎች እንደትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ መሰራታቸው

አሁን አሁን ብዙ የእጅ ስራዎች እንደ ትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ እየተሰሩ ነው። ምክንያቱም በርካታ ግለሰቦች አገልግሎት ሰጪ ወይም የጌጥ ዕቃዎችን ለራሳቸው ወይም ለጓደኞቻቸው በመስራት ትልቅ ግለሰባዊ እርካታ ማግኘት ይፈልጋሉ። ብዙ

መጽሐፎች በሽመና፣ በቤት ቁሳቁስ ስራ፣ በማዕድናት አንጥረኝነትና በመሳስሉት ላይ ያሰራር መመሪያዎችንና ቅርፆችን በትርፍ ጊዜያቸው ለሚሰሩ ሰዎች ያቀርባሉ:: ይህ መሆኑ የእቃዎችን ተወዳጅነትና የሰዎችን ባህላዊ እቃዎችን የመስራት ፍላጎት የሚያሳይ ነው:: ነገር ግን ሰዎች የእቃዎችን ቅርጽና የአሰራር ዘዴ ከመጽሐፍት ሲማሩ ዕቃዎች ባህላዊነታቸውን ያጣሉ:: በመሆኑም ለጊዜ ማሳለፊያ የሚሰሩ ዕቃዎችን ሙሉ በሙሉ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ናቸው ማለት ይከብዳል::

## 3.3 የቁሳዊ ባህል ሰሪዎች (የቁሳዊ ባህል ባለሙያዎች)

በጠቅላላው የቁሳዊ ባህል ሰሪዎችን (ባለሙያዎችን) ማንነት ለመገንዘብ ሲባል የተለያዩ የእጅ ስራ ውጤቶችን ወይም ሌሎችን የዘርፉን ንኡሳን ክፍሎች ስም በየተራ እየጠራን «ይህ የማን ስራ ነው?» ወይም «ይህንን ነገር ማን ነው የሰራው?» ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ «የእከሌ» ወይም «የእከሊት» አለበለዚያ ደግሞ «እከሌ የተባለው» የማህበረሰብ ክፍል የሚሉ ብዙም ሲገርሙን የማይችሉ መልሶችን በየአገሩ ልናገኝ እንችላለን:: ይህ መልስም እምብዛም የማያስገርመው በምን ምክንያት ነው? ብለን ብንጠይቅ በብዙ ማህበረሰቦች በተለይም በኢትዮጵያ የቁሳዊ ባህል ባለሙያነት በጾታ ወይም በጎሳ የሚከፈል በመሆኑ ነው:: Siliverman (1999) ስለዚህ ጉዳይ ሲገልጹ በጠቅላላው ኢትዮጵያ የፈጠራ ሂደት በተወሰነ ቡድን ውስጥ የተወሰነ ነው:: ጥቂት ልማዶች በማንኛውም ሰው ይተገበራሉ:: ነገር ግን የቁሳዊ ባህል ባለሙያነት በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ይለያል:: እነርሱም ፆታና ጎሳ ናቸው:: በብዙ ማህበረሰቦች የሴቶችና የወንዶች ተግባራት ግልጽ ልዩነት አላቸው:: ማህበራዊ ማንነት ለሚመረቱት ነገሮች መሰረት ይሆናል:: ለምሳሌ በቦረናና በሃረሪ ማህበረሰብ ስፌት መስፋት የሴቶች ተግባር ነው ይላሉ::

ይህ ጥቅስ በቁሳዊ ባህል ባለሙያነት ላይ «ቁሶችን ማን ይሰራቸዋል?» ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ነው:: ከጥቅሱ መረዳት የሚቻለው ነገር በእጅ ስራና አሰራር ሂደት «ይህ የሴቶች» «ይህኛው ደግሞ የወንዶች ነው» የሚባሉ ስራዎች እንዳሉና ጎሳም ለአንድ አይነት የቁሳዊ ባህል ባለሙያነት ባለቤትነትን የሚሰጥ መሆኑን ነው:: ለምሳሌ ምስጌ (1979) «የወይጦ ነገድ አጭር ታሪክ ና ባህል» በሚል ፅሁፋቸው በአማራ ክልል በባህርዳርና ዙሪያው የጣናን ሐይቅ ከብቦ የሚኖር ከአማራው ህዝብ በጋብቻ በሃይማኖትና በባህል የተገለለ «ወይጦ» የተባለ ጎሳ ባህላዊ ወፍጮንና ታንኳን በመስራት እንደሚታወቅና ሌላው ማህበረሰብም የእነዚህን ባህላዊ የእጅ ስራዎች ባለቤትነት ለወይጦ ጎሳ ሰጥቶ ለረጅም ዘመን ኖሯል ሲሉ የሚገልፁት ሀሳብ የላይኛውን አባባል የሚደግፍ ነው::

ነገር ግን እዚህ ላይ ሳይነሳ የማይታለፈው ጉዳይ አሁን አሁን ቀደም ሲል «በሃገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች» በሚል ንዑስ ርዕስ ስር በተነሱት አይነት ሀሳቦች የቁሳዊ ባህል ባለሙያነት ከሴቶች ወደ ወንዶች ከወንዶች ወደ ሴቶች ሊቀያየርና ከአንድ ጎሳ ወደ ሌላ ሊሸጋገር እንደሚችል ነው።

## 3.4 የቁሳዊ ባህል ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ

ቁሳዊ ባህሎች እንኳንስ እንደ እኛ ባለች በስልጣኔ ባልገፉችና በኢንዱስትሪ ሀብቷ ባልበለፀገች አይነት አገር ይቅርና እጅግ በሰለጠኑት እንኳን ከእለት እለት፣ ጠቀሜታቸውና ተፈላጊነታቸው እየጨመረ እንደመጣ ነው መገንዘብ የሚቻለው። ለምሳሌ እንደ አሜሪካና እንግሊዝ ባሉ ሀገሮች ለባህላዊ የእጅ ስራዎች እድገት ሲባል ስልጠና እየተሰጠ እንደሆነ Dorson (1972:225) «በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፣ እንግሊዝና በስካንዲኒቪያን ሃገሮች ባህላዊ የእደ ጥበብ ትምህርትቤቶች ግልጽ በሆነ መልኩ መመሪያዎችንና መጽሐፎችን እያሳተሙ ለሙያው አፍቃሪያን ትምህርትና ስልጠና ይሰጣሉ» ሲሉ ይገልጻሉ። ይህ ጥቅስም ባህላዊ የእጅ ስራዎች በእያንዳንዱ አገር ማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ጉልህ ስፍራ የሚያሳይ ነው። እንደዚሁ ሁሉ ወደ እኛ ሃገር ስንመጣ ቁሳዊ ባህሎች ለማህበረሰቡ እየሰጡ ያሉት ጥቅም እጅግ ብዙ ነው። ሰው በባህላዊ ልብሶችና ጌጦች ያጌጣል፣ በባህላዊ ቤቶች ይኖራል፣ በባህላዊ የእጅ ስራዎች የእለት ተእለት ተግባሩን ያከናውናል። ነገር ግን ሁሉም ሰው የሚገለገለው ራሱ ባልሰራው ዕቃ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በተለይ ባህላዊ የእጅ ስራዎች በአብዛኛው የአንድ ጎሳ የስራ ውጤቶች ናቸው። እንዲያውም ልብ ብለን ብንመለከት እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ያለው ሃገረሰባዊ የእጅ ስራ ሙያ በአብዛኛው በአንድ የትውልድ ሃረግ ውስጥ ሲተላለፍ የቆየ ነው። ነገር ግን ይህ ስራን ለተወሰነ ክፍል ከመተው ሌላ ባለሙያዎችን በማህበረሰቡ የተለየ ማህበራዊ ደረጃ እንደሚሰጣቸው የሚገልፁ ፀሃፍት ብዙ ናቸው።

ማህበረሰቡ ባለሙያዎች ከሚሰሩት ነገር (ከሙያቸው) አንጻር ሙያውን የሚያንቋሽሹ መጠሪያዎችን በመስጠት ሰሪዎችን ከጋብቻም ሆነ ከሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶች ሲያገልላቸው ኖሯል። ይህም በሰራተኞች ላይ ከፍተኛ የሆነ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ጫና ይፈጥርባቸዋል። «የባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ» በሚል ርዕስ ስለ ኢትዮጵያ የእጅ ስራ ባለሙያዎች የተጻፉ የተለያዩ ፅሁፎችም ይህንን ነው የሚያሳዩት። ለምሳሌ ስለ ኮንሶ የእጅ ስራ ባለሙያዎች Hallpike (1972) እንደገለጹት የኮንሶ የእጅ ስራ ባለሙያዎች ከሌላው ማህበረሰብ ተገልለው ነው የሚኖሩት እነዚህ ቡድኖች የእጅ ስራን ከመስራታቸው ውጭ በአለባበሳቸውም ሆነ በአነጋገራቸው ወይም በቤቶቻቸው

አሰራር ከሌላው ማህበረሰብ አይለዩም:: ግን በማንኛውም ማህበራዊ ግንኙነት ከሌላው ማህበረሰብ ተገልለዋል:: በጋብቻም አይገናኙም ቀደምት ትውልዶቻቸውም እንዲሁ ነው የኖሩት ይላሉ::

እንዲሁም Silverman (1999) በጠቅላላው ስለ ኢትዮጵያ የእጅ ስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ ሲገልጹ ቁሶችን የሚያመርቱ ሰዎች ማህበራዊ ደረጃቸው ከባህል ባህል ይለያያል:: በአብዛኛው ግን እነዚህ ቡድኖች የተገለሉ ናቸው:: ቡድኖች በሚያመርቱት ቁስ አሰባሳቢነት የራሳቸውን ቡድን መስርተው ይኖራሉ:: በተለይ ሸክላ ሰሪዎች፣ የቆዳ ሰራተኞችና አንጥረኞች ከሌላው ማህበረሰብ ተለይቶ የሚኖር ማህበራዊ (አልፎ አልፎ የጎሳ) ቡድን አላቸው:: ካሉ በኋላ ከዚሁ በማስከተል እነዚህን ቡድኖች ከሌላው ማህበረሰብ የለዩአቸውን ጉዳዮች ይገልጻሉ:-

እነዚህ ቡድኖች በሌላው ማህበረሰብ የተገለሉ የሚያደርጋቸው ተፈጥሮአዊ ኃይል ያላቸው ተደርገው መታወቃቸው ነው:: ይህ ደግሞ ቡድኖችን በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ አንድ ያደርጋቸዋል:: ማህበረሰቡ እነዚህን ቡድኖች አፈርን ወደ እንስራ፣ ብረትን ወደ የምርትና የጦር መሳሪያ የመቀየር ኃይል አላቸው:: ይህ ኃይልም አደገኛ በመሆኑ ስህመም ብሎም ለሞት ያደርሳል በማለት ባለሙያዎችን ያገልላቸዋል:: በጠቅላላው ግን የእጅ ስራ ባለሙያዎች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ሁለት አይነት ገጽታ አላቸው:: በአንድ በኩል ማህበረሰቡ ስለእውቀታቸውና ስለሚያበረክቱት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ይፈልጋቸዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ይፈራቸዋል፣ ይንቃቸዋል፣ ሁል ጊዜ አግልሏቸው ይኖራል ሲሉ ይገልጻሉ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ደግሞ Alula (2001፣1) ስለ ሃገረሰባዊ ጥበብ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ ሲገልጹ:-

> Craft workers . . . play important roles in the Societys among whom they live ,and yet they have such alow status thast many of them are considered to be not real people by the majority aroundnthem. Three paradoxes lie at the heart of this incongruity between the roles and statuses of these minorities.Firstly, whereas their products are vital for rural liveihood , the producers tend to be looked down up on by the rest of society. Iron plough shares, hoes and sickeles are vital for agriculture;pottery is essential for processing food and carring water ;leather productes are used for sleeping mats,storing and transporting grain; and cotton cloth is basic for clothing.And yet the specalised workers who produce these items are generally despised.Secondly , there is a diparty between the ideological marginalisatino and distancing of thes groups on the one hand,and the practical reality of personalized dyadic relation between individual farmers and artisians on the other. The need for economic .social and cultural exchanges generates a continuous structured interaction, which belies the image of total exclusion and segregation.And thirdly,although the ostracized and excluding from many areas of social life, some of the mainority groups also play significant social and cultural roles,notabley at life-cycle events.From birth,through puberty and initiation,to marrige and funerals the marginalised in various societies, perform special

services as midwives, circumcisors, initiators, musicians, and grave diggers, they are thus important for the social reproduction of the dominant society ይላሉ::

በአጠቃላይ የቁሳዊ ባህል ባለሙያዎችን ማህበራዊ ደረጃ አስመልክቶ በርካታ ፀሀፍት የሚገልጹት ዝቅተኛ ማህበራዊ ደረጃ ያላቸው መሆኑን ነው::

## 3.5 ቁሳዊ ባህልን ለበለጠ ጥቅም ማዋል

በነጠላው ስለ ቁሳዊ ባህል በጠቅላላው ደግሞ ስለ ፎክሎር ያለውን የማህበረሰቡን ግንዛቤ አስመልክቶ በስፋት ጎልቶ የሚታየው አመለካከት ገንዘብነቱን «ያልተማረው» ወይም «ያልሰለጠነው» ሕዝብ ሀብት አድርጎ የመቁጠር ሁኔታ ነው:: ፊቃደ (1991) ይህንን ሃሳብ በ<u>የስነ ቃል መምሪያ</u> ውስጥ «የሰዎች የተሳሳተ ሃሳብ» ሲሉ ይገልጹታል::

ከዚህም አንጻር ይመስላል በእኛ ሃገር ብዙውን ጊዜ ቁሳዊ ባህሎች ግፋቢል በሙዚየም ውስጥ ተቀምጠው በቅርስነት ከመጎብኘት የተሻለ ዕድል ሲገጥማቸው አይታይም:: ይህም ቢሆን አፍን ሞልቶ ቁሳዊ ባህሎችን በቅርስነት ተቀምጠዋል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም:: እንዲያውም ቁሳዊ ባህሎች በሚገባ ተደራጅተው ተቀምጠዋል ብሎ ለመናገር ቦታዎችን መቁጠር ቢያስፈልግ ረጅም ጊዜና ብዙ ጉልበት የማያስፈልገው ጉዳይ ነው:: ይህ ሁኔታም በቁሳዊ ባህል ጥናት ላይ ምንም ያልተሰራ መሆኑን የሚጠቁም ነው ከማለት ባሻገር ቁሳዊ ባህሎች ላሉበት ማህበረሰብ አሁን ከሚሰጡት በተሻለ እንዴት ጥቅም ሊሰጡ ይችላሉ? የሚለውን የሚያሳስብ ነው::

በእርግጥ አንድ ማህበረሰብ ለቁሳዊ ባህሎች ህልውና ሲሰጥ ለራሱ የዕለት ከእለት ተግባር መከወኛ፣ ለመጊያጊያጪያና ለመደሰት ሲል እንጂ ምናልባት ቁሶች ከዘመን ተሻግረው ወይም የሌላ አካባቢ ሰዎችን ወደ እሱ ስበው ጥቅምን አገኝባቸዋለሁ ብሎ ላይሆን ይችላል:: ነገር ግን ቁሶች ዘመንንና ድንበርን መሻገራቸው፣ ካሉበት ሆነው ሌላውን ህዝብ መጥራታቸው አልቀረም:: በመሆኑም ቁሳዊ ባህሎች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በፎክሎርነታቸው ከሚሰጡት (የታወቀ) ጥቅም ሌላ ተጨባጭ የሆነ ጥቅምን የሚያበረክቱበት መንገድ ሊኖር ይገባል:: እንደዚያ ሲሆንም ነው የፎክሎር ጥናት ረብ ያለው የሚሆነው:: ማለትም ማህበረሰቡ የራሱ ከሆነው እውቀትና ፈጠራ የተሻለ ጥቅም ማየቱና ለስራው ዋጋ ማግኘቱ ብሎም ዕድገት ከሀገረሰባዊ ዕውቀት መመንጨቱን ሲያውቅ ለራሱ ያለው አመለካከት ከፍ ያለ ይሆናል፤ በማንነቱ ይኮራል፤ ዕውቀትንም መቀበል ብቻ ሳይሆን መስጠት እንደሚቻል ይገነዘባል:: ይህ ካልሆነ ግን እንደዛሬውና እንደዛሬ በፊቱ ሁሉ ፎክሎር ሲነሳ የማንኛውም ሰው ግንዛቤ «ፎክሎር ስላረጁ ባህሎች የሚወራበት፣ ያልተማረውና ያልሰለጠነው ህዝብ ሃብት ነው» የሚለውን አመለካከት መቅረፍ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል::

ነገር ግን ማንኛውም ፎክሎራዊ ጥናት እንደ ጥናት፣ ፎክሎር ከቅርስነት ባሻገር በርካታ ፋይዳዎች ያሉት ሃሳብ እንደሆነ ሊያሳይ ይገባል ምክንያቱም ፎክሎር አያሌ ፋይዳዎች አሉትና። ለምሳሌ ፈቃደ (1991) ስነቃል ከትምህርት፣ ከታሪክ ጥናት፣ ከስነ ፅሁፍ መሰረትነት፣ ከፖለቲካና ከልማት መስክ አንጻር ጠቀሜታዎች ያሉት እንደሆነ ይገልጻሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ደግሞ Jones, <u>Putting folklore to use</u> (1994) በተባለው መፅሐፋቸው ፎክሎር የማስተማር ዘዴን በማበልጸግ፣ ማህበራዊ ችግሮችን በመፍታት፣ ባህላዊ ቅርስን በመጠበቅ፣ የአኗኗርን ሁኔታ በማሻሻል (ለምሳሌ በጤናና ማንነትን በማዳበር ባለ እጅ ሙያውን በማነቃቃትና በማበረታታት ሊጠቅም ይችላል) ይላሉ።

በአጠቃላይ የፎክሎርን፤ ገላጭነት፣ ውብነት፣ የአስተሳሰብ ስልትነት፣ የእውቀት ክምችትነት፣ አውዳዊነት፣ ማህበራዊነትና ባህላዊነት ከመገንዘብ ባሻገር ለልማት፣ ለዕቅድ ማቀጃነት፣ ለአንድ ማህበረሰብ የወደፊት እድገት መሪነትና ለማህበረሰብ ኑሮ ማሻሻያነት ሊጠቅም እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል።

እንግዲህ እነዚህ ትውራዊ ዳራዎች ከመስክ የተገኙ መረጃዎች እየተገናዘቡ የሚተነተኑባቸው ሲሆኑ ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ ደግሞ ለመስክ ጥናት ስለተመረጠችው ዘጌ ባህረ ሰላጤና ማህበረሰቧ ይገለፃል።

ውስጥ አዘዋ ማርያም፣ አባጢ፣ ዑራ፣ ጋሚ፣ ዋሻ፣ መቀላሜና ብሮራሜ የሚሰኙ ጎጦች ይገኛሉ (ግብርና ቢሮ፣ 1994) ::

ዘጌ የሰባት ደብር አገር ናት በመባል ትታወቃለች:: ይህም ሲሆን የቻለው ቀደም ሲል አገር የሚወሰነው በደብር ስለነበር ነው:: የደብሮች ስምም መሃል ዘጌ ጊዮርጊስ፣ አቡነ በትረማርያም፣ አዝዋ ማርያም፣ ዑራ ኪዳነምህረት፣ ደብረስላሴ ፣ ይጋንዳ ተክለኃይማኖትና ፋሬ ማርያም ናቸው (ገበየሁ፣ 1996) ::

የዘጌ ሰላጤ ወይናደጋ የአየር ንብረት ሲኖራት (አሁን ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ የአየር ሁኔታው እየተለወጠ እንደሆነ ነው ነዋሪዎች የሚናገሩት ) ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ 1770-1960 ሜትር ነው:: ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ 1160 ሚሊ. ሜትር ሲሆን የሙቀት መጠኑ ከፍተኛው 26.7 $^{0}$ሴ ዝቅተኛው 11.78 $^{0}$ሴ ነው:: የመሬቱ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ Longitude 37 18 43 - 37 21 26 Latitude $11^{0}$ $41^{1}$ 00 - $11^{0}$ $43^{1}$ $00^{1}$ ሰሜን ነው (የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲና ቁጥጥር፣ 1999 ዓ.ም.)::

አቶ ጀመረ ክብረት የተባሉ የ60 ዓመት የሰላጤዋ ነዋሪና ሌሎች የቃል መረጃ አቀባዮች እንደሚናገሩት ሰላጤዋ ዘጌ የሚለውን ስም እንዴት ልታገኝ እንደቻለች የሚገልፁ ሁለት አፈታሪኮች አሉ:: የመጀመሪያው አፈታሪክ የዘጌን ሰላጤ ከእየሩሳሌም ጋር የሚያገናኝ ነው:: ይኸውም የዘጌ ሰላጤ መሬቱ ከእየሩሳሌም ተነስቶ አሁን ያለበት ቦታ ላይ ሆነ የሚል ነው:: ነገሩ እንዲህ ነው በፊት ዘጌ የሚባል አገር አልነበረም:: ነገር ግን ዛሬ የዘጌን ከተማ (አፋፍን) በስተምዕራብ በሚያዋስነውና ወንጀጣ ተብሎ በሚጠራ ገጠር (የሰላጤዋን ካርታ ይመልከቱ) ውስጥ ሰዎች ይኖሩ ነበር:: ዛሬ ዘጌ ያለችበት ቦታም ሙሉ በሙሉ በውሃ (በጣና ሃይቅ) የተሸፈነ ነበር::

ታዲያ ይህ በእንዲህ እንዳለ በእየሩሳሌም የሚኖሩ ሁለት መነኩሴዎች የነበሩበት ቦታ ከሃይማኖታዊነት የራቀ ነበርና እግዚአብሔር የተቀደሰ ቦታ እንዲሰጣቸው ሲፀልዩ ፀሎታቸው ተሰምቶላቸው የቆሙበት መሬት ሁለቱን እንደያዘ ከነበረበት ቦታ ተቆርሶ ይዟቸው መጥቶ ጣና ሃይቅ ላይ ያርፋል:: ታዲያ አንድ ቀን ጠዋት በወንጀጣ ከሚኖሩ ሰዎች ወገን የሆነች አንዲት ልጃገረድ ግብር ውሃ (ደጅ) ስትወጣ በውሃው ላይ ያረፈውን መሬት ታይና ለዘመዶችዋ «ዛሬስ ውሃው ላይ ምኑ ዘግ ብሎ አደረ?» ስትል ትጠይቃለች:: ይህም ቃል ቀስ በቀስ «ዘጌ» በሚል ተቀየረና የሰላጤዋ መጠሪያ ሆነ::

በሌላ በኩል ደግሞ ከእየሩሳሌም የመጡት መነኮሳት በእየሩሳሌም ይኖሩበት የነበረው ቦታ ስሙ ደብረ ዝጋግ ይባል ነበር:: ይህ ስምም መነኮሳቱን ተከትሎ እንደመጣና የቃሉም ትርጓሜ ለቦታው ተስማሚ ሆኖ በመገኘቱ ለአሁኑ ዘጌ መጠሪያ እንደሆነ የሚናገሩ ሰዎች አሉ:: «ዝጋግ ማለት ሰዋራ ቦታ ማለት ነው» ዘጌም በውሃ የተከበበ መሬት በመሆኑ ሰዋራ ቦታ ነው በሚል :: በመሆኑም «ዝጋግ» የሚለው ቃል

የቦታው መጠሪያ ሆነና ቀስ በቀስ ቃሉ ከዝጋግ ወደ ዘጌ ተቀየረ የሚለው ደግሞ ሁለተኛው አፈታሪክ ነው።

በአጠቃላይ ምንም እንኳን ሁለት አፈታሪኮች ቢቀርቡ፣ የዘጌን ስያሜ አስመልክቶ የስሙ አመጣጥ አፈታሪክን መነሻ የሚያደርግ መሆኑን ነው መረዳት የሚቻለው። በእርግጥ ዘጌ ስያሜዋ ብቻ አይደለም አፈታሪክን መነሻ የሚያደርግ ስለ ህዝቧ አሰፋፈርም ቢሆን የሚተረክ ረጅም አፈታሪክ አለ።

## 4.2 የዘጌ ማህበረሰብ ታሪክ

እንደ 1994 ዓ.ም. ህዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት የዘጌ ሰላጤ አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር 6394 ሲሆን ወንዶች 2774፣ ሴቶች ደግሞ 3620 ናቸው። ይህ ህዝብ አፋፍ ከተማ ውስጥ ከሚኖሩት ጥቂት የእስልምና እምነት ተከታዮች በስተቀር (የእስልምናና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ቁጥር ለይቶ የሚያሳይ መረጃ አላገኘሁም) የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይና ሙሉ በሙሉ የአንድ ብሔረሰብ ( የአማራ) አባል ነው። የዚህች ሰላጤ ህዝብ ሕይወት በአካባቢው ጥንታዊነትና ታሪካዊነት ካላቸው ገዳማት ጋር በጣም የተቆራኘና የተዋሀደ ነው ለማለት ይቻላል ( የአካባቢ ጥበቃ ጥናት ፖሊሲና ቁጥጥር መምሪያ፣ 1996) ።

«ይህን ህዝብ ከአካባቢው ጥንታዊና ታሪካዊ ገዳማት ጋር ያቆራኘው ነገር ምንድን ነው?» ሲባል ደግሞ የሚገኘው ምላሽ ማህበረሰቡ ጥንተ አመሰራረቱ ከኦርቶዶክስ እምነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ እንደሆነ ሙሉጌታ(1996) መ/ር በቃሉ ተገኘን፣አቶ አለሙ ሙሉቀንን፣መርጌታ ወርቁ ደበብንና ሌሎችን አነጋግሬ አገኘሁት ሲሉ ያቀረቡት ቀጣዩ አፈታሪክ ያስረዳል ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዘጌ ሰላጤ የተመሰረተው ከእየሩሳሌም በመጡ ሁለት መነኮሳት ነው። ይሁን እንጂ መነኮሳቱ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በመሞታቸው ለዚያ ቦታ የተመረጡ ሰው ሆነው እንደገና ያቋቋሟት አቡነ በትረማርያም የተባሉ የሸዋ ሰው ናቸው። ዛሬ «የዘጌ አባት» በመባል ይታወቃሉ። እኒህ ሰው ከሸዋ ክፍለ ሃገር ሙገር ከተባለ ስፍራ የተነሱ ሲሆን በአካባቢያቸው አስፈላጊውን የቤተክህነት ትምህርት ተምረው ከጨረሱ በኋላ ጎጃም ውስጥ ዳሞት፣ ጎንደር ውስጥ ደንቢያና በጣና ሃይቅ ዙሪያ ደግሞ ገሊላ በተባለ ደሴት በመዘዋወር እውር እያበሩ፣ ድውይ እየፈወሱና ተዓምራትን እያደረጉ ይኖሩ ነበር። በኋላ ግን ሃይማኖታዊ ተጋድሎአቸው እያደገ ሲመጣ እግዚአብሔር ወደ ዘጌ እንዲሄዱ መረጣቸው። አቡነ ወደ ስፍራው ሲደርሱ ሰባት ቅዱሳን በስፍራው ተገኝተው ተቀብለዋቸዋል። እኒህ ቅዱሳንም በጣና ሃይቅ ዙሪያና ደሴቶች ያሉ ገዳማትን የሰሩ ቅዱሳን ናቸው ይባላል ።

አቡኑ በስፍራው ደርሰው ከመነኮሳቱ ጋር እየፀለዩ ሲኖሩ «በሽተኛን ይፈውሳሉ» የሚባል ወሬ በጣና ሃይቅ ዙሪያ ሰፍረው በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ ስለተሰማ በጊዜው የነበሩት ሰዎችና ንጉሱ ወደ እሳቸው እየመጡ ቡራኬ እየተቀበሉ ብዙ ህዝብ በስፍራው መስፈር ጀመረ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ከአቡኑ ቡራኬ ሊቀበል የመጣው ንጉስ አምደፅዮን ነበር። እሱም በስፍራው ልምላሜ እጅግ ከመገረሙ የተነሳ ዘጌን አርዘሊባኖስ ( ልምላሜ ያላት) ሲል ጠርቷታል። እንግዲህ የአቡኑን ከበሽታ ፈዋሽነት ሰምቶና ንጉሱን አጅቦ የመጣው ህዝብ ቀስ በቀስ በአካባቢው በመስፈር ሰላጤዋን የሰው መኖሪያ ሊያደርጋት እንደቻለ ነው ስነቃሉ የሚገልፀው።

አቡነ በትረማርያም በዘጌ ሰላጤ ረጅም ዘመን ይኖሩ እንጂ ከእግዚአብሔር ስላልተፈቀደላቸው በስፍራው በእሳቸው እጅ የተሰራ ቤተክርስቲያን የለም። ለመጀመሪያ ጊዜ መጥተው በአረፉበት መሃል ዘጌ፣ በአረፉበት ዘመን ተሰራ የሚባለው የጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን እንኳን በአፄ አምደፅዮን አማካኝነት እንጅ በእሳቸው የተሰራ አልነበረም። ይልቁንም እሳቸው ከሞቱ በኋላ እሳቸውን የተኩት አቡነ በርተሎሚዎስ በአቡነ በትረማርያም ስም ቤተክርስቲያን አሳንፀዋል። የአቡነ በትረማርያምን ገድል ጽፈዋል።

በአጠቃላይ በአቡነ በትረማርያም አማካይነት ተመሰረተች የምትባለው የዘጌ ባህረ ሰላጤ ተመሰረተች ከሚባልበት ከ14ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ እስካሁን ድረስ ስነ ቃሉ እንደሚለው የአቡኑን ፈውስ ሽተው፣ አፄ አምደፅዮንን አጅበውና የአካባቢው ልምላሜ ስቧቸው ከየቦታው ተነስተው መስፈር ከጀመሩ ሰዎች ተነስታ እስካሁን ድረስ ህልውናዋ የተጠበቀ ሲሆን ዛሬም ድረስ በአትክልት እርሻዋ በተለይም በቡናዋና በደን ሃብቷ ታውቃ ህዝቦቿም በዚህች በደን በበለፀገችና በቡና እርሻ በታወቀች መሬት ላይ መኖር ሲጀምሩ ማህበራዊ ትስስር እየተፈጠረ፣የህዝቡ አኗኗር አንድ አይነት መልክና ባህል እየያዘ መጥቷል። ከዚህም አንጻር የዘጌ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ በርካታ መለያዎች ኑረውት የሚኖርበትን ቦታ ስያሜ መነሻ ያደረገ ዘገኛ የሚባል ስም ተሰጥቷቸው መኖራቸውን ቀጥለዋል። ቀጥለን የዘገኞችን ማህበራዊ ግንኙነት እንመልከት፡-

## 4.3 የዘጌ ባህረ ሰላጤ ማህበረሰብ ማህበራዊ ግንኙነት

እድር ፣ ማህበር፣ ሰንበቴና ሰንበታሰንበቴ የዘገኞች ባህላዊ ማህበራዊ ተቋማት ናቸው። ዕድር ዘገኞች ለመረዳዳት ሲሉ የሚመሰርቱት ተቋም ነው። ማህበር ደግሞ በአንድ ሰፈር በሚኖሩ ቤተሰቦች ለአንድ «ፃድቅ» ወይም «ቅዱስ» ስም መታሰቢያ የሚደረጉ ዝግጅቶች ናቸው። ለእድር ወይም ለማህበር ቆሎና ጠላ ይዘጋጃል። ብዙ ጊዜም ከአባላቱ ውስጥ በአንዱ ቤት ሰዎች መታሰቢያ የሚደረግለት «ፃድቅ» ወይም «ቅዱስ» በሚታሰብበት ቀን አባላቱ ተሰባስበው ይካሄዳል። ሰንበቴ ደግሞ በሁለት

ማምንት አንድ ጊዜ እሁድ ( በሰንበት) ቀን አባላቱ በቤተክርስቲያን ወይም በሰንበቴው አባላት በተሰራ ቤት ውስጥ ተሰብስበው ጠላ እየጠጡ እንጀራ እየበሉ የሚከውኑት ነው:: የሰንበቴ አባላት ወንዶች ብቻ ናቸው:: የሚጠጡት ጠላ ግን በሴቶች የሚዘጋጅ ነው:: ሰንበታ ሰንበቴ፡ ይህም ከሰንበቴ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የዘገኞች ባህላዊ ተቋም ነው:: ከሰንበቴ የሚለየው አባላቱ የቆረቡና የመነኮሱ ሴቶችና ወንዶች በመሆናቸው ነው:: ሰንበታ ሰንበቴ በሶስት ወር አንድ ጊዜ የሚከወን ሲሆን አባላቱ 10 እንጀራና አንድ «ማዲጋ» (እንስራ) ጠላ በየተራ ያቀርባሉ:: በድግሱም የቤተሰብ አባሎቻቸውን መጋበዝ ይችላሉ::

በእነዚህ ተቋማት ውስጥ ሰዎችን ከመሳተፍ የሚከለክላቸው ነገር ቢኖር የኢኮኖሚ አቅም ነው:: የኢኮኖሚ አቅማቸው አናሳ የሆነ ቤተሰቦች በእነዚህ ተቋማት ውስጥ አይገቡም::Rahel (1999፣50) በጥናቷ እንደጠቆመችው በዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ ከሚኖሩት ሰዎች ጥናት በተደረገባቸው 152 ቤተሰቦች ውስጥ 91ዱ የዕድር፣ 63ቱ ደግሞ የማህበር አባላት ናቸው:: ከዚህ ውጭ በተቋማቱ ውስጥ ያልገቡት ቤተሰቦች አባል ላለመሆናቸው ምክንያቱ የኢኮኖሚ አቅም አናሳነት እንደሆነ ይናገራሉ::

ዘገኞች ማህበራዊ ተቋሞቻቸውን ጠላ ለመጠጣትና ቆሎ ለመብላት ሲባል ብቻ የፈጠሯቸው አይደሉም:: ስለተለያዩ ነገሮች ይወያዩባቸዋል:: የተጣላን ያስታርቁባቸዋል:: ስለ ሃገር ደህንነት ይመክሩባቸዋል፣ ለግለሰብ ለከበዱ ችግሮች በጋራ መፍትሄ ይፈልጉባቸዋል:: ግለሰቦች የሚሰሯቸውን ከልምድ የወጡ ድርጊቶች ይነቅፉባቸዋል:: ለልጆቻቸው ማንነታቸውን ስርዓቶቻቸውን፣ሃይማኖታቸውን፣ ዕውቀቶቻቸውን ያስተምሩባቸዋል::በዚህ የተነሳ ልጆች ከወላጆቻቸው ባላነሰ ሁኔታ ስለሰላጤዋ አመሰራረትና ሃብቶች መናገር ይችላሉ:: ወላጆችም ቢሆን ይህንን ያውቃሉ፤ ይመሰክራሉም[3]::

የዘጌ ባህረ ሰላጤ ነዋሪዎች በማህበራዊ ተቋሞቻቸው ከመወያየት በተጨማሪ የአንድ ጎጥ ነዋሪዎች በህብረት ማህበራዊ ተግባራትን ይከውናሉ:: ለምሳሌ በህብረት መንገድ ይሰራሉ፣ የአካባቢንና የጎረቤት ቤተ ክርስቲያን አጥር ያጥራሉ፣ በታላላቅ ቤተክርስቲያኖች ውስጥ በሚደረጉ የፆምና የክብረበዓል ዝግጅቶች ውስጥ ስራ ያግዛሉ፣ ወዘተ... ነገር ግን ከአካባቢው ነዋሪዎች በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚገልፀው የግለሰቦችን ሥራ በተመለከተ ቀደም ሲል በዘገኞች ውስጥ የነበረው የመረዳዳት ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ነው:: ለምሳሌ ድሮ አንድ ቤተሰብ ቤት እንደመስራት ያሉ ከባድ ሥራዎች ሲኖሩበት ከእርሱ የሚጠበቀው ጥሬ ዕቃዎችን ካቀረበ በኋላ የሚበላውን እህል ውሃ ማቅረብ ነበር:: ሥራውን መከወን የጎረቤቶች የዘመዶችና የጓደኞች ተግባር

---

[3] ለምሳሌ ቄሰገበዝ ይሄይስ እንግዳው የተባሉ የ70 ዓመት አዛውንት መረጃ እንዲሰጡኝ ወደ እርሳቸው የወሰዱኝን ወጣቶች ምነው እናንተ መናገር ስትችሉ አዋቂ ፍለጋ ትዞራላችሁ?! ሲሉ ያቀረቡላቸው ቁጣዊ ጥያቄ ይህንን አሳይቶኛል::

ነው፡፡አሁን ግን ሰዎች የራሳቸውን ሥራ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ብቻ ይሰራሉ፡፡ ተጨማሪ ጉልበት ሲያስፈልግ ደግሞ የቀን ሠራተኞችን ይቀጥራሉ፡፡

ይህም የማህበረሰቡ ሃብት ቀስ በቀስ እየቀነሰ መምጣትን ተከትሎ የመጣ እንደሆነ ነው በነዋሪዎች የሚነገረው፡፡ ማለትም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዘገኞች ዋነኛ መተዳደሪያ የቡና ምርት ነው፡፡ ይህ ምርት ደግሞ በአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ ከጊዜ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ በማህበረሰቡ ኑሮ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ህዝቡ በአነስተኛ ገቢ ኑሮውን የሚገፋ እየሆነ በመምጣቱ ሥራውን ለመከወን ብዙ ጉልበት ላያስፈልገው ይችላል፡፡ የሚከወኑ ሥራዎች ሁሉ አቅምን መሰረት ያደረጉ ናቸውና በጣም ትልልቅ ቤቶች አይሰሩም፣ የተትረፈረፈ ድግስ አይደገስም፡፡ ይህ በመሆኑ ደግሞ እያንዳንዱ ቤተሰብ የራሱን ሥራ ራሱ መስራት ይችላል፡፡ በዚህም የተነሣ በሰላጤው ውስጥ የህብረት ስራ ባህል ጨርሶ ባይጠፋም ቀስ በቀስ እየወደቀ ነው፡፡

ቀጥለን የማህበረሰቡን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንመልከት፡-

## 4.4 የዘጌ ሰላጤ ማህበረሰብ የኢኮኖሚ ተግባራት

የዘጌ ሰላጤ ህዝብ ኑሮው በእርሻ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ነገር ግን የእርሻ ስራ የሰላጤው ህዝብ ዋነኛ መተዳደሪያ ነው ቢባልም የምግብ ሰብል ግን በአካባቢው አይመረትም፡፡ ይልቁንስ የማህበረሰቡ ዋና መተዳደሪያ የቡና ሰብል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን ጌሾ፣ ሎሚ፣ ቦሆሮ(የሎሚ ዘር ነው) ወዘተ በሰላጤው ውስጥ እየተመረቱ ለህዝቡ መተዳደሪያነት ያገለግላሉ፡፡

ህዝቡ አሁን የሚተዳደርበት የቡና ልማት ከ700 ዓመት በላይ ዘመን ያስቆጠረ ነው፡፡ ይህ ማለት የዘጌ ሰላጤ ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የህዝቡ መተዳደሪያ በስፋት የቡና፣ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ የሌሎች አትክልቶች እርሻ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን መጠኑ የእርሻውን ያህል አይሁን እንጂ በባህረ ሰላጤው ከእርሻ ስራ ውጭ አነስተኛ በሆነ ደረጃ ሽመናን፣ ልብስ ስፌትን ፣ አናጢነትንና ፣ ሸክላ ስራን የመሳሰሉ የእደ ጥበብ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡ አሣ ማስገርና ፣ አነስተኛ ንግድም የተወሰኑ ነዋሪዎች መተዳደሪያዎችናቸው፡፡ ነገር ግን የእንስሳት እርባታን በተመለከተ ሰላጤዋ እጅግ ደካማ እቅስቃሴ ያለት ሲሆን አሁን ያሉት ጥቂት የእንስሳት ማርባት ሙከራዎችም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በጥቂቱ መከወን የጀመሩት የበግ ማድለብ፣ የዶሮ እርባታና የንብ ማነብ ተግባራት ናቸው (የአካባቢ ጥበቃ ጥናት፡ ፖሊሲና ቁጥጥር መምሪያ፣1996 )፡፡

ታዲያ ይህ አሁን በባህረሰላጤዋ ውስጥ የሚታየው የማህበረሰቡ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ልማድ ከየት መጣ? የሚለው ጥያቄ መልስ አፈታሪክን ይጠቅሳል፡፡ ቀደም

ሲል እንደተገለፀው የዘጌን ባህረሰላጤ በህዝብ መኖሪያነት የመሰረቷት አቡነ በትረማርያም ናቸው:: እኚህ ሰው ደግሞ በሰላጤው ውስጥ ረጅም ዘመን ኑረው ካለፉ በኋላ ገድላቸው እሳቸውን በተከትት አቡነ በርተሎሚዎስ በተባሉ መነኩሴ ተፅፏል:: እንግዲህ በዚሁ ገድል ላይ ነው የዘጌ ማህበረሰብ ለምን አትክልት አብቃይ እንጂ እንስሳት አርቢ እንዳልሆነ የሚገልፅ አፈ-ታሪክ ቀርቧል ሲሉ ገበየሁ(1996) የገለፁት::

ፀሃፊው በገድሉ ተገልጧል ብለው እንደፃፉት አቡነ በትረማርያም በስፍራው ለረጅም ጊዜ ኖረው ሃይማኖታዊ ክብራቸው ከፍ በማለቱ ከመሞታቸው በፊት እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል:: በቃል ኪዳኑም ተከታዮችህ (የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች) ኑሮአቸው የተደላደለ ይሁን፣ በሰላጤው ውስጥ ያሉ ሃብቶች ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገሩ እስከ ዘላለም ይኑሩ የዘጌ ህዝብ ብሩህ፣ብልህና ንቁ፣ፈጣን አእምሮ ያለው ይሁን ሲል አካባቢውንና ነዋሪውን ባርኳል:: እንዲሁም በሰላጤው ውስጥ የዱር አውሬ ሰው እንዳይበላ፣ መብረቅ ሰው እንዳይመታ አውግዟል::

ከዚህ በተጨማሪም አቡኑ ከእግዚአብሔር በታዘዙት መሰረት ህዝቡ በአካባቢው እንስሳት እንዳያረባ ከልክለዋል:: ይልቁንስ ህዝቡ የእሳቸውን ፈለግ በመከተል እፅዋትን እንዲያተክል አዝዘዋል:: ለዚህም ሲሉ እሳቸው ምርኩዛቸውን ከሶስት ሰብረው በመትከል አርአያ ሆነዋል:: ነገሩ እንዲህ ነው፡- ከላይ እንደተገለፀው አቡኑ ከሸዋ ተነስተው ነው ወደ ዘጌ የመጡ በዚህም ጊዜ ጣና ሃይቅን ለመሻገር ምርኩዛቸውን ነው እንደመቅዘፊያ የተጠቀሙበት::

ታዲያ ይህችን ምርኩዝ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከሶስት ሰብረው ቢተክሏት ቡና፣ ጌሾና አደስ አብቅላለች :: እዚህ ላይ አንዳንድ ሰዎች ሎሚና ትርንጎም ከምርኩዟ ላይ በቅለዋል ይላሉ:: እነዚህ ተክሎችም ለህዝቡና ለተከታዩ ትውልድ በእግዚአብሔር ተባርከው ለዘጌ ሰው ተሰጥተዋል:: ከዚህ ውጭ ግን አቡኑ «በበሬ እንዳይታረስ፣ጅራፍ እንዳይጮህ» ሲሉ በዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ እንስሳት እንዳይረቡ በበሬ እንዳይታረስ ከልክለዋል:: ከዚህም የተነሳ ዛሬም ድረስ የሰላጤው ነዋሪዎች አትክልትን ያለማሉ እንጂ እንስሳትን አያረቡም:: እርሻም አያርሱም:: በመሆኑም ማህበረሰቡ የእለት ምግቡን እንኳን የሚያገኘው በሸመት / በግዢ/ ነው (አቶ ጀመረ ክብረት፣27-9-1999፣አቶ ዋሴ እንየው፣26-8-1999 ) ::

ይህንን አፈ-ታሪክ በተመለከተ ዛሬም ድረስ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታመንበት መሆኑን እና አብዛኛው(ሁሉም ማለት ይቻላል) የሰላጤዋ ተወላጅ በቡና ምርት ብቻ የሚተዳደር መሆኑን በሰላጤዋ ውስጥ አፋፍ ከተባለው ዘገኞች «ከተማ» ከሚሉት ስፍራ በስተቀር በሌሎች ጎጦች እንስሳት ጨርሰው የማይረቡ እንዲሁም የማይታረዱ መሆኑን እኔም ተዘዋውሬ አይቻለሁ:: ከወጣት እስከ አዛውንት ያሉ መረጃ አቀባዮችም ይህንን የሚያረጋግጥ መረጃ ሰጥተውኛል::ለምሳሌ ጀመረ ክብረትየተባሉ የ60 ዓመት የሰላጤዋ

ተወላጅ እንደገለፁት፡- «ዘጌ ውስጥ እንስሳት እንዳይረቡና እንዳይታረዱ፣እርሻ እንዳይታረስ፣እባብ ሰው እንዳይነድፍ፣ መብረቅ ሰው እንዳይመታ አቡነ በትረማርያም አውግዘዋል፡፡ሰውም ውግዘቱን ስለሚፈራ ትዕዛዙን አክብሮ ይኖራል፡፡አምላክም ቃልኪዳኑን ስላከበረ መብረቅ ወድቆ አያውቅም፣እባብም ሰው አይነድፍም» ብለዋል(አቶ ጀመረ ክብረት፣27-9-1999) ፡፡ በዚህ ሃሳብም ከትልልቆች አልፎ በአስራዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችም የሚስማሙ መሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡

እዚህ ላይ አንድ የግድ ሳይታወስና አፅንኦት ሳይሰጥበት የማይታለፍ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም ስነቃል የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ እየተጫወተ ያለው ከፍተኛ ሚና ነው፡፡ በአንድ ቦታ እፅዋት መብቀል ካላባቸው የግድ እንስሳት መጥፋት አለባቸው ይህ ደግሞ ምናልባት በስምምነት ሊደረግ ይችላል፡፡ ነገር ግን የዘጌ ማህበረሰብ ይህንን ሁኔታ እየከወነ ያለው በስነቃሉ አስገዳጅነት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ማህበረሰቡ ከአቅሙ በላይ የሆኑ ነገሮች እስካላስገደዱት ድረስ በአካባቢው የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶችን ለእምነቱ ሲል ጠብቆ እየኖረ ነው፡፡

## 4.5 የዘጌ ባህረሰላጤ የተፈጥሮ ሃብቶች

ዘጌ በተፈጥሮ ሃብት እጅግ የታደለች መሬት ናት፡፡ በውስጧም በርካታ ተፈጥሮ የለገሰቻት ሃብቶች አሏት፡፡ ነገር ግን ለዚህ ጥናት ርዕስ የበለጠ ጠቃሚ ናቸው የተባሉ የሰላጤዋ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሃብቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

### 4.5.1 መሬት

የዘጌ ሰላጤ ሕዝብ ኑሮው በእርሻ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መሬት የአካባቢው ዋነኛ የተፈጥሮ ሃብት ነው፡፡ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲና ቁጥጥር መምሪያ (1996 ) እንደሚገልፀው የማህበረሰቡ የመሬት አጠቃቀም ልማድ ደንና ቡናን አጣምሮ ማብቀል /የደን ጥምር ግብርና / ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የሰላጤዋ መሬት በአብዛኛው በተለያዩ አይነት ዛፎችና በቡና ተክል የተሸፈነ ነው፡፡ በእርግጥ ዋሻና አራራት በተባሉት ጉጦች ውስጥ በጣም በጥቂት መሬት ላይ በቆሎ ይመረታል፡፡ ነገር ግን የሚመረተው በቆሎ ከቤት ውስጥ ፍጆታ አልፎ ለገበያ የሚተርፍ አይደለም፡፡ ይኸውም በቆሎ የማምረት ልማድ «ምናልባት ወርህ ቢከፋና ቡና ባያፈራ መጠባበቂያ» በሚል እንደተጀመረ የእድሜ ባለፀጎች ይናገራሉ (ቄሰገበዝ ይሄይስ እንግዳው፣25-8-1999፣መርጌታ ወርቁ ደበብ፣25-9-1999 ) ፡፡

የዘጌ ሰላጤ መሬት «አካላዊ የአፈር ሁኔታ» ምን እንደሚመስል የሚገልፀው የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ፡« በዘጌ ሰላጤ ውስጥ የሚታየው የአፈር ቀለም በአብዛኛው በጣም

ጥቁር ቀይ ቡናማ (very dark reddish brown) ሲሆን እስከ 60 ሳንቲ ሜትር ጥልቀት ባለው አፈር ላይ ይህ ቀለም ጎልቶ ይታያል። ከዚህ ጥልቀት በታች የሚታየው የአፈር ቀለም ደግሞ ጥቁር ቀይ (Dark red) ነው» (1996፣18) ይላል። ይህንን የአፈር አይነት የአካባቢው ነዋሪዎች ዋልካ አፈር ይሉታል። የድንጋይን ሁኔታ አስመልክቶ ግን ይኸው ቢሮ በሰላጤው ብዙ ድንጋይ እንደማይገኝ ነው የሚገልፀው።

## 4.5.2 ጣና ሃይቅ

ጣና ሃይቅ ለዘጌ ማህበረሰብ ብቸኛ የውሃ ማግኛ መንገዱና ምንጩ ነው። ይህም በመሆኑ ህዝቡ ለማንኛውም ውሃ ለሚያስፈልገው ክንዋኔ ጣናን ይጠቀማል። ሃይቁ ለነዋሪው ለመጠጥ፣ለምግብ ማብሰያ፣ለንፅህና መጠበቂያ፣ ለመጓጓዣ ለጥቂት ሰዎች ደግሞ ለመስኖ ያገለግላል ( ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የቦኖ ውሃ ጀምሯል) ።

ምንም እንኳን ከአምስትና ስድስት ዓመታት ወዲህ የመንገድ ትራንስፖርት ድርጅት ወደ ዘጌ የሚሄዱ መኪናዎችን በመመደቡ ነዋሪዎች አማራጭ የመጓጓዣ አገልግሎት ቢያገኙም ጣና ሃይቅ የዘገኞች የረጅም ዘመን የመጓጓዣ መስመር ሆኖ አገልግሏል። አሁንም እያገለገለ ነው። ዋና መስሪያ ቤቱ ባህር ዳር ከተማ የሆነውና በ1930 ዎች አካባቢ በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ እንደተጀመረ የሚነገርለት የጣና ሃይቅ ትራንስፖርት ድርጅት በየእለቱ ከባህር ዳር ዘጌ የደርሶ መልስ የጀልባ መጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል። ብዙ ሰውም በዚህ የመጓጓዣ ዘዴ ተጠቃሚ ነው። ከዚህ ውጭ ደግሞ ህዝቡ ራሱ በሰራው የደንገል ታንኳ ይጠቀማል።

የጣና ሃይቅ ለዘጌ ነዋሪዎች ከመጓጓዣም ሌላ አሳ ለማስገር ያገለግላል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ማህበረሰቡ ከእርሻ ሥራ ሌላ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ አሳ ማስገር አንዱ ነው። አሳው የሚሰገረው ደግሞ ከጣና ሃይቅ ነው። በመሆኑም ነዋሪው አሳን በማስገር የቤት ውስጥ የምግብ ፍጆታውን ይሸፍናል፣ ለገበያ ያቀርባል።

የዘጌ ማህበረሰብ ጣና የውሃ ምንጩ እንደመሆኑ የህልውናው መሰረት ነውና በጣም ይወደዋል። በማህበረሰቡና በሐይቁ መካከል ያለው ግንኙነት የጠበቀ ነው። ይሁን እንጂ ህዝቡ ሃይቁን እየወደደ ይፈራዋል። የዚህም ምክንያት በሃይቁ ውስጥ «ጂኒ» የሚባል ርኩስ መንፈስ እንዳለ ስለሚታመን ነው። እንደ አካባቢው ሰዎች እምነት በየአመቱ ቢያንስ አንድ ሰው ሃይቁ ውስጥ ሰምጦ ይሞታል። ይህ ደግሞ በሃይቁ ውስጥ ያለው ርኩስ መንፈስ የሚወስደው ዓመታዊ ግብርን ነው። መንፈሱ የሰው ደም ይጠጣል።ለዚህም ሲል ሰው ሰጥሞ እንዲሞት ያደርጋል። ሰው ሃይቁ ውስጥ በሰጠመ ጊዜ ሬሳውን ውሃ እንዲተፋው የሚች ዘመድ ጐረቤት በሃይቁ ዙሪያ ተሰብስቦ ያርዳል። ቡና አፍልቶ ይለማመናል። ይህ ሲደረግ ጠፍቶ የቆየው ሬሳ ይወጣል ይባላል። ከዚህም የተነሳ የጣና ሃይቅ፣ በዘጌ ነዋሪዎች ዘንድ ሁለት ተቃራኒ ስሜቶችን (መውደድና

መፍራት) የሚፈጥር የተፈጥሮ ሃብት ነው (ወ/ሮ ሰገነት አሸተ፣26-9-1999፣ወ/ሮ እናት ትሁን ተባባል 4-9-1999) ::

### 4.5.3 ደን

ደን ለዘጌ ማህበረሰብ ሌላውና ትልቁ የተፈጥሮ ሃብት ነው:: አብዛኛው የሰላጤው መሬት በደን የተሸፈነ ነው:: የደን ሽፋኑ የተለያዩ የሃገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን ያካተተ እንደሆነና አመሰራረቱ ከቡና ተክል ጋር የተያያዘ እንደሆነ የአካባቢ ጥበቃ ጥናት ፖሊሲና ቁጥጥር መምሪያ (1996 ዓ.ም) ይገልፃል:: በደኑ ውስጥ በርካታ የዛፍ አይነቶች አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ ዋንዛ፣ሰሳ፣ዝግባ፣ ብርብራ፣ ብሳና ፣ግራር፣ዕድ፣ ቃዋ፣ እሸ፣ ሰልቸን፣ ከነዳባ፣ የባህር ዛፍ፣ሰንሰል (ስሚዛ) ጥቂቶቹ ናቸው::
ይህ የደን ሃብት ለህብረተሰቡ፤ ለቡና ጥላነት፣ የመሬትን ለምነት ለማሻሻል፣ ለማገዶ ለባህላዊ መድሃኒት መቀመሚያና ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ሲያገለግል ለዱር እንስሳት ደግሞ መጠለያቸው ነው::

ነገር ግን ይህ የደን ሃብት ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠኑ እየተመናመነ እንደመጣ ነው የተለያዩ ጥናቶች የሚጠቁሙት :: ለምሳሌ የአካባቢ ጥበቃ ጥናት ፖሊሲና ምርምር ስለዚሁ ሁኔታ ሲገልፅ «የዘጌ ሰላጤ ህዝብ ዋና መተዳደሪያ የቡና ምርት ሲሆን በ1962 ዓ.ም በጣለው ሃይለኛ በረዶ እና ከዚያ በኋላ በተከታታይ በተከሰተው ድርቅ የቡናው ምርት እየቀነሰ በመምጣቱ ህዝቡ በተፈጥሮ ደኑ ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ እያካሄደ ይገኛል» (1996 ፣1) ይላል::

እንዲያውም ይህ የቡና ምርት መቀነስ ማህበረሰቡን የማገዶ እንጨት የመሸጥ ልማድ እንዲፈጥር እንዳደረገውና ይህ ልማድ በተራው በእንጨት የተሰሩ ጥንታዊ ቤቶችንና ትልልቅ የቤት ቁሶችን ሳይቀር እንዲያፈርስ እያስገደደው እንደሆነ ነው በመስክ ጥናት ወቅት የተገኘው የቃል መረጃ የሚጠቁመው (አቶ አለሙ ታዬ፣27-8-1999) ::

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ፅሁፍ የዘጌ ባህረ ሰላጤ በተፈጥሮ ሃብት የበለፀገ አካባቢ እንደነበረና ከእነዚህ የተፈጥሮ ሃብቶች ውስጥ መሬት፣ ውሃና ደን ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል:: ከዚህ በተረፈ ግን ከላይ እንደተገለፀው የሰላጤዋ አመሰራረትም ሆነ ሲጀመር አንስቶ እስካሁን ድረስ ያለው የህዝቧ አኗኗር አፈታሪክን መሰረት ያደረገ ነው:: በመሆኑም ከዚህ ተነስቶ ሰላጤዋን አፈታሪካዊ መሬት (Legendary land ) የሚል ስያሜ መስጠት ይቻላል::

ከዚህ በመቀጠል ቀጥለው በሚመጡት ሁለት ተከታታይ ምዕራፎች ስለዘጌ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በምልከታና ቃለ መጠይቅ ከመስክ የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች በምዕራፍ አንድ የቀረቡትን የምርምር ጥያቄዎች ሊመልሱ በሚችሉ

መልኩ በምዕራፍ ሶስት በቀረቡ ትውራዊ ዳራዎች እየተገናዘቡ በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል::

## 5. የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ በዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች ላይ

ይህ ክፍል በዘጌ ባህረሰላጤ ስለሚገኙ ባህላዊ ቤቶች የተገኘው መረጃ በምዕራፍ ሶስት ከቀረቡ ትውራዊ ዳራዎች ጋር እየተገናዘበ የሚተነተንበትና የሚብራራበት ነው።በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ስለሰላጤዋ ባህላዊ ቤቶች አይነትና ተግባር፣ስለባህላዊ ቤቶች የአሰራር ሂደት፣ስለባህላዊ ቤት ሰሪዎች ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ፣ባህላዊ ቤቶች በማህበራዊ፣ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ አውዶች ያላቸው መልክ፣በቤቶች ላይ ተፅዕኖ ስላሳረፉ ጉዳዮችና ከባህላዊ ቤቶች ጋር የተያያዙ እምነቶችና ትረካዎች በቤቶች ህልውና ላይ ያላቸው ተፅዕኖ በስፋት ቀርቧል ።

### 5.1 የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች አይነትና ተግባራቸው

በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ የነገሮችን ምደባ አስመልክቶ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። ከእነዚህ አመለካከቶች ውስጥ ቁሶችን በአገልግሎታቸው እንዲሁም ከተሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች አንፃር መመደብ የተለመዱት ናቸው Glassie (1991), Somjee (1993) ።

እንደዚሁም ሁሉ እንደ Ben Amos (1982) የመሳሰሉ ባለሙያዎች በቀያዊ ስያሜ የፎክሎር ዘርፎችን ማዋገን እንደሚቻል ይገልፃሉ። እንደባለሙያው ገለፃ ቀያዊ ስያሜ፣ ማህበረሰቡ ለዘርፉ የሰጠውን ስያሜ ተከትሎ መጠቀምን የሚጋብዝ የማዋገኛ ዘዴ ነው። እኔም ለዚህ ጥናት ከሌሎች የመመደቢያ ዘዴዎች ይልቅ የተሻለ ሆኖ ስላገኘሁት «ቀያዊ የማዋገኛ ዘዴ»ን በመጠቀም በዘጌ ባህረሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችን ማህበረሰቡ እራሱ ሰይሞ በመደባቸው መንገድ መድቤ አይቻቸዋለሁ።

በአጠቃላይ በሰላጤው ውስጥ የሚገኙ ቤቶች ምን አይነት እንደሆኑ ለመገንዘብ ስል በሰላጤው ውስጥ የሚገኙ ሃገር ቤት፣ሳር ወደብ፣መሃል ዘጌ፣ ደብር፣ይጋንዳ፣ ኮከል፣ ታንገደል ፣ ዑራ፣ አዘዋ ማርያም ፣ አጣጢ፣ ጋሚ፣ ዋሻ፣ መቀላሚና ብሮራሜ በተሰኙ ጎጦች ውስጥ ተዘዋውሬአለሁ። በዚህም ጊዜ የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ቤተሰሪዎችና ባለቤቶች በተለያዩ ስያሜዎች የሚጠሯቸው ባህላዊ ቤቶች እንዳሉ ተገንዝቤያለሁ። እነዚህ ቤቶች እሳተ ካላ፣ ደርብና ምድር፣ ጎጆ ቤት የሚባሉ ሲሆን ለስያሜያቸው መለያየት ምክንያት የሆኑት የቤቶች መጠንና ቅርፅ ናቸው።

በመሰረቱ ሶስቱም ዓይነት ባህላዊ ቤቶች ዋና ተግባራቸው ለሰዎች መጠለያነት ከመሆኑም በተጨማሪ ግድግዳቸው ክብ፣ ጣሪያቸው ሾጣጣ (cone shape) የሆኑና ሁሉም ከሳር፣ ከእንጨት፣ ከዛፍ ልጦችና ከአፈር የሚሰሩ ናቸው። ነገር ግን ከዚህ ባሻገር ቅርፃቸውና መጠናቸው፣በውስጣቸው የያዟቸው ክፍሎች ብዛት የተለያየ ስያሜ አሰጥቷቸዋል። እያንዳንዳቸው ቀጥለው ቀርበዋል።

እሳተከላ፡- ይህ የቤት ዓይነት ግድግዳው ክብና ከጭቃ ጡብ ጣሪያው ደግሞ ከሳር፣ከእንጨት ፣ ከጣውላ ፣ ከዛፍ ልጦችና ከሳር የተሰራ የ15ኛው ክ/ዘመን ቤት ነው (አቶ ዋሴ እንየው፡26-8-1999 ) ፡፡ የቃል መረጃ አቀባዮች እንደገለፁት በዚህ ዘመን ከሚኖሩ ሰዎች ውስጥ እሳት ከላ ቤት፣ ሰዎች ሲኖሩበት እንጂ ሲሰራ አይቶ የሚያውቅ የለም፡፡ ነገር ግን ብዙ ሰዎች አባቶቻቸው በቃል እያስጠኗቸው ከማደጋቸው የተነሳ እሳተ ከላ ቤት እንዴት እንደተሰራና በምን እንደተሰራ ያውቃሉ ፡፡በዚህም መሰረት መረጃ አቀባዮች እንደሚገልፁት ቤቱ እሳተ ከላ የሚለውን ስም ያገኘው ከአሰራር ዘዴው ሲሆን የእሳተ ከላ ቤት በድንገትም ይሁን ሆን ተብሎ በጠብ ምክንያት የሚነሳ እሳት በቤት ውስጥ ባለ ንብረትና ሕይወት ላይ አደጋ እንዳያደርስ ታስቦ የሚሰራ ቤት ነው፡፡





ጣሪያው ሳር የለበሰ ጣሪያው ቆርቆሮ የተከደነ

ሥዕል1፡- እሳተከላ ቤት

በዚህ ዙሪያ ቃለ-መጠይቅ ካደረግሁላቸው የሰላጤዋ ተወላጆች ውስጥ አንዱ የሆኑት ቄስገበዝ ይሄይስ እንግዳው (ሰውዬው በኡራ ኪዳነምህረት ገበሬ ማህበር በጋሚ ጎጥ ተወልደው ያደጉ የ70 ዓመት አዛውንት ናቸው፡፡) ስለሁኔታው ሲገልፁ ፡-

> ዛሬ በመሃል ዘጌም ሆነ በሌሎች ቦታዎች የምታያቸው የእሳተ ከላ ቤቶች አምስት ትውልድ[4] ኖሮባቸዋል፡፡ አባቶቻችን እነዚህን ቤቶች በእግዚአብሔር እርዳታ በከፍተኛ ጥበብና ጥንቃቄ ስለሰሯቸው በቀላሉ ሳይፈርሱ ይህን ያህል ዘመን ኑረዋል፡፡ ቤቶቹ ሌላው ቀርቶ እሳት እንኳን አያጠቃቸውም፡፡ እሳተ ከላ የሚለው ስምም ከዚህ የመጣ ነው፡፡ ቤቶች እሳት የማያስደርሱ/የሚከሉ ናቸው፡፡ እኔ በበኩሌ አምስት ጊዜ እሳት በልቶት ከውስጥ አንድም እቃ ሳይበላ የቀረበት ቤት አውቃለሁ ይላሉ(3-2-2000) ፡፡

---

[4] አንድ ትውልድ በቤተሰብ የዘር ሀረግ ከአባት እስከ ልጅ ያለውን ተዋረድ የሚመለከት ነው( አቶ ዋሴ እንየውና አቶ ጀመረ ክብረት 26-8-1999፣27-9-1999 ) ፡፡

ይህ እሳት እንዳያጠቃው የተሰራው ቤት መጠኑ እጅግ ግዙፍ ባለሶስት ክፍል ቤት ነው። ክፍሎች ሁሉም ክቦች ሲሆኑ አንዱ ሌላውን በመዞር የተሰሩ ሆነው እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ስያሜ አላቸው። ከውጭ ወደውስጥ ሲገባ የመጀመሪያው ክፍል «ዛኒጋባ»፣ሁለተኛው «የሴት ቤት»፣ ሶስተኛው መቅደስ ይባላሉ።

የክፍሎችን አገልግሎት በተመለከተ መረጃ የሰጡኝ መርጌታ ወርቂ ደበብ ና እታየ(ወ/ሮ) ሰገነት አሸተ እንደገለፁልኝ (ሁለቱም ሰዎች በሰላጤዋ ውስጥ በበትረማርያም ጎጥ ተወልደው ያደጉና ዕድሜያቸውን በሙሉ በሰላጤዋ ውስጥ የኖሩ በቅደም ተከተል የ68ና የ60 ዓመት ሰዎች ናቸው።) «ዛኒጋባ» ግድግዳው ከሸንበቆ የተሰራ በዓመት በዓል ጊዜም ሆነ «በአዘቦት» (የስራቀን) የእንግዳ ማስተናገጃ ክፍል ነው። ቤተሰቡም ቡና ሲጠጣና ምግብ ሲበላ በዚህ ክፍል ይሰበሰባል። ይህ ክፍል በዘመናዊ ቤቶች ውስጥ «የሳሎንን»ተግባር የሚተካ ነው።

ሁለተኛው «የሴት ቤት» ተብሎ የሚጠራው ክፍል ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እንደሞሰብ፣ ድስት፣ «ማድጋ» (እንስራ)፣ ጉታ (ጎተራ) ወዘተ ያሉ ዕቃዎች ይቀመጡበታል። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚቀመጡት ዕቃዎች የምግብ ማስቀመጫ፣ የምግብ ማብሰያና የምግብ ማቅረቢያ ናቸው። እነዚህን ዕቃዎች ደግሞ ማህበረሰቡ «የሴት እቃዎች» ይላቸዋል። ምክንያቱም በማህበረሰቡ የስራ ክፍፍል ልማድ መሰረት የቤት ውስጥ ስራ ምንጊዜም የሴት ነው። ይህም በመሆኑ የቤት ውስጥ ስራ የሚከወንባቸው ዕቃዎች የሚቀመጡበት ክፍል «የሴት ቤት» የሚል ስያሜ አለው። በዚህ ክፍል ምንጊዜም ቢሆን ወንዶች አይገቡም።

ሶስተኛው ክፍል «መቅደስ» የሚባለው ነው። ክፍሉ ከውጭ ወደ ውስጥ የመጨረሻው ክፍል ነው። በውስጡም ከጠፍርና ከእንጨት የተሰሩ ዙፋንና ድንክ የሚባሉ አልጋዎች፣ ወንበሮች ወንዶች የሚገለገሉባቸው የጦር መሳሪያዎች (ጦር፣ጐራዴ፣ጠበንጃ) ይቀመጡበታል። አገልግሎቱ ለቤተሰቡ መኝታ ቤት ነው። ለደህንነት ሲባል ወደዚህ ክፍል ከቤተሰቡ አባላት በስተቀር ሌላ ሰው አይገባም።

መርጌታ ወርቂ ደበብና ሌሎች ሰዎች እንደገለፁት የእሳተ ከላ ቤት ቅርፅ በአካባቢው ከሚገኙ ቤተክርስቲያኖች የተኮረጀ ነው። ይህንን ጉዳይ ለማረጋገጥ በሰላጤው ውስጥ ከሚገኙ ሰባት ቤተክርስቲያኖች ውስጥ አቡነ በትረማርያም፣ ኡራ ኪዳነምህረት፣መሃል ዘጌ ጊዮርጊስ የተባሉ ቤተክርስቲያኖች ላይ ባደረግሁት ምልከታ ሶስቱም ቤተክርስቲያኖች የእሳተ ከላውን ቤት የመሰሉ ሶስት ክፍሎች ያሏቸው መሆኑን ተመልክቻለሁ።

በእርግጥም እሳተ ከላ ቤት ባለ ሶስት ክፍል መሆኑን ብቻ ሳይሆን የክፍሎችን ተግባርም ነው ከቤተክርስቲያኖችን የወሰደው። ምክንያቱም በእሳተ ከላ ቤት፣ የቤት

እቃዎች የሚቀመጡትና እንግዶች የሚስተናገዱት ቤተክርስቲያኖች በሶስቱ ክፍሎቻቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት መሰረት አድርገው ነው፡፡

የዘጌ ቤተክርስቲያኖች የአሰራር ቅርፃቸው አባ ጎርጎርዮስ (1991፣138) «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስርዓት ሶስት ዓይነት የቤተክርስቲያን አሰራር አለ፡፡» ሲሉ ከሚገልፆቸው የቤተክርስቲያን ቅርፅ አይነቶች «ቤተ ንጉስ ቅርፅ» የሚባለውን አይነት የተከተሉ ናቸው፡፡

አባ ጎርጎርዮስ እንደሚገልፁት ቤተ ንጉስ ዙሪያው ክብ የሆነና በግድግዳ ከሶስት የተከፈለ ህንፃ ነው፡፡ ከክፍሎቹ የመጀመሪያው «ቅኔ ማህሌት» ይባላል፡፡ ይህ ክፍል መዘምራንና ደብተራዎች ለእግዚአብሔር ምስጋናና ፀሎት የሚያደርሱበት ነው፡፡ ሰራውም ከዚሁ ተግባሩ የተቀዳ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል «ቅድስት» ይባላል፡፡ የቤተክርስቲያኑ ማዕከላዊ ቦታ ነው፡፡ የኤጲስቆጶሱ (የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ) ወንበር በዚህ ክፍል ውስጥ ይቀመጣል፤ በጥንቱ ስርዓት ለቁርባን የተዘጋጁ ምዕመናን ቆመው የሚያስቀድሱበት ነው፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ክፍል «መቅደስ» ነው፡፡ በዚሁ ክፍል ስጋውና ደሙ«ይፈተትበታል» መንበረ ታቦቱና ሌሎችም ንዋየ ቅድሳት ይገኙበታል፡፡ የኢጲስቆጶሱ ማስቀደሻ ልዩ ወንበር በዚህ ክፍል ይገኛል፡፡ ወደዚህ ክፍል ለመግባት የሚችሉ ስልጣነ ክህነት ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

እንግዲህ ዘገኞች እንደሚሉት እሳተ ከላ ቤት «ቤተ ንጉስ» የተባለ ቅርፅ ካላቸውና በሰላጤው ውስጥ ከሚገኙት ቤተክርስቲያኖች ተኮርጀው የተሰሩ ናቸው፡፡ መሪጌታ ወርቁ ደበብ ይህንን ሲገልፁ የሚከተለውን ይላሉ፡-

> እሳተ ከላ ዛኒጋባ፣ የሴት ቤትና መቀደስ የሚባሉ ክፍሎች አሉት፡፡ ዛኒጋባ፣ የእንግዳ ማስተናገጃና የድግስ መደገሻ ክፍል ነው፡፡ ይህ ክፍል የዝማሬ ድግስ ከሚቀርብበት ቅኔ ማህሌት ከተሰኘው የቤተክርስቲያ ክፍል የተኮረጀ ነው፡፡ የሴት ቤት፣ በቤት ውስጥ ምግብና መጠጥ የሚዘጋጁባቸው፣ የሚቀመጡባቸውና የሚቀርቡባቸው ቤትን ቤት የሚያደርጉት ዕቃዎች የሚቀመጡበት ክፍል ነው፡፡ ካልተበላበትና ካልተጠጣበት ቤት ቤትነቱ አይታወቅምና በዚህ ክፍል የሚገኙ ዕቃዎች ለቤቱ ቤትነትን የሚሰጡ ናቸው፡፡ ክፍሉ ቅድስት ከተሰኘው የቤተክርስቲያን ክፍል ጋር እንዲመሳሰል ታስቦ የተሰራ ነው፡፡ቅድስት በቤተክርስቲያን ውስጥ ምዕመናን ቆመው የሚያስቀድሱበት ክፍል ነው፡፡ ምዕመናን ደግሞ ለአንድ ቤተክርስቲያን ህልውና ዋና ብቻ ሳይሆን ወሳኝም ናቸው፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ክፍሎች በያሉበት ቦታ የግድ አስፈላጊ የሆኑ «ጉዳዮች» ናቸውና ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ሦስተኛው ክፍል መቀደስ ነው፡፡ እሳት ከላ ይህንን ክፍል ተግባሩን ብቻ ሳይሆን ስሙንም ነው በቀጥታ የወሰደው፡፡ ክፍሉ አልጋ ይቀመጥበታል፤ አገልግሎቱ መኝታ ቤትነት ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ታቦትና ንዋየ ቅድሳት የሚቀመጡበትን መቅደስ የተባለውን ክፍል መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ አልጋ የመቀመጡ ምክንያት ክፍሉ በሌሎች የተከበበና መሃል ላይ የሚገኝ በመሆኑ ለደህንነት ሲባል ነው፡፡ የአልጋው እዚህ የመቀመጥ ምስጢር ግን የጋብቻን ክቡርነት ለመግለጽ ሲባል ነው፡፡ በቤተክርስቲያን መቅደስ ውስጥ የሚቀመጥ ታቦት ነው፡፡ ታቦት ደግሞ የቤተክርስቲያኑ መጠሪያ ነው፡፡ ገብርኤል ቤተክርስቲያን፣ ማርያም ቤተክርስቲያን እንዲሉ አማኞች ፡፡ በእሳተ ከላ ቤት

መቅደስ የሚቀመጠው ደግሞ አልጋ ነው። በተለይም ባልና ሚስት የሚተኙበት አልጋ። ይህም የጋብቻን ክቡርነት፣ የወሲብን ምስጢርነት ለመግለጽ ሲባል የተደረገ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ ክፍል ውስጥ መግባት መውጣት የሚችሉት የቤተሰቡ አባላት ብቻ ናቸው። በቤተክርስቲያን መቅደስም መግባት የሚችሉት ስልጣነ ክህነት ያላቸው ብቻ ናቸው (መርጌታ ወርቄ ደበብ፣25-9-1999) ።

በአጠቃላይ መሪጌታ ወርቄ ደበብና ሌሎችም መረጃ አቀባዮች እንደገለፁት እሳተ ከላ ቤት በአካባቢው ከሚገኙ ቤተክርስቲያኖች ተኮርጆ የተሰራ የቤት ዓይነት ነው።

እሳተ ከላ ሁለት በሮች ሲኖሩት መስኮቶች ግን የሉትም። በሮች አንዱ በምስራቅ ሌላው ደግሞ በደቡብ ይገኛሉ። በምስራቅ የሚገኘው በር የአባወራውና የእንግዳ መግቢያና መውጫ ነው። « አውራ በር » ይባላል። በስተደቡብ ያለው በር ደግሞ የቤቱ እመቤት መውጫና መግቢያ ነው። ስሙ «የሴት በር» ይባላል። አባወራው በሴት በር አይገለገልም። መስኮቶችን በተመለከተ ግን ሁሉም እሳተ ከላ ቤቶች የሚከፈቱና የሚዘጉ (ብርሃንና አየር የሚያስገቡ) መስኮቶች የሏቸውም።ይህም በመሆኑ በተለይም ወደ ሴት ቤት ሲገባ ሁልጊዜም ኩራዝ ተበርቶ ነው። ነገር ግን ግድግዳዎችን ለማስጌጥ ሲባል የሚሰሩ የመስኮት ቅርፅ ያላቸው ጣውላዎች ግድግዳዎች ላይ ይኖራሉ።(ዝርዝሩ ወደ ኋላ «ቤቶችን ማስጌጥ» በሚል ርዕስ ስር ይገለፃል)።

እንደ መረጃ አቀባዮች ገለፃ የጥንቶቹ የእሳተ ከላ ቤት ባለቤቶች «ምስለኔ» ወይም «ሊቀረድ»[5] የሚባል የማዕረግ ስያሜ የነበራቸው ሰዎች ሲሆኑ ዛሬም ቢሆን በእነዚህ ቤቶች የሚኖሩ ሰዎች የእነዚህ ሰዎች የልጅ ልጆች በመሆናቸው ከቤተሰቦቻቸው ከወረሷቸው ጥሪቶች የተነሳ ኑሯቸው ከአብዛኛው የሰላጤዋ ነዋሪዎች የተሻለ ነው።

ይህ የሆነበት እሳተ ከላ ግዙፍ ቤት እንደመሆኑ ግንባታው ሰፊ የሰው ሃይል የሚጠይቅ ስለሆነ ከፈቃደኝነት ውጭ ሰውን አዝዘው ሊያሰሩ የሚችሉ ከተራው ሰው ይልቅ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ስለሆኑ ነው።ሁለተኛው ቤት ደርብና ምድር ነው።

**ደርብና ምድር[6]** :- ደርብና ምድር እንደ እሳተ ከላ ሁሉ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የተሰራ ሌላው የዘጌ ባህረ ሰላጤ ባህላዊ ቤት ነው። ይህ ቤት የአሰራር ቅርፁ በዘመናዊ የቤት

---

[5] ምስለኔና ሊቀረድ የአካባቢው ባህላዊ የማዕረግ ስሞች ናቸው ። የማዕረጐች አመጣጥ ሰላጤዋን ከማስተዳዳር ጋር የተያያዘ ነው። አፄ አምደፅዮን (1314-44) ወደ ዘጌ መጥተው ከዘጌ መስራች ከአቡነ በትረማርያም ቡራኬ ከተቀበሉ በኋላ የዘጌን ገዳምነት አፅንተው ነው የተመለሱት ። ከዚህም በኋላ የሰላጤዋን ህዝብ በበላይነት የማስተዳዳር ስልጣን የገዳሙ መምህር ድርሻ ሆነ። ነገር ግን የገዳሚ መምህር ረዳት የሚሆናቸውን ሰዎች ይመርጡ ነበር። መምህሩ የሚመርጧቸው ሰዎች ምስለኔ (ሰለ እኔ) የሚባል ማዕረግ ሲኖራቸው ህዝቡ ደግሞ ሊቀረድና ጭቃ ሹም የሚባል ስልጣን ያላቸውን ሰዎች ይመርጣል። ምስለኔና ሊቀረድ ህዝቡን የመዳኘት ስልጣን ሲኖራቸው ጭቃሹም ደግሞ ከህዝብ ግብር የመሰብሰብ ለምስለኔውና ለሊቀረዱ የመታዘዝ ተግባር ይከውናል (ምስጌ፣ 1979 ዓ.ም) ።

[6] ምድር «መሬት» (ሰ)፣ምድር ቤት «ፎቅ ሆኖ በተሰራ ቤት ውስጥ ከመሰራቱ በላይና ከአንደኛው ፎት ስር ያለው

አሰራር ልማድ «ፎቅና ምድር» የሚባለውን የቤት አይነት ይመስላል:: ስያሜውም ከዚሁ ቅርፁ የተነሳ የተሰጠው ነው:: ቤቶች አንዱ በሌላው ላይ ተደራርበው የቆሙ መሆናቸውን ለማሳየት የላይኛው ቤት «ደርብ/የተደረበ» የሚል ስያሜ ሲኖረው የታችኛ ው ደግሞ ምድር (ቤት) ይባላል::




*ሥዕል 2፡ ደርብና ምድር ቤት*

ምድር ቤቱ በቁመቱ፣በግድግዳው ቅርፅ፣በክፍሎቹ ብዛትና መጠን ሙሉ በሙሉ ከእሳተከላ ቤት ጋር ተመሳሳይ ነው:: ግድግዳው እንደ እሳተከላ ቤት ሁሉ ክብ ነው:: ክፍሎቹም ዛኒጋባ፣ የሴት ቤትና መቅደስ ይባላሉ:: ዛኒጋባ፤ለእንግዳ ማስተናገጃና ለቤተሰቡ ምግብ መብያና ቡና፣መጠጫ፣ የሴት በር፣ ለምግብ ማስቀመጫ፣ መቅደስ ደግሞ ለመኝታ ቤት የሚያገለግል በመሆኑ የክፍሎች ተግባርም ከእሳተ ከላ ቤት ጋር አንድ አይነት ነው:: አሰራሩም ቢሆን እንደ እሳተ ከላ ቤት እሳት የማያስደርስ ነው:: ነገር ግን ሁለቱ ቤቶች የሚለያዩት እሳተከላ ቤት ግድግዳው ካለቀ በኋላ ሽጣጣ ቅርፅ ያለው የቤቱ ጣሪያ ሲገኝ በደርብና ምድር ቤት ግን የታችኛው ቤት ግድግዳ እንዳለቀ ጣሪያ በመገኘት ፈንታ«ጠፍጠፍ» በተባለ ጠፍጣፋ ጣውላ ግድግዳው ይከደናል:: ከጣውላውም በኋላ እንደገና ግድግዳ መስራት ይጀመራል:: ይህ ጣውላ ለታችኛው ቤት ጣሪያ (ኮርኒስ)፣ ለላይኛው ቤት ደግሞ ወለል ሆኖ ያገለግላል:: የላይኛው ቤት (ደርቡ) ባለአንድ ክፍል ቤት ነው:: ከቃል መረጃ አቀባዮች ውስጥ ቄስ ገበዝ ይኄይስ እንግዳው እንደገለፁት «የደርብ ቤት አገልግሎት ለቡና ማጠራቀሚያ ነው:: በአንዳንድ ቤቶች

---

ቤት» (አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993.81-82)

ደረበ (ግ) ፡-አንዱን በሌላው ላይ አደረገ፣ ጨመረ፣ጫነ፣ አነባበረ

ደርብ (ስ) በድሮ ጊዜ የሚሰራ ባለአንድ ፎቅ ቤት:: (አማርኛ መዝገበ ቃላት፣1993.460)

ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ ለጠበንጃ ማኖሪያም ያገለግላል። ነገር ግን አሁን ተዘዋውሬ ባየኋቸው ቤቶች አንድም ደርብ ቤት ቡና ተቀምጦበት አላየሁም። ይልቁንም የመኝታ ክፍል ሆኖ ነው ያየሁት፡ ይህም ዛሬ አንድ ቤት የሚይዝ ቀርቶ ለአይን የሚሞላ የቡና ምርት እንኳን ማግኘት ካለመቻሉ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ እንደሆነ ቄስገበዝ ይሄይስ እንግዳውና ወ/ሮ ስገነት አሸተ የተባሉ መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ።

በተለይም ቆየት ባለው ጊዜ ከደርብ ቤቱ ከቤተሰቡ በስተቀር ሌላ ሰው መግባትና መውጣት አይችልም። የቤተሰቡ አባላት ከታችኛው ቤት ተነስተው ወደ ላይኛው ቤት ለመውጣት የሚጠቀሙት በደረጃ ነው። የደረጃው ቁጥር አስራ ሁለት ነው። አስራ ሁለት የመሆኑ ሚስጥርም ለ12ቱ ሃዋርያት ተምሳሌት ነው ሲሉ መርጌታ ወርቁ ደበብ መረጃ ሰጥተዋል ። ደርብና ምድር ቤት የታችኛው ክፍሉ ከእሳተ ከላ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ እንደ እሳተ ከላ ቤት ሁለት በሮች አሉት። መስኮቶች ግን የሉትም ። ደርቡ ግን አንድ በር ብቻ ነው ያለው። ከደርቡ ቤት ዙሪያም ሰው ሊያስቆምና ሊያስቀምጥ የሚችል ቦታ (በረንዳ) አለው። የደርብና ምድር ቤት ባለቤቶች እንደ እሳተ ከላ ቤት ሁሉ አያቶቻቸውና አባቶቻቸው ምስለኔ ወይም ሊቀረድ የነበሩ እነሱ ደግሞ በአካባቢው ከሚኖረው ሰው የተሻለ የኑሮ ደረጃ ያላቸው ናቸው።

በአጠቃላይ እሳተከላና ደርብና ምድር ቤት ከተሰሩ ረጅም ዘመን የሆናቸው ዛሬ ሰዎች የሚኖሩባቸው እንጂ የማይሰሩ ቤቶች ናቸው። እነዚህ ቤቶች ከአሰራራቸው ዘዴ የተነሳ በእሳት ጉዳት የማይደርስባቸው ዛኒጋባ፣ የሴት በርና መቅደስ የተባሉ ክፍሎች አሏቸው። ክፍሎች ቅኔ ማህሌት፣ቅድስትና መቅደስ የተባሉ የቤተክርስቲያን ክፍሎችን ምሳሌ አድርገው የተሰሩ ናቸው። እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ባለቤቶቻቸው፣ አያቶቻቸውና አባቶቻቸው ምስለኔ ወይም ሊቀረድ የነበሩ እነሱ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ያላቸው መሆኑ የሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች ሲሆኑ በሁለቱ መካከል ደግሞ እሳተ ከላ ምድር ቤት ብቻ፣ ደርብና ምድር ደግሞ ሁለት ቤቶች ተደራርበው የቆሙበት መሆናቸው፣ደርብና ምድር ቤት ከእሳተ ከላው ቤት ይልቅ ቁመቱ ረዥምም መሆኑ፣ መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት ደግሞ ደርብና ምድር ቤት የጥሬ ዕቃ ፍጆታው ከእሳተ ከላው የሚበልጥ መሆኑ የተለያዩ አድርጓቸዋል። ከዚህ ቀጥሎ የሚነሳው ሶስተኛው ባህላዊ ቤት ደግሞ ጎጆ ቤት ነው።

ጎጆ ቤት፡- ጎጆ ቤት በሰላጤው ከሚገኙ ባህላዊ ቤቶች ውስጥ አንዱ ነው። ሳር ቤት እየተባለም ይጠራል። «ከጥንት ከአባት የመጣ ነው።» ከሚለው ከዘገኞች መልስ በስተቀር ከመቼ ጀምሮ በሰላጤው ውስጥ መሰራት እንደጀመረ የሚገልፅ መረጃ የለም። ነገር ግን በሁሉም መረጃ አቀባዮች ዘንድ የሚታመነው ጎጆ ቤት የቡና ምርት ከእለት እለት እየቀነሰ፣ እሳተ ከላና ድርብና ምድር ቤት የመስራት አቅም እየጠፋ ሲመጣ

መስራት የተጀመረና የተስፋፋ ቤት መሆኑን ነው፡፡ እናም እስከ 1980ዎቹ መጀመሪያ ድረስ በስፋት በመሰራትና (ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን ቆርቆሮ ቤት የመስራት ባህል ተስፋፍቷል) በማገልገል ላይ ያለ የባህላዊ የቤት አይነት እንደሆነ የቃል መረጃዎችና ለዚህ ጥናት የተደረገው ምልከታ ይገልፃሉ፡፡ ዳሩ ግን ዘገኞች ከዚህ በኋላ ምናልባት ጎጆ ቤት መስራት ሊቀር እንደሚችል ፍርሃታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ አቶ ጀመረ ክብረት የተባሉ የ60 ዓመት የሰላጤዋ ነዋሪ ስለዚሁ ጉዳይ ሲናገሩ፡-

> አባቶቻችን ሲነግሩን ጥንት ዘጌ ውስጥ ቤቶች ሁሉ እሳተ ከላና ደርብና ምድርቤት ብቻ ነበሩ፡፡ በእኛ ዕድሜ ደግሞ በተለይ በ1962 ዘጌን በረዶ ደብድቦት ቡናው ያለምርት ከቀረ ወዲህ እስከ 1980ዎቹ ድረስ ሰው ሁሉ ሳር ቤት ይሰራ ነበር፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ሳር እየጠፋ ስለሆነ ሰዉ ሁሉ ቆርቆሮ ቤት ወደ መስራቱ አተኩሯል፡፡ ሁሉም በየጊዜው የሚቀያየር ሳር ከመግዛት ይልቅ አንድ ጊዜ ቆርቆሮ ቤት ሰርቶ ማረፍ ይፈልጋል፡፡ እንዲያውም እኔ ከዚህ በኋላ የሚወለዱ ልጆች ጎጆ ቤት ምን አይነት እንደሆነ የማያውቁ ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ እፈራለሁ (27-9-1999 ) ፡፡

ሲሉ በዘጌ ባህረሰላጤ ውስጥ ቤቶች ከምን ተነስተው የት እንደደረሱ ይናገራሉ፡፡ ከንግግራቸውም በዘጌ ባህረሰላጤ ቤቶች ከጅምሩ ደርብና ምድርና እሳተ ከላ ነበሩ፤ ከዚያ ጎጆ ቤት ሆኑ፤ አሁን ደግሞ ቆርቆሮ ቤት እየተሰራ ነው የሚል ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ በእርግጥ በምልከታ ማረጋገጥ የተቻለውም ዛሬ የብዙ ሰዎች ቤት ቆርቆሮ መሆኑን ነው፡፡


ጎጆ ቤት እንደመጀመሪያዎቹ ሁለት ቤቶች ሁሉ ግድግዳው ክብ ነው፡፡ ነገር ግን ባለ አንድ ክፍል ቤት ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን አንዳንድ ጎጆ ቤቶች «የአልጋ ጓሮ» የሚባል በአልጋ ቅርፅና መጠን የቤቱ ግድግዳ ወደ ኋላ ተስቦ የሚሰራ ክፍል አላቸው፡፡ ይህ ክፍል የተደረገባቸው ቤቶችም በመጠኑ ክብነታቸውን ያጣሉ፡፡

ጎጆ ቤት እንደ ባለቤቱ አቅምና ፍላጎት (በተለይም አቅም) አንፃር ቤተ12 (ከቤቱ መሃል (ምሰሶ) እስከ ግድግዳው 6 ክንድ)፣ ቤተ9 (ከምሰሶ እስከ ግድግዳው 5 ክንድ) ቤተ6 (ከምሰሶ እስከ ግድግዳው 3 ክንድ) በሚባል መጠን ተወስኖ ይሰራል፡፡ የጎጆ ቤት ጣሪያ እንደ እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ሁሉ ሾጣጣ ቅርፅ (cone shape) ያለው ነው፡፡ የሚከደነውም ሳር ነው፡፡ ነገር ግን የጣሪያው አሰራር እንደ እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ቤቱን ከእሳት አደጋ የሚታደግ አይደለም፡፡ ሆኖም ከሚከደንበት ሳርና የአከዳደን ስልት አንፃር ሁለት ዓይነት የሳር ቤት አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም «ክፍክፍ»ና «አልባሶ» ይባላሉ፡፡

ክፍክፍ፣ ለጣሪያው ከሚከደነው የሳር ዘርና ከአከዳደኑ ስልት በስተቀር ከሌላኛው የጎጆ ቤት ዓይነት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለክፍክፍ ቤት ጣሪያ መክደኛ የሚውሉ የሳር አይነቶች «ቋያ» ና «ሲላ» / «ስርሰራ» ይባላሉ፡፡ እነዚህ ሳሮች ባለ አንጓ ሲሆኑ ቤቱ

ላይ ተከድነው ለረጅም ጊዜ ሳያረጁ ስለሚቆዩና ለቤቱ ውብትን ስለሚሰጡ ዋጋቸው ውድ ነው።

እነዚህ ሳሮች ቤቱ ላይ ሲከደኑ የአቀማመጥ ቅርፃቸው፣ ሳሮች ከመሬት የሚበቅሉበት አቅጣጫ ወደታች የሚያድጉበት አቅጣጫ ደግሞ ወደ ላይ እየተደረገ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን የሳር ቤት ከደና ከጣሪያው ጠርዝ የሚጀምር ስለሆነ አንዱ ሳር በሌላው ላይ እየተሰካካ የሳሮችን አቀማመጥ የተወሳሰበ ቅርፅ እንዲይዝ ያደርጋል። ይህም የሳር ክዳኑ በቤቱ ጣሪያ ላይ የሚያምር ቅርፅ እንዲያመጣ የሚያደርገው ሲሆን ለበለጠ ውብት ሲባልም ጣሪያው ላይ የተከደነው ሳር በሚበቅልበት አቅጣጫ ከዋንዛ ዛፍ በተሰራ የጎራዴ ቅርፅ ባለው «መከፍከፊያ» በተባለ እንጨት በቀላል ምት ይደበደባል።



*ሥዕል3 ፡ ክፍክፍ ጎጆ ቤት*

ለክፍክፍ ቤት መስሪያ የሚውሉ ሳሮች ዋጋቸው ውድ በመሆኑ እነዚህን ቤቶች የሚሰሩ የኑሯቸው ደረጃ በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ መካከለኛ የሚባሉ ሰዎች ናቸው።

አልባሶ ሁለተኛው የጎጆ ቤት አይነት ነው። ይህ ቤት የሳር አከዳደኑ ሳሩ የሚያድግበት በኩል ወደ ታች የሚበቅልበት ደግሞ ወደ ላይ (የክፍክፍ ተቃራኒ) በመሆን የሚሰራ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ለአልባሶ ክዳን የሚውለው አኩሲ የተባለ የሳር አይነት ውስጡ ክፍት ስለሆነ ዝናብ በዘነበ ጊዜ ውሃው ውስጡ ገብቶ ጣሪያውን በቀላሉ እንዳያበሰብሰው ነው። አኩሲ ዕድሜው አጭር፣ ዋጋው አናሳና በየዓመቱ መቀየር የሚፈልግ በኑሯቸው ዝቅ ያለ ደረጃ ያላቸውና የአካባቢው ነዋሪ «ደሃ» የሚላቸው ሰዎች ቤት የሚከደንበት ሳር ነው።

ለምሳሌ በሰላጤዋ ውስጥ ተዘዋውሬ ካየኋቸው አልባሶ ክዳን ካላቸው የጎጆ ቤቶች ውስጥ የወ/ሮ ስንታየሁ ዕድሜነው ቤት አንዱ ነው። ሴትዬዋ ስለራሳቸው እንደገለፁት የ60 ዓመት ባለፀጋ ናቸው። የሚኖሩት በአፋፍ/ 01 ቀበሌ ውስጥ ነው። ቤታቸው ጎጆ ሲሆን የሳሩ አከዳደን ስልት አልባሶ ነው። ለ30 ዓመታ በዚህ ቤት ውስጥ ኑረዋል። ለረጅም ዓመታትም በየአመቱ የቤቱን ሳር ሲያስቀይሩ ኑረዋል። በፊት ትዳር

የነበራቸው ሲሆን የእሳቸው፣ መሃል ዘጌ የባለቤታቸው ደግሞ ይጋንዳ ተክለሃይማኖት በተባሉ ጎጦች ውስጥ የቡና መሬት ነበራቸው:: ነገር ግን በ1967 ዓ.ም በተደረገው የመሬት ሽግሽግ ወቅት አፋፍ ያለውን ቦታ ትተው ለመሄድ ስላልፈለጉ የቡና መሬታቸው ለሌላ ሰው ተሰጠ:: በዚህ የተነሳ ኑሮ ቀስ በቀስ እየከበደ መጣ:: ከስድስት ዓመት በፊት ደግሞ ባለቤታቸው ሲሞቱ ኑሮን መሸከም ከበዳቸው:: ምንም እንኳን ጌሾና ብቅል እየሸጡ የሚተዳደሩ ቢሆንም ንግዱሆድ ከመሙላት አልፎ ቤት የሚያሳድስ አይደለም:: በመሆኑም ከዛሬ ስድስት ዓመት ጀምሮ የቤቱ ሳር ተለውጦ አያውቅም:: ከዚህም የተነሳ«ቅንቡርስ» የተባለ ትል ሳሩን እየበላ ስለጨረሰው ቤቱ ያፈሳል ግድግዳውም መበስበስ ጀምሯል:: ይህ የወ/ሮ ስንታየሁ ቤትም የሌሎች መሰሎቻቸውን ቤቶች የሚያሳይ ነው:: ጎጆ ቤት በጠቅላላው አንድ በር ብቻ ያለው ሲሆን እሱም በምስራቅ አቅጣጫ ይሰራል::



ሥዕል 4: አልባሶ ጎጆ ቤት

በጠቅላላው ከሚከደኑበት የሳር አይነትና ከሳር አከዳደናቸው የተነሳ ክፍክፍና አልባሶ የተባሉ ሁለት አይነት ጎጆ ቤቶች ያሉ ሲሆን እነዚህ ቤቶችም የባለቤቶቻቸውን ማህበራዊ ደረጃዎች የሚያሳዩ ናቸው::

ሠንጠረዥ 1 የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች አማካይ መጠን

| የቤቱ ዓይነት | | ስፋት | ቁመት | የጣሪያ ቁመት | ዙሪያ | የበር ቁመት | የበር ስፋት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እሳተ ከላ | | ቤተ 14 (ከመሃል እስከ ግድግዳ 7 ክንድ) / 7ሜ | 8 ክንድ (4ሜ) | 26 ክንድ (13 ሜ) | 60 ክንድ (30 ሜ) | 6 ክንድ (3 ሜ) | 3 ክንድ (1 1/2ሜ) |
| ደርብና ምድር | | ቤተ 14(ከመሃል እስከ ግድግዳ 7 ክንድ) / 7ሜ | 14 ክንድ (7 ሜ) | 26 ክንድ (13 ሜ) | 60 ክንድ (30 ሜ) | 6 ክንድ (3 ሜ) | 3 ክንድ (1 1/2ሜ) |
| ጎጆ ቤት | ትልቁ | ቤተ 12 ከምሰሶ አስከ ግድግዳ 6 ክንድ/ 6ሜ | 6ክንድ (3 ሜ) | 20 ክንድ (10 ሜ) | 52 ክንድ (26 ሜ) | 6 ክንድ (3 ሜ) | 3 ክንድ (1 1/2ሜ) |
| | መካከለኛ | ቤተ 9 ከምሰሶ እስከ ግድግዳ 5 ክንድ/ 5ሜ | 5ክንድ (2 1/2 ሜ) | 16 ክንድ (8 ሜ) | 34 ክንድ (17 ሜ) | 4ክንድ (2 ሜ) | 2 ክንድ (1ሜ) |
| | ትንሹ | ቤተ 6 ከምሰሶ አስከ ግድግዳ 3 ክንድ/ 3ሜ | 4 ክንድ (2 ሜ) | 10 ክንድ (5 ሜ) | 26 ክንድ (13 ሜ) | 3 ክንድ (11/2ሜ) | 2 ክንድ ( 1 ሜ) |

ከሰንጠረገፑ ማየት እንደሚቻለው በሰላጤው በጠቅላላው ደርብና ምድር ና እሳተ ከላ በቁመታቸው አንዱ 7 ሌላው ደግሞ 4 ሜትር ሆነው ከመለያየታቸው በስተቀር በአብዛኛው መጠናቸው አንድ አይነት ነው:: በአንፃሩ ወደ ጎጆ ቤት ሲመጣ ደግሞ ጎጆ ቤት በራሱ ትልቅ፣ መካከለኛ ና ትንሽ ተብሎ የሚከፈል ሲሆን ትልቅ ጎጆ ቤት በበር ቁመትና ስፋት ከደርብና ምድር እንዲሁም ከእሳተ ከላ ጋር ይመሳሰላል:: ከዚህ ውጭ ግን ጎጆ ቤቶች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከሁለቱ ጥንታዊ ቤቶች ጋር ሰፊ የመጠን መለያየት አላቸው::

በአጠቃላይ የሰላጤዋ ነዋሪዎች ቅርፃቸውንና መጠናቸውን መሰረት አድርገው በወገኗቸው መሰረት በዘጌ ባህረ ሰላጤ እሳተ ከላ፣ ደርብና ምድር ና ጎጆ ቤት የሚባሉ ሶስት ዓይነት ባህላዊ ቤቶች አሉ:: ከእነዚህ ቤቶች ውስጥ ደግሞ ጎጆ ቤት ትልቅ፣ መካከለኛ ና ትንሽ ተብሎ የሚከፈል ሲሆን ጣሪያው ከሚከደንበት የአከዳደን ስልት የተነሳ ደግሞ ክፍክፍና አልባሶ ተብሎ በሁለት ይከፈላል:: እነዚህ ቤቶች ሁሉም ለሰዎች መኖሪያነት የሚያገለግሉ ቢሆንም የባለቤቶቻቸው ደረጃ ያሳያሉ:: በእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት የሚኖሩ ሰዎች ኑሯቸው ከአካባቢው ነዋሪዎች የተሻለ ነው:: ይህም የሆነው እነዚህ ሰዎች ቤቶችን ከሌሎች ጥሪቶች ጋር የሊቀረድነትና ምስለኔነት ማዕረግ ካላቸው አያቶቻቸው በውርስ ያገኟቸው ስለሆነ ነው:: በክፍክፍ ጎጆ ቤት የሚኖሩት ደግሞ መካከለኛ ኑሮ ያላቸው ሲሆኑ በአልባሶ ጎጆ ቤት የሚኖሩት «ድሆች» ናቸው::

## 5.2 ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች

የተለያዩ የፎክሎር ባለሙያዎች እንደሚገልጹት ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች ቤቶቹ ከሚገኙበት አካባቢ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው:: ጥሬ ዕቃዎች የሚይዙት ትርጉምም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ነው:: እንዲያውም አካባቢ የበለጠ ብዙ ነገሮችን ይወስናል (Oring 1986, Glassie 1999) ::

በዘጌ ባህረሰላጤ ውስጥ የቤቶችን የመስሪያ ቁሶች አስመልክቶ ቃለመጠይቅ ያደረግሁላቸው መረጃ አቀባዮች ሁሉ እንደገለፁልኝና በአስራ አራቱም ጎጦች ተዘዋውሬ እንደተመለከትኩት በሰላጤዋ ውስጥ ሳር፣ ጭቃ፣ እንጨት፣ ሃረጎች፣ ድንጋይ ና ሸክላ ዋና ዋና የባህላዊ ቤቶች መስሪያ ጥሬ ዕቃዎች ናቸው:: እነዚህ ጥሬ ዕቃዎችም ከሳር በስተቀር ሁሉም በሰላጤዋ ውስጥ የሚገኙ ናቸው::

ሳር ለቤቶች ጣሪያ መክደኛና ለጭቃ ማቡኪያ ያገለግላል:: ለጣሪያ መክደኛ የሚያገለግሉ የሳር አይነቶች አኩሲ፣ ቋያ፣ ሲላ/ስርስራ ሲባሉ ለጭቃ ማቡኪያ የሚያገለግል ሳር ደግሞ «ጭድ» ይባላል:: ጭድ፣ ዳጉሳና ጤፍ ከተባሉ የእህል ምርቶች የሚገኝ ተረፈ ምርት ነው:: ነገር ግን የአካባቢ ጥበቃ ጥናት ፖሊሲና ቁጥጥር መምሪያ (1996) እንደሚገልፀው ዘጌ ባህረሰላጤ፣ ቡና፣ ሎሚ፣ ጌሾ፣ ቦህሮ(የሎሚ ዘር)፣ እንጂ

የሰብል ምርት የማታመርት በመሆኗ ቤት ሰሪዎች ወንጀጣና ሰቀለጥ (የሰላጤዋን ካርታ ይመልከቱ) ከተባሉ የሰብል ምርት አምራች የሰላጤዋ ጎረቤት ገጠሮች ገዝተው በታንኳ ወደ ሰላጤዋ ያስገባሉ:: ለቤት መክደኛ የሚያገለግሉት ሳሮችም ከአኩሲ በስተቀር እንደ ጭዱ ሁሉ ከወንጀጣና ሰቀለጥ በግዢ ይገባሉ:: አኩሲ ግን እዚያው ሰላጤው ውስጥ ይበቅላል::

ጭቃ፣ አፈር ውሃና ጭድ ተቀላቅለው የሚሰራ ለስስቱም ባህላዊ ቤቶች ለግድግዳ መስሪያ የሚያገለግል ጥሬ ዕቃ ነው:: ሆኖም ከጎጆ ቤት ይልቅ ለእሳተ ከላ እና ደርብና ምድር ቤቶች ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው:: ምክንያቱም የጎጆ ቤት ግድግዳ ከእንጨትና ከጭቃ የሚሰራ ሲሆን ሁለቱ ቤቶች ግን ከጣሪያቸው ላይ ጭቃ ከመፈለጋቸው ባሻገር ግድግዳዎቻቸውም ሙሉ በሙሉ ከጭቃ ብቻ የሚሰሩ ናቸው:: ለሁሉም አይነት ቤቶች ግድግዳ መስሪያ የሚሆነው ጭቃ የሚሰራው ከዚያው ከሰላጤው ውስጥ ከሚገኘው «ዋልካ» አፈር ሲሆን ቤቱን በማስዋብ ጊዜ የምስጥ አፈር (ቀይ ቀለም ያለው ምስጥ የተባለ ነፍሳት ቤቱን የሚሰራበት አፈር) ተፈልጎ አገልግሎት ይሰጣል:: ነገር ግን ቤቶች የሚጠቀሙት ጭቃ የመቡካት መጠን ይለያያል:: በኡራ ኪዳነ ምህረት ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆነውና ስለ እሳተ ከላ ቤት አሰራር የቃል መረጃ የሰጠው አቶ ዋሴ እንየው እንደገለፀው አንድ እሳተ ከላ ወይም ደርብና ምድር ቤት ሲሰራ ለመስሪያ የሚውለው ጭቃ ቢያንስ ለመንፈቅ (ስድስት ወር) ያህል በሂደት ላይ መቆየት አለበት:: ውሃው፣ ጭዱና አፈሩ ከተገናኙበት ቀን ጀምሮ ሲረዝም በየወሩ ሲያጥር ደግሞ ከወር በፊት የተቦካው ጭቃ «እየተገላበጠ» (መልሶ እየተቦካ) የእለቱ ስራ ሲያልቅ ጭድ እየለበሰ በደንብ እንዲቦካ ይደረጋል:: የመቡካቱ መጠን ጭቃው እስኪገማ (መጥፎ ጠረን አምጥቶ እስኪያስቸግር) ድረስ ይደርሳል:: ይህ ከሆነ ጭቃው ግድግዳ ሆኖ ሲቆም በቀላሉ እንዳይፈርስ ይረዳል::ለጎጆ ቤት መስሪያ የሚውለው ጭቃ ግን ከ1-2 ወር ድረስ በሂደት ከቆየ ይበቃዋል::

እስካሁን ከቀረቡት በተጨማሪ ሌላው ለቤት መስሪያ የሚያገለግለው ጥሬ ዕቃ እንጨት ነው:: እንጨት ለዘጌ ሰላጤ ባህላዊ ቤቶች በስፋት አገልግሎት የሚሰጥ የቤት መስሪያ ቁስ ነው:: እጅግ ረጅም ዕድሜ ያላቸው እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶችን የሰሩ ሰዎች እንጨትን ለጣሪያ፣ ለበርና ለቤቶች የውስጥ ማስዋቢያ የተጠቀሙበት ሲሆን ጎጆ ቤቶች ደግሞ ጣሪያዎቻቸው፣ ግድግዳዎቻቸውና በሮቻቸው ሙሉ በሙሉ ከእንጨት የተሰሩ ናቸው::

በዘጌ ባህረሰላጤ ዋንዛ፣ ምሳና(ብሳና)፣ ሰሳ፣ ዝግባ፣ ብርብራ፣ ቃዋ፣ እሸ፣ ሰልቸን፣ ከነዳባ፣ የባህር ዛፍ፣ ሰንሰል የተባሉ የእንጨት ዘሮች ሲኖሩ (የአካባቢ ጥበቃ ጥናት ፖሊሲና ምርምር 1996) ከእነዚህ ውስጥ ዋንዛ፣ ዝግባ፣ አኮማ፣ እሼ፣ ሰሳ፣ ብርብራና ቃዋ ባህላዊ ቤቶችን ለመስራት ያገለግላሉ:: እነዚህ እንጨቶች በቀላሉ

በነፍሳት የማይጠቁ፣ ቁመታቸው ከሰላሳ ሜትር በላይ የሆነ፣ ወርዳቸውም ሰፋፊ ስለሆነ የሚመረጡ ሲሆን ዋንዛ ግን ከስፋቱ ባሻገር ቅርፅ ለማውጣት ብዙ የማያስቸግር በመሆኑ ለእሳተ ከላና ለደርብና ምድር ቤት የውስጥ ማስዋቢያ ለሁሉም ቤቶች ደግሞ ለመዝጊያ መስሪያ ያገለግላል።

ዛፎች ከእንጨታቸው ባሻገር ልጣቸውም(እርጥብ ቅርፊት) ለባህላዊ ቤቶች መስሪያ ያገለግላል። የዛፎች ልጥ የቤቶች ጣሪያና ግድግዳ ሲሰራ ለእንጨት ማሰሪያ በማገልገል የምስማርን ቦታ ይተካል። የሰላጤዋ ነዋሪ አቶ ወርቂ ተባባል እንደገለፁት ከልጥ ሌላ ራሳቸውን ችለው የሚበቅሉ «ልንኩኪ»ና «ሎቻ» የሚባሉ በባህላዊ ቤቶች ስራ ወቅት የምስማርን ተግባር የሚከውኑ የእፅዋት አይነቶች አሉ።

«ልንኩኪ» ጠንካራና በጣም ተፈላጊ የሃረግ አይነት ነው። ይህ ሃረግ ጥንካሬው ከቆዳ ጠፍር ይበልጣል። ሃረጉ ጠንካራ ስለሆነ ከበቀለበት ቦታ ከተቆረጠ በኋላ ውሃ ውስጥ (ጣና ሃይቅ) ይነከርና ሲርስ ይወጣል። በውሃ ሲርስ በቀላሉ የመታጠፍና የመዘርጋት ባህርይ ይይዛል። ከዚህ በኋላ ሃረጉ እየተሰነጣጠቀ ለማገርና ጣሪያ ማሰሪያ ይውላል።

«ሎቻ» ደግሞ ከእርጥብ ደንገል የሚሰራ ነው። ደንገሉ ጣና ሃይቅ ድንበር ይበቅላል። ሎቻ ሲዘጋጅ በመጀመሪያ ደንገሉ ይቆረጣል። ከዚያ ደንገሉ እየተጠመዘዘ «እንዲለፋ» (በቀላሉ እንዲታጠፍና እንዲዘረጋ) ይደረጋል። በዚህ ሁኔታ በርካታ ደንገል ወደ ሎቻነት ይቀየርና ለማገርና ጣሪያ ማሰሪያነት ያገለግላል።

ሸክላም እንዲሁ ለባህላዊ ቤቶች መስሪያ የሚያገለግል ጥሬ ዕቃ ነው። ሸክላ በአካባቢው ከሚገኝ «ዋልካ» ከሚባል የአፈር አይነት የሚሰራ ሲሆን በአብዛኛው አገልግሎቱ ለቤት ቁሶች መስሪያ ነው። ይሁን እንጅ በቤት ስራ ወቅት በቤቱ ጣሪያ ላይ ለሚቀመጥ «ቤተ ሞገስ» ለተባለ ቁስ መስሪያ ያገለግላል። ይህ ቁስም ቤቱ በዝናብ እንዳይበሰብስ የሚያደርግና ለቤቱ ግርማሞገስን የሚሰጥ ነው። የማህበረሰቡን ሃይማኖትም ያንፀባርቃል። (ዝርዝሩ ወደ ኋላ ይገለጻል )።

ከዚህ በተረፈ ድንጋይ፤ ለእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት መሰረት ማውጫ፣ ሰኔል፤ ለጣሪያ ንጣፍ፣ ሸንበቆ፤ ዛኒጋባ ለተባለው የቤት ክፍል ግድግዳ መስሪያ፣ ጠፍር፤ ለማገር ማሰሪያ የሚያገለግሉ ቁሶች ናቸው።

በአጠቃላይ የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች የሚሰሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች ሳር፣ ጭቃ፣ እንጨት፣ ልጥ፣ ሃረግ፣ ሸክላ፣ ሰኔል፣ ሸንበቆ፣ ድንጋይ ሲሆን እነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ደግሞ በአየር ንብረት ሳቢያ በአካባቢው ካልተገኘው ከሳር በስተቀር ሁሉም በአካባቢው የተገኙ (ሃገር በቀሎች) ናቸው።

## 5.3 የባህላዊ ቤቶች የአሰራር ሂደትና ዘዴ

Oring (1986,210 «ባህላዊ ቤቶች ሲሰሩ ስራው የራሱ ሂደት ያለውና ቀስ በቀስ በደረጃ የሚከናወን ተግባር ነው።» ሲሉ እንደገልፁት በዘጌ ባህረ ሰላጤ የቤት አሰራርን በተመለከት የተሰበሰበው መረጃም የሚገልፀው የቤት ስራው ሂደቶች እንዳሉትና ሂደቱም ከቁስ ስብሰባ የሚጀምር መሆኑን ነው።

### 5.3.1. ጥሬ እቃ ስብሰባ

የተለያዩ የቃል መረጃ አቀባዮች እንደገለፁልኝ አንድ ሰው ቤት ለመስራት በፈለገ ጊዜ የመጀመሪያው ተግባር ለቤቱ መስሪያ የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችን መሰብሰብ ነው። በዚህም መሰረት ሰውየው እንደሚሰራው የቤት አይነትና መጠን የጥሬ ዕቃዎቹን መጠን ወስኖ የጥሬ ዕቃ ስብሰባውን ይጀምራል።

የሚሰራው ቤት እሳተ ከላ ወይም ደርብና ምድር ቤት የሆነ እንደሆነ የቤቱ ሥራ ከመጀመሩ አምስትና ስድስት ዓመታት አስቀድሞ የጥሬ ዕቃ ስብሰባ ይጀመራል። ይህም ሆኖ ግን እነዚህ ቤቶች እጅግ ግዙፎችና ለልጅ ልጅ እንዲተላለፉ ታስበው የሚሰሩ በመሆናቸው የቁስ ስብሰባው ሂደት በአንድ ቤተሰብ ብቻ የሚከወን አይደለም። ዘመድ ጎረቤት አስቀድሞ ተነግሮት ሁሉም የአቅሙንና የችሎታውን ስራ በመስራት ይተባበራል። ለምሳሌ የተወሰነው ሰው አፈር ሲቆፍር ሌላው አፈር ወደ ሚቦካበት ቦታ ሊያግዝ ይችላል። ሌላው እንጨት ይቆርጣል፤ የተረፈው ደግሞ ለማሰሪያ የሚሆን ልጥ ይልጣል ወዘተ። በዚህ ሁኔታ በወዳጅ ዘመድ እርዳታ ለባህላዊ ቤቶች መስሪያ የሚያገለግሉ ቁሶች በሙሉ ይሰባሰባሉ። ነገር ግን የሚሰራው ቤት ጎጆ ቤት ከሆነ የቁስ ስብሰባው የቤቱ ስራ ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት ሊጀምር ይችላል። በስብሰባውም እንደ እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ብዙ ሰው ላይሳተፍ ይችላል። እንዲያውም በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚገልፀው በሰላጤዋ ውስጥ የነበረው ስራን ተረዳድቶ የመስራት ባህል እየቀረ ነው። የሰላጤዋ የቡና ምርት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣት በህዝቡ ኑሮላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። ከዚህም የተነሳ ነዋሪዎቿ ለሚሰሯቸው ቤቶች እንደ ጥንቱ ብዙ ጥሬ ዕቃዎችን አይጠቀሙም። በመሆኑም በተለይ አሁን አሁን የሚሰሩት ቤቶች ጥሬ ዕቃዎቻቸው የሚሰበሰበው ቤት እንዲሰራለት በሚፈልገው ሰው (በባለቤቱ) ብቻ ነው። ቁሶችን ራሱ አቅርቦ ቤት ስራውን ብቻ እንዲያግዙት ሰዎችን ይጠይቃል። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ቤት ስራው ራሱ በአንድ ቤተሰብና በጥቂት ወዳጆችና ዘመዶች ብቻ ሊከወን ይችላል። ተጨማሪ ጉልበት ካስፈለገ ደግሞ ብዙ ጊዜ

ተመራጭ ባይሆንም የቀን ስራተኛ ይቀጠራል (አቶ አለሙ ታዬ 27-8-99፣ቄስ ገበዝ ይሄይስ እንግዳው 3-2-2000) ::

ነገር ግን የተሳታፊው ቁጥር ይብዛም ይነስ ለቤት መስሪያ የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎች የሚሰበሰቡት በሰዎች ትብብር ነው:: ይህ ትብብርም በቁስ ስብሰባ ብቻ የሚቆም አይደለም:: ቤቱ ተሰርቶ እስኪያልቅ ይዘልቃል:: ታዲያ የቤቱ ባለቤት ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው ስራውን ለሚያግዙት ሰዎች ገንዘብ አይከፍላቸውም:: እህል ውሃ አቅርቦ ቁርስ፣ ምሳና እራታቸውን ያበላቸዋል እንጅ:: ለዚህም ስራዬ ብሎ ድግስ ያዘጋጃል:: የድግስ ዝግጅቱም በቤት ስራ ሂደት ሁለተኛው ተግባር ነው::

## 5.3.2 ድግስ

በዘጌ ባህረ ሰላጤ ባህላዊ ቤቶች፣ የቤት ስራን መተዳደሪያ ብለው በያዘ ወገን ሣይሆን በወዳጅ ዘመድ ትብብር የሚሰሩ ሲሆን ለሰሪዎች ጥሬ ገንዘብ አይከፈልም::ነገር ግን ምን ጊዜም ቤት ለሚያሳሩ ሠዎች ጉልበታቸውን የሚተካ «እህል ውሃ» ማቅረብ ባህል ነው:: በመሆኑም ድግስ በቤት ስራ ወቅት የግድና አይቀሬ ጉዳይ ነው::

ስለዚህ ቤት የሚሰራለት ቤተሰብ ቤቱ ከተጀመረበት እስከሚያልቅበት ድረስ ባሉት ጊዜያት ሁሉ ቤተሰሪዎችን መመገብ ስላለበት ድግሱ አስቀድሞ መዘጋጀትን ይጠይቃል::

በምዕራፍ 4 የዘጌ ማህበረሰብ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲገለፅ እንደተጠቆመው የዘገኞች መተዳደሪያ የቡና ሰብል ሲሆን የቡና ምርት «የሚለቀመው» በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በየካቲት ወር ነው::ስለዚህ ቤት የሚያሰራው ቤተሰብ የሚሰራው ቤት እሳተከላና ደርብና ምድር ቤት ከሆነ ለስድስትና ሰባት፣ጎጆ ቤት ከሆነ ደግሞ ለሁለትና ሦስት በጋዎች ለመደገሻ የሚሆነውን ገንዘብ ማጠራቀም ይኖርበታል:: ከዚያ የቁስ ስብሰባው እንዳለቀ ወደ መደገስ ይሄዳል::

በእርግጥ ቤት ሰሪው ለቤት ሰሪዎች ምግብ የሚጋብዛቸው ከቁስ ስብሰባው ጀምሮ ነው:: ይሁን እንጅ የቁስ ስብሰባው ተግባር ካለቀ በኋላ «ለቤተሰሪዎች» በሚል በይፋ የድግስ ዝግጅት ይጀምራል:: ድግሱም የእንጀራ፣ የጠላና የአረቄ በመሆኑ የስራ ድርሻው በተለይ የሴቶች ነው:: ስለዚህ የአባወራው ሚስት ጎረቤቶቿንና የእድር፣የሰንበቴና የማህበር ጓደኞቿን አሳሩኝ ብላ ለእንጀራ የሚሆን ዳጉሳ ታስፈጫለች:: የጠላና አረቄ እህሎችን ታዘጋጃለች (ጌሾ ትለቀማለች ወይም ትገዛለች፣ ብቅል ታበቅላለች፣ አሻሮ ትቆላለች ወዘተ...)፣ ጠላ ትጠምቃለች፣ አረቄ ታወጣለች::

በአካባቢው በብዙ ቤቶች ስራ ላይ የተሳተፉና አሁንም እየተሳተፉ ያሉት አቶ ወርቄ ተባባል እንደገለፁልኝ ምንም እንኳን የድግሱ መጠን በአባወራው የኢኮኖሚ አቅም የሚወሰን ቢሆንም ብዙ ጊዜ ግን የሚዘጋጀው ምግብ ብዙ ነው:: ምግቡ ከመብዛቱ

የተነሳ ተርፎ የሚደፋው እንኳን ብዙ ነው። ምናልባት ቤት አሰሪው ቤቱን ለቀን ሰራተኛ ገንዘብ ከፍሎ ቢያሰራው ለድግስ ከሚያወጣው ወጪ ግማሽ ያህሉን ያተርፋል። ግን ያን የሚያደርግበት ምክንያት አለው። «ገንዘብ ተከፍሎት የሚሰራ የቀን ሰራተኛ የዘመድና የጎረቤትን ያህል ተጨንቆ ጥራት ያለው ስራ አይሰራም» ስለሚባል ቤተሰሪው «ያስቡልኛል፣ ይቆረቆሩልኛል» የሚላቸውን ሰዎች መርጦ ቤት እንዲያሳሩት ይለምናል። የሚለመኑትም ሰዎች አንመጣም ብለው አይቀሩም ምክንያቱም በዘጌ ቤት ስራ «ወንፈል» ነው። ወንፈል ማለት ወረፋ ማለት ነው። በመሆኑም ዛሬ ቤት እንዲያሳራ የተጠየቀው ሰው እሱም ከዚህ በፊት ለምኖ ቤት ተሰርቶለታል። ወይም ወደፊት ቤት አሳሩኝ ብሎ መጠየቁ አይቀርም። ስለዚህ የተለመኑት ሰዎች በተቀጠረው ቀንና ቦታ ተገኝተው ቤቱ ይሰራል። ባለቤቱ ደግሞ ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት፣ ያበላቸዋል። አረቂና ጠላ ያጠጣቸዋል (ደግሶ ያበላቸዋል) ። ለዚህም ሲባል ቤት ስራው ከመጀመሩ በፊት «ወገቡን ታጥቆ» የድግስ ዝግጅቱን ያጠናቅቅና ቁሶችን ለግንባታ ወደ ማመቻቸት ተግባር ይሄዳል።

### 5.3.3 ቁሶችን ለግንባታ ማመቻቸት

ይህ ተግባር በባህላዊ ቤቶች ስራ ወቅት ሶስተኛው ደረጃና ለቤት መስሪያ የተሰበሰቡት ጥሬ ዕቃዎች ለግንባታ እንዲመቹ ሆነው መልክ የሚይዙበት ነው። ጥሬ ዕቃዎች ለግንባታ የሚመቻቹት በህብረት ነው። ለዚህም ሲባል ቤት ለመስራት የተሰበሰበው ሰው እንደየችሎታው የስራ ክፍፍል ያደርጋል። ስለዚህም ቀደም ሲል ለቤት መስሪያ እንዲሆኑ ተመርጠው በበቀሉበት ቦታ ምልክት የተደረገባቸው ዛፎች ይቆረጣሉ፣ ተቆርጠው የተቀመጡ እንጨቶች እንደሚሰራው የቤት አይነት ቁመታቸው እየተለካ ይቆረጣሉ። ለምሰሶ፣ለግድግዳና ለጣሪያ የሚሆኑ እንጨቶች ተለይተው ይቀመጣሉ።ለበርና ለሣንቃ የሚሆኑ ጣውላዎች ይጠረባሉ። በተለይም ቀደም ባለው ጊዜ እንጨቶችን ለመቁረጥና ለመጥረብ፣ መጥረቢያ አገልግሎት ላይ ይውል ነበር። አሁን አሁን ግን መጋዝም እነዚህን ተግባራት እየከወነ ነው።

ለእንጨቶች ማሰሪያ የሚያገለግሉት ልጦችና ሃረጎችም በዚህ ጊዜ ይዘጋጃሉ። እርጥብ ደንገል ይቆረጥና እየተጠመዘዘ ይቀመጣል፣«ሎቻ» ይሆናል፣ «ልንኩኪ» እየተሰነጠቀ ጣና ሃይቅ ውስጥ ይነከራል። ሽክላ ሰሪዎች ከቤቶች ጣሪያ ላይ የሚቀመጥ «ቤተ ሞገስ» የተባለ ቁስ እንዲሰሩ ይነገራቸዋል። ለእሳተ ከላና ለደርብና ምድር ቤት መሰረት ማውጫ የሚሆኑ ድንጋዮች የተስተካከለ አራት ማዕዘን ቅርፅ እንዲይዙ በመዶሻ ይጠረባሉ። ለጭቃ እንዲሆን ታስቦ የቀረበው አፈርም በዚህ ጊዜ ይቦካል።

እንደ መረጃ አቀባዮች ገለፃ ጭቃ ለቤት መስሪያነት ከመዋሉ በፊት የዝግጅት ጊዜ አለው። በመጀመሪያ አፈር ይቆፈራል፤ ከዚያም በሰዎች ትብብር ወደ ሚቦካበት

ቦታ ይመጣና ከጭድ ጋር እተቀላቀለ፣ በውሃ እየራሰ በእግር ይረገጣል:: ይህም በትብብር የሚደረግ ነው:: ለጭቃ ማቡኪያ የሚውለው ውሃ ከጣና ሃይቅ ይቀዳል:: ውሃውን የሰፈር ሴቶች በህብረት የሚቀዱት ሲሆን በ«ማዲጋ» (እንስራ) እየተሸከሙ ጭቃው ወደሚቦካበት ቦታ ያመጣሉ:: ከዚያም« የጥሬ ዕቃ ስብሰባ» በሚለው ንዑስ ርዕስ እንደተገለፀው የጎጆ ቤት መምረጊያ ጭቃ ለ1 እና2፣ የእሳተከላና ደርብና ምድር ቤት ግድግዳ መስሪያ ጭቃ ደግሞ «ለመንፈቅ» በሂደት ላይ ይቆያል::

በዚህ ሁኔታ የተቦካው ጭቃም ለእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ከሆነ ጡብ ሆኖ ይሰራል:: የጡቡ መጠን ቁመቱ 4 ክንድ(2 ሜትር)፣ ስፋቱ 2 ክንድ (1 ሜትር)፣ ውፍረቱ 2 ክንድ (1 ሜትር) ነው:: ስለዚህ እሳተ ከላ ቤት ቁመቱ አራት ዙሪያው ደግሞ 30 ሜትር በመሆኑና አንድ ጡብ ደግሞ ቁመቱ 2 ስፋቱ 1 ሜትር በመሆኑ (ይህንን በመፍረስ ላይ ካሉ ቤቶች ውስጥ ያልተሰበሩ ጡቦችን በመለካት አረጋግጫለሁ) አንድ እሳተ ከላ ቤት በቀላሉ በግምት 120 ጡብ ያስፈልገዋል:: ቤቱ ደርብና ምድር ሲሆን ደግሞ ከዚህ የበለጠ በግምት 180 ያህል ጡብ ያስፈልጋል:: በመሆኑም ለእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት የሚሆኑ ጡቦችን መስራት ብዙ ጊዜ ይጠይቃል:: በዚያ ላይ ደግሞ ጡቦች ከጭቃ የሚሰሩ በመሆናቸው በመስራት ላይና በመድረቅ ላይ እያሉ ዝናብ ቢመታቸው ስለሚጎዱ የጡብ ስራ የበጋ ወቅት ስራ ነው:: ስለዚህ ስራው በበጋ እየተሰራ ክረምት ሲገባ ይቋረጣል::የተሰሩት ጡቦች ዝናብ እንዳይመታቸው ዳስ ይሰራላቸዋል:: በጋው ሲመጣ ስራው ይቀጥላል:: በየጊዜው የሚሰሩት ጡቦችም እንደደረሱ በፀሐይ እንዲደርቁ ይደረጋል:: በፀሐይ ሲደርቁ የቆዩት ጡቦች ሙሉ በሙሉ ርጥበታቸው እንዲጠፋ ሲባል በላይና በታች እየነደደባቸው በእሳት ይቃጠላሉ:: በዚህ ሂደት ጡቦችን ለመስራት ሶስትና አራት በጋዎች ያስፈልጋሉ:: ለጎጆ ቤት ከሆነ ግን ጭቃው ለግድግዳ በቆመው እንጨት ላይ የሚለጠፍ በመሆኑ ጡብ አይሰራም:: ቤት መስራት እንደታሰበ መቦካቱ ይጀምርና ከአንድ እስከ ሁለት ወር ድረስ በየሳምንቱ በአዲስ ውሃና ጭድ እየተረገጠ፣ ሲያበቃ ጭድ እየለበሰ እንደገና እየተረገጠ ጭድ እየለበሰ ግድግዳው እስኪቆም ድረስ እዚያው በተቦካበት ቦታ ጭድ ለብሶ ይቆያል:: ይህ ሁሉ ስራ ካበቃ በኋላ ተከታዩ ሂደት ይቀጥላል:: እሱም ግድግዳ መገንባት (ማቆም) ነው::

### 5.3.4 ግድግዳ መገንባት (ማቆም)

ግድግዳ በመገንባት ሂደት ውስጥ ቀዳሚው ተግባር ለቤት መስሪያ የሚሆን ቦታ መምረጥ ነው:: መረጃ አቀባዮች እንደገለፁልኝ ባህላዊ ቤቶች ሲሰሩ ለመስሪያ የሚሆነው ቦታ የምስጥ ኩይሳ የሌለበትና የቡና ተክሉን ለመጠበቅ አመቺ የሆነ ነው:: ይህ ቦታ ከተመረጠ በኋላ ቦታው ለቤት መስሪያ የተመረጠ መሆኑን ለመግለጽ «ቸሃል»(የእንጨት

ምልክት) ይተከላል:: ነገር ግን ምልክት ከመተከሉ በፊት የሚከወን አንድ ባህላዊ ልማድ አለ:: ይኸውም የአገር ሽማግሌዎች ምርቃት ነው:: የሰላጤዋ የአገር ሽማግሌዎች ቄስ ገበዝ ይሄይስ እንግዳው፣ አቶ ጌጤ በርሄ፣ ምስለኔ ተመስገን አለሙና ሊቀረድ ዕጌ ገነት የተባሉ የሰላጤዋ የሃገር ሽማግሌዎች እንዳብራሩልኝ አንድ ሰው ቤት ሲሰራ ሽማግሌ ካልመረቀ ቤቱ የሰላም ቤት አይሆንለትም፣ ልጆች አያወጣም (ልጆቹ ጥሩ ደረጃ አይደርሱም)፣ ትዳሩ አይሰምርም:: በመሆኑም ቤተሰሪው ግድግዳ በሚቆምበት ቀን የሃገር ሽማግሌዎችን «ግድግዳ ላቆም ነውና መጥታችሁ እንድትመርቁ» ሲል አስቀድሞ ቀጠሮ ያስይዛቸዋል:: ሽማግሌዎቹም በተባለው ቀን መጥተው እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ምርቃት መርቀው፣ ቤቱ የሰላም ቤት እንዲሆን ተመኝተው ከአገር ልማድና ባህል አንፃር ቤቱ እንዴት እንደሚሰራ ሃሳብ ሰጥተው ሲያበቁ ከሁሉም ሽማግሌዎች በዕድሜ ገፋ ያለው ለቤቱ መስሪያ በተመረጠው ቦታ መሃል መጀመሪያውን «ችሃል» (ምልክት) ተክሎ ቀደም ሲል ከተደገሰው ድግስ ቁርስ ይቀርባል:: ከዚያም ግድግዳ የማቆሙ ተግባር ይጀምራል:: ይህ ልማድ ዛሬ ዛሬ በሚሰሩት ቆርቆሮ ቤቶች ላይ እንኳን አልቀረም:: ነገር ግን ሽማግሌዎች በምንም ሰበብ ሳይመቻቸው ቀርቶ ቢቀሩ የቤት ስራው ለሌላ ቀን ይተላለፋል እንጂ «ችሃል» የሚተክል ሰው የለም:: በመሆኑም ይህ የሽማግሌዎች ምርቃት የግድና የማይቀር ነው::

ምርቃት ካበቃና ምልክት ከተተከለ በኋላ የግድግዳ ስራ ይጀመራል:: ሆኖም ተግባር የእሳተ ከላና የደርብና ምድር ቤቶች ግድግዳና የጎጆ ቤቶች ግድግዳ ስራ የተለየ ነው:: ግድግዳ ሙሉ በሙሉ ከጭቃ የሚሰራ ሲሆን የጎጆ ቤት ግድግዳ ደግሞ ከእንጨትና ከጭቃ የሚሰራ ነው::

የእሳተ ከላና የደርብና ምድር ቤቶች ግድግዳ መሰራት የሚጀምረው ለመሰረት ማውጫ የሚሆን 1ሜ. በ1ሜ. የሆነ ጉድጓድ ዙሪያውን በክቡ በመቆፈር ነው::ክቡ ምንጊዜም ዙሪያው 30 ሜ. ስፋቱ ደግሞ 7 ሜ. ነው:: በዚህ በተቆፈረው ቦታም ተጠርበውና ተስተካክለው በተቀመጡ ድንጋዮች መሰረት ይወጣል:: መሰረቱ እንዳበቃ የጭቃ ጡቡ በምስራቅና ደቡብ አቅጣጫ ለበር ከተወሰነው ቦታ ውጭ ዙሪያውን በጭቃ እየተጣበቀ አንዱ በሌላው ላይ እየተደራረበ በመሰረቱ ይደረደራል አደራደሩን በተመለከተ ግድግዳው ከተገነባ በኋላ እንዳይናድ ከላይ የሚሆኑት ጡቦች ከታች በተቀመጡት ጡቦች መጋጠሚያ ላይ ያርፋሉ:: በዚህ ሁኔታ የመጀመሪያው« መቅደስ» የተባለው ክፍል ተሰርቶ ያልቃል::ይህ ዙር ተሰርቶ እንዳበቃም በዚያኑ ያህል ርቀት ሌላ ጉድጓድ ዙሪያውን ይቆፈራል፤ ሌላ መሰረት ይወጣል፤ ከመሰረቱ በላይ ጡቦች በእርጥብ ጭቃ እየተጣበቁ ይደረደራሉ:: በዚህ ክፍልም በመጀመሪያው ትይዩ ለበር የሚተው ቦታ አለ:: በዚህ ሁኔታ ሁለተኛው «የሴት ቤት» የተባለው ክፍል ይሰራል:: ይህ ክፍል ተሰርቶ እንዳበቃ ደግሞ ሶስተኛውና ለእንግዳ ማስተናገጃ የሚሆነውን ክፍል ለመስራት ዙሪያውን

በየአምስት ክንድ (2.5 ሜ) ርቀት 12 ድፍን እንጨቶች ዙሪያውን ይተከላሉ:: ስማቸውም ምሰሶዎች ይባላሉ:: ምሰሶዎች ለጣሪያው ማረፊያ የሚያገለግሉ ሲሆን ቁመታቸው ከግድግዳው እኩል 8 ክንድ (4 ሜትር) ነው:: እንጨቶች እሼ፣ ሰሳ፣ ብርብራ፣ ዝግባ፣ አኩማ፣ ናቸው:: የአስራሁለትነታቸው ትርጉምም ለ12ቱ ሐዋርያት ተምሳሌት መሆኑን መሪጌታ ወርቁ ደበብ ገልፀዋል::

አስራሁለቱ እንጨቶች ከቆሙ በኋላ ያለው ክፍት ቦታ ደግሞ ለበር ከሚተወው ቦታ በስተቀር ዙሪያውን በሸንበቆ ይሞላና በማገር ይማገራል:: በዚህ ሁኔታ ሶስቱ ግድግዳዎች ተሰርተው ያልቃሉ:: ተግባሩም ግድግዳ መገንባት ይባላል:: ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የእነዚህ ቤቶች ግድግዳዎች የሚሰሩት ከውስጥ ወደ ውጭ ነው:: ይህ የሆነበት ምክንያትም ግድግዳዎች ከውጭ ወደ ውስጥ የተሰሩ እንደሆነ የውጩ የውስጡን እየሸፈነ ግድግዳው ቶሎ እንዳይደርቅ ይከለክለዋል:: ነገር ግን ከውስጥ ወደ ውጭ ሲሰራ የፊት የፊቱ ስለሚደርቅ ቤቱ ብዙ ጉዳት ሳይደርስበት (ለምሳሌ ግድግዳው ሳይሸብት) ይደርቃል:: ስለዚህም ግድግዳዎች ከውስጥ ወደ ውጭ ከመቅደሱ ተጀምረው ዛኒጋባው ላይ ያልቃሉ:: እስከዚህ ጊዜ ድረስ የእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶች ግድግዳ አሰራር ተመሳሳይ ነው እዚህ ላይ ሲደረስ ግን ልዩነት ይፈጠራል::የእሳተ ከላ ቤት ግድግዳ ስራ እዚህ ላይ ሲያበቃ ደርብና ምድር ግን ለላይኛው ቤት የሚሆነው ግድግዳ መሰራት ይጀምራል::ስለዚህም ከታች በነበረው መልኩ ጠቦች እንደገና መደርደር ይጀምራሉ::

የጎጆ ቤት ግድግዳ አሰራር ግን ከእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶች የተለየ ነው:: ቤት ለማሳራት የተጠሩት ሰዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የቤቱ ባለቤት እንደአቅሙ መጠን ምን አይነት ቤት መስራት እንደሚፈልግ ቤተ 12፣ ቤተ9 ና ቤተ6 በማለት ይናገራል:: በዚህ መሰረት የግድግዳው ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ የቤቱ መሃል (የምሰሶ መትከያው ቦታ) ይወሰንና ከምርቃት በኋላ ከአገር ሽማግሌዎች አንዱ ከዚህ ቦታ «ችካል» /ምልክት/ ይተክላል:: ከዚያ፣ ካሉት ሰዎች ሁሉ የተሻለ ቤት የማሳራት ልምድ ያለው አንድ ሰው በሸንበቆው እየለካ የቤቱ ግድግዳ የሚያርፍበትን ቦታ ዙሪያውን ያስምራል:: ከዚያ ገደል መቆፈር ይጀመራል:: የሚቆፈሩት ገደሎች በየ2 ክንድ (1ሜ) ርቀት የሚቆፈሩ ሲሆን ወደ ውስጥ ጥልቀታቸው 60 ሳንቲ ሜትር ይሆናል:: ገደሎቹ ተቆፍረው ሲያበቁ በውስጣቸው ባለባላ እንጨቶች ዙሪያውን ይተከላሉ:: እነዚህ እንጨቶች «ቋሚ» ይባላሉ:: ቋሚዎች ተተክለው ሲያበቁ በባላዎች ላይ በማለፍ ዙሪያውን በክቡ እንጨት ይታሰርባቸዋል:: ቀጥ ቀጥ ብለው የነበሩት እንጨቶች አግድም ዙሪያውን በሚያርፍባቸው እንጨት የተነሳ ይደመደማሉ:: ያ ቦታም «ድምድም» ይባላል::

ከዚህ በኋላ ቋሚዎች በየአንድ ሜትሩ ርቀት የተተከሉ በመሆናቸው ግድግዳው ክፍተት ስላለው ለበር ከተወሰነው ቦታ በስተቀር በክፍተቱ ሁሉ ቁመታቸው ከባላዎች

ጋር እኩል የሆነ /ያላጠረ፣ ያልበለጠ/ እንጨቶች ዙሪያውን ይገባሉ:: በዚህ ሁኔታም ግድግዳው ተሰርቶ ያልቃል:: ተግባሩም ግድግዳ ማቆም ይባላል:: ለበር የሚሆነው ቦታ የሚወሰነው በዚህ የቤት ስራ ደረጃ ነው:: በር በምስራቅና ደቡብ አቅጣጫ ይሰራል:: የዚህን ምክንያት የገለፁልኝ ቄስ ገበዝ ይሄይስ እንግዳው እንዳሉት በር ምንጊዜም ምስራቅን አይለቅም:: ይህም አንድም ብርሃንን ፍለጋ ሁለትም «ገነት» በምስራቅ በኩል ትገኛለችና ገነት ባለችበት አቅጣጫ መውጣት መግባት የወዲያኛውን አለም ተስፋ ማድረግ ነው::የግድግዳ ሥራ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ጣሪያ ማዋቀር ነው::

## 5.3.5 ጣሪያ ማዋቀር

በእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት አሰራር የጣሪያ ስራ የሚጀምረው ክብ ሆኖ የተሰራውን ግድግዳ በጠፍጣፋ ጣውላ በመሸፈን ነው:: ይህ ጣውላ «ጠፍጠፍ» ይባላል:: ጠፍጠፍ ወፍራምና ወደ ቤቱ ውስጥ የሚሆነው ገፅታው የተለያየ አቅጣጫን ተከትለው በተሰመሩ መስመሮች የተጌጠ ነው:: ይህ ቁስ ለጣሪያ መክደኛ ከመሆኑም ባሻገር ለቤቱ ውበትንም ያላብሰዋል:: ግድግዳው በጠፍጠፍ ከተሸፈነ በኋላ ወደ ሰማይ ያለው የእንጨቱ ገፅ በሰኔል ይሸፈናል:: ሰኔሉ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በጭቃ ይሸፈናል:: ከጭቃው ላይ አመድ ይደረግበታል:: ይህ እንደሆነም ለዚህ ተብለው የተዘጋጁ ወፍራምና ጠንካራ እንጨቶች መነሻቸውን ጠፍጠፉ ካረፈበት የግድግዳው ጠርዝ እየተነሱ ሾጣጣ ቅርፅ እንዲይዙ ተደርጎ ወደ ላይ ይወጡና ጫፋቸው አንድ ላይ ይታሰራል:: እነዚህ እንጨቶች «ወራጆች» ይባላሉ:: ተግባሩ ደግሞ «ባጥ መስራት» ይባላል:: ከዚህ በኋላ በየክፍት ቦታው እንጨቶች እየተሳገ (ሳጋ እየገቡ)፣ ሳጋዎችም ከባጥ እንጨቶች ጋር በለንቋጣና ስሚዛ ማገሮች ቢያንስ በየአንድ ስንዝር ርቀት በልጥ ወይም በቆዳ ጠፍር ይማገራሉ:: በዚህ መልክ ባጡ ተሰርቶ ያልቃል:: ይህ የባጥ አሰራር ሂደት ቤቱ በእሳት ቢቃጠል እሳቱ ከጣሪያው አልፎ በቤት ውስጥ ያለን ንብረትና ህይወት መጉዳት እንዳይችል ያደርገዋል:: ምክንያቱም ከጠፍጠፉ ላይ የተደረጉት ጭቃና አመድ በእሳት አይቀጣጠሉም::

ከዚህ በኋላ ቤቱ እሳተ ከላ ከሆነ ጣሪያውን ሳር ወደማልበስ ተግባር ይሄዳል:: ነገር ግን ቤቱ ደርብና ምድር ከሆነ ከጠፍጠፉ በላይ የጡብ ግድግዳ ይገነባል:: እሳት የሚከላከለው ክፍልም ከግድግዳው በኋላ ይሰራል::

የጎጆ ቤት ጣሪያ መዋቀር የሚጀምረው ምልክት በተደረገበት የቤቱ መሃል ላይ ምሰሶ በመትከል ነው:: ምሰሶው ቁመቱ እንደሚሰራው ቤት አይነት የግድግዳውንና የጣሪያውን ቁመት ጠቅልሎ የያዘ ለምሳሌ ለቤተ 12 ጎጆ ቤት 26 ክንድ (13 ሜ)፣ማለትም 3 ሜ.ግድግዳ + 10ሜ ጣሪያ) ድፍን /ያልተፈለጠ ዝግባ፣ እሸ፣ አኰማ ወይም ሰሳ እንጨት ነው:: ይህ እንጨት የጣሪያው ተሸካሚ ነው:: ለዚህም ሲባል

ግድግዳው ከቆመ በኋላ በቤቱ መሃከል ይተከላል:: ከመተከሉ በፊት ግን ወደ መሬት በማይገባው የእንጨቱ ጫፍ መሃሉ የተበሳ ጠፍጣፋ እንጨት (ጣውላ) ይገባበታል:: ይህ ጣውላ «ዋልቃ» ይባላል:: ዋልቃ የቤቱን ግድግዳ እኩል ሲያካፍል የሚችል የተስተካከለ ክብ ነው:: ምሰሶው በዋልቃው ቀዳዳ ሲገባ ጫፉ ከዋልቃው አልፎ መታየት አለበት:: ይህም በኋላ በቤቱ ላይ ለሚቀመጠው «ቤተሞገስ»ለተባለው የሸክላ ቁስ ማስቀመጫ የሚውል ነው:: ስሙም «ቁንጮ» ይባላል:: ከዚህ በኋላ ምሰሶው ይተከላል:: ተከላው እንዳበቃም የተመረጡ እንጨቶች ከድምድሙ ተነስተው ወደ ዋልቃው በመጋደም በሁለቱም ጫፍ በልጥ ይታሰራሉ:: እነዚህ እንጨቶች «ወራጆች» ይባላሉ:: በዚህ ሁኔታ ወራጆች ታስረው ሲያበቁ አግድም ይማገራሉ:: በሚማገሩበት ጊዜ የተፈጠረው ክፍተት እንዲሞላ በመሃል እንጨቶች ይሳጋሉ:: ይህ ሳጋ እያስገቡ ወራጁን በማገር እያጠበቁ የመስራት ተግባር «ጭምጭም» ይባላል::

በዚህ ሁኔታ ወራጆችን ከላይ ከዋልቃው አንስቶ ቁልቁል ወደ ድምድም በማውረድ ጀምሮ አግድም በመማገር በመሃል ክፍተት እንዳይኖር ሳጋ እያስገቡ የሚሰራው ቤት የመስራት አንድ ደረጃ ጣሪያ ማዋቀር ይባላል:: ከጣሪያ ማዋቀር ቀጥሎ ያለው ተግባር ደግሞ ሳር መክደን ነው::

### 5.3.6 ሳር መክደን

ጣሪያ ተዋቅሮ ሲያበቃ ፀሃይና ዝናብ እንዲሁም ሌሎች ባዕዳን ነገሮች በክፍተቱ እንዳይገቡ ሲባል በሳር ይሸፈናል:: ይህ ተግባርም «ሳር መክደን» ይባላል:: ክፍክፍና አልባሶ የሚባሉ ሁለት የሳር አከዳደን አይነቶች አሉ:: ክፍክፍ ለእሳተ ከላና ደርብና ምድርቤት እንዲሁም መካከለኛ ኑሮ ያላቸው ሰዎች ለጎጆ ቤቶቻቸው የሚያስከድኑት የሳር አከዳደን አይነት ነው:: አልባሶ ደግሞ ኑሯቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች ያሰሩታል::

ለክፍክፍ የአከዳደን ስልት የሚሆኑት የሳር አይነቶች ቋያና ሲላ ይባላሉ:: ለአልባሶ የሚሆነው ደግሞ አኩሲ ይባላል:: ዘገኖች ሳርከደናንም እንደ ሌሎች የቤት ሥራ ተግባራት ሁሉ እንደየችሎታቸው ሥራን ተከፋፍለው በህብረት የሚሰሩት ነው:: በሣር ከደና ልምድና ችሎታ ያላቸው ሰዎች (ብዙ ጊዜ ሁለት) ጣሪያው ላይ ይወጣሉ:: ሌሎች በርካታ ሰዎች ደግሞ ከታች ሆነው የሚከደነውን ሳር እየመጡና እንዳይበታተን ጫፉን በልጥ እያሰሩ ጣሪያው ላይ ላሉ ሳር ከዳኞች እየወረወሩ ያቀብላሉ::

«ከዳኞችም ከድምድሙ ተነስተው ወደ ቁንጮው(ከታች ወደ ላይ) ሳሩን ያለብሳሉ:: እንደመረጃ አቀባዮች ገለፃ ሳር የሚለብሰው ቤት እሳተ ከላ ወይም ደርብና ምድር ቤት ከሆነ ጣሪያው ላይ የሚያርፈው ሳር ቤት ከዳኙ ሳር ካልለበሰው ቦታ ላይ ተቀምጦ እስከትከሻው ይደርሳል:: ይህ ደግሞ 35-40 ሳ.ሜ ይሆናል:: ይህ ማለት ሳሩ

በጣም ይደራረባል ማለት ነው። በመሆኑም አንድ ጊዜ ሳር የተከደነ እሳተ ከላ ወይም ደርብና ምድር ቤት ሳሩ ሳይቀየር ከ 20-50 ዓመት ድረስ ሊቆይ ይችላል።

ነገር ግን በክፍክፍ የአከዳደን ስልት ቤቱ ጎጆ ከሆነ የሳሩ ከፍታ ከ15-20 ሳ.ሜ ይደርሳል። በዚህ ሁኔታ የተከደነው ሳርም ከ 5 ዓመት በላይ ሊቆይ ይችላል። በአልባሶ አከዳደን ግን ሳሩ ራሱ በባህርይው ደካማ በመሆኑ ጣሪያው ላይ የተከደነው ሳር በየአመቱ መቀየር አለበት።

የሳር ማልበሱ ተግባር ሲያበቃ በቤቱ ቁንጮ ላይ «ቤተ ሞገስ» ይቀመጣል። ቤተ ሞገስ ከሸክላ የሚሰራ ከወገብ በላይ የእንስራ ቅርፅ ያለው ቁስ ነው። እንደ እንስራ «አፍ» አለው ። ነገር ግን ይህ አፉ ጠቅላላ ቅርፁ እንደ ኩባያ ሆኖ ተሰርቶ ጫፍ ላይ አምስት የሰው ጣት ቅርፅ ያላቸው ቅጥሎች ባሉት ክዳን ይዘጋል። ስለዚህ የቤተ ሞገሱ ጫፍ የተዘረጋ የሰው መዳፍ የመሰለ ቅርፅ አለው። ቤተ ሞገስ ቁሳዊ ተግባሩ ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ በቤቱ ቁንጮ ገብቶ ሳሩ እንዳይበሰብስ መከላከል ነው። ነገር ግን ከዚህ በተረፈ ለቤቱ ግርማ ሞገስ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል። ከዚህ ውጭ ግን መሪጌታ ወርቁ ደበብ የቤተሞገስን ተምሳሌታዊ ትርጉም ሲገልፁ፡-

> ቤተ ሞገስ ባለአምስት ጣት ነው። ይህም በአንድ በኩል ሳዶር፣ አላዶር፣ ዳናት፣ አዴራ፣ ሮዳስ የተባሉት የአምስቱ ጌታ ሲሰቀል የተቸነከረባቸው ችንካሮች ተምሳሌት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ቤት ሃገር ነውና፣ ኢትዮጵያ ታበፅ እንደዊሃ ሃበ እግዚአብሔር (ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለውን የመፅሃፍ ቃል መተግበሪያ ነው ብለዋል። ከዚህ ተጨማሪ አቶ ዋሴ እንየው «ቤተ ሞገስ ለሰላምታ የተዘረጋ እጅ ይመስላል። ይህ ደግሞ ሰላጤው ሰላም ነው፤እንኳን በሰላም መጣችሁ ማለት ነው» ብለዋል። እነዚህን አሳቦች የተለያዩ መረጃ አቃባዮችም ይደግፏቸዋል። በመሆኑም ቤተ ሞገስ ከቁሳዊ ባሻገር ተምሳሌታዊ ተግባር ያለው ቁስ ነው (26-9-1999) ።

ሳር ተከድኖ እንዳበቃ ለእሳተ ከላና ለደርብና ምድር ቤት ቀጣዩ ተግባር ቤት ማስዋብ፣ ለጎጆ ቤት፣ ደግሞ ግድግዳ መምረግ ነው። ሆኖም ጎጆ ቤት ግድግዳው ከተመረገ በኃላ «ማስዋብ» የሚባል ደረጃ ያለው በመሆኑ በቅድሚያ ግድግዳ መምረግ የሚለውን ደረጃ እንይ፡-

### 5.3.7 ግድግዳ መምረግ

ይህ ደረጃ ጎጆ ቤቶችን እንጂ እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤትን አይመለከትም። ምክንያቱም እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ገና ከጀምሩ ግድግዳቸው ክፍተት እንዳይኖረው ተደርጎ የተሰራ በመሆኑ ምርግ አያስፈልጋቸውም። ነገር ግን ጎጆ ቤቶች ግድግዳቸው በእንጨት የተሰራ ከመሆኑ የተነሳ በእንዳቾ ነገር ካልተሸፈነ በስተቀር ፀሃይ ንፋስና ሌሎች ባዕዳን ነገሮችን ወደ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ክፍተት አለው።ይህ

እንዳይሆን ደግሞ ግድግዳው በጭቃ ይሸፈናል:: ይህ ድርጊትም «ግድግዳ» መምረግ ይባላል::

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ለቤት መምረጊያ የሚውለው ጭቃ የተቦካው ቤቱ ሰሪው ገና ቤት ለመስራት ሲያስብ ነው:: የማቡካቱ ሂደትም ከተቻለ ከወርና ከሁለት ወር በላይ በየሳምንቱ ጭቃው እየተገለበጠ (መልሶ እየተቦካ) ውሃና ጭድ እንደ አዲስ እየተጨመረበት ይቆያል:: ከዚያ የቤቱ ጣሪያ ሳር ለብሶ እንዳበቃ ቤት ለማሳራት የተለመኑት ሰዎች በመተባበር በእንጨት የተሰራውን ግድግዳ «ይመርጉታል» ( በጭቃ ይሸፍኑታል):: ቀድሞ የሚመረገው የውስጡ ሲሆን የውጩ ውስጡ ከደረቀ በኋላ ይመረጋል:: ይህ የሚሆነው ጭቃው ከእንጨቱ ጋር በደንብ እንዲጣበቅ ነው:: ጭቃው ለረጅም ጊዜ እንዲቦካ መደረጉ ግን የማጣበቅ ሃይሉ እንዲጨምር ያደርጋል:: ከዚህ በኋላ የሚቀረው ተግባር ቤቶችን ማስዋብ ነው::

## 5.3.8 ቤት ማስዋብ

ሶስቱንም ቤቶች በማስዋብ ሂደት ውስጥ ትኩረት የሚደረግባቸው የቤት ክፍሎች ግድግዳና ወለል ናቸው:: ዘገኞች ሶስቱም አይነት ቤቶች ውበት እንዲኖራቸው ሲሉ የቤቶችን ግድግዳ በጤፍ ጭድ ብቻ በተቦካ የቀይ አፈር ጭቃ ይለስኗቸዋል:: ለልስን የሚያገለግለው ጭቃ ለምርግ እንደሚሆነው ጭቃ ብዙ ጊዜ ላይቦካ ይችላል:: በአጭር ቀን ውስጥ የተቦካው ጭቃ ግድግዳው ላይ እየተቀባ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ «መለሰኛ» በሚባል ጠፍጣፋ ጣውላ ይለሰልሳል:: በዚህ ጊዜም የቤቶቹ ግድግዳ ወጣ ገባ የሌለውና ለስላሳ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ቤቶችን ማስለሰን የግድ ላይሆን ይችላል::

ከዚህ በተረፈ ግን እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶች ከቤት ውስጥ ከግድግዳዎች ጋር ተያይዘው ለሚቆሙ የጣውላ ጌጦች ከፍተኛ ትኩረትና ጥረት ያደርጋሉ:: ምክንያቱም እነዚህ ጌጦች ለቤቶች ትልቅ ውበት ከመሆናቸው በሻገር የማህበረሰቡ እውቀትና እምነት መገለጫዎችም ናቸው::

ጌጦች የሚሰሩት መቅደስ ለተባለው ክፍል ነው:: የዚህ ክፍል ግድግዳ ዙሪያውን ላዩ ላይ ቅርፅ በወጣለት ጣውላ ይለበጣል:: ቅርፆቹ የመስኮት «ሞዴሎች» ናቸው:: የመስኮቶቹ አቀማመጥ ደግሞ ሶስት ቦታ ላይ ሆኖ በተቀራረበ አቀማመጥ ከላይ አንድ፣ ከታች ሁለት በአጠቃላይ ሶስት ነው:: ይህም «የስላሴ ምሳሌ ነው::» ይላሉ መረጃ አቀባዮቹ :: ከዚህ ሌላ ደግሞ የመስኮቶች ቅርፅ በሌለባቸው በሌሎች ቦታዎች የመስቀልና የሰላጤዋ ካርታ ተቀርፀዋል:: መስቀሉን ባለቤቶች ከክፉ መንፈስ ይጠብቀናል ብለው ከማመናቸው ባሻገር የክርስቲያንነታቸው መገለጫ ነው:: የሰላጤዋ ካርታ ደግሞ ለልጆቻቸው ማስተማርያ የሚደረግ (መኖሪያቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ) እንደሆነ ነው ቄሰ ገበዝ ይሄይስ እንግዳው የሚናገሩት::

በአጠቃላይ በእነዚህ መልኮች ግድግዳው ይዋባል። ከግድግዳው ወጥተን ወደ ወለል ማስዋብ ስንመጣ ደግሞ ወለል የሚዋበው « በድልደላ» (ወለሉ ወጣ ገባ እንዳይሆን በማስተካከል) ነው። ይህም የሚደረገው የቤቱን ወለል በመቆፈር አባጣ ጐርባጣው ከተስተካከለ በኋላ ከውጭ አፈር በማስገባት እኩል ወለሉ ላይ ይበተናል፤፡ ከአፈሩ ላይ ውሃ ይርከፈከፍና የጤፍ ጭድ እየተነሰነሰ መሬቱ እንዲጠብቅ ስልት ባለው አረማመድ በእግር ይጠቀጠቃል።

በዚህ ሁኔታ ቤቱ ተሰርቶ ይጠናቀቃል። በአጠቃላይ በዘጌ ባህረ ሰላጤ የባህላዊ ቤት አሰራር ሂደቶች ያሉት ሲሆን ሂደቶቹ ለመስሪያ የሚሆኑ ቁሶችን መሰብሰብ፣የድግስ ዝግጅት ማድረግ፣ ቁሶችን ለግንባታ ማመቻቸት፣ ግድግዳ ማቆም ፣ ጣሪያ ማዋቀር፣ ሳር መክደን፣ ግድግዳ መምረግ፣ ቤት ማስዋብ ናቸው። እንደ ቁስገበዝ ይሄይስ እንግዳውና አቶ ዋሴ እንየው ገለፃ አንድ ጠንካራና ሐብታም ሰው እነዚህን ሂደቶች ሁሉ አከናውኖ አንድን እሳተ ከላ ወይም ደርብና ምድር ቤት ለመስራት በትንሹ አምስት አመት ይፈጅበታል። ጎጆ ቤት ከሆነ ደግሞ አንድ አመት ይጠይቃል። ቤት ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ቤት ማሰናዳት ነው።ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባል።

## 5.3.9 ቤት ማሰናዳት / እቃዎችን በቦታቸው ማስቀመጥ/

ቤት ማሰናዳት የሴቶች ተግባር ነው። አንዲት ሴት በቤት አያያዝዋ ትመስገንበታለች ወይም ትነቀፍበታለች። በመሆኑም እያንዳንዷ የቤት እመቤት የአካባቢው ሰው እንዲያደንቃትና እንዲያከብራት ባሏም እንዲኮራባት ስትል ቤቷን ለማሳመር ትጥራለች። ሆኖም በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ የእቃዎች አቀማመጥ ብዙ አይለያይም። እሳተ ከላና ደርብ ምድር ቤት ባለ ሶስት ክፍል ቤቶች በመሆናቸው እቃዎች የየራሳቸው ክፍሎች አሏቸው። እንደመረጃ አቀባዮች ገለፃ የአባወራውና የሚስቱም ሆነ የልጆቹ አልጋ መቅደስ ውስጥ ይቀመጣሉ። ምንጊዜም የአባወራውና የሚስቱ አልጋ ከበሩ በስተቀኝ ከመዝጊያው በስተኋላ ትራሱ በምዕራብ፣ ግርጌው በስተምስራቅ አቅጣጫ ከግድግዳው ተጠግቶ ይቀመጣል። የልጆች አልጋም አቀማመጡ ልክ እንደ አባወራው ትራሱ በምዕራብ ፣ግርጌው በስተቀኝ ሆኖ ከአባወራው አልጋ በተቃራኒ ከበሩ በስተግራ ይሆናል። ይህ የሚደረግበት ምክንያት 1ኛ. የተኛ ሰው ምንጊዜም ከራሱ ወደ ግርጌው ስለሚነሳ ያን ጊዜ ሳያውቀው በምስራቅ አቅጣጫ ትገኛ ለች ለምትባለው ገነት እንዲሰግድ 2ኛ. ሰው ሁሉ ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነሳ «ቸር አውለኝ» ብሎ መፀለይ ልማድ ነው። ከዚህ በላይ የተገባ ነው። ታዲያ የኦርቶዶክስ እምነት የፀሎት ስርዓት ፊት ወደ ምስራቅ ተደርጐ ነውና ማንም ሰው ከአልጋው ሲነሳ ቸር አውለኝ ሲል ፊቱ ወደምስራቅ ይሆናል። አልጋዎች አራት ማዕዘን ቅርፅ ፣አራት እግሮች አላቸው። እነዚህ አራቱ እግሮቻቸውና በአራቱ ማዕዘን ዙሪያቸው ከእንጨት

ይሰራሉ:: መሃሉና ሰው የሚተኛበት ክፍል ደግሞ በጠፍር (በቆዳ ገመድ) እየተጠላለፈ ይሰራል:: አልጋው ቁመቱ ረዥም ነው:: በመሆኑም ከስሩእንደ መጥረቢያ፣ አካፋ፣ ደማ የመሳሰሉ መሳሪያዎችና  የተለያዩ እቃዎች ይቀመጣሉ:: በዚህ ክፍል ከአልጋዎች በተጨማሪ ከጠፍርና ከእንጨት የተሰሩ ወንበሮችም ይቀመጣሉ::

በሁለተኛውና «የሴት ቤት» ተብሎ በሚጠራው ክፍል ለምግብ ማዘጋጃ ፣ማቅረቢያና ማብሰያ የሚያገለግሉ (ማህበረሰቡ የሴት የሚላቸው ) እቃዎች ይቀመጣሉ::

ዛኒጋባ የእንግዳ ማስተናገጃ ክፍል ነው :: በዚህ ክፍል ቡና በሚፈላበት፣ ጠላ በሚቀርብበትና ምግብ በሚበላበት ሰዓት ከሚገኙ እቃዎች በስተቀር እቃዎች በቋሚነት አይቀመጡበትም :: በክፍሉ ቋሚ ሆኖ የሚኖረው በቤቱ ዙሪያ ግድግዳውን ተደግፎ የሚሰራውና ለመቀመጫ  የሚያገለግለው መደብ ብቻ ነው:: መደብ ፣ስኔል ወይም አጐዛ ተነጥፎበት መቀመጫ ይሆናል:: ይህ እንግዲህ የእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶች የእቃ አቀመማጥ ሲሆን ደርብ ቤት ከእሳተ ከላ በተለየ አንድ ክፍል ከላዩ ላይ ያለው በመሆኑ ቀደም ባለው ጊዜ ይህ ክፍል ቡና ይቀመጥበት ነበር:: ዛሬ  ግን ማንኛውም ሰው አንድ ቤት ሲይዝ የሚችል ቡና የሌለው በመሆኑ ብዙ ደርብና ምድር ቤቶች የላይኛው ክፍላቸው የመኝታ ቤት ሆኗል::

ጎጆ ቤት ባለአንድ ክፍል ቤት በመሆኑ የእቃ አሰነዳዱ ከእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ይለያል:: በቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ቁሶች ሁሉ በአንድ ክፍል ይቀመጣሉ::

ነገር ግን የአልጋ አቀማመጥ በማንኛውም ቤትና ጊዜ ተመሳሳይ መሆን እንዳለበት ስለሚታመን በጐጆ ቤት ውስጥም እንደ እሳተከላና ደርብና ምድር ቤት ሁሉ አልጋው ከበሩ በስተቀኝ ከመዝጊያው ስር ራስጌው ወደምዕራብ ግርጌው ደግሞ ወደምስራቅ ተደርጎ ይቀመጣል:: ሌሎች እቃዎች ግን ከቤቱ መሃል በሚቀመጠው ጐታ (ከጭቃ የተሰራ ጐተራ) አካፋይነት በሚሰራው ማጀት (እቃ ቤት) ውስጥ ይቀመጣሉ:: በጎጆ ቤትውስጥ ማጀት፣ በእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ደግሞ «የሴት ቤት » ወንድ የማያውቃቸው የሴት ክፍሎች ናቸው:: ወንድ፣ የሴት ክፍል ውስጥ አይገባም:: እነዚህ ክፍሎች «የሴት እቃ» ብቻ ይቀመጥባቸዋል:: ባልና ሚስት ተጣልተው ሴቷ ሮጣ ወደ ማጀት/የሴት ቤት ከገባች ባሏ ተከትሎ ገብቶ አይመታትም:: ራሷን በዚህ መልኩ ከዱላ ታድናለች::በመሆኑም ይህ ክፍል በምንም በምንም ለሴቷ የተሰጠ ክፍል ነው::

## 5.4 የዘጌ ባህረ ሰላጤ ቤት ሰሪዎች

Silverman (1999) እንደሚገልፁት በጠቅላላው ኢትዮጵያ የእጅ ስራ ውጤት በተወሰነ ቡድን ውስጥ የሚከወን ተግባር ነው:: ጥቂት ሙያዎች በማንኛውም ሰው ይተገበራሉ:: ነገር ግን የቁሳዊ ባህል ባለሙያነት በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ይለያል::

እነርሱም ፆታና ጐሳ ናቸው። በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ የሴቶችና የወንዶቸ ተግባራት ግልፅ ልዩነት አላቸው።

የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶችም ቁሳዊ ባህሎች ናቸውና ስለ እነሱ ሲነሳ ማን ሰራቸው ወይም ማንነው የሚሰራቸው የሚለው ጥያቄ መልስ መሻቱ አይቀርም። በመሆኑም ይህንን ጥያቄ ይዤ የባህላዊ ቤቶች ሰሪዎች እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ባደረግሁት ጥረት የተገኙት መረጃዎች በዘጌ ባህረ ሰላጤ ቤት መስራት የወንዶች ተግባር እንደሆነ ይገልፃሉ። ይህ ሲባል ግን ዛፍ መቁረጥ፣ ግድግዳ ማቆም፣ጣሪያ ማዋቀር፣ ሳር መክደን፣ ወዘተና የመሳሰሉት ስራዎች በወንዶች ይሰሩ እንጂ ቤት በመስራት ወቅት ባሉ እንደ ውሃ መቅዳት፣ ለቤት ሰሪዎች ድግስ ማቅረብ የመሳሰሉት ስራዎች በሴቶች ይከወናሉ፤ ቤቶች ከተሰሩ በኂላ ንፅህናቸውንና ውበታቸውን መጠበቅ የሴቶች ተግባራት ናቸው። በመሆኑም በዘጌ ባህረ ሰላጤ ቤት ስራ ፆታን መሰረት ያደረገ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ በተረፈ ግን በምዕራፍ አራት የሰላጤዋና የማህበረሰቡ ጠቅላላ መልክ በሚለው ርዕስ ላይ እንደተገለፀው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አፋፍ 01 ቀበሌ ውስጥ ከሚኖሩት ጥቂት የእስልምና እምነት ተከታዮች ውጭ ( አስቀድሜ እንደገለፅኩት ትክክለኛ ቁጥራቸውን የሚገልፅ ጥናት አላገኘሁም) የዘጌ ባህረሰላጤ ከጅምሩ አንስቶ እስከአሁን ያሉት ነዋሪዎቿ ሐይማኖታቸው ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ብሔራቸውም አማራ ነው።

በመሆኑም ሌላ ቅልቅል ብሔር የሌለባቸው በመሆኑ ቤት ሰሪዎችም እነሱ ናቸው። ስለዚህ ቤት ስራው በጎሳ የተከፈለ አይደለም። ይልቁንስ ከላይ እንደተጠቀሰው በሰላጤዋ ውስጥ ቤት ስራ ዘመድ ጎረቤት፣ የማህበርና የሰንበቴ አባላት ተሰብስበው በህብረት የሚሰሩት ስራ ነው። አንድ ሰው ቤት ለመስራት በፈለገ ጊዜ ዘመድ ጓደኞቹን ቤት እንዲያሳሩት ይለምናል። እነሱም የአገር ደንብ ነውና እንቢ አይሉትም በዚህ መሰረት ቀን ተቀጥሮ የተለመኑት ሰዎች ሁሉ መጥተው ቤቱን ይሰራሉ። እንዲያውም አሁን አሁን የኑሮ ውድነት ሰውን ቆጣቢ አደረገው እንጂ ሰዎች፣ ቤተሰሪውን በጉልበት ብቻ ሳይሆን በጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት ጭምር ያግዙት እንደነበር ነው አቶ አለሙ ታዬ የሚባሉ በይጋንዳ ጎጥ የሰላጤዋ ተወላጅ የሆኑ የ54 ዓመት መረጃ አቀባይ የገለፁት ((አቶ አለሙ ታዬ፣27-8-1999 ዓ.ም) ።

ቄስ ገበዝ ይሔይስ እንግዳው ደግሞ ይህንን ሲያጠናክሩት፣ አንድ ሰው ቤት ሲሰራ አንዱን ጎረቤቱን ወይም ዘመዱን የምስሶ እንጨት ስጠኝ ወይም ቤት አሳራኝ ብሎ ሳይለምነው ቢቀር «ምነው እከሌ ምን በድዬው ነው ይሔን ያላለኝ» ብሎ ሰው መጠየቁ አይቀርም ብለዋል። በመሆኑም ማንም ዕድሜው አስራዎቹ ውስጥ የሆነ ወንድ ልጅ «ቤት አሳሩኝ» ሲለምን ከአባቱ ጋር ወይም ከትልቅ ወንድሙ ጋር ተከትሎ

በሚሄድባቸው አጋጣሚዎች ስራውን ያያል የአቅሙን ስራ ያግዛል ቀስ በቀስም ሙያውን ይለምድና እሱ ደግሞ በተራው የቤት ስራ « ወንፈል» ውስጥ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በሰላጤዋ ውስጥ አፋፍ 01 ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ የሆኑትና ብዙ ጊዜ በቤት ስራ ውስጥ የተሳተፉ አቶ ጉዳይ ሙጩ ስራውን እንዴት እንደለመዱት ሲገልፁ ፡- «ቤት ሲሰራ እንጨት እቆርጣለሁ፣ እጠርባለሁ መቼ እንደ ጀመርኩ ግን አላስታውስም ልጅ ሆኜ አባቴን ተከትዬ እሄድ እንደነበር ትዝ ይለኛል፡» ብለዋል፡፡ አቶ ጀመረ ክብረት ደግሞ «መቼም ቁጭ አድርጎ የሚያስጠና የለም ወንዶች ጋር አብረው እየዋሉ ወንዶች የሚያደርጉትን ማድረግ ነው እንጂ» ብለዋል፡፡ ያም ሆኖ ግን በቤት ስራው ወቅት ብዙሃኑ ጉልበት ሲሆኑ ወግና ልማድ በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱና ስራውን የሚያስተባብሩ ማህበረሰቡ የሚያከብራቸው ሰዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ይሆኑ ዘንድም የሁለት ሰዎች ታሪክ ቀርቧል፡፡ ሰዎች ቄስ ገበዝ ይሄይስ እንግዳውና አቶ ጀመረ ክብረት ይባላሉ፡፡

ቄስ ገበዝ ይሄይስ እንግዳው በሰላጤዋ ውስጥ ጋሚ በተባለው ጕጥ ውስጥ ተወልደው ያደጉ የ70 ዓመት አዛውንት ናቸው፡፡ የተለያዩ ሰዎች ስለሰውየው እንደሚገልፁት የተጣላን በማስታረቅ፣ ያጠፋን በመገሰፅና በሌሎች ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ሁሉ የሚጠሩ ማህበረሰቡ የሚያከብራቸው የሃገር ሽማግሌ ናቸው፡፡ እኚህ ሰው የሃገር ሽማግሌ እንደመሆናቸው በባህላዊ ቤቶች ስራ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ዛሬ ማህበረሰቡን የሚያገለግሉት ግድግዳ ከመቆሙ በፊት ሽማግሌዎች በሚያደርጉት ምርቃት ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ነው፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሽማግሌዎች ከመመረቅ ባሻገር ቤት እንዴት እንደሚሰራ፣የእያንዳንዱ ነገር መጠን ምን ያህል መሆን እንዳለበት፣ በር በየት በኩል መውጣት እንዳለበትና የመሳሰሉ ሃገረሰባዊ ልማዶችን በመግለጽ እንዲጠበቁ ያስተባብራሉ፡፡ ቄስገበዙም እንደሽማግሌነታቸው ይህንን ነገር በማድረግ ማህበረሰባዊ ግዴታቸውን ይወጣሉ፡፡ በተለይ ደግሞ ስለራሳቸው ሲገልፁ እንዳሉት በወጣትነታቸው በአያሌ ቤት ስራዎች ውስጥ ይሳተፉ ስለነበር የቤትስራን ሃገረሰባዊ ደንብ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ማህበረሰቡም ይህንን ስለሚረዳ እሳቸውና መሰሎቻቸው ባልመረቁበት ሁኔታ ግድግዳ አያቆምም፡፡

ሌላውና በዚሁ ሁኔታ ማህበረሰቡ የሚያከብራቸው በቤት ስራ ማስተባበር ውስጥ ጥሩ እውቀትና ልምድ ያላቸው ማህበረሰቡም ያሉትን ይሰማቸዋል ተብሎ የተገለፀልኝ ሰው አቶ ጀመረ ክብረት ናቸው፡፡ እኚህ ሰው በሰላጤዋ ውስጥ መሃል ዘጌ በተባለው ጕጥ ውስጥ ተወልደው ያደጉና አሳ በማስገር የሚተዳደሩ የ60 ዓመት ጐልማሳ ናቸው፡፡ እንጨት ከመቁረጥ ጀምሮ ቤት እስከማሳራት ባሉ ህብረትን በሚጠይቁ ስራዎች ሁሉ የመሳተፍ የረጅም ጊዜ ልምድ አላቸው፡፡ ለማህበረሰቡ ወግ ፣ልማድና ደንብ መከበር ከፍተኛ ቀናኢነት ስላላቸው ቤት በማሳራትም ሆነ በማንኛውም ጊዜ ሰዎች እሳቸው

ያሉትን ከመቀበል ወደኋላ አይሉም:: እሳቸውም ይህንን ተሰሚነታቸውን በመጠቀም ቤት እንዲያሳሩ በተለመኑባቸው ቦታዎች ሁሉ የማስተባበር፣ የሀገር ወግና ልማድ የማስጠበቅ ተግባር ያከናውናሉ::

በአጠቃላይ መረጃ አቀባዮች ከሰጡት መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ቤት ወንዶች በማህበር የሚሰሩት ተግባር እንደሆነ ነው:: ይሁን እንጂ ዛሬ ዛሬ ጭቃ ማቡካትና ሳር መክደን የተወሰኑ ሰዎች ስራ እየሆነ መጥቷል:: ከሚሰሩት ቤቶች መጠን አነስተኛነትና (አሁን በሰላጤው ውስጥ የሚሰሩት ባህላዊ ቤቶች ጎጆ ቤቶች ብቻ ናቸውና) ከመደገሻ አቅም ማነስ የተነሳ ሰዎች ቤት ሲሰሩ ጭቃ ማቡካትንና ሳር መክደንን ለቀን ስራተኛ ገንዘብ ከፍለው ያሰራሉ:: እነዚህን ስራዎች የሚሰሩት ግን የሰላጤዋ ተወላጆች አይደሉም:: ለምሳሌ ሳር በመክደን ላይ ያገኘሁት አቶ ግርማ ይታየው ስለራሱ ሲገልፅልኝ ዕድሜው 42 አመት የትውልድ ቦታው ደግሞ ባህርዳር ዙሪያ ወረዳ 42 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ከሚገኝ «አዴት» የተባለ ቦታ ነው:: ወደ ሰላጤዋ ከመጣ 10 ዓመት ሞልቶታል:: የሰላጤዋ ተወላጅ የሆነች ሴት አግብቶ ይኖራል:: በሰላጤዋ ውስጥ ዛፍ መቁረጥ፣ እንጨት መሰንጠቅ፣ ጓሮ መመንጠር ሳር መክደን የመሳሰሉ የቀን ስራዎችን በመስራት ይተዳደራል:: አንድ ቤት ሳር ሲከድን በቀን 20.00 ብር ይከፈለዋል:: አልፎ አልፎ በኮንትራትም ይሰራል:: ነገር ግን ምንም እንኳን መተዳደሪያ ብሎ የሚሰራው ስራ ቢሆን ወዳጅ ጎረቤት «አሳራኝ ብሎ ከለመነው» ገንዘብ ሳይጠይቅ ይሰራል:: ሌላ ጭቃ በማቡካት የሚተዳደሩት አቶ በለጠ ወርቁም የሰላጤዋ ተወላጅ እንዳልሆኑና ለቀን 10.00 ብር እየተከፈላቸው ለቤት መምረጊያ የሚሆን ጭቃ እንደሚያቦኩ ነው የገለፁልኝ::

## 5.5 የቤት ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃ

የተለያዩ ምሁራን የእጅ ስራ ባለሙያዎችን ማህበራዊ ደረጃ አስመልክቶ ሲናገሩ በተለይ በኢትዮጵያ፣ የተለያዩ የእጅ ስራ ባለሙያዎች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ የተገለሉና ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው እንደሆኑ ይገልፃሉ::

በዘጌ ባህረሰላጤ ውስጥ የቤት ሰሪዎችን አኗኗርና ማህበራዊ ደረጃ አስመልክቶ የተገኘው መረጃ ግን ከላይኛው ሃሳብ ጋር የሚቃረን ነው:: ቤት የዘገኞች የእጅ ስራ ውጤት ነው:: ይህ የእጅ ስራ ውጤት ደግሞ በትብብር የሚሰራ በመሆኑ እከሌ የተባለ ባለቤት የለውም:: ነገር ግን ማህበረሰቡ የቤትን አስፈላጊነት እንዲሁም የስራውን ከባድነት አምኖ ስራውን ተጋግዞ ይሰራል:: በመሆኑም ቤት ሰሪነትን በተመለከተ ማህበረሰቡ ራሱን ያከብራል፤ ያወድሳል እንጂ ማንም ማንንም አይንቅም:: ይልቁንስ በቤትስራ ዙሪያ የሚያስንቅ ዘመድ ጎረቤት ተባብሮ የሰራውን ቤት በወቅቱ አለማደስ፣ በእጅ ስራዎች (በስፌቶች) አለማስዋብ ፣የቤቶችን ንፅህና አለመጠበቅ ሲሆን

ለማስዋቡና ንፅህና ለመጠበቁ ደግሞ ሴቶች ሃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን አሁንአሁን ከሌላ ቦታ መጥተው በጭቃ ማቡካትና በሣር መክደን የሚተዳደሩት ሰዎች እንኳን ጥራት ያለው ስራ እንዲሰሩ የሚጠበቅ ከመሆኑ ባሻገር ከሙያው ጋር በተያያዘ የተለየ ክብር እንኳን ባይሰጣቸው እንደ ማንም ሰራተኛ ስራቸውን አምኖ በመቀበልና እንዲሰሩበት ያደርጋል እንጂ አይንቃቸውም፡፡

በአጠቃላይ በዘጌ ባህረሰላጤ የቤት ስራ ባለሙያነት ቀስ በቀስ ከማህበራዊነት ወደ ግለሰብ እየወረደ የመጣ ሲሆን የባለሙያዎችን ማህበራዊ ደረጃ በተመለከተ ዛሬም ሆነ ትናንት ሃብታምም ይሁን ደሃ በቤት ስራ ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ ስለዚህም ቤት ሰሪ ስለሆኑ ብቻ ሰዎች አይከበሩም አይናቁም፡፡ ይህ በመሆኑ ደግሞ የቤት ሰሪዎች ማንነትና ደረጃ በቤት ስራው ባህል ላይ የሚያሳርፈው ተፅዕኖ የለም፡፡

## 5.6 የዘጌ ባህረ ሰላጤ ባህላዊ ቤቶች በማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ አውዶች

አውድ፣ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የተሟላና ትርጉም ያለው ጥናት ለማድረግ ይቻል ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት ሊደረግበትና እንደ የፎክሎር ጥናት ስርዓት አስይዞ ሊገልፀው የሚገባ ፎክሎራዊ ጉዳይ እንደሆነ ብርሃኑ(1995) ይገልፃሉ፡፡

ብርሃኑ Bauman(1983) ን ጠቅሰው እንደፃፉት ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች እንደ የፎክሎር ጥናት የግድ ሊገልፃቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

> ማህበራዊ አውድ ፎክሎሩ የሚከወንበት ስነልሳናዊ ማህበረሰብ ማህበራዊ አደረጃጀትና አወቃቀር፣በከዋኙና በተደራሲው መካከል የሚኖሩ ተራክቦዎችንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይይዛል፡፡ባህላዊ አውድ ደግሞ የፎክሎር አተረጓጎም ዘልማድን ወይም የፍቺ ስርዓትን (Semantic System) ለምስሳሌ ተምሳሌታዊ/ ዘይቤያዊ ውክልናን እንዲሁም በልዩ ልዩ ኪናዊ ቅርፆች መካከል የሚኖሩትስስሮችን ወዘተ የሚመለከቱ እሳቤዎችንና አገራዊ እውቀቶች ያካትታል(ብርሃኑ፣38-39)፡፡

በመሆኑ በማህበራዊ አውዶች የባለሙያዎችና የተጠቃሚዎች ማንነት(ዘር፣ሃይማኖት፣ ስራ ወዘተ)፣በመካከላቸው ያለው ተራክቦ፣አደረጃጀታቸው፣ማህበራዊ ተቋሞቻቸው፤በባህላዊ አውድ ደግሞ የፎክሎሩ ባለቤቶች ፎክሎሩን የተረዱበት መንገድ፣በፎክሎሩ የተገለፀው የህይወታቸውክፍል፣አገራዊ ዕውቀቶች የሚነሱ ነጥቦች እንደሆኑ(Dorson:1983) ገልፀዋል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ Glassie (1999) በተለይም በቁሳዊ ባህል ጥናት ኢኮኖሚያዊ አውድ ከማህበራዊና ባህላዊ አውዶች ጋር ተጨምሮ ሊታይ የሚገባው የአውድ አይነት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በስሩም የጥሬ ዕቃዎችና ያለቀላቸው ዕቃዎች ዋጋ፣የገገርዎች የኢኮኖሚ አቅም ወዘተ ሊጠኑ የሚገባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ቀጥሎ የሰላጤዋ ባህላዊ ቤቶች በማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ አውዶች ምን እንደሚመስሉ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### 5.1.6.1 ቤቶች በማህበረ ባህላዊ አውዶች

ብዙ ቁጥር ያለው የዘጌ ባህረ ሰላጤ ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነው። ይህ ህዝብ ለዘመናት ስራን ተረዳድቶ እየሰራ ኖሯል።ተረዳድቶ ለመስራት ባህሉ ደግሞ ጉርብትናን፣ማህበርን፣ሰንበቴንና የመሳሰሉትን ባህላዊ ተቋማቱን ቡድንን መፍጠሪያ መንገዶች አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል።በዚህም መሰረት እንደሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ቤት ስራ በዘጌ ባህረ ሰላጤ ቤቶች የሚሰሩት በህብረት ነው። ከአምስት ትውልድ በላይ ሰዎች ኑረውባቸዋል ከሚባሉት የእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶች አንስቶ አሁን እስከሚሰሩት ጎጆ ቤቶች ድረስ የህብረት ስራ ውጤቶች ናቸው። በሰላጤው የቤት ስራ ወንፈል (ብድር) ስለሆነ በማንኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ ያለ ሰው ሃብታምም ይሁን ደሃ ቤት በመስራት ተግባር ይሳተፋል። ይህም በመሆኑ ለቤት ሰሪዎች ተለይቶ የሚሰጣቸው ማህበራዊ ደረጃ የለም።

ምንም እንኳን ምግብ በማዘጋጀትና ቤቶችን በማስዋብ ሂደት ሴቶችም የሚሳተፉ ቢሆን ሌላው ስራ ሁሉ በወንዶች የሚሰራ በመሆኑ የቤት ባለቤት ሆነው የሚጠሩት ወንዶች ናቸው። አንድ ወንድ የቤት ባለቤት የሚሆነው ሚስት ካገባ በኋላ ነው። ቀደም ሲል አንድ ወንድ ለአቅመ አዳም ሲደርስ ወላጆቹ «ትሆነዋለች» የሚሏትን ሴት መርጠው ያጋቡት ነበር።አሁን ግን ራሱ ባለቤቱ መርጦ ያገባል። ታዲያ በፊትም ይሁን አሁን አንድ ወንድ ካገባ በኋላ እሱና ሚስቱ ከእርሱ ወላጆች ጋር መኖር ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜም «ከእናቷ የጎደለውን ከአማቷ» እንዲሉ ከአማቷ ቤት የቤት ሙያ ትማራለች፣ ስፌት እየሰፋችና ሌሎች ስራዎችን እየሰራች ትቆያለች። በዚህ ሁኔታም ከ1-3 ዓመት ድረስ ከአማቶቿ ቤት ልትቆይ ትችላለች። በኋላ ግን ነፃነቷን በፈለገችበት ጊዜ ብቻዋን መኖር እንደምትፈልግ ለባሏ ነግራ ቤት ይሰራል። ለለዚያም ወላጆቹ እሳተ ከላ ወይም ድርብና ምድር ቤቶችን በውርስ ይሰጡታል። ከዚያም ወደ አዲሱ ቤታቸው ይገባሉ። ወደ ቤት በገቡ ጊዜ የቤት ዕቃዎችን ማሟላትና ማሰናዳት የሴቷ ድርሻ ነው።ስለዚህም የሃገሩ ባህል ነውና ብዙ ዕቃዎችን ከእናቷ፣ ከእህቶቿ፣ ቀድመው ካገቡ ጓደኞቿና ከአማቷ በስጦታ ታገኛለች። በዚህ አጋጣሚም ማዲጋዎች (እንስራዎች)፣ ድስቶች፣ ገንቦዎች በስጦታነት«የጎጆ መውጫ» ተብለው ይበረከቱላታል። እሷም ዘመዶቿ፣ ጎረቤቶቿና ጓደኞቿ የሰጧትን እንዲሁም አባወራዋ የገዛላትን የቤት ዕቃዎች በሚገባ ታስቀምጣለች ከአማቷ ቤት እያለች በሰፋቻቸው ስፌቶች ቤቷን ታስውባለች። ይህ ድርጊት የሙያዋ መለኪያም ነውና ትጠነቀቃለች።

ከዚህ በኋላ ቤት ተሠርቶና ተሠናድቶ እንዳለቀ የሙሽሮችን «ጎጆ መውጣት» አስመልክቶ ቤት መመረቅ ባህል ስለሆነ በቤት ውስጥ ድግስ ይደገሳል። የአካባቢ ነዋሪዎች፣ የእድርና የፀበል ፀዲቅ አባላት፣ዘመድ ወዳጅም ጠላ በገንቦ፣ አረቄና እንጀራ

እየያዘ በመምጣት እንኳን ደስ አላችሁ «ቤት ለእምቦሳ» ይላል፡፡እንደ መረጃ አቀባዮች ገለፃ ትርጓሜው ሃብታም ሁኑ፣ ችግር አያግኛችሁ ማለት ነው፡፡ ባለቤቶችም « እንቦሳ እሰሩ» በማለት ያንኑ ትርጉም ያዘለ መልሳቸውን ይሰጣሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ቤቱ ባለቤቶች በፈለጉ ጊዜ ሁሉ ጐረቤቶች ተሰባስበው ቡና ይጠጡበታል፡፡ ዘመድ አዝማድ ይጋብዙበታል፡፡ በዓላት ያከብሩበታል፡፡ ለምሳሌ በልደት፣ በጥምቀት፣ በፋሲካ ሰው ተጠርቶ የሚጋበዝ ሲሆን የቤቱ ባለቤቶች በተለይ በሚያከብሩት «መልዐክ» ወይም «ፃድቅ» ስም ድግስ ይደግሳሉ፡፡ በእነዚህ አጋጣሚዎች ሰዎች በቤቶች ውስጥ ይሰበሰባሉ፡፡

በአጠቃላይ ሁሉም ባህላዊ ቤቶች አሰራራቸው፣ በማህበር ሲሆን የቤት ውስጥ ዕቃዎችን የማሟላት ተግባርም የማህበረሰቡ ድርሻ ነው፡፡ ከዚያም በኋላ ቢሆን ሰዎች በማህበር ይበሉባቸዋል፤ ይጠጡባቸዋል፡፡ ይህም ለዘመናት ባህል ሆኖ የዘለቀ ጉዳይ ነው፡፡ እስካሁንም ድረስ ይህ ማህበራዊነት ጥቂት በማይባል መልኩ ተጠብቆ ቆይቷል፡፡ቤቶቻቸው ደግሞ የማህበረሰቡን ሃይማኖት የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

## 5.1.6.2 ባህላዊ ቤቶች በኢኮኖሚያዊ አውዶች

የዘጌ ባህላዊ ቤቶች የሰሪዎቻቸውን ማህበራዊ ደረጃ ባያሳዩም የባለቤቶቻቸውን ማህበራዊ ደረጃ ያሳያሉ፡፡ አሁን ባሉበት ሁኔታ ሲታዩ የእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ባለቤቶች ወላጆቻቸውና አያቶቻቸው ሊቀረድና ምስለኔ የነበሩ እነሱም ከወላጆቻቸው በተላለፉላቸው ጥሪቶች የተነሳ ኑሯቸው ከአካባቢው ነዋሪዎች የተሻለ ናቸው፡፡ በክፍክፍ ጎጆ ቤት የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሲሆኑ በአልባሶ ጎጆ ቤት የሚኖሩት ማህበረሰቡ ደሃ የሚላቸው ናቸው፡፡ ይህንንም የፈጠረው ቤቶች የተሰሩበት ጥሬ ዕቃ መጠንና ቤቶች የሚከደኑበት ሳር የሚቀያየርበት ጊዜ ነው፡፡ ታዲያ ሁሉም የቤት ባለቤቶች ቤቶቻቸውን የሚሰሯቸው ከቡና ሽያጭ በሚያገኙት ገቢ ነው፡፡

በምዕራፍ 4 «የዘጌ ማህበረሰብ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ» በሚል ንዑስ ርዕስ ስር እንደተገለፀው የዘጌ ሰላጤ ሕዝብ ዋነኛ መተዳደሪያ የቡና ሰብል ነው፡፡ ሰዉ በቡና ምርቱ የዕለት እለት ኑሮውን ይገፋበታል፤ልጆቹን ያሳድግበታል፤ያስተምርበታል፡፡ እንዲሁም ከቤት ስራ ጋር በተያያዘ የሚከናወኑና ወጪን የሚጠይቁ ተግባራት ሁሉ ከቡና ሽያጭ በኋላ የሚደረጉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ድግስ መደገስ በቤት ስራ ወቅት አንዱ ተግባር እንደመሆኑ ለድግስ መደገሻ የሚሆነው ገንዘብ ቡና ከተሸጠ በኋላ የሚገኝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለቤት መስሪያ የሚሆን የሳር መግዣ ገንዘብ ለማግኘትም እንዲሁ ቡና ይሸጣል፡፡ይሁን እንጂ በሰላጤዋ ውስጥ የቡና ምርት « የሚለቀመው» በዓመት አንድ ጊዜ በየካቲት ወር ስለሆነ ቤቶች የሚሰሩት ከየካቲት እስከ ግንቦት ባሉት የበጋ ጊዜያት ነው፡፡ ዳሩ ግን የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲና ምርምር (1996) እንደሚገልፀው

የሰላጤዋ የቡና ምርት በየጊዜው ባጋጠመው በረዶና ድርቅ የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ ምርቱ እየቀነሰ ነው። ይህ ደግሞ በተራው በቤቶች አሰራር ማህበራዊነት ላይ የራሱን ጥላ እያጠላበት ነው። ለምሳሌ የቃል ማስረጃዎች ቀደም ሲል እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ለማሳራት የሚለመኑ ሰዎች ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን ብቻ ሣይሆን ለቤት መስሪያ የሚሆኑ እንጨቶችንም አዘጋጅተው ይመጡ ነበር። ያ ባይሆን ደግሞ ቤተሰሪው ያስፈለገውን ያህል እንጨቶ ከጓሯቸው እንዲወስድ ይፈቅዱ ነበር። ዛሬ ግን ቤት ለማሳራት የሚመጡ ሰዎች ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ብቻ ነው ይዘው የሚመጡ። ሁሉንም ጥሬ ዕቃዎች ቤት የሚሰራለት ሰው ነው የሚያቀርበው። እንዲሁም እንጨቶችን ከርሱ ጓሮ ብቻ ነው የሚቆርጠው። ይህንንም ቢሆን በመጀመሪያ ለማዘጋጃ ቤት እንጨት ለመቁረጥ መፈለጉን ገልፆ የትኛውንና ምን ያህል መቁረጥ እንዳለበት ከተወሰነ በኋላ ነው። አለበለዚያ ይቀጣል። ይህም የትልልቅ ቤቶችን መስራት ብቻ ሣይሆን የቤቶችን ቶሎ ቶሎ መሰራትም እንዳስቀረው የቃል መረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ።

ከዚህ ውጭ ደግሞ የኑሮ ውድነት ዘጌን ብቻ ሣይሆን ጎረቤት ገጠሮችንም የነካ በመሆኑ ለጣሪያ ማልበሻ የሚሆኑ ሣሮች ዋጋቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል። ለምሳሌ እንደመረጃ አቀባዮች ገለፃ የአንድ እሳተ ከላ ቤት ጣሪያ የሚከደንበት ሳር አንድ ሺህ ብር ይፈጃል። አንድ ክፍክፍ ጎጆ ቤት ደግሞ ሶስትና አራ መቶ ብር የሚፈጅ ሳር ሊያስፈልጋቸው ይችላል። አሁን ደግሞ በመሰራት ላይ ያሉት ጎጆ ቤቶች እንደመሆናቸው የቤቶችን ሳር በየጊዜው መቀየር ያስፈልጋል። የክፍክፍ ጎጆ ቤት ሳር በአምስት፣ የአልባሶ ደግሞ በአንድ ዓመት መቀየር ይፈልጋል። በየጊዜው ሳር መቀየር ግን የሰዎቹን አቅም የሚፈታተን ነገር እየሆነ መጥቷል። ታዲያ የሰላጤዋ ነዋሪዎች ይህንን ችግር ለመፍታት መፍትሄ አድርገው የወሰዱት ቆርቆሮ ቤቶችን መስራት ነው። የቆርቆሮ ቤቶች ደግሞ የባህላዊ ቤቶችን ቅርፅ የለቀቁ ጣሪያቸው ቆርቆሮ የለበሰና ግድግዳቸው አራት ማዕዘን ነው።

በአጠቃላይ በዘጌ ባህረ ሰላጤ ቤት ስራ ሙሉ በሙሉ በማህበር የሚሰራ ሲሆን ይህ ሁኔታ ግን አሁን አሁን ሰላጤዋ እየገጠማት በመጣ ድህነት የተነሳ መልኩን እየቀየረ ነው። የቤቶች ባህላዊ መልክም እየተቀየረ ነው።

## 5.8 ከባህላዊ ቤቶች ጋር የተያያዙ እምነቶች፣ትረካዎችና ስነቃሎች በቤቶች ህልውና ላይ ያላቸው ተፅዕኖ

ከባህላዊ ቤቶች ጋር በተያያዘ እምነቶች ፣ትረካዎችና ስነ ቃሎችን ለማግኘት ባደረግሁት ከፍተኛ ጥረት ያገኘሁት መረጃ በአካባቢው ከቁሳዊ ባህሉ ጋር በተያያዘ

የተወሰኑ እምነቶችና ጥቂት ስነቃሎች እንዳሉ የሚገልፅ ነው። የተገኙትን እንደሚከተለው አቀርቤያቸዋለሁ፡-

«‹‹ቾሃል›› (ምልክት) ሲተከል ሽማግሌዎች ካልመረቁ የቤቱ ባለቤት ጥሩ ኑሮ አይገጥመውም»

በገጽ 63 «ግድግዳ መገንባት» በሚለው ንዑስ ርዕስ እንደተገለፀው ግን ግድግዳ ከመቆሙ በፊት ቤተሰሪዎች የቤቱን ግድግዳ ለማቆም በወሰኑበት ቀን «የሃገር ሽማግሌዎች» ተገኝተው መመረቅ አለባቸው። ይህ የአገር እምነት ነው። ዕምነቱ በሁሉም ቤተሰሪዎች ዘንድ ስርጰ የገባ በመሆኑ ሽማግሌዎች ሳይመርቁ ቤቱን የሚሰራ ሰው የለም። በእርግጥ ሽማግሌዎቹ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልገጠማቸው በስተቀር ዕምነቱ የእነሱም ስለሆነ በተቀጠሩበት ቀን አይቀሩም።ከመጡ በኋላ ይመርቃሉ እንዲሁም በአንባቢው ወግና ልማድ መሰረት ቤቱ እንዴት መሰራት እንዳለበት ይናገራሉ። ታዲያ ይህ ዕምነት ልጆች የአባቶቻቸውን ቤት አሰራር ባህልና ልምድ ተከትለው እንዲሰሩ የማስገደድ ባህሪ ሲኖረው አባቶችም በበኩላቸው የቤት አሰራር ስርዓታቸውን ደንባቸውንና ልማዳቸውን ለልጆቻቸው የሚያስተላልፉበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል።

«እግዚአብሔር ለአቡነ በትረ ማርያም በሰላጤው ውስጥ ያሉ ሃብቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገሩ ለዘላለም ይኑሩ ሲል ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል።»

ዘጌ ባህረ ሰላጤ አመሰራረቷ፣ የህዝቧ አሰፋፈርና የሕዝቧ የአኗኗር ፈሊጥ አፈ ታሪክን መሰረት ያደረገ እንደሆነ በምዕራፍ ሦስት ተገልጿል። ታዲያ ስነ ቃሉ እንደሚያስረዳው አቡነ በትረ ማርያም የአካባቢው ሰው «የዘጌ አባት» ብሎ የሚጠራቸው የሰላጤዋ መስራች ናቸው። እኚህ ሰው መንፈስ ቅዱስ መርቷቸው ሰላጤዋን ከመሰረቱ በኋላ እግዚአብሔር ሕዝቡ አትክልት እየተከለ እንዲኖር እንዲገልፁ ትዕዛዝ የሰጣቸው ሲሆን ዘገኞች ንቁና ፈጣን አዕምሮ ይኑራቸው፣ የሰላጤዋ ሃብቶች ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ ይኑሩ . . . ብሎ ሰዎችንና ሰላጤዋን ባርኳል። ታዲያ የሰላጤዋ ነዋሪዎች፣ ባህላዊ ቤቶችም ከተባረኩት የሰላጤዋ ሃብቶች ውስጥ የሚመደቡ ስለሆነ ይህንን ያህል ጊዜ ሳይፈርሱ እስከ አምስት ትውልድ ድረስ ተሸጋግረዋል። ይህም ሊሆን የቻለው በእግዚአብሔርና በአቡነ መካከል ባለው ቃል ኪዳን የተነሳ ነው ብለው ያምናሉ። ነገር ግን እምነቱ የሙያው ተስተላልፎ እየጎዳው ነው። ምክንያቱም ትልልቆቹ ብቻ ሳይሆኑ ወጣቶችም ይህንን ዕምነት አጥብቀው የያዙት ስለሆነ ሰዎች በምን ዓይነት ጥበብና ዕውቀት እነዚህን ዘመን አልፈው ከትውልድ የደረሱ ቤቶችን ሊሰሩ እንደቻሉ ከመመርመርና እነሱ ደግሞ ሲሆን የተሻለ አለበለዚያ ደግሞ ያሉትን የመሰሉ ቤቶች እንዳይሰሩ፣ እንዲሁም የሰሪዎችን የፈጠራ ችሎታ እንዳያደንቁ ሆነዋል። የቤቶችን የአሰራር ጥበብና የመቆየት ጊዜ ሙሉ በሙሉ

ከተዓምር ጋር ያያይዙታል፡፡ ዕምነቱም በቤት ስራውና በሙያው ሕልውና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ነው፡፡

ቀጣዩ እምነትም በቤቶች ህልውና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ነው፡፡

«እሳተ ከላ ቤቶች ደም ለምደዋል»

የቃል መረጃ አቀባዮች እንደሚገልፁት ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ ደርግ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የእሳተ ከላ ቤት ባለቤቶች ሲቀረደችና ምስለኔዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ደግሞ ሃብት ሞልቶ የተረፋቸው ስለነበሩ «ለቤቱ» በሚል «ደም የማፍሰስ » (እንስሳትን የማረድ) ልማድ ነበረባቸው ፡፡ ነገር ግን በ1962 ዓ.ም በዘጌ ባህረ ሰላጤ የበረደ መዝነብን ተከትሎ (የአካባቢ ጥበቃ ጥናት፣1996) የቡና ምርቱ በመውደሙና ከዚያ በኋላ የቀጠለው ድርቅም ህዝቡን ወደ ደህነት ስለአሽጋገረው «ለቤት» ብሎ እንስሳትን ማረድ ይቅርና ሰው እንኳን የእለት ጉርሱን ለማግኘት ሌላ የገቢ ምንጭ ፍለጋ ሄዷል፡፡ ነገር ግን «ቤቱ ደም ለምዷል» የሚለው እምነት ሰዎች በድፍረት በቤቶች ውስጥ እንዳይኖሩ ስላገዳቸው «እነዚህን ደም የለመዱ» ቤቶች በመዝጋት በሌላ ቤት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በአንድ በኩል ቤቶች በመዘጋታቸው ምን አይነት መልክና ቅርፅ እንዳላቸው አይቶ ለመማር ከማስቸገሩም በላይ ራሳቸው ቤቶችም የጣሪያቸው ሳር የማይቀየር በመሆኑ በዓመት ዓመት የለበሰት ሳር እየሳሳ ጣሪያቸው እያፈሰሰ ግድግዳቸው በመበስበስ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም «ቤቶች ደም ለመደዋል» የሚለው እምነት በአንድ በኩል የሙያውን ተስተላልፎ የገታ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸውን ቤቶች እንዲፈርሱ እያደረገ ነው፡፡

«እሳተ ከላ ቤቶች ውስጥ ጠገራ ብር (ማሪያ ትሬዛ) ተቀብሯል»

ዘገኖች እንደሌሎች የሃገራችን ህዝቦች ሁሉ በማሪያ ትሬዛ ይገበያዩ ነበር፡፡ ስሙንም «ጠገራ ብር» ሲሉ ይጠሩታል፡፡ ታዲያ ቀደም ሲል የነበሩት ሰዎች ይህንን ገንዘብ ለማጠራቀም ብሎም ደህነነቱ ተጠብቆ ለልጅ ልጅ እንዲተላለፍ ሲሉ በማዲጋ (እንስራ) ውስጥ ከትተው መሬት ውስጥ ይቀብሩት ነበር፡፡ ታዲያ ዘገኖች እንደሚያምኑት እሳተከላ ቤቶች ውስጥ ጠገራ ብር ተቀብሯል፡፡ ነገር ግን ሰዎች ገንዘቡን መውሰድ የማይገባው ሰው እንዳይወስደው ሲሉ በሚቀብርበት ጊዜ አጋንንት እንዲጠብቁት ይዋዋላሉ፡፡ ስለዚህም ማንም ሰው ያንን ቦታ ቢነካ አጋንንቱ ይጣሉታል፡፡ እስከ ቤተሰቡ አካል ጉዳተኛ ያደርጉታል ፡፡ ብሎም ያጠፉታል፡፡ ስለዚህ በእውቀትም ሆነ ሳይታወቅ ጠገራ ብሩ ያለበትን ቦታ በመንካት ሊፈጠር የሚችለውን ጉዳት ለማምለጥ መፍትሄ ሆኖ የተገኘው ቤቶችን ዘግቶ ከአገልግሎት ውጭ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ልክ ከላይ እንደቀረበው የማህበረሰቡ እምነት የቤቶችን አሰራር የሙያ ተስተላለፎ ብሎም የቤቶችን ህልውና አደጋ ላይ ጥሏል፡፡

በአጠቃላይ በሰላጤዋ ውስጥ ከቤቶችጋር በተያያዘ ሊገኙ የቻሉት ማህበረሰቡ ያለው እምነትና አመለካከት በቤቶች ህልውና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው ናቸው፡፡ ቃል ግጥሞችንና ትረካዎችን የመሳሰሉ ስነ ቃሎችን ግን አላገኘሁም ፡፡

## 5.7 በዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች ላይ ተፅዕኖ ያደረጉ ነገሮች

አስቀድሞ እንደተገለጸው የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ ቤቶች መልክ ከጊዜ ወደጊዜ እየተለወጠ ከፍተኛ ጥሬ እቃ ፈጅተው በከፍተኛ ጥበብ የሚሰሩ እሳተከላና ደርብና ምድር ቤቶች በአነስተኛ ወጭ በሚሰሩ የሳር ቤቶች ተተክተዋል፡፡ የሳር ቤቶች ደግሞ በቆርቆሮ ቤቶች ተተክተዋል፡፡በመሆኑም የባህላዊ ቤቶች ህልውና አሣሣቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ለዚህ ደግሞ አያሌ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም ዋናዋናዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

### 5.7.1 የአየር ንብረት ፀባይ ለውጥ

ዘጌ በቡና ምርት የምትተዳደር በደን ሃብቷም የበለፀገች በአጠቃላይ በተፈጥሮ ሃብቷ የታደለች መሬት ነበረች፡፡ የአየር ንብረቷም ወፃ በሆነ መንገድ ወይና ደጋ ነበር፡፡ ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የአየር ንብረቷ እየተለወጠ መጥቷል ( የአማራ ክልል ቱሪስት መስህብ ሃብቶች 1991፣የአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥር (1996) ፡፡

የዚህ የአየር ንብረት ፀባይ መለወጥ ደግሞ በቡና ምርቷ ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረና ይህም ቡና የሰላጤዋ ህልውና እንደመሆኑ በህዝቡ ኑሮ ላይ ጥላውን እንዳጠላበት ነው ከተገኙት መረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው፡፡ የእድሜ ባለፀጋ በሆኑት የሰላጤዋ ነዋሪዎች ትውስታ መሰረት የሰላጤዋ የአየር ንብረት ፀባይ መዛባት ሁኔታ በግልፅ የታየው በ1962 ዓ.ም. በሰላጤው ውስጥ በረዶ ከዘነበ በኋላ ነው፡፡ በጊዜው የዘነበው በረዶ የቡና ምርቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፡፡ በጊዜው አፍርቶ የነበረው ቡና በእጅጉ በመጎዳቱ ነዋሪዎች የኑሮ ህልውናቸው የሆነው የቡና ምርታቸውን መጎዳት ተከትሎ ሌላ ህልውናቸውን የሚያረጋግጥላቸው ነገር ፍለጋ እንዲሄዱ ተገደዋል፡፡ በዚህም ጊዜ በቅርባቸው ያገኙት «የክፉ ቀን ማሳለፊያ» በሰላጤዋ የሚገኘው የደን ሃብት ነው፡፡ በመሆኑም ነዋሪዎች ከደኑ ውስጥ የተለያዩ ዝርያ ያላቸውን በርካታ ዛፎች እየቆረጡና በታንኳ ጭነው ወደ ባህር ዳር እየወሰዱ መሸጥ ጀመሩ፡፡ ነገር ግን የአየር ሁኔታው ከመሻሻል ይልቅ እየባሰበት ስለመጣ የዛፍ ቆረጣ ደረጃው እያደገ መጥቶ ወደ ደን ጭፍጨፋ ተሸጋገረ፡፡ የችግሩ ፅናት ግን ህዝቡን በደን ጭፍጨፋ ብቻ እንዲቆም አላደረገውም፡፡ የተሰሩ ቤቶችን እንዲያፈርስ አደረገው እንጂ፡፡ ለዚህም በር የከፈተው ቤቶች የተሰሩበት ቁስ ነው፡፡ እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶች የሚሰሩት በከፍተኛ

የእንጨት ፍጆታ ነው፡፡ የእንጨቶች አይነት ደግሞ ከጥራቱ ከቁመቱና ከስፋቱ አንፃር የተመረጠ ነው፡፡

ቤቶቹ ከውጭ ሲታዩ ዙሪያቸው ጭቃ ይሁን እንጂ ጭቃው በውስጥ በኩል ያለውን በከፍተኛ ጥበብ ተጌጦ የተሰራውን የጣውላ እንጨት የሚሸፍን ነው፡፡ በሮችና የበሮች መቃንም እንዲሁ ከዋንዛ እንጨት የተሰሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን የቤቶች እንዲህ በከፍተኛ የእንጨት ፍጆታ መሰራት ለህልውናቸው አስጊ ሁኔታን ፈጥሮባቸዋል፡፡ ምክንያቱም በሰላጤዋ ውስጥ የተከሰተው የአየር ንብረት መዛባት የእንጨት መሸጥ ባህልን የመሰረተበት የዘጌ ህብረተሰብ ደኑን ጨፍጭፎ ሲጨርስ ቤቶችን የተሰሩበትን ጣውላ እያፈረሰ መሸጥ ጀመረ፡፡ እንዲውም ቤቶች በውስጣቸው የያዙት የእንጨት መጠንና የእንጨት ጥራት ሰዎች ዛፎችን በመቁረጥና በመፍለጥ ከሚያጠፉት ጊዜና ጉልበት ሽጠውም ከሚያገኙት ገቢ ጋር ሲነፃፀር ቤቶችን እያፈረሱ መሸጥን የተሻለ አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት አሁንም ድረስ ቤቶች እየፈረሱ ህልውናቸው እየጠፋ ነው፡፡

ከዚህ ውጭም ቢሆን የአየር ንብረት ፀባይ ሲቀየር በሰላጤው የሚገኙ ዛፎች ብቻ ሳይሆኑ በጎረቤት ገጠሮች የሚገኙ ሳሮችም እየጠፉና ቢኖሩም ዋጋቸው እየጨመረ በመምጣቱ የሳር ክዳን ያላቸውን ቤቶች መስራት አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ ቢሰሩም እንኳን በየጊዜው የሚቀየር ሳር ማግኘት ከባድ ነው፡፡ በመሆኑም ዘገኞች ጎጆ ቤት የመስራት ባህላቸውን እየተው ቆርቆሮ ቤት እየሰሩ ነው፡፡ የእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶችን ጨርሰው እንዳይወድሙ የሚፈልጉ ሰዎችም የቤቶችን ጣሪያ በቆርቆሮ ለመሸፈን ተገድደዋል፡፡

## 5.7.2 የቤቶች ከአምልኮ ጋር መያያዝ

«ቁሶች ከእምነቶች ጋር ሊያያዙ ይችላሉ፡፡ የፍርሃት ሀሳቦችንና አስተሳሰቦችን፣ እድሎችን ወይም ሃይማኖታዊ ልማዶችንም ሊያሳዩ ይችላሉ» (Oring 1986፣ 207) ፡፡ በዘጌ ባህረሰላጤ የባህላዊ ቤቶች በተለይም የእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶች ባለቤቶቻቸው ከቤቶቻቸው ጋር በተያያዘ የሚያምኗቸው እምነቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ እምነቶች ውስጥ ባለቤቶች በግልጽ ከሚታወቁበትና እነሱም «እንከተለዋለን» ብለው ከሚናገሩት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ውጭ ቤታቸው ውስጥ በምናባቸው ፈጥረው የሚያምኑት አምላክ አላቸው፡፡ ይህንን አምላክ «ቆሌ» ሲሉ ይጠሩታል፡፡

ይህንን አምላካቸውንም ሰው በታመመ ጊዜ ይለማመኑታል፣ አገር ሰላም እንዲሆን ይለምኑታል፡፡ በቤታቸው ውስጥ እንስሳትን በማረድ መስዋዕት ያቀርቡለታል፡፡ ምንም እንኳን ቆሌን ማምለክ ዛሬም ድረስ በየቤቱ ያለ ጉዳይ ቢሆንም ቀደም ሲል ግን

ጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ይከወን እንደነበረ ነው የቃል መረጃ አቀባዮች የሚገልፁት::

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት ባለቤቶች ምስለኔና ሊቀረድ የሚባል ስልጣን ያላቸው ባለብዙ የቡና መሬት ባለቤቶች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ደግሞ ለቆሌያቸው አምልኮ የሚያቀርቡት መስዋዕት እጅግ የተትረፈረፈ ነበረ:: ብዙእንስሳት[7] (በግና ከብት) ያርዳሉ፤ ብዙ ጠላ ይጠመቃል፤ ጠጅ ይጣላል:: ሰዎቹ እየተጠራሩ ይበላሉ ይጠጣሉ:: ይህ ሁኔታም ቀስ በቀስ እየተለመደ ስለመጣና ሳይደረግ ቢቀር «በቤተሰቡ ብሎም በሃገር ላይ አንዳች መዓት ይመጣል» የሚል ፍርሃት እየተወለደ መጣ:: ይህም በመሆኑ ጊዜ ወስኖ «ለቤቱ» በሚል ደም ማፍስ (እንስሳት ማረድ) የረጅም ጊዜ ባህል ሆኖ ኖረ::ነገር ግን ይህ ሁኔታ የሰላጤዋን የቡና ምርት መቀነስ እንዲሁም በ1969 ዓ.ም. ሁሉም ሰው እኩል የቡና መሬት ባለቤት እንዲሆን የሚያደርግ አዋጅ መውጣቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የነበረው የኑሮ ደረጃ ልዩነት አስተካክሎ ነዋሪው በአብዛኛው በተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ መኖር ስለጀመረ በነበረበት መልክ ሊቀጥል አልቻለም::

ሰዎች ጊዜ ወስነው «ለቤቱ» ሲሉ የሚያደርጉትን የተትረፈረፈ ግብዣና ቅጥ ያጣ ድግስ በዚያ መልክ ለመቀጠል የሃብት ችግር ስላጋጠማቸው ድርጊቱን ያቆማሉ:: ነገር ግን ይህን ማድረጋቸው አንድ ነገር እንሆናለን ብለው እንዲሰጉ ስላደረጋቸው በቤቶች ውስጥ ለመኖር ድፍረት አጥተዋል:: ስለዚህም ቤቶችን በመልቀቅ ሌሎች ቀለል ያሉ የቆርቆሮ ቤቶችን ሰርተው መኖር ጀምረዋል:: ለምሳሌ በዚህ ሁኔታ ካገኘኋቸው ቤቶች ውስጥ በኡራ ኪዳነ ምህረት ገበሬ ማህበር ጋሚ ጎጥ ውስጥ የሚገኘው የእማሆይ ወለላ ቤት አንዱ ነው::

የቤቱ ባለቤት ዕድሜያቸው 80 አካባቢ እንደሆነ ይናገራሉ:: ቤቱ ደርብና ምድር ነው:: በዚህ ቤት ውስጥ ከ50 ዓመት በፊት ነው መኖር የጀመሩት:: ቤቱ የባለቤታቸው ቤተሰቦች ሲሆን እሳቸው ባላቸውን ሲያገቡ ነው ወደዚህ ቤት የመጡ :: አሁን ግን ባለቤታቸው ስለሞቱ ልጆቻቸውንና የልጅ ልጆቻቸውን ጎረቤት አድርገው በደርቡ ቤት (በላይኛው ክፍል) ይኖራሉ::የታችኛው ቤት ግን ከተዘጋ አመታት ተቆጥረዋል::

እንዳየሁት በቤቱ ዙሪያ ያለው ቆሻሻ የቤቱን በር መቼም የማይከፈት አስመስሎታል:: የቤቱን ሁኔታ አስመልክቶ ለሴትዬዋ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ሲመልሱ:-

> እኔ የምኖረው በዚህ ቤት ነው (ያሉበትን ቤት እየጠቆሙ)::የታችኛው ቤት ተጎሳቁሏል ያ ቤት ብዙ የለመደ በመሆኑ ደፍሮ ከዚያ መኖር አይቻልም:: ቤቱ ደም ለምዷል፣ ጠጅ ለምዷል ዛሬ ያንን ለማድረግ እኔ አቅም የለኝም አርጅቻለሁ፣ ጉልበቴም ደክሟል፣ ባሌም ሞቷል:: በዛ ላይ የቡና መሬቴን

---

[7] እንስሳት በሰላጤዋ ውስጥ እንደማይታረዱና ከሰላጤዋ ውጪ ባለ ቦታ ታርዶ ስጋው እንደሚገባ ያስተውሏል::

ባሌ ሳይሞት «የባላባት ርዝራዥ» እሱ ከሞተ በኋላ ደግሞ «የሙተ ከዳ» በማለት መንግስት ስለወሰደብኝ የቤቱን ልማድ ለማድረግ አልተቻለም እና ቤቱ ቢዘጋ ይሻላል:: አለበለዚያ ሰው ጤና ያጣል ብለዋል (እማሆይ ወለላ፣5-9-1999) ::

ይህ ሀሳብ ግን የሴትዩዋ ብቻ አይደለም:: ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸውም ይጋሩታል:: የቤቱን ውስጥና ክፍል ለማየት ያቀረብኩትን ጥያቄ አልተቀበሉትም «ተዘግቶ የኖረ ቤት ስለሆነ ይጣላናል አንከፍተውም፤ ትልልቅ ሰዎች ባሉበት ደም ፈስሶ ነው የሚከፈት!» ብለዋል::

እንግዲህ በዚህ ምክንያት ቤቶች ከአገልግሎት ውጪ እየሆኑ ነው:: ይህም በቤቶች ህልውና ቀጣይነት ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው::

## 5.7.3 የነዋሪዎች ለተሻለ ኑሮ ቀያቸውን መልቀቅ

የቃል መረጃ አቀባዮች እንደሚገልፁት በርካታ የሰላጤው ነዋሪዎች ልጆቻቸውን ዘመናዊ ትምህርት በማስተማር ለወግ አብቅተዋል:: የተማሩት ልጆችም ከሰላጤዋ ውጭ በተለያዩ የሃላፊነት ቦታ ላይ ሆነው አገራቸውንና ወገናቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ:: ለምሳሌ ብዙ ሰዎች በአዲስ አበባና በባህር ዳር ከተሞች በመንግስት ስራ ተቀጥረውና የራሳቸውን ስራ እየሰሩ ይኖራሉ::

ይህ መሆኑ ደግሞ የተወሰኑ ወላጆች በቅርብ የሚከታተላቸውና የሚደግፋቸው ሰው እንዲያጡ ስላደረጋቸው ዕድሜያቸው በጨመረ ቁጥር ለቤቶቻቸው የሚያደርጉትን እንክብካቤ መቀጠል አልቻሉም:: ሳር አሳጭደው የቤቶችን ክዳን ለመቀየር የጉልበትም ሆነ የገንዘብ አቅም የላቸውም:: ስለዚህ ቤት የተከደነበት ሳር ያረጅና ጣሪያው ማፍሰስ ይጀምራል:: ፍሳሹ ደግሞ ከግድግዳው ላይ ሲያርፍ ጡቡ እየራሰ መፈራረስ ይጀምራል:: ቀስ በቀስም በጠቅላላ ቤቱ ይፈርሳል:: በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ የተማሩና በከተማ የሚኖሩ ልጆች በቅርብ ለመርዳት ሲሉ ወላጆቻቸውን ወደሚኖሩበት የከተማ አካባቢ ይወስዳሉ:: ወላጆችም የተሻለ ኑሮ ከመፈለግ አንፃር የትውልድ ቦታቸውንና ባህላዊ ቤቶቻቸውን እየተው ከተማ ገብተው እየኖሩ ነው:: ስለዚህም እነዚህ ባለቤትና ተንከባካቢ ያጡ ቤቶች ሳሮቻቸው በወቅቱ ባለመቀየሩ ማፍሰስ ስለሚጀምሩ ቀስ በቀስ ግድግዳዎቻቸው እየፈራረሱ ቤቶች ሙሉ በሙሉ እየፈረሱ ነው::

በአጠቃላይ በእነዚህ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የቤቶች ከአምልኮ ጋር መያያዝ፣ የነዋሪዎች ለተሻለ ኑሮ ቀያቸውን መልቀቅ በሚሉ ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች የተነሳ በዘጌ ባህረ ሰላጤ ከሚገኙ በርካታ የእሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤቶች ውስጥ ከመቶ በላይ የሚሆኑ ፈርሰዋል:: ሌሎች ደግሞ አሁንም በመፍረስ ላይ ናቸው:: እንዲሁም ቆርቆሮ ቤት የመስራት ባህል ተፈጥሯል::

## 5.8 ባህላዊ ቤቶችን እንዴት ለበለጠ ጥቅም ማዋል ይቻላል?

ዘጌ ከረጅም አመታት በፊት ተሰርተው ማህበረሰቡ ሲገለገልባቸው የኖሩና የማህበረሰቡን ዕውቀት፣ አስተሳሰብ፣እምነትና ፍልስፍና ሲገልፁ የቆዩ ሦስት አይነት ባህላዊ ቤቶች አሏት፡፡ነገር ግን ዛሬ እነዚህ ቤቶች ቀስ በቀስ ህልውናቸው እየጠፋ የተለመደውን መጠለያ የሚለውን አገልግሎታቸውን ሳይቀር በአግባቡ መወጣት ከማይችሉበት ደረጃ እየደረሱ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ዋና ምክንያት ተደርገው የሚጠቀሱት የአየር ንብረት ፀባይ ለውጥ፣የቤቶች ከአምልኮ ጋር መያያዝ፣የነዋሪዎች የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ቀያቸውን መልቀቅ ናቸው፡፡ በመሆኑም« የቤቶች ህልውና ጨርሶ እንዳይጠፉ ምን መደረግ አለበት?» የሚለው ጥያቄ ማንኛውንም ጉዳዩን ቀርቦ የተመለከተ ሰው ሁሉ የሚያሳስብ ቢሆንም በተለይ እኔ ደግሞ በጥናቱ ምክንያት ጉዳዩን ጠልቄ የተረዳሁት በመሆኑ ጥያቄው በአግባቡ መልስ ያገኝ ዘንድ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ለዚህም « የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ እንዲሉ » የችግሩን መፍትሄ ከራሱ ከማህበረሰቡ ለማግኘት ሞክሬያለሁ፡፡

ይህም የአንድን ማህበረሰብ ችግር« አውቅልሃለሁ መፍትሄውንም እኔ እሰጥሃለሁ» ከሚል ግዕብታዊነት ርቆ ማህበረሰቡ ሃገራዊ እውቀቱን በመጠቀም ስለችግሮቹ መፍትሄዎች የሚሰጠውን አስተያየት ማድመጡ፣በጠባቡ በዚህ ጥናት ላይ የሚሰጠውን አስተያየት የበሰለ ለማድረግ፣በሰፊው ደግሞ የሰላጤዋን ቤቶች በተመለከተ ጥናቱን መነሻ ያደረገ ተግባራዊ ርምጃ ቢደረግ የማያዳግም ስራ ለመስራትና ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት ይቻላል ከሚል ያደረግሁት ነው፡፡

በመሆኑም በቤቶች ላይ እየደረሰ ያለውን ችግር በመቀነስ ቤቶች የተሻለ ጥቅም የሚሰጡበትን መንገድ ከመፍጠር አንፃር ምን ማድረግ ይቻላል?ለሚለው ጥያቄ ነዋሪዎች የሚሰጧቸው አስተያቶች አሉ፡፡ ቀጥለው ቀረበዋል፡-

ለምሳሌ አቶ ጀመረ ክብረት የተባሉ መረጃ ሰጪ፡-

> ቤቶች እንዳለ አልቀዋል፡፡ ከመቶ በላይ የሚሆኑ እሳተከላና ደርብና ምድር ቤቶች ፈርሰዋል፡፡ ጎጆ ቤት መስራት ደግሞ እየቀረ ነው፡፡ አሁን የቀሩትን ለመጠበቅ መንግስት ካልተቃወመ በቀር እንደነበሩ አድርጎ እንዲይዝ መክሮ ለሃብታም መሸጥ ነው፡፡ወይም ደግሞ መንግስት ራሱ ተረክቦ ጥሩ አድርጎ አሰናድቶ ለፈረንጅ ማደሪያ ቢያደርጋቸውም ጥቅም ነው ( 27-9-1999 ) ፡፡

አቶ ዋሴ እንየው በበኩላቸው፡-

«እሳተከላ ቤት ከጥንት ከአባቶቻችን የወረስነው ነው፡፡ ዛሬ ልስራ በቢባል ሁሉም ነገር ከባድ ነው፡፡ መስሪያው እንጨቱም ሆነ ጥበቡ ይቸግራል፡፡ መደረግ ያለበት ያሉትን መጠበቅ ብቻ ነው፡፡ለመጠበቅ ደግሞ ቤቶችን ወደ ሙዚየምነት መቀየር ጥሩ ነው

እላለሁ »(26-2-2000 ) ይላሉ። ቄሰገበዝ ይሄይስ እንግዳው ደግሞ በሁለቱ ሰዎች አስተያየት አይስማሙም። ሆኖም መፍትሄ የሚሉትን የራሳቸውን ሃሳብ«እኔ መቼም ቤቶች ይሸጡ ወይም መንግስት ይውሰዳቸው አልልም ። ይልቅስ ይሄ በየስፍራው ያለ የተማረ ልጅ ገንዘብ እየላከ እናት አባቱን ቢረዳ፣ቤቱንም ቢያድስ የሳር መግገ ቢልክ ሰው ቤቱን እየጣለ መሄዱን ይተዋል» (3-2-2000 ) ሲሉ ይገልጻሉ ።

በአጠቃላይ ከሶስቱ ሰዎች ንግግሮች ቤቶች መፍረስ የለባቸውም የሚል ሃሳብ የሚደመጥ ሲሆን ሰዎቹ ለዚህ ሃሳባቸው ለየራሳቸው መፍትሄ የሏቸውን ቤቶችን መሸጥ ወይም ወደ መንግስት ሃብትነት መቀየር፣ወደ ሙዚየምነት መቀየርና ወላጆችን በገንዘብ በማገዝ ቤቶች እንዲታደሱ ማድረግ የሚሉ ሃሳቦችን ሰንዝረዋል።

## 6. የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ በዘጌ ባህረሰላጤ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች

የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ናቸው፡፡ ሆኖም ጥናቱ ስለባህላዊ ቤቶች ሲነሳ ስለ ባህላዊ የቤት ዕቃዎችም ቢነሳ መልካም ነው ከሚል ሃሳብ የተነሳ ከቤቶች በተጨማሪ የቤት ዕቃዎችንም ያነሳ እንደመሆኑ በቀጥታ ከሸክላ ስለተሰሩ የቤት ቁሶች ከማውራት ይልቅ በጠቅላላው« በሰላጤዋ ውስጥ በሚገኙ ባህላዊ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ የቤት ዕቃዎች ምንምን ናቸው?» የሚለውን ማሳየት እንደዳራ ስለሚያገለግል ቀጥሎ የሰላጤዋ ባህላዊ የቤት ቁሶች ቀርበዋል፡፡ አቀራረባቸው ግን ዕቃዎች የተሰሩበትን ቁስና አገልግሎታቸውን በመግለጽ የተገታ ነው፡፡ ስራው ከዚህ ያለፈ እንደሆነ ግን ጉዳዩ ይሰፋና የጥናታዊ ፅሁፉን አላማ ያስታል፡፡

### የዘጌ ባህረሰላጤ ባህላዊ የቤት ቁሶች

ዘጌ ከተመሰረተች ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረች እንደመሆኗና አስቀድሜ በምዕራፍ አንድ እንደገለፅኩት የበርካታ ቁሳዊ ባህላዊ ባለቤት እንደመሆኗ እነዚህ ቁሶች ከተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች የተሰሩ ሲሆን ከእነዚህ ቁሶች ውስጥ ምሳሌ የሚሆኑ የተወሰኑ ባህላዊ የቤት ቁሶች ቀጥለው ከተግባራቸው አንጻር ተመድበው ቀርበዋል፡

### የቡና ማዘጋጃና ማቅረቢያ ቁሶች

መደቆሻ ፡- አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው የተቆላ ቡና ለመፍጨት የሚያገለግል ትንሽ ባለ ዓይን ድንጋይ፡፡

አለሎ፡- ድንቡልቡል ቅርፅ ያለው ከመደቆሻ ጋር ሆኖ ቡና የሚደቆስበት (የሚፈጭበት) ለስላሳ ድንጋይ፡፡

ሙሬ ፡- ጥቁር ፍሬ ካለው ቀጭን የሳር ዘር የሚዘጋጅ የቡና መደቆሻው ላይ የላመው ቡና የሚጠረግበት መጥረጊያ፡ ሙሬ ለእህል መፍጮ መጥረጊያም ያገለግላል፡፡

ሰዴቃ፡- ከእንጨት የሚሰራና ቡና በሚቀርብበትም ጊዜ ሆነ በሌላ ጊዜ ፍንጃሎች (የቡና ስኒዎች ) የሚቀመጡበት አራት ማዕዘን የሆነና አራት እግሮች ያሉት ቁስ፡፡

ጀበና ፡- ከሸክላ የተሰራ ከአንገቱ ቀጠን ብሎ ከሆዱ ሰፋ ያለ ፈሳሹን ማውረጃ አንዱር (ማንቆርቆሪያ ) የሚባል አካል ያለው የቤት ቁስ፡፡

የጀበና ማስቀመጫ ፡- ከጭቃ የሚሰራ ጀበናውን ደግፎ የሚይዝ ክብ እቃ፡፡

እጣን ማጤሻ፡- ከሸክላ የተሰራ ዕጣን፣ጥሩ ሽታ ያለው ጢስ የተባለ የዛፍ እንጨት፣ ጥንጁት የሚጤስበት የቤት ዕቃ፡፡

## የእንጀራ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ቁሶች

ዘገኞች፣ በምግብነት የሚታወቀው ዋናው ምግባቸው እንጀራ ነው፡፡ እንጀራን ከጤፍና ከዳጉሳ ያዘጋጃሉ፡፡ነገርግን ሰላጤዋ እህል አምራች ባለመሆኗ እነዚህ እህሎቹ በግገር የሚገኙ ናቸው፡፡ቀጥሎ ከእነዚህ እህሎች የሚዘጋጀውን እንጀራ ለማዘጋጃና ለማቅረቢያ የሚሆኑ ባህላዊ የቤት ቁሶች ቀርበዋል፡-

ገበታ፡- ከላይ ሰፊ ከታች ጠባብ የሆነ ከዋንዛ፣ ከዋርካና ከኮሶ እንጨት የሚሰራ ለሊጥ ማቡኪያ የሚያገለግል ቁስ፡፡ገበታ ከመጠኑ አንጻር በሶስት ሊከፈል የሚችል ሲሆን ትልቁ እስከ ሃምሳ ኪሎ፣መካከለኛው እስከ 25 ኪሎና ትንሹ ደግሞ ከዚያ በታች ይይዛል፡፡ ብዙ ጊዜ ትንሹ ገበታ ለእግር መታጠቢያ ያገለግላል፡፡

ቡሃቃ፡- ከቅል የተሰራ ለእንጀራ የተቦካው ሊጥ ቦክቶ ለመጋገር እስኪደርስ ድረስ የሚቀመጥበት ከቅል የተሰራ የቤት ቁስ፡፡

መቅቢያ ቅል፡- ከቅል የተሰራ ሆዱ ሰፋ ብሎ አንገቱ እንደ ብርሌ አንገት ጠበብ ብሎ የወጣ፣ ከሆዱ ላይ ለሊጥ መቅጃ እንዲሆን ቀዳዳ የተበጀለት ሊጡን ምጣዱ ላይ በማዞር እንጀራ ለመጋገር የሚያገለግል ቁስ፡፡

ምጣድ፡- ከሸክላ የተሰራ፣ ክብ የሆነ፣ ለእንጀራና ዳቦ መጋገሪያ የሚያገለግል ቁስ፡፡

ሙግድ፡- ከቀርከሃ ( ሸንበቆ) እንዲሁም በጭድ የተቦካ ጭቃ የሚሰራ የምጣድ መከደኛ መጠኑ በምጣዱ የሚወሰን ነው፡፡

ሞሰብ፡- ሰበዝና ግራምጣ ከተባሉ የሳር ዘሮች የተሰራ ከወደ ላይ ቀነፍ ብሎ የወጣና ወደ ታች እየሰፋ የሚወርድ የእንጀራ ማሳቀመጫ ስፌት፡፡

ሞሰብ እፊያ፡- ሰበዝና ግራምጣ ከተባሉ የሳር ዘሮች የተሰራ የሞሰብ ክዳን፡

መሳቢያ፡- ከሰበዝና ግራምጣ የተሰራ ትኩስ እንጀራ ከምጣድ ለማውጣት የሚያገለግል ዝርግና ክብ ስፌት፡፡

## የወጥ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ዕቃዎች

መክተፊያ፡- ከጥርብ እንጨት የተዘጋጀ ስጋ፣ ሽንኩርት፣ድንች የሚከተፍበት ጣውላ

ካራ:- እጀታው በእንጨት ሌላው አካሉ ከብረት የተሰራ በአንድ ወገን ስለት በአንድ ወገን ደነዝ ወይም በሁለቱ ወገን ስለት ያለው የቤት ቁስ::

ሞረድ:- ካራ ስለት እንዲያወጣ የሚሞረድበት ስለት የሌለው ካራ መሰል ቁስ::

ማንካ:- ጠቀን ካለ እንጨት (ብዙጊዜ ዋንዛ) ተጠርቦ የሚሰራ ርዝመቱ ከ40 ውፍረቱ ከ 5 ሳ.ሜ ያልበለጠ የሚሰራው ወጥ እንዳያርር፣ እንዲሁም ወጡ ውስጥ የተጨመሩ ቅመሞች ለምሳሌ ሽሮ፣በርበሬ፣ዘይት፣ሽንኩርት እንዲቀላቀሉ የሚማሰለስበት ቁስ::

የቅቤ ቅል:- ከቅል የሚሰራ የቅቤ ማስቀመጫ::

በገፊጅ:- ከሸክላ የሚሰራ ጉንና ጉት ለመያገ የሚያገለግሉ ሁለት ጆሮዎች ያሉት ትልቅ ድስት ከትልቅነቱ የተነሳ የአንድ በግ ስጋ በአንድ ጊዜ ይሰራበታል ይባላል ስሙም አቅሙን ለመግለፅ የተሰጠው ነው::

ወጪት:- ከሸክላ የተሰራ ለአሳ ወጥ መሰሪያ ብቻ የሚያገለግል ዝርግ ቁስ::

ድስት:- ከሸክላ ዙሪያው ጉድጉድ ብሎና ክብ ሆኖ የሚሰራ፣ ወጥ ለመስራት የሚያገለግል ቁስ ::

የድስት እፊያ:- ድስቱን ለመክደን የሚያገለግል የሸክላ ቁስ

ወስከንቢያ:- ግራምጣና ስበዝ ከተባሉ የሳር ዘሮች የሚሰራ የድስት እፊያ

## የጠላ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ዕቃዎች

ዋንጫ: ከበሬ ወይም ከላም ቀንድ የሚሰራ ከታች ጠበብ ብሎ ከላይ ሰፋ ያለ ለጠላ መጠጫ የሚያገለግል ብርጭቆ ወይም ጣሳ የመሰለ ቁስ ::

የአውራሪስ ዋንጫ:- ከላም ወይም ከበሬ ቀንድ የሚሰራ ለጠላ ፣ለጠጅ መጠጫ የሚያገለግል ትልቅ ዋንጫ አንድ ዋንጫ 2 ሊትር ይይዛል::

ጋን:- ከሸክላ የሚሰራ አንገቱ ጠበብ ያለ ከወደ ሆዱ ሰፊ የሆነና ለመያገ የሚያገለግሉ ሁለት ጆሮዎች ያሉት አራትና አምስት እንስራ ውሃ በአንድ ጊዜ ለመያዝ የሚችል ለጠላ መደፍደፊያና ለጠላ ማስቀመጫ የሚያገለግል የቤት ዕቃ::

ማዲጋ:- ከጋን አነስ ያለ ለጠላ መጥመቂያ ለውሃ መቅጃና ማስቀመጫ የሚያገለግል ቁስ

ትዝቢ:- ከጋን አነስ ያለ ከማዲጋ የሚበልጥ ቅርፁ እንደ ጋንና ማዲጋ ከአንገቱ ጠበብ ከሆዱ ደግሞ ሰፋ ያለ በድግስ ጊዜ ለጠላ ማቅረቢያ የሚገለግል የሸክላ ዕቃ::

ሽንክላ:- ከማዲጋ አነስ ያለ ለውሃ መቅጃ የሚያገለግል የሸክላ ዕቃ::

ቶፋ:- ለትንንሽ ሴት ልጆች ውሃ መቅጃ፣ ለጥራጥሬ (ንፍሮ) መቀቀያ የሚያገለግል ከሽንክላ የሚያንስ የሸክላ ዕቃ::

ገንቦ:- እንደ ብርሌ አንገቱ ረጅምና ጠባብ ፣ሆዱ ሰፊ፣ አንድ ጆሮ ብቻ ያለው ጠላ የሚቀርብበት እንዲሁም ወደ ሰው ቤት የሚሄድበት የሸክላ ቁስ።

የእንጨት በርሜል:- ስጠላ መበጥበጫና ማስቀመጫ የሚያገለግል ከእንጨት የተሰራ ትልቅ ቁስ።

ገንዳ:- ጎኑ ከተቦረቦረ አግድም እንጨት የሚሰራ ስጠላ መበጥበጪያ የሚያገለግል የእንጨት ቁስ ይህ ቁስ በሌሎች አካባቢዎች የከብቶች ውሃ መጠጫ ሆኖ ያገለግላል።

## የአረቄ ማውጫና መጠጫ ዕቃዎች

የአረቄ ማዲጋ:- ከሸክላ የተሰራ በመጠን፣ በቅርፅና በአሰራር ከሌሎች ማዲጋዎች (እንስራዎች)

የማይለይ ነገር ግን አረቄ የሚጣድበት ስለሆነ ብቻ የአረቄ ማዲጋ የሚል ስም ያገኘ የሸክላ ቁስ ነው።

ጎራሽ:- ትልቅ ድስት የመሰለ ቅርጽ ያለው በአረቄ ማውጣት ስራ የተጣራውን አረቄ የሚይዘው ኮዳ የሚቀመጥበት ከሸክላ የተሰራ ዕቃ። ጎራሽ የሚለው ስሙ ኮዳውን ስለሚጎርስ የተሰጠው ነው።

መሳቢያ:- የአረቄው ማዲጋ የአረቄ ድፍድፍ ተደርጎበት ሲጣድ ከተጣደው ማዲጋ የሚወጣው እንፋሎት ከማዲጋው ተነስቶ ጎራሹ ውስጥ ከተቀመጠው ኮዳ እንዲደርስ የሚያደርግ ቁመቱ ከአንድ ሜትር የማይበልጥ ሸንበቆ።

መለኪያ (የአረቄ መለኪያ):- አረቄ እየተመጠነ የሚቀዳበት ከቀንድ የተሰራ ቁስ።

## የእህል መያዣ ዕቃዎች

ስፌድ :- ከሰበዝና ግራምጣ የሚሰፋ እህልን ለማንፈሻና ለማበጠሪያ የሚገለግል የቤት ቁስ።

ቁና :- ከሰበዝና ግራምጣ የሚሰፋ ጎድጓዳ ሳህን የሚመስል ስፌት። መጠኑ አነስተኛ፣ መካከለኛና ትልቅ ሊሆን ይችላል። ቀደም ሲል ለመገበያያ (የእህል መስፈሪያ) ያገለግል ነበር።

ወንፊት:- ከሰበዝ፣ግራምጣና ከገመድ የሚሰፋ ቅርፁ ክብ ሆኖ መሃሉ በጣም የላመ ዱቄት ወይም ፈሳሽ ብቻ እንዲሳልፍ ሆኖ የተሰራ የላመ ዱቄት ካልላመ፣ ጠላን ከገፈቱ የሚያጣራ የቤት ቁስ።

ዘንቢል፡- ከሰሌን እንዲሁም ከገመድ የሚሰራ የዕቃ መያዣ በተለይም ገበያ የሚገዙ እንደ ሽንኩርት ፣ድንች፣ ወዘተ.. የመሳሰሉ እቃዎች የሚያዙበት ቁስ፡፡

ወራንታ፡- ከሰበዝና ግራምጣ የሚሰፋ ጎድጓዳ ሰሃን የሚመስል መጠኑ ከቁና የሚበልጥ ስፌት፡

ጎታ፡- ከጭቃ የተሰራ ለጤፍ ዳጉሳ ወይም ለቡና ማስቀመጫ የሚያገለግል ጎተራ፡፡

## የወፍጮ ዕቃዎች

ወፍጮ ፡- አራት ማዕዘን፣ መሃሉ ጠፍጣፋ የሆነ፣ እህል ለማድቀቂያ፣ ለመፍጪያና ለመከኪያ
የሚያገለግል ድንጋይ

መጅ (የወፍጮ ልጅ)፡- ባንድ ወገን ከወፍጮ ጋር እንዲስማማ ተስተካክሎ የተወቀረና በወፍጮው መካከል የሚመላለስ እህል መፍጫ መከኪያ .... ድንጋይ

ቋት፡- ከወፍጮው ልሞ የሚመጣውን ዱቄት ወይም ክክ የሚቀመጥበት ከጭቃ የተሰራ ቁስ፡፡

ሙቀጫ ፡- ከወፍራም ግንድ ተጠርቦ የሚሰራ ላይኛው አካሉ ክፍትና ሰፊ የሆነ የታችኛው አካሉ ደግሞ ድፍን የሆነ እህል ጌሾ ወዘተ ለማድቀቅ የሚያገለግል ቁስ፡፡

ሙቀጫ ልጅ፡- ወፈር ያለ እንጨት ተጠርቦ ተድበልብሎ የሚሰራ በሙቀጫ ውስጥ የገባው እህል ፣ጌሾ፣ ቡና፣ወዘተ.. ተደብድቦ የሚልምበት ቁስ፡፡

## ለመኝታ የሚያገለግሉ ቁሶች

ዙፋን አልጋ፡- ከጠፍርና ከእንጨት የሚሰራ አራት ማዕዘን የሆነና አራት እግሮች ያሉት መጠኑ ትልቅ የሆነ የመኝታ ቁስ፡፡

ድንክ አልጋ፡- ከጠፍርና ከእንጨት የሚሰራ አራት ማዕዘን የሆነና አራት እግሮች ያሉት መጠኑ ትንሽ የሆነ የመኝታ ቁስ፡፡

መደብ ፡- ከድንጋይና ካፈር የሚሰራ ከመሬት ከፍ እንዲል ተደርጎ የሚሰራ መኝታ

ሳምነት ፡- የበሬ ወይም የላም ቆዳ በሚገባ ለስልሶና ከነፀጉሩ ደርቆ አልጋ ላይ ወይም መደብ ላይ ተነጥፎ ለመኝታ የሚያገለግል ቁስ፡፡

ጀንዲ፡- የበሬ ወይም የላም ቆዳ በሚገባ ለስልሶና ፀጉሩ ተነስቶ ደርቆ አልጋ ላይ ወይም መደብ ላይ ተነጥፎ ለመኝታ የሚያገለግል ቁስ፡፡ከሳምነት የሚለየው ፀጉሩ ስለሚነሳ ነው፡፡

ትራስ፡- የጀንዲ ቁራጭ በአራት ማዕዘን ቅርፅ ቀረጢት ሆኖ ተሰፍቶ ውስጡ ሳር ገብቶበት የሚሰራ ቁስ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ የቤት ቁሶችን ከሞላ ጐደል ለማሳየት ተሞክሯል። ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ዘገኞች ባህላዊ የቤት ዕቃዎቻቸው ከእንጨት፣ ከብረት፣ከጭቃ፣ከቀንድ፣ከድንጋይ ፣ከሸክላ፣ ከሳር የተሰሩ ናቸው። ለእነዚህ ዕቃዎች ደግሞ በመስራቱም ሆነ በመገልገሉ በኩል ባለቤትነቱ የጠቅላላው ማህበረሰብ ነው። በሌላ አባባል እዚህ ከተዘረዘሩት የቤት ዕቃዎች ውስጥ ከሸክላና ከብረት ከተሰሩት ውጭ ያሉት ዕቃዎች ሁሉ «እከሌ» ተብሎ የሚጠራ የተወሰነ ግለሰብ ወይም ቡድን ባለቤት ተብሎ ሲቀርብላቸው አይችልም። ማንም ሰው በቤቱ ውስጥ የቸገረውን ዕቃ ራሱ ሰርቶ ይጠቀማል እንጂ ለምሳሌ ማኛዋም ሴት ጀበናዋ ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቀመጥ ማስቀመጫውን ከጭቃ ትሰራለታለች። በቤት ውስጥ ለክረምት መውጫ የሚሆን እህል ማስቀመጫ የሚሆነውን ጐታ (ጐተራ) ራሷ ትሰራዋለች። ለእህል ማበጠሪያ ፣መንፊያና ማስቀመጫ የሚሆኗትን ሰፌድ፣ ወንፊት፣ ቁናና ወራንታ ረሷ ከሰበዝና ግራምጣ ትሰፋለች። እንዲያውም ማንኛዋም እድሜዋ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ሴት ሁሉ ይህንን እንድታደርግ የማህበረሰቡ ወግ ያስገድዳታል። ስለዚህ ዘገኞች ለባህላዊ ዕቃዎቻቸው ባለሙያነት የጋራ ድርሻ ያላቸው ናቸው እንጂ ለአንድ እቃ እከሌ የሚባል ቡድን መጥራት አይቻልም።

ከዚህ በተረፈ ደግሞ ብዙ ሰዎች ቤት ያሉ እንደ ገበታ፣ የእንጨት በርሜል፣ አልጋ፣ ዋንጫ የመሳሰሉት ቁሶች አሁን አሁን ጭራሽ የማይሰሩ ናቸው። ባለቤቶቻቸውም እነዚህን ቁሶች ከወላጆቻቸው በውርስ ያገኟቸው ናቸው። ለምሳሌ መሪጌታ ወርቁ ደበብ በቤታቸው ውስጥ ስላለ አንድ የእንጨት በርሜልና ገንዳ ሲገልፁልኝ እነዚህ ዕቃዎች ሁሉም የጥንቶች ናቸው ዛሬ የእንጨት በርሜል ፣ዙፋን አልጋ፣ ገበታ፣ ዋንጫ የሚሰራ የለም። ያለው እንዳይጠፋ መጠበቅ ብቻ ነው ብለውኛል። ከዚህ በተረፈም በሌሎች ቤቶች ሁሉ የሚገኙ ቁሶች ብዙዎች ዛሬ የማይሰሩና የጥንት ናቸው። ለዚህም ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው «የዘጌ አባት» በሚባሉት በአቡነ በትረ ማርያምና በእግዚአብሔር መካከል ያለው «የሰላጤዋ ሃብት ለልጅ ልጅ እየተላለፈ ለዘላለም ይኑር።» የሚለው ቃል ኪዳን ነው። ይህ ቃል ኪዳን በሰላጤዋ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ በጥብቅ የሚታመንበት መሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖር ቤተሰቦች መካከል የእቃ ቅብብሎሽ (ውርስ) እንጂ የሙያ ተስተላለፎ እንዳይኖር ያደረገ ይመስላል። ነዋሪዎችም የሚገልፁት ይህንን ነው። ለምሳሌ መርጌታ ወርቁ ደበብና ወ/ሮ ሰገነት አሸተ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልፁ የዘጌ ሰው፣ የዘጌ ንብረቶች፡- መሬቱ፣አትክልቱ፣ቤቶችና የቤት ዕቃዎች ሁሉ አንድ ጊዜ በአቡነ በትረ ማርያም የተባረኩ ስለሆነ ሰው ሁሉ ጥበበኛ ነው። የራሱን ንብረት ይሰራል፣ ሰሪ አያስፈልገውም

ሃብቱም እስከ ዘላለም ተጠብቆ ይኖራል እንጂ አይጠፋም:: ሁላችንም በቤቶቻችን ያሉ ዕቃዎች ዘመን ካመጣቸው በስተቀር ከአባቶቻችን የወረስናቸው ናቸው:: እኛ ደግሞ በተራችን ለልጆቻችን እናወርሳለን ብለዋል::

በአጠቃላይ በሰላጤው ውስጥ ከሚገኙ ባህላዊ የቤት ቁሶች ውስጥ እነዚህ አብዛኞች ሲሆኑ (ከሸክላ የተሰሩት ብዙ መሆናቸውን ማጤን ይገባል) እነዚህ ቁሶች ደግሞ እከሌ የተባለ ሰሪ የሌላቸው እንዲሁም ብዙዎቹ በነበር የሚታወሱ ናቸው:: ለምሳሌ የቡና መደቆሻ አይገዛም እንዲሁም አይሰራም:: በፊት ከጣና ሃይቅ አጠገብ ከሚገኙ ድንጋዮች የተመቸውን በማምጣት አገልግሎት ላይ ይውላል:: ዛሬ ግን ይኸ የለም::ነገር ግን ከዚህ ወጣ ብለን የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ወደ ሆኑት የሸክላ ቁሶች ስንመጣ ፣ የሸክላ ቁሶች ለቤት ውስጥ ተግባር ሰፊ ግልጋሎት ከማበርከታቸው ሌላ ከጥንት ጀምረው እስካሁን ድረስ በሰላጤው ውስጥ የሚሰሩ ሲሆን እነዚህ ዕቃዎች ከሌሎች ቁሶች በተለየ «እከሌ» የሚባል ሰሪ ያላቸው ናቸው:: አሰራራቸውንና በዘመናት መካከል ያለውን ታሪካቸውንም ማጥናት ይቻላል:: ስለዚህም ከባህላዊ የቤት ቁሶች አንፃር የዚህ ጥናት ከፊል ትኩረት እነሱ ናቸውና ቀጥሎ በጥልቀት ይቀርባሉ::

## 6.1. የሸክላ ቁሳቁስ ዓይነቶችና ተግባራቸው

በፎክሎር የጥናት መስክ በቁሳዊ ባህል ዘርፍ የዕቃዎችን ምደባ በተመለከተ የተለያዩ አመለካከቶች ያሉ ቢሆንም ቁሶችን በተግባራቸው መክፈል የሚቻል መሆኑን (Kenneth 1978 ፣Somjee 1993 ፣Glassie 1999 ) ይገልፃሉ ::

በዚህ ጥናትም በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙ የሸክላ ቁሶች በተግባራቸው ተመድበው ቀርበዋል::

በሰላጤው ውስጥ በጠቅላላው የሚገኙት የሸክላ ቁሶች ምጣድ፣ ጋን፣ማዲጋ፣ትዝቢ፣ ሸንክላ፣ ቶፋ፣ ገንቦ፣ ጎራሽ፣ በገፌጅ፣ ድስት፣ ወጨት ፣ማጤሻ፣ ምድጃ፣ናቸው:: እነዚህን ዕቃዎች ከተግባራቸው አንፃር ሳያቸው ለወጥ መስሪያ የሚሆኑ፣ ለፈሳሽ ነገር መያዣ የሚሆኑ፣ ለቡና ማፍያ የሚሆኑ፣ ለእሳት መያዣ የሚሆኑና ለእንጀራ መጋገሪያ የሚሆኑ በሚሉ ንዑሳን ክፍሎች ውስጥ ይመደባሉ:: ቀጥሎ በየምድባቸው ቀርበዋል:-

### ለወጥ መስሪያ የሚሆኑ የሸክላ ቁሶች

በገፌጅ:- ቅርፁ ክብ ሆኖ ውስጡ ጎድ ጎድ ያለ ከታች ደግሞ ጠፍጠፍ ብሎ የሚሰራ ከጎንና ከጎኑ ለመያዣ የሚያገለግሉ ሁለት ጆሮዎች ያሉት ከትልቅነቱ የተነሳ የአንድ በግ

ስጋ በአንድ ጊዜ ያስራል የሚሉት ለወጥ መስሪያ የሚያገለግል የሸክላ ቁስ ነው፡፡ ይህ ቁስ፣ በገፈጅ የተባለው በአንድ ጊዜ የአንድ በግ ስጋ ይሰራበታል ስለሚባል ሲሆን ስያሜውም በግ የሚፈጅ (የሚጨርስ) የሚል ትርጓሜ ያለውና መጠኑን ለመግለፅ የተሰጠው ነው፡፡ ቁሱ አገልግሎት የሚሰጠው በበዓላትና ሰርግ በመሳሰሉ እንግዳ በሚበዛባቸው ጊዜያት ብቻ ነው፡፡ የሸክላ ስራ ባለሙያዎች በገፈጅን እንዲሰሩ ሲጠየቁ (በትዕዛዝ) ብቻ ይሰሩታል እንጂ እንደሌሎች ዕቃዎች በማንኛውም ጊዜ ሰርተው ገበያ ይዘውት አይወጡም እንዲያውም እንደ መረጃ ሰጪዎች ገለፃ በገፈጅ ብዙ ጊዜ የሚሰራው በዓላት በደረሱ ጊዜ ነው፡፡ የአንድ በገፈጅ አማካይ ዋጋ ስድስት ብር ነው፡፡ በገፈጅ በበዓላትና ለሰርግ የሚያገለግል በመሆኑ፣ መጠኑ ትልቅ በመሆኑና ዋጋውም ትንሽ ስላልሆነ የሚገዙት ለድግስ ገንዘብ ማውጣት የሚችሉ የተሻለ ኑሮ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡

ድስት ፡- ጠቅላላ ቅርፁ በገፈጅ የተባለውን የሸክላ ቁስ የሚመስል ሲሆን ከታች ጠፍጣፋ ሆኖ ጎንና ጎኑ ዙሪያውን እንደ ግድግዳ ቀጥ ብሎ የቆመ ጎድጓዳ የሸክላ ቁስ ነው፡፡ ድስት፤ ትልቅ፣ መካከለኛ፣ ትንሽ የሚባል መጠን አለው፡፡ ትልቁ ድስት «አንድ ዶሮ አገላብጦ የሚሰራ» መጠን ሲኖረው አማካኝ ዋጋው 4 ብር ነው፣ መካከለኛ ድስት ከ10-12 የሚደርስ ቁጥር ላለው ቤተሰብ ወጥ ይሰራበታል፡፡ ዋጋው 3 ብር ነው፡፡ ትንሽ ድስት ደግሞ ደግሞ ለባልና ሚስት (ለ2) ሰው የሚሆን ወጥ ይሰራበታል፡፡ ዋጋውም 2 ብር ከ50 ሣንቲም ነው፡፡ ዛሬ ዛሬ ምንም እንኳን የሸክላ ድስት ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባፈራው የብረት ድስት እየተተካ ቢሆንም የሸክላ ድስት ከእሳቱ ከወጣ በኋላ እንኳን ቶሎ የማይበርድ በመሆኑ በድስት የተሰራ ወጥ ከልቡ ስለሚበስል ይጣፍጣል ስለሚባል መጠኑ ይለያይ እንጂ በሁሉም ሰው ቤት የሸክላ ድስት አለ፡፡




ሥዕል5፡- ድስትና በገፈጅ

ወጪት ፡- እንደ ብረት ምጣድ የተዘረጋና በትንሹ ብቻ ወደ ላይ ሰብሰብ ያለ የሸክላ ዕቃ ነው። ይህ የሸክላ ቁስ የልስላሴው መጠን ከሌሎች በሰላጤው ውስጥ ከሚገኙ የሸክላ ዕቃዎች የተለየ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ዕቃው በሰላጤው ውስጥ የሚሰራ ባለመሆኑ የሚሰራበት አፈር በሰላጤው ውስጥ ካለው የሸክላ አፈር የተለየ ስለሆነ እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ዘገኞች ይህንን ቁስ ደቅ ከተባለ የሰላጤዋ ጎረቤት ከሆነ ቦታ ያስመጡታል። ወጪት ወደሰላጤዋ መቼ እንደገባ የሚታወቅ ነገር የለም። ነገር ግን ከአብዛኛው ሰው ቤት ውስጥ አለ። ምክንያቱም ዘገኞች ጣና ሐይቅ አጠገብ የሚኖሩ በመሆናቸው አሳ ወጥ ተዘውታሪ ምግባቸው ነው። በሰላጤው ደንብ መሰረት ደግሞ አሳ ወጥ የሚሰራው በወጭት ብቻ ነው። እንዲያውም ብዙ እማወራዎች እንደሚናገሩት በየቤታቸው ያሉት ወጪቶች ከሃያ አመት በላይ የሆናቸውና ከወላጆቻቸው በስጦታ ያገኟቸው እንደሆነ ነው። ይህ ለምን እንደሆነ ሲገልፁ አሳ ወጥ እንደሌሎች ወጦች በየትኛውም የድስቱ አቅጣጫ እየተደባለቀ የሚማሰል ከሆነ ቦክቶ መልኩን ያጣል በዝርግ ድስት ከተሰራ ግን መልኩን እንደጠበቀ ሰርቶ ማውጣት ይቻላል። ስለዚህ የግድ በወጭት መስራት አለበት። ይህንን እናቶቻችን አቆይተውናል እኛም እያደረግነው ነው ይላሉ።

እንደ ቃል መረጃ አቀባዮች ገለፃ ምንም እንኳን ወጪት ዘጌ ውስጥ የማይሰራ ቁስ ቢሆን ከሚሰራበት ደቅ ከተባለው አካባቢ ይልቅ ብዙ ግልጋሎት የሚሰጥ ለዘገኞች ነው። በአካባቢው ከሚገኙት ገጠሮች ሁሉ በወጭት የመገልገል ባህል በዘገኞች ይዘወተራል። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም በለያዩ የአገራችን አካባቢዎች፡-

«ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ
አሁን ምን ያደርጋል <u>ድስት</u> ጥዶ ማልቀስ» የሚባለውን ቃል ግጥም ዘገኞች፡-

«ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ፣
አሁን ምን ያረጋል <u>ወጪት</u> ጥዶ ማልቀስ» ሲሉ የሚገጥሙት

ሁለቱም ቃል ግጥሞች ነገር ሳይሆን እንጂ አንድ ጊዜ ለሆነ ነገር መጨነቅ እንደማይገባ የሚገልፁ ቢሆንም የላይኛው ቃል ግጥም ሆነ የሚለውን ነገር «ድስት ጥዶ ማልቀስ» ብሎ ሲገልፀው ሁለተኛውንና የዘገኞች ግጥም ደግሞ «ወጪት ጥዶ ማልቀስ» ይላል።በአጠቃሳይ ቃል ግጥሙ (ሁለተኛው) ወጪት ከዘገኞች ጋር ያለውን ባህል የመግለፅ አቅም ያለው ነው።




ሥዕል6 ፡ ወጭትና ክዳኑ

## ለፈሳሽ ነገር መያዣ የሚሆኑ የሸክላ ቁሶች

ጋን፡- ጋን አንገት፣ ደረት፣ ሆድ፣ ቂጥ፣ ጆሮ የሚባሉ ክፍሎች ያሉት ከታች ጠባብ ከሆዱ ሰፋ ከአንገቱ ጠበብ ያለ ቅርፅ ያለው፣ ለመያዣ የሚያገለግሉ ሁለት ጆሮዎች ከጐንና ጐን ያሉት ትልቅ የሸክላ ቁስ ነው፡፡ ይህ ቁስ ለውሃ ማጠራቀሚያ (ማስቀመጫ)፣ ለጠላ መሾሚያ፣ (በድግስና በበዓል ወቅት ብዙ ተጋባዥ ሲኖር ጠላ ማቅረቢያ)፣ ከተሰነጠቀ በኋላ ደግሞ ሊፈስሱ ለማይችሉ እንደ ዱቄትና ጥራጥሬ ላሉ ነገሮች ማስቀመጫ ያገለግላል፡፡ አንድ ጋን ዋጋው 20 ብር ነው፡፡ ይህም የሆነው ዕቃው መጠኑ ትልቅ ስለሆነ ሲሰራ የሚፈጀው ጭቃ፣ ለማቃጠል የሚወስደው ጊዜ፣ ለማቃጠል የሚፈጀው እንጨት ብዙ ስለሆነ በተለይ ደግሞ ሰራዎች ጋንን በሚሰሩበት ጊዜ የሚያጠፉት ጊዜ የሚያጠፉት ጉልበት ብዙ ስለሆነ ነው፡፡ ወ/ሮ አንጓች አንባዬ የተባሉ የሸክላ ስሪ ባለሙያ እንደገለፁልኝ ሸክላ ሰሪዎች ጋን ሲሰሩ በየአቅጣጫው ዙሪያውን እየተሸከረከሩ ስለሆነ ያደክማል፣ እቃው ሲደርቅም ቀን ማውጣት ማታ ማስገባቱ አድካሚ ነው፡፡ በመሆኑ ሸክላ ሰሪዎችጋን መስራትን ብዙ አይወዱትም «ሰሪልኝ» ተብለው ከታዘዙ ብቻ የሚሰሩት የሸክላ ቁስ ነው፡፡ ተጠቃሚዎችም ቢሆኑ ጋን ዋጋው ብዙ ስለሆነ እንዲሁም ከገዙ በኋላ ተሸክሞ ወደቤት መውሰድ ስለሚከብድ አንድ ጊዜ የገዙትን ጋን ወይም ከቤተሰቦቻቸው የተሰጣቸውን ጋን እንዳይሰበር ከሌሎች የሸክላ እቃዎች በተለየ ጥንቃቄ ይይዙታል፡፡

ጋን የኑሮ ደረጃን ይገልፃል:: ብዙ ጊዜ ከዋጋውም አንፃር ይሁን ከተግባሩ የተነሳ በቤታቸው ውስጥ ጋን ያላቸው ሰዎች ማህበረሰቡ «ሃብታም» የሚላቸው ናቸው:: አንድ ጋን አማካኝ ዋጋው 20 ብር ነው:: ተግባሩ ደግሞ ጠላ መደፍደፊያ ጠላ መበጥበጫና ጠላ መሸሚያ ነው:: ታዲያ የጋን መጠን ትልቅ እንደመሆኑ (መጠኑ በኋላ ይገለፃል) በጋን ሙሉ ድፍድፍ ሊደፈድፉና ጠላ ሊያቀርቡ የሚችሉ ጥሩ አቅም ያላቸው ሰዎች ናቸው:: እንዲሁም በሰርግና በተዝካር «ይህን ያህል ጋን ጠላ ሾመ /አቀረበ» መባል የደረጃ መገለጫ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ጋን ትልቅነትን ይገልፃል:: ለምሳሌ ዘገኞች «ጋኖች አለቁና ቶፋዎች ጋን ሆኑ» ሲሉ ይተርታሉ:: ቶፋ ለፈሳሽ ነገር መያዣ በሚለው በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኝ መጠኑ ትንሽ የሸክላ እቃ ነው:: በሁለቱ እቃዎች መካከል ወደኋላ የሚገለፁ ትዝቢ፣ማዲጋና ሽንክላ የሚባሉ ሶስት የሸክላ እቃዎች አሉ:: ታዲያ ስነ ቃሉ እንደሚለው ጋን ተሰብሮም ይሁን በሌላ ምክንያት (ምክንያቱን ስነ ቃሉ አይገልፅም) በሌለ ጊዜ ከሁሉም ትንሽ የሆነው ቶፋ እንደ ጋን ተቆጠረ:: ከተለያዩ ሰዎች ምን ማለት ነው ብዬ ለመረዳት እንደሞከርኩት «ጋን» የትልቅ ሰው ፣ ቶፋ ደግሞ ደረጃቸው ትንሽ የሆነ ሰዎች ምሳሌ ነው:: ታዲያ ብዙጊዜ ይህንን ስነ ቃል በሰላጤዋ ውስጥ በ1967 ዓ.ም ከተደረገ የመሬት ሽግሽግ ጋር ተያይዞ ይተረታል:: በዚህ ጊዜ ቀደም ሲል «ባላባቶች» ተብለው ብዙ መሬት የነበራቸውና ዘራቸው ተንቆና መጤ ተብለው ያለመሬት የነበሩ ሰዎች እኩል የመሬት ባለቤት ሆነዋል:: በዚህ ጊዜ ግን ባላባት ይባሉ የነበሩ ሰዎች ሁኔታውን አምነው መቀበል ስላልቻሉ «ሞራላቸው ተነክቶ» ራሳቸውን ዝቅ ሲያደርጉ ትንሽ የተባሉ ሰዎች ደግሞ ቀና ብለው መሄድ በአደባባይ መናገር ሲጀምሩና በየስፍራው ሲታዩ «ትልቆች» «ስለሌሉ» ትንሾች ራሳቸውን እንደ ትልቅ ቆጠሩ ለማለት ተረቱን ይጠቀሙበታል:: ከዚህ በተጨማሪ ግን ዘገኞች የትልልቆች ቦታ በትንንሾች መተካቱን መግለፅ በሚያስፈልግባቸው በተለያዩ አውዶች ተረቱን ይገለገሉበታል::

ማዲጋ:- እንደጋን አንገት ፣ደረት፣ ሆድ፣ የሚባሉ ክፍሎች ያሉት ከታች ጠባብ ከሆዱ ሰፋ፣ ከአንገቱ ደግሞ ጠበብ ያለ ቅርፅ ያለው ለመያዥያ የሚያገለግሉ ሁለት ጆሮዎች ከጐንና ጐን ያሉት የሸክላ ቁስ ነው:: ማዲጋ ከጋን ያነሰ ለውሃ መቅጃ፣ ለአረቄ ማውጫ ለጥሬ ቡና መለኪያ፣ ከተሰነጠቀ ደግሞ ለጥራጥሬና ለዱቄት ማስቀመጫ ያገለግላል:: አንድ ማዲጋ ዋጋው 10 ብር ነው::

ትዝቢ :- ይህ የሸክላ ዕቃ በጠቅላላ ቅርፁ ማዲጋ ይመስላል:: ነገር ግን እንደማዲጋ ሁለት ሳይሆን ሶስት ጆሮ ያለው ነው:: ትዝቢ ዋና ተግባሩ በድግስና በአመት በዓል ጊዜ ጠላ ማቅረቢያ ነው:: መጠኑ ከማዲጋ በሶስት እጥፍ የሚበልጥ ሲሆን ከጋን በትንሹ

ያንሳል፡፡ ነገር ግን አሰራሩ ከቁመቱ አጠር ከወርዱ ሰፋ ያለ ስለሆነ ለአይን ሲታይ ይህንን ያህል ትልቅ አይመስልም በዚህ የተነሳም ነው«ትዝቢ» የሚባል ስም የተሰጠው፡፡ አቶ ዋሴ እንየው እንደገለፁልኝ ትዝቢ ማለት የማይመስልበት ግን የሆነ ማለት ነው፡፡

ትዝቢ እንደሌሎች የማዲጋ ዘሮች መሬት ላይ አይቀመጥም «ተጋፍቼ» የተባለ ከእንጨት የተሰራ የሙቀጫ ቅርፅ ያለው መቁመጫ አለው፡፡ ሁልጊዜ በተለይም ትዝቢው ጠላ ሲይዝ በተጋፍቼው ላይ ጉባ (የቡና ፍሬ ሽፋን) ይደረግበትና ከጉባው ላይ ትዝቢው ዘንበል ብሎ ይቀመጣል፡፡ ይህም ጉባው የማንሸራተት ባህርይ አለውና ትዝቢውን በቀላሉ ከፍና ዝቅ እያደረጉ ለመቅዳት ያስችላል፡፡ የትዝቢው ማስቀመጫም እንደ ትዝቢው ሁሉ ስሙን ያገኘው ከተግባሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀጂው ጠላውን ለመቅዳት ትዝቢውን ከፍና ዝቅ ሲያደርግ ከእንስራው ጋር ይገፋፋል፡፡



ሥዕል7 :ትዝቢ በተጋፍቼ ላይ ተቀምጦ

ዛሬ ትዝቢ በሰላጤዋ ውስጥ አይሰራም፡፡ከወላጆቻቸው በውርስ ካገኙ አንዳንድ ሰዎች ቤት ብቻ ይገኛል፡፡ ስለዚህም «ነበር» የሚባል ዕቃ ከሆነ የዋለ ያደረ መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይጠቁማሉ፡፡

ሸንክላ ፡- ጠቅላላ ቅርፁ ማዲጋ ይመስላል፡፡ ከማዲጋ የሚለየው በመጠኑ ነው፡፡ ማዲጋ ቁመቱ 50 ሳ.ሜ ሲሆን ሸንክላ 43 ሳ.ሜ ያህል ነው፡፡ ሸንክላ ለውሃ መቅጃ፣ለሰንበቴና ለሰንበታ ሰንበቴ ድግስ የሚሆን ጠላ ወደ ቤተክርስቲያን መውሰጃ ያገለግላል፡፡ አንድ ሸንክላ አማካይ ዋጋው 8 ብር ነው፡፡ ሸንክላ መጠኑ «ትንሽ» በመሆኑ «ሃብታም» ሆነ «ደሃ» በተባሉ ሰዎች ቤት ውስጥ ይገኛል፡፡


ቶፋ፡- ቅርፁ እንደጋን እንደማዲጋ ወይም ሸንክላ ይመስላል፡፡ አንገት፣ደረት፣ሆድ ቂጥ የሚባል ክፍል አለው፡፡ ለመያዣ የሚያገለግሉ ሁለት ጆሮዎች አሉት፡፡ ለትንንሽ ልጆች

ውሃ መቅጃ ለንፍሮና ለስጋ መቀቀያ ያገለግላል:: ቶፋ በመጠኑ ከሁሉም የፈሳሽ ነገር መያዣ ከሆኑት የሸክላ ዕቃዎች ያንሳል:: የአንድ ቶፋ ዋጋ እስከ 3 ብር ይደርሳል:: ቶፋ በተለይም በሚያዚያ ወር የመጨረሻዎቹ ቀናት ዋጋው ወዳድ ይላል:: ይህም ለግንቦት ልደታ የንፍሮ መቀቀያ ሲባል እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ::



ሥዕል 8:- የማዲጋ ዘሮች

ገንቦ:- ሆድ፣ቂጥ የሚባሉ ክፍሎች ያሉት ልክ እንደማዲጋ (እንስራ) ከታች ድፍን ሆኖ ወደ ሆዱ አካባቢ  እየሰፋ የሚመጣ አንገቱ ረጅምና ከአንገቱና ከሆዱ ላይ ተያይዞ የተሰራ ለመያዣ የሚሆን አንዱ ጆሮ ያለው የሸክላ ቁስ ነው:: ገንቦ ከቤት ውስጥ ለአጭር ጊዜ ጠላ ማስቀመጫ፣ «የተከበረ ሰው» ወደ ቤት በመጣ ጊዜ ለጠላ ማቅረቢያ፣ አብሮ መኖር በመስረታቸው እንደየወለደችን መጠየቅ፣ አዲስ ቤት የሰራን እንኳን ደስ ያለህና በመሳሰሉ ማህበራዊ ግንኙነቶች ወደ ሰው ቤት ጠላ መውሰጃ ሆኖ ያገለግላል:: ገንቦዎች ከሰው ፊት የሚቀርቡና ወደ ሰው ቤት የሚሄዱ የስነስርአት (ceremonial) ዕቃዎች በመሆናቸው ብዙ ጊዜ ሲሰሩ ላያቸው ላይ ጌጥ ይደረግባቸዋል:: ጌጦችም በሚሰሩበት ጊዜ ከመድረቃቸው በፊት ላያቸው ላይ የሚሰመሩ መስመሮችና የሚወጡ ቅርፆች ናቸው::



ሥዕል 9:- ገንቦ

እስካሁን ከላይ የተዘረዘሩት ከሸክላ የተሰሩ የፈሳሽ ነገር መያዣ ቁሶች ውሃ ሲመጣባቸውም ሆነ ጠላ ሲወሰድባቸው በጀርባ ይታዘላሉ:: ገንቦዎች ግን ከተቀመጠበት ቦታ (በሴት ቤት ወይም በዕቃ ቤት) ወይም ወደሚፈለግበት ቦታ ሲወሰዱም ሆነ ከቤት ወደሌላ ሰው ቤት ጠላ ሲወሰድባቸው ተሚቅለው (በጉን ተይዘው) ነው::

ዘገኞች ወደ ሰው ቤት ጠላ በሚወስዱባቸው ገንቦዎች ጠላው ለሚወሰድበት ቤት ያላቸውን ቅርበትና ስሜት ይገልፃሉ :: ወደሚያከብሩት፣ ወደሚወዱት ሰው ቤት ሲሄዱ ጠላ የሚወስዱባቸው ገንቦዎች ከማንኛውም ቤት የሚወስዱባቸው አይነቶች አይደሉም:: ጌጣቸውና መጠናቸው (ትልቅ ነው) ከሌሎች ይለያል:: ገንቦ ለስአት መለኪያም ያገለግላል:: ሰዎች ለግብዣ ቤታቸው የሚጠሩትን ሠው የገንቦ ጠላ እንጠጣ ካሉት ተሎ ና /እንዳትቆይ/ ማለታቸው ነው:: የአንድ ገንቦ አማካይ ዋጋ አምስት ብር ነው::

ጎራሽ:- ከወገብ በታች የግሚ እንስራ ቅርህ ያለው ለመያዣ የሚያገለግሉ ሁለት ጆሮዎች ያሉት አረቄ በሚወጣበት ጊዜ ከአረቄ ማዲጋው» እየተነነ በሸንበቆው አልፎ ወደ ኮዳው የሚደርሰው እንፋሎት ወደ አረቄነት እንዲቀየር ኮዳው ቀዝቃዛ መሆን ስላለበት ኮዳውን የሚያ.ቀዘቅዝ ውሃ ተሞልቶ የሚቀመጥበትና ኮዳ የሚቀመጥበት የሸክላ ዕቃ ነው:: የአንድ ጉራሽ ዋጋ ከ5-6 ብር ድረስ ነው:: ነገር ግን አረቄ የሚያወጡ ሰዎች ሁልጊዜ ጉራሽ መግዛት ላይጠበቅባቸው ይችላል::: የውሃ እንስራቸው ሲሰበር አሰባበሩ ወደታች ያለውን ክፍል ያልጐዳው ከሆነ ቅርፁን ቢላዋ አስተካክለው ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: ይህም በመሆኑ ሸክላ ሰሪዎች ከታዘዙ ብቻ ጉራሽ ይሰራሉ እንጂ በማንኛውም ጊዜ ሰርተው ገበያ አያወጡም::




*ሥዕል 10: ወ/ሮ አንጓች በጎራሽ ስራ ላይ*

ጉራሽ የደሃ ሴቶች ሃብት ነው:: ምክንያቱም አልፎ አልፎ ለበዓል ሲሉ በቤታቸው ውስጥ አረቄ ከሚያዘጋጁ ሰዎች በስተቀር አብካኛው (ሁሉም ሰው ማለት ይቻላል) አረቄ የሚጠቀመው ገዝቶ ነው::አረቄ ማውጣት ደግሞ በጣም አድካሚ ስራ

በመሆኑ አረቂ የሚያወጡት ሌላ አማራጭ የሌላቸው ሴቶች ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ የነዚህን ሴቶች ደረጃ ሲገልፅ «የአረቂ ማዲጋ ቂጥ ፈቅፍቃ የምታድር ደሃ» ይላል፡፡ በመሆኑም ጉራሽ «የደሃ» ሴቶች ሃብት ነው፡፡ ይህ ቁስ ስያሜውን ያገኘው ከአገልግሎቱ ነው፡፡ ይኸውም ኮዳው ጉራሹ ውስጥ ስለሚቀመጥ ኮዳው በሸክላ ዕቃው ተጉረሰ ለማለት ነው፡፡ ጉራሽ የሚቀመጠው መሬት ተቆፍሮ ነው፡፡ ይህም ሚዛኑን (Balance) ለመጠበቅ ሲባል ነው፡፡ ሆኖም በየጊዜው ቦታው ስለማይቀያየር አንድ ጊዜ ደህና ቦታ ተመርጦ ይቀመጣል፡፡ ይህ ቦታ ከአረቂ አወጣጥ ባህሪይ አንፃር ተመርጦ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ዘገኞች አረቂ ጥላና ግርግር አይወድም ይላሉ፡፡«ጥላ» ማለት የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ ሰው ወደአረቂው መጠጋት አይገባውም ማለት ነው፡፡ «ግርግር» ደግሞ ብዙ ሰው ፣ጮሆ መናገር፣ ሳቅ፣ ሁካታ ማለት ነው፡፡ አረቂ እየተወጣ ጥላና ግርግር ካጋጠመው ይበላሻል፡፡ ወደ ኮዳው መምጣት ያለበት እንፋሎቱ ሆኖ ሳለ በእንፋሎቱ ፋንታ ድፍድፉ ሊመጣ ይችላል እንዲሁም ይገነፍላል ይላሉ፡፡ ስለዚህ ይህን ለመከላከል ሲባል ጉራሽ የሰው እግር የማይበዛበት ደበቅ ያለ አካባቢ ተመርጦ መሬት ተቆፍሮለት ይቀመጣል፡፡ አንድ ጊዜ ቦታ ተመርጦለት ከተቀመጠ በኋላ ግን አስገዳጅ ነገር ካልተፈጠረ በስተቀር ከዚያ ቦታ አይነሳም ፡፡ እንዲያውም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነገር አንድ ታሪክ አለ፡፡ ሴትየዋ ለረጅም ዘመን አረቂ እያወጣች በመሸጥ ራሷንና ልጆቿን የምታስተዳድር ደሃ ነበረች፡፡ አንድ ቀን እንደልማዷ አረቂ ልታወጣ ፈልጋ ጉራሹ ወደተተከለበት ቦታ ስትቀርብ ጉራሹ ሙሉ በሙሉ በጉንዳን ተሸፍኖ አላስቀርብ ይላል፡፡ ብትጠብቅ ጉንዳኖቹ አልለቅላት ይላሉ፣ ጉንዳኖቹን ለማባረር ብላ ውሃ ብትረጭም አልሳካላት ይላል፡፡ ይህን ጊዜ አረቂውን ማውጣት ግዴታ ነውና ልጅዋን ጠርታ ሌላ ቦታ ላይ ለጉራሹ ማስቀመጫ እንዲቆፍርላት ትነግረዋለች፡፡ ይህን ጊዜ ልጁ ጉራሹ ቀድሞ ከነበረበት ቦታ ራቅ አድርጎ ሲቆፍር መሬቱ በመደደር ፈንታ መቆፈሪያው በቀላሉ ወደ መሬት ይሰርግና የሚሰበር ዕቃ ድምፅ ይሰማዋል፡፡ ይህን ጊዜ ለእናቱ ነግሮ ጉዳዩ ምን እንደሆነ ሲያጣሩ በማዲጋ (እንስራ) የተቀበረ ጠገራ ብር (ማሪያ ትሬዛ) ሆኖእንዳገኙትና ኑሮአቸው እንደተለወጠ ይነገራል፡፡ ከዚህም ሁኔታም ሴትየዋ በጉንዳኖች አማካኝነት የጉራሹን ቦታ ለመልቀቅ ስለተገደደች የተፈጠረ መሆኑን ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡

## ለቡና ማፍያ የሚያገለግሉ የሸክላ ቁሶች

ጀበና፡- ጀበና ከአንገቱ ቀጠን፣ ከሆዱ ሰፋ ያለ በአንድ በኩል ቡናውን ማንቆርቆሪያ «አንዱር»የሚባል አካል ያለው በአንዱሩ ተቃራኒ ደግሞ መያዣ የሚሆን አንድ ጆሮ ያለው ለቡና ማፍያና መቅጃ የሚያገለግል ከሸክላ የሚሰራ የቤት ቁስ ነው፡፡ ይህ ቁስ

መጠኑ እንደታዳሚው መጠን ይለያያል፡፡ ትልቅ መካከለኛ ትንሽ የሚባሉ ጀበናዎች አሉ፡፡ በመሆኑም በጣም ትልቅ ጀበና 8 ሊትር ፈሳሽ መያዝ የሚችል ሲሆን እሱም በሰርግ፣ በሃዘን በክርስትናና ለአመት በዓል በሚደረጉ ግብዣዎች ወቅት ቡና የሚፈላበት ነው፡፡ ይህ ጀበና ቡና ለማፍያ እንጂ ለመቅጃ አያገለግልም፡፡ ምክንያቱም ጀበናው መጠኑ ትልቅ በመሆኑ አንስቶ ለመቅዳት የቡና አፍይዋን አቅም ይፈትናል፡፡ ስለዚህ ቡናው በዚህ ጀበና ከተፈላ በኋላ በትንንሽ ጀበናዎች እየተቀነሰ ይቀዳል፡፡

መካከለኛ ጀበናዎች ዋጋቸው 2 ብር ነው 6 ሊትር የሚይዙ ሲሆን «የተርቲም» ቡና ይፈላባቸዋል፡፡ ተርቲም፤ ተራ፣ ስልፍ የሚል ትርጓሜ የያዘ ነው፡፡ ተርቲም በአንድ አካባቢ ያሉ ጐረቤቶች ተሰባስበው የሚያከናውኑት የቡና ማህበር ነው፡፡ የማህበሩ ስርዓት አንድ ቀን ከአንዱ ሌላው ቀን ከሌላው ቤት በየተራና በየቀኑ ቡና እየተፈላ ጐረቤቱ ተሰብስቦ ቡና የሚጠጣበት ነው፡፡ ይህ የቡና ስርዓት ብዙ ጊዜ በጠዋት ይከናወናል፡፡ ይህም በመሆኑ የቡና ጠጪዎችን (የታዳሚዎችን) ቁርስ የምትችለው ተርቲሙ የደረሳት ሴት ናት፡፡ ለቡና ቁርስ በሚል ሰበብ ግማሽ እንጀራ በሽሮ ወጥ ለሁሉም ሰው ይታደላል፡፡ በዚህ ሁኔታ በየቀኑ ቤት እየተቀያየረ ቡና ይጠጣል፡፡ ነገር ግን ተርቲም በሁሉም መንደሮች ላይኖር ይችላል፡፡ አንዳንድ መንደሮች ውስጥ በማህበር መልኩ ሳይሆን ሰዎች ባደረሳቸው ጊዜ ሁሉ ቡና አፍልተው ጐረቤቶችን ጠርተው ቡና ሊጠጡ ይችላሉ፡፡ ዳሩ ግን ተርቲም ይሁን የመጠራራት ቡና የግድ «ብዙ» ሰው ስለሚታደምባቸው ለቡና ማፍያ የሚያገለግሉ መካከለኛ መጠን ያላቸው ጀበናዎች ናቸው፡፡

ትንንሽ ጀበናዎች ዋጋቸው ከ 1.ብር እስከ 1.ብር ከ50 ሳንቲም ነው፡፡ የሚይዙት የቡና መጠን ከ1-3 ሊትር ሲሆን በእነሱ የሚገለገሉ ተርቲም የሌለባቸው፣ የቤተሰቦቻቸውና የጐረቤቶቻቸው ቁጥር አናሳ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡

ጀበናዎችን ከትልልቅና ነባር ባለሙያዎች ይልቅ ወጣቶች ይሰሯቸዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የጀበና መጠን ከአብዛኛዎቹ እቃዎች ስለሚያንስ መስራቱ ስለማይከብድ ነው ይላሉ ባለሙያዎች፡፡

በጀበናዎች የሚፈላ ቡና ከሱስነት ባሻገር የሆነ ተግባር አለው፡፡ አባወራዎች ለንግድ ስራም ይሁን ለሌላ ጉዳይ ከቤት ከመውጣታቸው በፊት ቡና «ይቋደሳሉ»፡፡ ይህ ሲሆን ገበያ ይቀናቸዋል፡፡ የሄዱበት ጉዳይ ይሳካላቸዋል፡፡ እቤት ውስጥ ሰው በታመመ ጊዜ ቡና ተፈልቶ በቡና ስርዓት «አምላክ» ይለመናል፡፡ በመሆኑም ዘገኞች ቡናን ከሱስነቱ ባሻገር ከጐረቤት ጋር ተሰባስበው ይወያዩበታል፤ እንግዳ ያስተናግዱበታል፤ ከውቃቢ ጋር መታረቂያ ነው፡፡ ስለዚህ መጠናቸው የተለያየ ይሁን እንጂ ሃብታምም ይሁን ደሃ በሁሉም ሰው ቤት ጀበናዎች አሉ፡፡




*ሥዕል11 : ጀበና*

ጀበናዎች እንደ ገንቦዎች ሁሉ የስነስርዓት (ceremonial) ቁሶች በመሆናቸው ላያቸው ላይ በተለያዩ መስመሮች የተሠሩ ጌጦች አሏቸው:: ጀበናዎች ቁሳዊ ብቻ ሳይሆን ባህላዊም ፋይዳ አላቸው:: አንድ ቤት ውስጥ ሰው ሞቶ ሬሳው ለቀብር ከቤት ሲወጣ ወዲያውኑ የቡና ጀበናዎች ይሠበራሉ:: ለዚህም ምክንያቱ ሟቹን የገደለው ርኩስ መንፈስ ተመልሶ መጥቶ ሌላ ሰው እንዳይገድል ለማስደንገጥ ነው ሲሉ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ:: ወ/ሮ እናት ትሁን ተባባል የተባሉ መረጃ ሰጪ ከሌሎች የሸክላ ዕቃዎች ይልቅ ጀበና ለምን ለዚህ ተግባር እንደተመረጠ ሲገልፁ:- ጀበና ከውቃቤ ጋር መታረቂያ የተከበረ ዕቃ ነው:: ነገር ግን ሰው በሞተ ጊዜ ይህ ክቡር ዕቃ መሰበሩን የሚያይ ርኩስ መንፈስ የሰዎች ሃዘንና ምሬት ምን ያህል ጥልቅ መሆኑን ስለሚረዳ ይደነግጣል:: ተመልሶ መጥቶ ሌላ ሰው ለመግደል አይደፍርም ብለዋል::

## ለእሳት መያዣ የሚሆኑ የሸክላ ቁሶች

(የእጣን) ማጨሻ:- ከላይ ዝርግ ሆኖ ነገር ግን ፍም እሳት ማስቀመጥ እንዲችል ጉድጉድ ያለ፣ከወገቡ እየጠበበ የሚመጣና ወደታች ደግሞ እንዲቆም እየተዘረጋና ሰፋ እያለ የሚመጣ የሸክላ ዕቃ ነው:: የእጣን ማጨሻ፣ ቡና በተፈላ ጊዜ እጣን፣ ሴት ስትወልድና ሰው ሲሞት ደግሞ ጥንጁት (ልዩ ሽታ ያለው ቅጠል) ይጨስበታል:: ይህ ቁስ መጠኑ ሊለያይ ቢችልም ብዙ ጊዜ ግን ተመሳሳይ ቁመትና ስፋት ያለው ሆኖ ይሰራል:: ተግባሩ በአብዛኛው ከቡና ማፍላት ጋር የተያያዘ በመሆኑና ቡና ደግሞ በማንኛውም ቤት በየቀኑ የሚፈላ ስለሆነ ሰሪዎች የእጣን ማጨሻ ለመስራት ጊዜም ሆነ ትዕዛዝ አይጠብቁም:: ሁልጊዜ ይሰራሉ:: ሁልጊዜ ለገበያ ያቀርባሉ:: በአመዛኙ የእጣን ማጨሻ ከሁሉም ሰው ቤት ይገኛል:: ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች የነበራቸው በመሰበሩ ወይም ለአስፈላጊነቱ ብዙም ካለመጨነቅ የተነሳ እጣንም ይሁን ጥንጁት በገል(በሸክላ ዕቃ ስባሪ) ያጨሳሉ::



*ሥዕል 12:- (የእጣን) ማጤሻ*

ምድጃ :- ከመጠኑ መተለቅና አንዳንድ ክፍሎች ከመጨመራቸው በስተቀር ማጨሻ ይመስላል:: ከማጨሻ የሚለየው ግን ወደታች እየተዘረጋ በሚመጣው ክፍሉ (በእግሩ) ላይ ለነፋስ ማስገቢያ የሚሆን ሰፊ ቀዳዳ ስላለው ነው:: በዚህ ቀዳዳ የገባው ንፋስ ደግሞ ከሰሉን እንዲያቀጣጥለው የከሰል ማስቀመጫ በሆነው በላይኛውና በዝርጉ የዕቃው ክፍል ላይ በትንንሹ የተበሱ ቀዳዳዎች አሉት:: ይህ የሸክላ ቁስ የሚያገለግለው በቤት ውስጥ ለሚሰሩ እንደ ቡና ማፍላትና በብረት ድስት ወጥ መስራት ተግባር ነው:: ነገር ግን የሰላጤው ተዘውታሪ የሆነ የምግብ አሰራር ልማድ በእንጨት ማገዶ ስለሆነ የከሰል ምድጃው ብዙ አገልግሎት የሚሰጥ አይደለም:: አመጣጡም ቢሆን እጅግ በቅርቡ ሲሆን የሚሰሩትም የተወሰኑ ሰዎች ለዚያውም «ነገር ፈጥኖ የሚገባቸው» የሚባሉ አይነት ናቸው:: የምድጃ ስራ እንዴት ወደሰላጤዋ እንደገባ የገለፁልኝ ወ/ሮ አንጓች አንባዬ(በሰላጤዋ ውስጥ ከሚኖሩ ሸክላ ሰሪዎች አንዷ ናቸው::የ50 ዓመት ወ/ሮ ሲሆኑ ከ25 ዓመት በላይ በሸክላ ስራ ተሰማርተው ኑረዋል:: አሁንም በዚሁ ሙያ ይተዳደራሉ):-

> ምድጃ መስራት የተጀመረ አሁን በቅርቡ ነው:: መጀመሪያ ዘጌ ላይ ምድጃ የሰራሁ እኔ ነኝ:: ምድጃውን መስራት ያስተማረችኝ አንዲት አዲሳባ ኑራ የመጣች ሴትዮ ናት:: ይህቺ ሴት ብዙ አመት አዲሳባ ኑራ እህቷ ጎረቤቴ ነበረችና ከእህቷ ቤት ትመጣለች :: ሸክላ ስሰራ ስታየኝ ፣ለምን ምድጃ አትሰሪም?፣ አለችኝ እንደማይሆንልኝ ነገርኳት:: ይህን ግዜ ከአጠገቤ ቁጭ ብላ እንዲህ አድርጊ እያለች እየነገረችኝ ሰርቼ ጨረስኩት:: ከዚህ በኋላ ሙያውን ለመድኩት:: እኔ ደግሞ በተራዬ ለምቀርባቸው ሰዎች አሳየኋቸው:: የሆነለትም ሆነለት ብዙውም አቃተው:: ከዚያ ወዲያ እየተሰራ ገበያ መዋል ያዘ:: ግና ብዙ ሴት አይወደውም በዚያው በእንጨቱ ነው የሚያበስል ብለዋል (1-2-2000) ::

መረጃ ሰጪዎች እንደገለፁትና በብዙ ቤቶች ተዘዋውሬ እንዳየሁት ከሸክላ የተሰራ የከሰል ምድጃ የሚጠቀሙ ሰዎች እጅግ ጥቂቶች ናቸው:: ብዙ ሰዎች በተለይም ወጣት አማወራዎች ከሰልን ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀሙ ቢሆንም ከሰል የሚያነዱት ከቆርቆሮ በተሰራ የከሰል ማንደጃ (ፌርሜሎ) ነው::



ሥዕል 13፡- (የከሰል) ምድጃ

## ለእንጀራ መጋገሪያ የሚሆን የሸክላ ቁስ

ምጣድ፡- ሙሉ ለሙሉ ዝርግና ክብ የሆነ ለእንጀራና ለዳቦ መጋገሪያ የሚያገለግል የሸክላ ቁስ ነው፡፡ ይህ ቁስ ላይኛውም ሆነ ታችኛው ክፍሉ ለስላሳ ሲሆን በንፅፅር ሲታይ ደግሞ ላይኛው ክፍሉ ከታችኛው ይልቅ በጣም ለስላሳ ነው፡፡ ይህ ክፍልም እንጀራው የሚጋገርበት ገፅ ነው፡፡ እንጀራ የዘገኞች ዋነኛ ምግብ ነው ይህም በመሆኑ ምጣድ የሌላት እማወራ የለችም ከሁሉም ሰው ቤት ምጣድ አለ፡፡ ምጣዶች ትልቅና ትንሽ መጠን አላቸው፡፡ ነገር ግን ይህ መጠናቸው የተጠቃሚዎችን ማህበራዊ ደረጃ የሚገልጽ አይደለም እንዲያውም «በትልቅ ምጣድ የተጋገረ እንጀራ ትንሹ ይበቃል፤ በሊታን አያስገመግምም» ስለሚባል ሁሉም ሰው በተቻለ መጠን ትልቅ ምጣድን ይገዛል፡፡ አልፎ አልፎ ግን ቤት ውስጥ እንጀራ የሚጋግሩ ልጆች ካሉ እነሱ እንዳይቸገሩ ሲባል መጠናቸው አነስ ያለ ምጣዶች ይገዛሉ፡፡



ሥዕል 14፡ምጣድ

ምንም እንኳን ምጣድ በሰላጤዋ ውስጥ በሁሉም ሰው ቤት የሚገኝ የሸክላ እቃ ቢሆንም በሰላጤዋ ውስጥ አይሰራም:: እንደ ወጪት ደቅ ከተባለው አካባቢ ተገዝቶ ይመጣል:: ይህም ከሚሰራበት አፈር የተነሳ እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ:: ወ/ሮ አንጓች አንባዬ ስለዚህ ሲናገሩ:-

> ምጣድን አንሰራውም ደቆች ናቸው የሚሰሩት:: የእኛ አፈርና የእነሱ አፈር ይለያያል:: እኛ የምንሰራው ዋልካ አፈር ነው:: እነሱ የሚሰሩት ደግሞ ከወንዝ የሚወጣ ደለል አፈር ነው:: የእኛው አፈር ጥቁር ነው የእነሱ ደግሞ ቀይ ነው አሰራራችንም ይለያያል:: እነሱ አፈሩን ይወስዳሉ፣ ጭቃውን ለውሰው ሲቦካላቸው ምጣዱን ይሰሩታል እኛ አፈሩን አምጥተን አቡክተን፣አድርቀን፣ እናቃጥለዋለን፣፣ ከዚያ ወቅጠን ፈጭተን ከሌላ ከቦካ ጭቃ ጋር ለውሰን እንሰራዋለን:: የኛውን አፈር ምጣድ ልሰራው ሞክሬ አልቻልኩም እንደ ደቆች ሆኖ አይለሰልስም፤ ካልለሰለሰ ደግሞ እንጀራ አያወጣም ብለዋል (2-2-2000) ::

ዘገኞች ምጣዱን የሚገዙት ከእራሳቸው ገበያ ሲሆን የሚያገኙት የደቅ ሸክላ ሰሪዎች ይዘውት ስለሚመጡ ነው:: መደበኛው የምጣዱ ዋጋ ከ15-20 ብር ሲሆን አሁን አሁን ግን እስከ 25 ብር መድረሱን መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ:: እስካሁን ከቀረበው የመረጃ ትንታኔ እንደሚታየው ከሁሉም የሸክላ ቁሶች የምጣድ ዋጋ ይበዛል:: ለዚህም ምክንያቱ ምጣድ ከሰላጤዋ ውጭ የሚመጣ ቁስ እንደመሆኑ ሰሪዎች ቁሱን ከገበያ ለማድረስ የሚያጠፉትን ጉልበት ለማካካስ ሲባል የተደረገ ይመስላል::

በአጠቃላይ በሰላጤው ውስጥ በገፎ፣ድስት፣ወጭት፣ጋን፣ማዲጋ፣ትዝቢ፣ሸንክላ፣ ቶፉ፣ ገንቦ፣ ጎራሽ፣ (የእጣን) ማጤሻ፣ የከሰል ምድጃ ፣ምጣድ የሚባሉ በጠቅላለው 14 ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ሲኖሩ እነዚህ ቁሶች ከዋናዋና ተግባራቸው አንጻር ለወጥ መስሪያ የሚሆኑ፣ ለፈሳሽ ነገር መያዣ የሚሆኑ ፣ለቡና ማፍያ የሚሆኑ፣ ለእሳት መያዣ የሚሆኑና ለእንጀራ መጋገሪያ የሚሆኑ በሚል 5 ምድብ ውስጥ ይመደባሉ:: ሆኖም ከዚህ ጥናት አመቺነት ጋር በተያያዘ እቃዎች በዋና ተግባራቸው ተመደቡ እንጂ ምናልባት ከዚህ በተለየ መልኩ እቃዎችን በተግባራቸው መመደብም ይቻላል:: ምክንያቱም ብዙዎች የሸክላ ቁሶች በተለይም ለፈሳሽ ነገር መያዣ የሚሆኑት የሸክላ ዕቃዎች ከአንድ በላይ ተግባር ያላቸው ናቸው:: እንዲያውም ቁሶች ተሰርተው ለአገልግሎት በቀረቡበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ተሰብረው እንኳን ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎት ውጭ አይሆኑም:: ለምሳሌ የማዲጋ (እንስራ) ዘሮች ቢሰነጠቁ አይጣሉም:: በስንጥቁ ሊፈሱ የማይችሉ ጥራጥሬ ነገሮች ማስቀመጫ ይሆናሉ:: ከወገብ በታች የሆነውን ክፍላቸው ደህናና የማያፈስ ከሆነ ደግሞ አረቄ ሲወጣ ለኮዳ ማስቀመጫ ይሆናል:: ጨርሰው ቢሰበሩ ደግሞ ተወቅጠው ተፈጭተውና ተቦክተው እንደ አዲስ የሸክላ ዕቃ መስሪያ ጥሬ ዕቃ ይሆናሉ:: ከዚህ ውጭም ስባሪያቸው («ገል» ይባላል) ለእሳት መጫሪያ ያገለግላል:: በአግባቡ ተስተካክሎ አዳዲስ የሸክላ ቁሶች ሲሰሩ ማስቀመጫ ይሆናል:: ከእያንዳንዱ ክፍል ያሉት ቁሶች ደግሞ በአብዛኛው ከሞላ ጐደል ቅርፃቸው

የሚመሳሰል ሲሆን ተግባራቸው ደግሞ ቅርፃቸውንና መጠናቸውን መሰረት ያደርጋል። ቀጥሎ የሸክላ ዕቃዎችን መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2፡ የሸክላ ቁሶችን አማካይ መጠን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| የቁሱ አካባቢያዊ መጠሪያ | | የቁሱ ቁመት | የቁሱ ዙሪያ | የአፍ ዙሪያ | የአንገት ቁመት | የቁሱ ውፍረት | የቁሱ የመያዝ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በገፊጅ | | 7-8 ሴሜ | 42 ሴሜ | 38 ሴሜ | - | 1 ሴሜ | የአንድ በግ ስጋ በአንድ ጊዜ ይሰራል |
| ድስት | ትልቅ | 6 ሴሜ | 43 ሴሜ | 36 ሴሜ | - | 0.5 ሴሜ | «አንድ ዶሮ አገላብጦ ይሰራል» |
| | መካከለኛ | 5 ሴሜ | 31 ሴሜ | 29 ሴሜ | - | 0.5 ሴሜ | ከ10-12 የሚደርስ ቁጥር ላለው በቤተሰብ ወጥ ይሰራል |
| | ትንሽ | 4 ሴሜ | 14 ሴሜ | 12 ሴሜ | - | 0.5 ሴሜ | ለባልና ሚስት ወጥ መስሪያ(ለ2) ሰው |
| ወጪት | | - | 38 ሴ.ሜ | 43 ሴሜ | - | 2 ሴሜ | ከ5-70 አሳ የሚያሰራ |
| ጋን | | 80 ሴሜ | 160ሴሜ | 100 ሴሜ | 16 ሴሜ | 1 ሴሜ | 50 ሊትር (100 ጆግ[7]) |
| ማድጋ | | 50 ሴሜ | 100ሴሜ | 50 ሴሜ | 16 ሴሜ | 1 ሴሜ | 20 ሊትር (40 ጆግ) |
| ትዝቢ | | 40 ሴሜ | 250-260ሴሜ | 50 ሴሜ | 13 ሴሜ | 1 ሴሜ | 60 ሊትር (120 ጆግ) |
| ሸንክላ | | 43 ሴሜ | 80 ሴሜ | 44 ሴሜ | 13 ሴሜ | 1 ሴሜ | 10 ሊትር (20 ጆግ) |
| ቶፋ | | 32-34 ሴሜ | 72 ሴሜ | 37 ሴሜ | - | 1 ሴሜ | 6-8 ሊትር (12-16 ጆግ) |
| ገንቦ | ትልቅ | 36 ሴሜ | 120 ሴሜ | 43 ሴሜ | 22 ሴሜ | 0.5 ሴሜ | 14 ሊትር (28 ጆግ) |
| | መካከለኛ | 33 ሴሜ | 118 ሴሜ | 40 ሴሜ | 20 ሴሜ | 0.5 ሴሜ | 12 ሊትር (24 ጆግ) |
| | | 25-30 ሴሜ | 100-110 ሴሜ | 30 ሴሜ | 10 ሴሜ | 0.5 ሴሜ | 6 ሊትር (12 ጆግ) |
| ጕራሽ | | 7-8 ሴሜ | 42 ሴሜ | 38 ሴሜ | - | 1 ሴሜ | 6 -8 ሊትር (12-16ጆግ) |
| ጀበና | ትልቅ | 26 ሴሜ | 46 ሴሜ | 21 ሴሜ | 13 ሴሜ | 0.5 ሴሜ | 8 ሊትር (16 ጆግ) |
| | መካከለኛ | 23 ሴሜ | 43 | 18 ሴሜ | 10 ሴሜ | 0.5 ሴሜ | 6 ሊትር (12 ጆግ) |
| | ትንሽ | 20 ሴሜ | 40 ሴሜ | 15 ሴሜ | 7 ሴሜ | 0.5 ሴሜ | 2-3 ሊትር (4-6 ጆግ) |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምድጃ | ትልቅ | 25 ሴሜ | 70 ሴሜ | - | - | 1 ሴሜ | ከሰል ነው የሚደረግበት |
| | መካከለኛ | 21 ሴሜ | 66 ሴሜ | - | - | 1 ሴሜ | » |
| | ትንሽ | 17 ሴሜ | 62 ሴሜ | - | - | 1 ሴሜ | » |
| ማጤሻ | | 17 ሴሜ | 53 ሴሜ | - | - | 1 ሴሜ | - |
| ምጣድ | | - | 58 ሴሜ | - | - | 3-3.5 | - |

ከሠንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው በሰላጤዋ ውስጥ ያሉት የሸክላ ዕቃዎች ቅርፃቸው የሚመሳሰል ቢሆንም እንኳን ከዚያ ባሻገር የመጠን ልዩነት እንዳላቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ዕቃዎች ከቅርፃቸው ባሻገር መጠናቸውም አገልግሎታቸውን ይወስነዋል፡፡ ቀጥሎ የሸክላ እቃዎች የሚሰሩበት ጥሬ እቃ ምንነትና እንዴት እንደሚገኝ ይገለፃል፡-

## 6.2. በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሸክላ ቁሶች መስሪያ ጥሬ ዕቃና መገኛው

(Rice 1987) እና (Hodge 1989) እንደሚያስረዱት የሸክላ አፈር በዓለም ላይ ከቅድመ ታሪክ ጊዜ ጀምሮ ለሸክላ ቁሶች መስሪያነት በስፋት አገልግሎት እየሰጠ ያለ ጥሬ ዕቃ ነው፡፡

በእርግጥም በዘጌ ባህረሰላጤ እንደዚሁ ሸክላ አፈር ይህን ያህል ጊዜ ሲባል በማይችል መልኩ ለበርካታ ከሸክላ ለተሰሩ የቤት ቁሶች መስሪያነት ውሏል፡፡ እንደ Dorson (1972) ያሉ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት ደግሞ የቤት ቁሶች ከምንና እንዴት እንደሚሰሩ፣ እንዴት ቅርጽ እንደሚወጣላቸውና እንዴት አገልግሎት እንደሚሰጡ ማጥናት የቁሳዊ ባህል ከሚያጠናቸው ጉዳዮች ውስጥ ይመደባል፡፡ በመሆኑም በሰላጤው ውስጥ ስለሚገኘው የሸክላ ቁስ መስሪያ ጥሬ ዕቃ ለማወቅ ተጠይቆ የተገኙ የቃል መረጃዎች እንደሚገልፁት በዘጌ ባህረሰላጤ የሚገኙ ሸክላ ሰሪዎች ሁሉ ለሚሰሯቸው የሸክላ ዕቃዎች «ዋልካ» የተባለ የአፈር ዘርን ይጠቀማሉ፡፡ ዋልካ መልኩ ጥቁርና የማጣበቅ ባህርይ ያለው አፈር ነው፡፡

ሸክላ ሰሪዎች ይህንን አፈር የሚያገኙት የትም ሳይሄዱ ከዚያው ከሰላጤው ውስጥ ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስ የታወቀውና ሁሉም የሸክላ ሰሪዎች አፈር የሚያመጡበት ቦታ አፋፍ 01 ቀበሌ ውስጥ ያለ «ዱቢት እሼ» ወይም «ኳስ ሜዳ» ተብሎ የሚጠራ ስፍራ ነው፡፡ ይህ ቦታ እንዲሁ ጠሙን ያደረ የመንግሥት ቦታ እንጂ እከሌ የሚባል ግለሰብ ባለቤት የሌለው በመሆኑ ሸክላ ሰሪዎች አፈሩን ለማግኘት ገንዘብ አይከፍሉም፡፡ ባስፈለጋቸው ጊዜ ሁሉ አቅማቸው በፈቀደው መቆፈሪያ (መኮትኮቻ፣ (ዶማ የመሰለ ባለሁለት ጣት መቆፈሪያ)፣ በቀጭን እንካሴ ወይም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ጫፉ ሹል እንጨት) በመቆፈር የቆፈሩትን አፈር በማዳበሪያ ከትተው ተሸክመው ወደ

መስሪያ ቦታቸው ያመጣሉ:: በሰላጤው ውስጥ የሚኖሩት ሸክላ ሰሪዎች የሚኖሩባቸው ጎጦች አፋፍ 01 ቀበሌ ጋሚ፣ ሰጎዳ (አፋፍ ውስጥ ያለ ቦታ) እና ዋሻ ይባላሉ:: ሰዎች ከመኖሪያ ቦታቸው ተነስተው አፈሩን ወደሚቆፍሩበት ቦታ ለመድረስ ከ5 ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት ድረስ ይፈጅባቸዋል:: ይህንንም ከባለሙያዎች በመጠየቅና ከቦታው በመሄድ አረጋግጫለሁ:: ነገር ግን ምንም እንኳን ቦታው ለአብዛኞቹ ሩቅ ባይሆንም የሚሸከሙት አፈር ግን እጅግ ከባድ እንደሆነ ነው ባለሙያዎች የሚናገሩት በመሆኑም አልፎ አልፎ የቤተሰቡ አባል የሆኑ ወንድ ወይም ሴት ልጆች አፈር በመሸከም ያግዟቸዋል::

በነገራችን ላይ ለመስሪያ የሚያገለግለውን አፈር በመቆፈርም ሆነ የሸክላ ሥራን በመሥራት ሂደት ሸክላ ሰሪዎች በማህበር የተደራጁ አይደሉም:: እያንዳንዱ ቤተሰብ የየራሱን ነው የሚሰራው:: ትብብሩ ከቤተሰብ ደረጃ አያልፍም:: በአኗኗራቸውም ቢሆን ሸክላ ሰሪዎች ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው ይኖራሉ እንጂ በአንድ ሰፈር ውስጥ የሰፈሩ አይደሉም:: በአጠቃላይ የሸክላ ሰሪዎች አኗኗራቸውም ሆነ ስራቸው በቤተሰብ ደረጃ እንጂ በማህበረሰብ ደረጃ አይደለም::

በመሆኑም እያንዳንዷ ባለሙያ የሸክላ አፈር ለማምጣት በፈለገች ጊዜ ማንንም ሳትጠብቅ ሄዳ ታመጣለች:: ነገር ግን ሸክላ ሰሪዎች አፈር የማይቆፍሩባቸው ጊዜያትም አሉ:: እነዚህ ጊዜያቶችም የወርና የዓመት በአላት ናቸው:: ሁሉም ባለሙያዎች (ወጣቶችም ሆኑ ትልልቆች) በባለእግዚአብሔር (29)፣ በማርያም (21)፣ በሚካኤል (12)፣ በሰንበት (ቅዳሜና እሁድ) አፈር አይቆፍሩም:: ከዚህ ውጭ ደግሞ ሁሉም እያንዳንዳቸው የእኔ ብለው የሚያከብሩትን የበዓል ቀን አይቆፍሩም «በዓል ያከብራሉ»:: ከዚህ በተረፈ ግን ባስፈለጋቸውና ማምጣት ባለባቸው ቀን ሁሉ ቆፍረው ያመጣሉ::

ሠንጠረዥ 3. ሸክላ ሰሪዎች የሚኖሩባቸው ጎጦችና አፈር ለማግኘት የሚጓዙት ሰዓት

| ጎጥ | የሚጓዙት ሰዓት |
|---|---|
| ሰጎዳ | 5-10 ደቂቃ |
| አፋፍ | 10 ደቂቃ |
| ጋሚ | 10-15 ደቂቃ |
| ዋሻ | 1 ሰዓት |

ይህ በባለሙያዎች ብቻ ወይም በቤተሰቦቻቸው እገዛ አፈር በማምጣት የተጀመረው ተግባር ሌሎች ሂደቶችንም ያስከትላል:: ይህም በቀጣዩ ርዕስ ይታያል::

## 6.3. የሸክላ ቁሶች አሰራር

Flencher (1983) እና Hodges (1989) እንደሚያመለክቱት የሸክላ ስራ የባለሙያዎችን የተለያዩ ችሎታዎችና ደረጃዎችን የሚጠይቁ ብዙ ሂደቶችና ደረጃዎች ያሉት ተግባር ነው። እንደዚሁ ሁሉ በዘጌ ባህረሰላጤ የሚኖሩ ሸክላ ሰሪዎች የተዋጣለት የሸክላ ስራ ዕቃ ለመስራት ጥሬ ዕቃውን ከማግኘት ጀምሮ ምርቱ ለገበያ እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያደርጉና በርካታ ተግባራትን እንደሚያከናውኑ ይናገራሉ። ከነዚህ ተግባራት ውስጥ የመጀመሪያው አፈሩን መቆፈርና ለሥራ ማዘጋጀት ነው።

### 6.3.1 የሸክላ አፈርን መቆፈርና ለመስራት ማዘጋጀት

ይህ ተግባር ለዘጌ ሸክላ ሰሪዎች የመጀመሪያው የሸክላ ስራ ተግባር ነው።በመሆኑም ምንጊዜም የሸክላ ቁስ መስራት ሲኖርባቸው የሸክላ አፈር ለመቆፈር ከቤታቸው ይወጣሉ። ከመኖሪያቸው ተነስተው መንገዱ የሚፈጅባቸውን ያህል ጊዜ ፈጅቶ አፈሩን የሚያመጡበት ቦታ ሲደርሱ አፈር ፍለጋ የሚያባክኑት ምንም ጊዜ የለም። ምክንያቱም ከዛሬ በፊት እነሱም ሆነ ሌሎች ባለሙያዎች መቆፈር የጀመሩበት ቦታ በየቦታው ጉድጓድ ሰርቶ አለ። ይህንን ቦታ የአካባቢው ሰው «የፈላሾች ጉድጓድ» ሲል ይጠራዋል። በመሆኑም በቅርብ ካገኙትና ከፈለጉት ጀምር ቦታ ላይ አፈሩን ቆፍረው ወደ ቤታቸው ይወስዳሉ። በመካከላቸው «ለምን የእኔን ወሰድሽ?» ተብሎ ጥያቄ አይነሳም።

አፈሩን ወደ ቤታቸው ከወሰዱት በኋላ የመጀመሪያው ሥራ ዋልካ ያልሆኑ አፈሮችን፣ ሳሮችን፣ ቅጠሎችንና ሌሎች ባእዳን ነገሮችን ለቅመው ማስወገድ ነው። ሁሉም የሸክላ ስራ ባለሙያዎች «የሸክላ ስራ ንፅህና ይወዳል።» ይላሉ።

ወ/ሮ አንጓች አንባዬ እንደገለፁልኝ ከዋልካ አፈር ውጭ የሆነ ማንኛውም ዓይነት ባዕድ ነገር ቢቀላቀል ሸክላው ተሰርቶ ለአገልግሎት ሳይደርስ ገና በእሳት ሲቃጠል[8] ይሰበራል። ይህ ደግሞ የጉልበትና የጊዜ ኪሳራ ያመጣል። በመሆኑም ከዋልካ አፈር ውጭ ያሉ ባዕዳን ነገሮች ሁሉ በጥንቃቄ ተለቅመው ይወጡና አፈሩ ከአመድ ጋር ተቀላቅሎ በወፍራሙ ይቦካል፣ ከዚያም ዝርግ ሆኖ ይጠፈጠፍና ፀሐይ ላይ ይሰጣል በዚህ ሁኔታ ለሁለትና ሦስት ቀን ከቆየ በኋላ ሲደርቅ በላይና በታች እንጨት እየነደደበት በእሳት ይቃጠላል፣ ከዚያም ከእሳት ወጥቶ እንዲቀዘቅዝ ይደረግና በባህላዊ ሙቀጫ ይወቀጣል፣ የተወቀጠው አፈር ፍጹም እንዲልም ሲባልም በሰፌድ

---

[8] ማቃጠል በሸክላ ስራ ሂደት አንድ ደረጃ ነው።

«እየተንጓለለ» ጥሬው እንደገና እየተወቀጠ መወቀጡ ብቻ ስለማይበቃ በባህላዊ ወፍጮ ተፈጭቶ አፈሩ እንዲልም ይደረጋል:: ሸክላ ሰሪዎች ከዚህ አፈሩን ራሳቸው ከመሬት አፍሰው፣ ባዕድ ነገር እንዳይኖረው ተጠንቅቀው ለቅመው፣ በወፍራሙ አቡክተው፣ በእሳት አቃጥለው፣ ሲቀዘቅዝ ወቅጠው የሚያዘጋጁበት አዲስ (original) የሸክላ አፈር በተጨማሪ ቀደም ሲል በእነሱም ይሁን በሌሎች ሸክላ ሰሪዎች ተሰርተው አገልግሎት ሲሰጡ ኖረው ከተሰበሩ እንዲሁም በመስራት ላይ እያሉ የተሰበሩ የሸክላ ዕቃዎችን ስባሪ ወቅጠውና ፈጭተው አዲስ እቃዎችን ለመስሪያ ይገለገሉባቸዋል::

የሸክላ ዕቃዎች በዚህኛው አፈር ብቻ አይሰሩም ሌላም የሚያስፈልጋቸው አፈር አለ:: ሸክላ ሰሪዎች ይህንን አፈር የሚያመጡት የሚቃጠለውን አፈር ያመጡ ዕለት ወይም በበነጋታው ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ግን ይህኛው አፈር ከሚቃጠለው የበለጠ «ንፅህናና ጥንቃቄ» የሚፈልግ ነው:: የሚቃጠለው አፈር ምናልባት በስህተት ቅጠልና ሳር የመሳሰሉ ነገሮች ቢኖሩት በእሳት ሲቃጠል ሊጠፉ ይችላሉ:: ይህኛው ግን ዕቃ ሆኖ ሳይሰራ በእሳት ስለማይቃጠል የበለጠ ጥንቃቄን ይጠይቃል:: በመሆኑም አፈሩን አምጥተው ተጠንቅቀው ከለቀሙት በኋላ የመስሪያ ቦታቸው ላይ ቆፍረው ባዘጋጁት ጉድጓድ ዉስጥ ያቦኩትና ቢያንስ ለሦስት ቀን ያህል እዚያው ይተውታል:: ጭቃው ጉድጓድ ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ በረዘመ ቁጥር የሚሰራውን ዕቃ በቀላሉ ያለመሰበር ዕድል ያሰፋዋል:: ሆኖም ሸክላ ስራ የሰዎች መተዳደሪያ ነውና በጊዜ ለገበያ ለማቅረብ ሲሉ ረጅም ጊዜ ላይሰጡት ይችላሉ:: ሦስት ቀን ግን ግዴታ ነው:: ከዚህ በኋላ ምናልባት በአራተኛው ቀን የመስሪያ ቦታውን በደንብ ጠርገው ንጹህ ካደረጉ በኋላ የተወቀጠው «የሸክላ ዱቄት» በትንሹ መሬት ላይ ይነሰንሱና የተቦካውን ጭቃ አውጥተው ያስቀምጡታል:: ከዚያም በትንሽ በትንሹ «ዱቄቱን» ጭቃው ላይ እያደረጉ በእግራቸው ያቦኩታል:: የወፈረ ሲመስላቸው ውሃ በትንሹ እያደረጉ በደንብ በእግራቸው ያሹታል:: ጭቃውና ዱቄቱ ተመጣጣኝ ሆነዋል፣ መታሸቱም በቃው ሲሉ ዕቃውን መስራት ይጀምራሉ::

## 6.3.2 የሸክላ ቁሶች ቅርጽ እንዲይዙ ማድረግ

ተቦክቶ የሰነበተው ጭቃና ተወቅጦ የተዘጋጀው የሸክላ አፈር በአግባቡ ከተቀላቀሉ በኋላ የሸክላ ቁስ ስራው ይጀመራል:: ሁሉም ሸክላ ሰሪዎች አፈሩን የሚያመጡበት ቦታ አንድ እንደመሆኑ በሁሉም የሸክላ ዕቃዎች ተመሳሳይ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም በአመዛኙ ተመሳሳይ ቁሶችን ይሰራሉ:: ባለሙያዎች ጋን፣ማዲጋ (እንስራ)፣ትዝቢ፣ ሸንክላ፣ ቶፋ፣ በገፊጅ፣ ድስት፣ ገንቦ፣ ጀበና፣ ማጨሻ፣ጎራሽ፣ ምድጃና ቤተሞገስ የተባሉ ዕቃዎችን ይሰራሉ:: ነገር ግን ምድጃ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሰላጤው ውስጥ መስራት የጀመረ የሸክላ ዕቃ ሲሆን ምድጃ የመስራት ችሎታ ያላቸው

የተወሰኑ ባለሙያዎች ብቻ ናቸው። እንዲሁም ቤተሞገስን ሁሉም ሰዎች አይሰሩም። ይህ የሸክላ ቁስ በባህላዊ ቤቶች ቁንጮ ላይ የሚቀመጥ ሲሆን ሁሉም ሸክላ ሰሪዎች «እሱን መስራት የሚችሉት የጥንቶቹ ነበሩ።» ይላሉ በመሆኑም የረጅም ጊዜ ሸክላ ስራ ልምድ ያላቸውን አንዲት ባለሙያ ብቻ ነው ቤተሞገስ ሲሰሩ ያገኘኋቸው።

በአንጻሩ ደግሞ ጀበና ሁሉም ሰዎች የሚሰሩት የሸክላ ቁስ ነው። ነገር ግን የረጅም ጊዜ የስራ ልምድ ካላቸው ባለሙያዎች ይልቅ ወጣቶች ጀበና መስራት ያዘወትራሉ።ትልልቆችም ቢሆኑ «ጀበና የወጣቶች ነው» ይላሉ አልፎ አልፎ መስራታቸው ባይቀርም። በአጠቃላይ ከእነዚህ ልዩነቶች በስተቀር ሁሉም ባለሙያዎች በተመሳሳይ ጥሬ ዕቃ ተመሳሳይ ዕቃዎችን ይሰራሉ።

ሸክላ ሰሪዎች የሸክላ ዕቃዎችን ሲሰሩ በእጃቸው ብቻ ይሰራሉ እንጂ የሚጠቀሙበት ምንም አይነት ማሽን ወይም የቴክኖሎጂ ውጤት የለም። ምናልባት አለ ከተባለ እንኳን ጭቃውን ለማርጠብ የሚይዙትን ውሃ የሚቀርቡበት ዕቃ በፋብሪካ የተመረተ የጎማ ወይም የብረት ዕቃ ሊሆን ይችላል። ይህም ግን ምናልባት እንደ አጋጣሚ ይሆናል እንጂ በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ ከእንጨት ተጠርቦ የተሰራ ገበታ ነው የሚጠቀሙ። በመሆኑም ዕቃዎችን ለመስራት ሲያስቡ ውሃ በገበታ የተሰነጠቀ ቀርከሃና ቁረንጮ( የቆዳ ቁራጭ)፣ ገል (የሸክላ ዕቃ ስባሪ) ይዘው ይቀርባሉ። ከዚያ ከተቦካው ጭቃ በትንሹ በመቆንጠር ገሉ ላይ ያስቀምጡና ዕቃውን መስራት ይጀምራሉ።

በሸክላ ዕቃዎች ስራ ወቅት ማንኛውም ዕቃ በአንድ ጊዜ ተሰርቶ አያልቅም። ይልቁንስ ጭቃው በትንሽ በትንሹ እተመጠነ የተወሰነ ክፍል ይሰራና ክረምት ከሆነ በፀሐይ፣ በጋ ከሆነ በነፋስ ጠፈፍ እንዲል ይደረጋል። ከዚያ እንደገና ሌላ ይቀጠልበታል። አሁንም ጠፈፍ እንዲል ይደረጋል። እንዲህ እንዲህ እያለ የዕቃው ስራ ከታች ይጀመርና ወደ ላይ ይሄዳል። ሸክላ ሰሪዎች ምንም አይነት ዕቃ ይስሩ የዕቃው የአሰራር ቅደም ተከተል ከዕቃው ቂጥ (የታችኛው ክፍል) ይጀምራል። ከዚያ ቀስ በቀስ ወደ ላይ ይሄዳል። ቀጥሎ ተማመሳሳይ ቅርፅ ካላቸው የሸክላ ቁሶች ውስጥ ወካይ ሊሆን የሚችል እቃ ለመምረጥ ቁሶች እንዴት ቅርፅ እንደሚይዙ እንመልከት፡-

1. ማዲጋ፣ ጋን፣ ትዝቢ፣ ሸንክላ፣ቶፋ
2. በገፊጅ ፣ድስት
3.ማንደጃ፣ ማጨሻ
4. ጀበና፣ ገንቦ
5. ቤተሞገስ

እነዚህ ከላይ ቁጥር ተሰጥቷቸው የተደረደሩት የሸክላ ቁሶች ወደጉን ሲታዩ የመጠን መለያየት ያላቸው ከመሆኑ በስተቀር በአመዛኙ ቅርፃቸው ተመሳሳይ ነው። በመሆኑም በተራ ቁጥር 1 ለተዘረዘሩት ቁሶች ማዲጋን፣ በተራ ቁጥር 2 ለተዘረዘሩት

በገፈጅን፣ በተራ ቁጥር 3. ለተዘረዘሩት ማንደጃን በተራ ቁጥር 4 ለተዘረዘሩት ደግሞ ጀበናን ወኪል አድርጎ በመምረጥ ተራ ቁጥር 5 ላይ የቀረበውን ደግሞ ራሱን በመውሰድ ቁሶች እንዴት ቅርፃቸውን እንደሚይዙ አሳያለሁ።

ማዲጋ (እንስራ)፡- ይህ ቁስ ሲሰራ የማዲጋው ቂጥ (የታችኛው ክፍል) በመጀመሪያ ከገሉ ላይ ይጠፈጠፍና ወደላይ ትንሽ ቀልበስ ቀልበስ ተደርጎ ይተዋል። ከዚያ ጅምሩ በነፋስ ወይም በፀሐይ ጠፈፍ እስኪል ድረስ ለተወሰነ ጊዜ ስራው ይቋረጣል። ጠፈፍ ሲል ስራው ይጀመርና አሁንም ጠፈፍ እስኪል ይተዋል። እንዲህ እንዲህ እያለ ቀስ በቀስ ከጠባብ ወደ ሰፊ ከዚያም ወደ ጠባብ ይሄድና በመጨረሻ የማዲጋው «አንገት» ይሰራል።

እንስራው ከታች ወደ ላይ እያደገ ሲመጣ ባለሙያዋ ወደ ላይ በሽምበቆው እየላገች ታስተካክለዋለች። የምትሰራውን ዕቃም የፊት የፊቱን የቆዳውን ቁራጭ ከአጠገቧ በገበታ ካቀረበችው ውሃ እያስነካች በቆዳው ታለሰልሰዋለች። የእንስራው ስራ ከአንገቱ ከደረሰ በኋላ ለጆሮ የሚሆን ጭቃ በደጋን መልክ ይሰራል። ከዚያ የእንስራው ጎንና ጎን ሚዛኑን እንዲጠብቅ ተገምቶ ይበሳና የተሰራው «ጆሮ» በቀዳዳው ይገባል። መልሶ እንዳይሾልክም በውስጥ በኩል በሌላ ጭቃ ይደመደማል።

በገፈጅ፡- ይህ ከመጠኑ ትልቅነት የተነሳ ስሙን ያገኘው የድስት አይነት የአንድ በግ ስጋ በአንድ ጊዜ ሊሰራ የሚችል መጠን አለው ሲሉ ባለሙያዎችና ተጠቃሚዎች ይገልፃሉ። ይህ ቁስ ሲሰራ ጭቃው ከገሉ ላይ ከተደረገ በኋላ በገሉ ልክ ተጠፍጥፎ ሲያበቃ ወደ ላይ ዙሪያው ይቀለበሳል። ነገር ግን ማንኛውም የሸክላ ዕቃ በአንድ ጊዜ ተሰርቶ ማለቅ ስለሌለበት ወደ ላይ የሚቀለበሰው ጭቃ ቁመቱ አጭር ነው። ከዚያም ጅምሩቁስ ንፋስ ላይ ይደረግና ጠፈፍ እስኪል ድረስ ስራው ይቋረጣል። በዚህ ጊዜ ግን ባለሙያዎች ሌላ አዲስ እቃ መስራት ይጀምራሉ እንጂ ስራ አይፈቱም።

ቁሱ ጠፈፍ ሲል (ጭቃው እጅ ማጣበቁን ሲያቆም) እንደገና ሊሰራ ከተዘጋጀው ጭቃ ይቆነጥሩና በእጃቸው ያድቦለቡሉታል። ከዚያም የተድቦለቦለው ጭቃ በጅምሩ ቁስ ላይ ዙሪያዉን በማጋደም በእጃቸው እየደፈጠጡ ከታችኛውና ጠፈፍ ካለው ጭቃ ጋር ያጠብቁታል። ከዚህ በኋላ ጭቃው የተቀጠለበት ቦታ በደንብ እንዲያያዝና ቅጥልነቱ እንዲቀር እንዲሁም የእቃው ውፍረት እንዲመጣጠንና የእቃው ቁመት ወደ ላይ እንዲዘረጋ በተሰነጠቀ ሸንበቆ፣ ሸንበቆውን ውሃ እያስነኩ ወደ ላይ ይልጉታል። ይህንን በማድረግም የበገፈጁን ቁመት ይበቃዋል እስከሚሉት ደረጃ ድረስ ካደረሱት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ጠፈፍ እንዲል ንፋስ ላይ ያስቀምጡታል። ንፋሱ ጠፈፍ ካደረገው በኋላ ደግሞ መልሰው ያመጡትና ርጥብ ጭቃ አድቦልቡለው ብዙውን ወደ ውስጥ ጥቂቱን ደግሞ ወደ ውጭ በማድረግ በጅምሩ ቁስ ጠርዝ ዙሪያ ያስቀምጡታል። ከዚያም እጃቸውን ውሃ እያስነኩ አዲሱ ጭቃ ለቁሱ ከንፈር (ጠርዝ) እንዲሆነው ያደርጋሉ።

ሲጨርሱም ነፋስ ላይ ያደረጉትና ጠፈፍ ካለ በኋላ መያዣ የሚሆነውን ጆሮ ይሰሩታል:: ጆሮው የሚሰራው ከእንፊሩ (ከጠርዙ) ዝቅ ብሎ ነው:: መጠኑን በመዳፋቸው ለክተው ክብ ቅርፅ «ሁለት» ጭቃዎችን ካዘጋጁ በኋላ ከእንፊሩ ዝቅ ብሎ በእንጨት በመብሳት ተሰርቶ ያለቀውን ቅርፅ እስከ ግማሽ ያስገቡታል:: ተመልሶ እንዳይወጣም ከውስጥ በኩል አዲስ የገባውን ጭቃ ከበገፊጁ ግድግዳ ጋር በእጃቸው እየጨፈለቁ ያጣብቁታልና በውጭ በኩል ክፍተት እንዳይኖረው በጭቃ ይሸፍኑታል:: ከዚህ በኋላ ቆረንጮ (የቆዳ ቁራጭ) በውሃ እያስነከሱ ተሰርቶ ያለቀውን ዕቃ ያለሰልሱታል:: ሲጨርሱም እንደወቅቱ ክረምት ከሆነ ፀሃይ ላይ በጋ ከሆነ ደግሞ ነፋስ ላይ ያስቀምጡትና እንዲደርቅ ያደርጉታል::

የድስት አሰራርም ከበገፊጅ ጋር ተመሳሳይ ነው:: በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የመጠን ብቻ ነው:: ይህንን ሁኔታ በምልከታ ያረጋገጥኩ ሲሆን ሁኔታውን አስመልክቶ መረጃ የሰጡኝ ወ.ሮ ማረፊያዬ ወርቄ እንዲህ ይላሉ:-

> በገፊጅና ሌሎች ድስቶች ትንሽና ትልቅ ከመሆናቸው በቀር አሰራራቸው ሁሉ አንድነው:: በመጀመሪያ በገሉ ላይ ጭቃውን እንጠፈጥፈውና ወደ ላይ ቀና ቀና አድርገን እንተወዋለን:: ያ ጠፈፍ ሲል ደግሞ ሁለተኛው ጭቃ እንቀጥልበትና በሸንበቆ እየላግን ጐኑን እንሰራዋለን:: አሁንም ንፋስ እስቲያደርቀው ጠብቀን እንፊሩን እንሰራዋለን:: በኋላም ጭቃውን እናረግና በቆረንጮ እናለሰልሰዋለን:: እንዲያ ሆኖ ሲያበቃ ክረምት በፀሃይ በንፋስ አድርቀን ኋላ ይቃጠላል:: ግና በገፊጅና ሌሎች ድስቶች የሚቀመጡባቸው ገሎች መጠናቸው የተለያየ ነው:: ለትንሿ ድስት ትንሽ ለትልቁ ደግሞ ትልቅ ገል አለ:: አለዚያ በትንሿ ገል ላይ ትልቁን አስቀምጠን የሰራነው እንደሁ የድስቱ ቂጥ ከገሉ ተርፎ መሬት ላይ ይሆንና በኋላ አልላቀቅም ብሎ ያስቸግራል:: ስለዚህ ለሁሉም ዕቃዎች እንደየአቅማቸው ገል አላቸው:: በተረፈ ግን ድስቶች ሁሉ እንደ በገፊጅ ሁነው ነው የሚሰሩ:: በገፊጅ ግን ለመድረቅ ብዙ ቀን ይላል (ወ/ሮ ማረፊያዬ ወርቄ:27-01-2000) ::

ሲሉ ድስቶች እንዴት ቅርፅ እንደሚይዙና አሰራራቸው እንዴት እንደሚመሳሰል ገልፀዋል::

(የከሰል) ምድጃ:- የማንደጃን አሰራር አስመልክቶ ባለሙያዎች እንደገፁልኝና እኔም እንዳየሁት በመጀመሪያ ለመስሪያ በቀረበው ክብ ገል ላይ ተቃጥሎ ከታወቀጠው «የሸክላ ዱቄት» በጥቂቱ ይነሰነስበታል:: ይህም ዕቃው ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ሲነሳ ገሉን አልለቅም እንዳይል ያገለግላል:: ከዚህ በኋላ በትንሹ ጭቃ ይቆነጠርና በገሉ ላይ በማድረግ ከታች ጠባብና ድፍን ወደ ላይ ደግሞ ሰፊና ክፍት ቅርፅ ይዞ እንደዲወጣ ተደርጉ ትንሽ እየተሰራ በመሃል በፀሃይ ወይም በንፋስ እየደረቀ ደግሞ እየተሰራ የተገለበጠ «ፒራሚድ» የመሰለ ቅርፅ ያለው ቁስ ተሰርቶ ያልቃል:: ከዚህ በኋላ በደንብ ጠፈፍ እስኪል ድረስ ሰራው ተቋርጦ ይቆይና በደንብ ጠፈፍ ሲል የተሰራው ዕቃ ከገሉ

ተላቅቆ ተገልብጦ መሬት ላይ ይቀመጣል:: አሁን እቃው ተገልብጦ ሲቀመጥ የላይኛው ክፍሉ ድፍን ነው:: ይህን ድፍን ቦታ በእጃቸውን በውሃ እያስነኩና አዲስ ጭቃ እየጨመሩ ይዘረጉትና ጠፍጣፋ ሆኖ እግሩ ክብ የሆነ ጠረጴዛ ቅርፅ ይይዛል:: ከዚህ በኋላ ጠፈፍ እንዲል ለትንሽ ጊዜ ስራው ተቋርጦ ይቆያል:: ጠፈፍ ሲል ደግሞ ዝርግ የነበረው ጭቃ ከሰል አቅፎ መያዝ እንዲችል ወደ ላይ ይቀለበስና ጠፈፍ እንዲል ይተዋል:: ይህ ሁሉ የሚሰራው በእጅ ሲሆን ጭቃው በሁሉም ቦታ እኩል ውፍረት እንዲኖረው በተስነጠቀ ሸንበቆ ይላጋል:: አዲስ የተቀጠለው ጭቃ ጠፈፍ ሲል በቁሱ እግር ላይ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያላት ለንፋስ ማስገቢያ የምትሆን ቀዳዳ ትበጃለች:: ይህም በሸንበቆ የሚደረግ ሲሆን ጭቃው እርጥብ ስለሆነ ቁሱ መሰንጠቅም ሆነ ሌላ ጉዳት ሳይደርስበት ይከናወናል:: ከዚያም የከሰል ቤቱ እሳት በሚነድበት ጊዜ አመዱን እንዲያሳልፍ መሃሉ አልፎ አልፎ ይበሳል:: ይህ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ ዕቃው ይገለበጥና ክፍት የነበረው እግሩ አመድ እንዳያፈስ በጠፍጣፋ ጭቃ ይከደናል:: ግን የቁሱ አካል እንጂ ትርፍ እንዳይሆን ባለሙያዎች እጃቸውን በውሃ እየነኩ ጭቃውን በሸንበቆው በመላግ ከዋናው አካሉ ጋር ያጣብቁታል:: በመጨረሻም ቁረንጮ ውሃ እያስነኩ በማሻሸት እንዲለሰልስ ያደርጉታል:: ማጨሻም ከመጠኑ ማነስ በስተቀር አሰራሩ ሙሉ በሙሉ ከምድጃ ጋር ይመሳሰላል::

ጀበና:- የጀበና ስራ እንደሌሎች ቁሶች ሁሉ ከቂጡ ይጀምራል:: ባለሙያዎች ለመስሪያ ከተዘጋጀው ገል ላይ የሸክላ አፈሩን ነስንሰው ጭቃ ካደረጉበት በኋላ እየጉደጎደ እንዲመጣ በማድረግ የክብ ቅርፅ እያስያዙ ቁሱን መስራት ይጀምራሉ:: ይህ ቁስ የግማሽ ኳስ ቅርፅ እንደያዘ ጠፈፍ ይል ዘንድ ንፋስ ላይ ወይም ፀሃይ ላይ ያስቀምጡታል:: ጠፈፍ ሲል ጅምሩን ዕቃ ያመጡትና ትንሽ ትንሹን ጭቃ በእጃቸው እያድቡለቡሉ እየቀጠሉ በሸንበቆውና በእጃቸው ወደ ላይ እየሳቡ ጫፍ ላይ ትንሽ ክፍተት ሲቀር በስተቀር የሚሰራው ዕቃ ሙሉ ኳስ እስኪመስል ድረስ ይሰሩታል:: በዚህ ሁኔታ የጀበናው ቂጥ ሆድና ደረት ተሰርቶ ሲያበቃ በቀረው ክፍተት ጭቃውን በትንሽ በትንሹ በመጨመር ወደ ላይ ቀጥ ብሎ የሚወጣ አካል ይበጃል:: ይህ አካል «አንገት» ነው:: ከዚህ በኋላ ጀበናው ጠፈፍ እስኪል ይጠበቅና ጠፈፍ ሲል ከጐኑ ላይ ተበስቶ ቁመቱ አጠር ያለ ድንቡልቡል ጭቃ ይገባበታል:: የገባበት ቦታ ክፍት እንዳይሆን ዙሪያውን በጭቃ ይደፍናል:: ከዚያም የተቀጠለውን ጭቃ እስከዋናው አካል ድረስ በደረቅና እዚያው ተሰብሮ ሊቀር በማይችል ጠንካራ እንጨት በመብሳት ማንቆርቆሪያ ይሰራል:: ማንቆርቆሪያው ባለበት ተቃራኒ ደግሞ ጭቃ አድቦልብሎ በመቀጠል መያዣው ይሰራል::

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ጀበና ቅርፅ ሲወጣለት ስራው በየመሃሉ እየተቋረጠ ዕቃው በነፋስ ጠፈፍ እንዲል የሚደረገው ለሶስት ጊዜ ብቻ ነው። ይህ ማለት ከሌሎች እቃዎች አንፃር ሲታይ ትንሽ ነው ማለት ነው። ከላይ እንደተገለፀው ደግሞ ጀበናን መስራት የሚያዘወትሩ ወጣቶች ናቸው። ይህ እንግዲህ ከሌሎች ቁሶች ይልቅ ጀበናን መስራት ብዙ ልምድን የማይጠይቅ መሆኑን የሚያሳይ ይመስላል። ገንቦ መጠኑ ትልቅ መሆኑና «አንዱር» ስለሌለው እንጂ አሰራሩ ከጀበና ጋር ይመሳሰላል።

ቤተሞገስ፡- ቤተሞገስ ከሸክላ የሚሰራ በተዘረጋ የሰው መዳፍ በመሰለ ቅርፅ የተከደነ ከወገብ በላይ የእንስራ ቅርፅ ያለው ቁስ ነው። እንደ እንስራ «አፍ» አለው። ነገር ግን ይህ አፉ ጠቅላላ ቅርፁ እንደ ኩባያ ሆኖ ተሰርቶ ጫፍ ላይ አምስት የሰው ጣት ቅርፅ ያላቸው ቅጥሎች ባሉት ክዳን ይዘጋል። ይህም በመሆኑ በጠቅላላው ሲታይ የተዘረጋ የሰው መዳፍ የመሰለ ቅርፅ ያለው ቁስ ነው። ይህ ቁስ በቤቶች ቁንጮ ላይ የሚቀመጥ ሲሆን አሰራሩ የሚከተለው መልክ አለው፡-

አንድ ቤተሞገስ ሶስት ቁሶች[9]አንድ ላይ ሁነው ይሰሩታል። ሁለቱ ቁሶች አንዱ ትልቅ ሌላው ትንሽ ከመሆናቸው በስተቀር ከወገብ በላይ የእንስራ ቅርፅ አላቸው ሌላውና የቀረው አንዱ ደግሞ እንደ ኩባያ «አፉ» ክፍት «ቂጡ» ድፍን ሆኖ ተሰርቶ «ከቂጡ» ላይ ጣት የመሰሉ አምስት ቅጥሎች አሉት።



*ሥዕል15 ፡ ቤተሞገስ*

---

[9] ሶስቱ ቁሶች ቤት ላይ ሲቀመጡ በመጀመሪያ ትልቁ ሳሩን እንዲደግፍ በቀዳዳው የቤቱ ቁንጮ ገብቶ ይቀመጣል። ከትልቁ ላይ ትንሽና ተመሳሳዩ ቁስ ይቀመጣል። ከዚያ ላይ በመዳፍ ቅርፅ የተሰራው ይቀመጣል።

ቤተሞገስ ሲሰራ በመጀመሪያ ከገሉ ላይ የሸክላ አፈር ይነሰነሳል:: ከዚያም ልክ ምድጃው ሲሰራ በነበረው ቅርፅ ግን ሰፋ ብሎ በየጊዜው ስራው እየተቋረጠ በነፋስ ጠፈፍ እያለ ተሰርቶ ያልቅና በደንብ ጠፈፍ እንዲል ንፋስ ላይ ይደረጋል:: ሁለተኛው ቁስም በመጠኑ አነስ ብሎ ብቻ እንደመጀሪያው ሆኖ ይሰራል:: ከዚያ ሁለቱም ጠፈፍካሉ በኋላ ፀሃይ ላይ የደረጋሉ:: የተጀመሩበት ቦታ ይነደልና አንገት ይወጣላቸዋል:: ከዚያ በቆረንጮ ለስልሰው እንዲደርቁ ይደረጋል:: ከዚያ ሶስተኛው ቁስ ይሰራል::ይህ ቁስ እንደሌሉች «ገል» ላይ የተደፋ ኩባያ መስሎ ይሰራል:: ጠፈፍ ካለ በኋላ ደግሞ አምስት ቅጥሎች ቂጡ ላይ ይደረጉለታል:: ከዚያ ይደርቃል:: በዚህ ሁኔታ ተሰርቶ ያልቅና ይቃጠላል::

ባለሙያዎች የሚሰሯቸው ዕቃዎች እንደ ድስት፣ ጀበና፣ ማጨሻና ማንደጃ ያሉ መጠናቸው ትንንሽ የሆኑ እንደሆነ እነሱ ተቀምጠው ዕቃዎች የተቀመጡበትን ገል በማሽከርከር ይሰራል:: ነገር ግን የሚሰሩት ዕቃዎች እንደ ጋንና ትልልቅ እንስራዎች ያሉ መጠናቸው ትልልቆች ከሆኑ እነሱ እየተዟዟሩ ይሰራሉ::

ባለሙያዎች የሚሰሯቸው ዕቃዎች መጠን፣ ወፍራምነትና ስስነት፣ የቅጥሎቻቸውን ሚዛን መጠበቅ (ለምሳሌ የእንስራ ጆሮ ሲያስገቡ) የሚጠቀሙባቸው ዘመናዊ መለኪያዎች የሏቸውም:: ነገር ግን ሁሉን የረጅም ዘመን ልምዳቸው በሰጣቸው ዕውቀት ተጠቅመው በዓይናቸው በመገመት በእጃቸው በመመጠን ይሰሯቸዋል:: ዕቃዎች ከተሰሩ በኋላ ደግሞ ቀጣዩ ተግባር ማስጌጥ ነው::

## 6.3.3 የሸክላ ቁሶችን ማስጌጥ

የሸክላ ቁሶችን በሚፈለገው ቅርጽና መጠን ተሰርተው ካለቁ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ሸክላዎችን ማስጌጥ ነው:: ባለሙያዎች በሰሯቸው እቃዎች ላይ ጌጦችን የሚሰሩ ወዲያውኑ ስራው እንዳለቀና ጭቃው ሳይደርቅ ነው:: የሚሰሯቸው ጌጦችም በጠቅላላው ሲታዩ ከዕቃው ላይ የሚቀጠሉ ቅጠሎችና የተለያዩ መስመሮች ናቸው:: ቅጠሎቹ በአብዛኛው የሚደረጉት በማድጋዎች (እንስራዎች) ላይ ሲሆን ጆሮዎች በሌሉበት በኩል ይደረጋሉ:: ሁልጊዜም ቁጥራቸው ሁለት ብቻ ነው:: ስማቸው «ጉጥ» ይባላል:: ጉጦች የሚደረጉት «ደረት» ተብሎ በሚጠራው ከማዲጋው (እንስራው) አንገት ወረድ ብሎ ባለው ስፍራ ነው:: ከሚገኙበት ቦታና ከቅርጻቸው አንጻር ጉጦቹ «ጡት» ይመስላሉ::

ምንም እንኳን ሸክላ ሰሪዎች መጠናቸው ግዙፍ ከሆነ እስከ ትንሽ እቃዎች የሚሰሩ ቢሆን መረጃ አቀባዮች እንደገለጹልኝ በምልከታም እንዳረጋገጥኩት ብዙ ጊዜ ጌጥ የሚደረገው በትንንሽ እንስራዎች በገንቦዎችና በጀበናዎች ላይ ነው:: የዚህ ምክንያት አስመልክቶ ጥያቄ ካቀረብኩላቸው ባለሙያዎች ውስጥ ወ/ሪት መሰረት ጓዴ የተባለች የ23 ዓመት የሸክላ ስራ ባለሙያ እንደገለጸችልኝ ትንንሽ ዕቃዎች ከዕለት ዕለት የቤት

ውስጥ ግልጋሎት በተጨማሪ ከቤት ውጪም ውሃ ስለሚቀዱባቸው፣ በማህበራዊ ኑሮ ሳቢያ ለሚኖሩ ሰርግ፣ ለቅሶና በዓልን ለመሰሉ ግንኙነቶች በጎረቤት ወይም በዘመድ ቤት እንደ ስጦታ ለሚወሰድ ጠላ ማድረሻ የሚያገለግሉ ስለሆነ፣ የቡና ጀበናዎችም እንዲሁ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ የሚቀርቡ ዕቃዎች ስለሆኑ በጠቅላላው ከሰው ፊት የሚደርሱ ዕቃዎች ስለሆኑ ጌጥ ቢደረግባቸው ሰው ደስ ያሰኛሉ ብላለች።

ሆኖም ግን ሸክላ ሰሪዎች በሸክላ ዕቃዎቻቸው ላይ ሁል ጊዜ ጌጥ አያደርጉም ከፈለጉ ያደርጋሉ፤ ካልፈለጉ አያደርጉትም። እንዲያውም ይህ ደረጃ በሸክላ ስራ የግድ ያልሆነ ነው። ባለሙያዎችም የሚሉት ይህንኑ ነው። ነገር ግን ለሁሉም እንስራዎች የሚደረገውና የማይቀረው ጌጥ «ማተብ» ተብሉ የሚጠራው ከአንገቱ መጨረሻና ከእንስራው ደረት መጀመሪያ ላይ ዙሪያውን የሚደረግ ጎልቶ የሚታይ ጠርዝ ነው። የዚህን ጌጥ ትርጉም የነገሩኝ ወ/ሮ አንጓች አምባዬ፡

> ሌላው ጌጥ የሚደረግ ዕቃው ለሰው ደስ እንዲልና ገበያ እንዲስብ ነው። ባይደረግም ዕቃው ጥሩ ሆኖ ከተሰራ ሰዉ ይወደዋል። መሸጡም አይቀርም «ማተብ» ግን ግድ ነው።ማድጋ ማተብ ከሌለው አያምርም «እስላሙን» ይሆናል። ማተብ ያላደረገ አንገት አያምርም። ደሞ ዘጌ ያለው ሸክላ ሰሪ ሁሉ አማራ ስለሆነ ሁሉም ለማዲጋው «ማተብ» ያደርጋል ብለውኛል (30-8-1999)።

ሸክላ ሰሪዎች በሰሯቸው ዕቃዎች ላይ ጌጥ ለመስራት የሚጠቀሙት እጣታቸውን፣ ሳር ወይም የቅጠል ስባሪ ነው። ጌጥ የመስራቱ ሂደትም ከአዋቂዎች ይልቅ በወጣቶች ይዘወተራል።

በአጠቃላይ ዕቃዎች ተሰርተው እንዳበቁ ከመድረቃቸው በፊት ጌጦች የሚወጡላቸው ሲሆን የጌጦች ጥቅም የዕቃዎችን ውበት ለመጨመር ነው። ነገር ግን በዕቃዎች ላይ ጌጥ ማውጣት እንደ ባለሙያዎች ፍላጎት የሚወሰን እንጂ የግድ አይደለም።

### 6.3.4 የሸክላ ቁሶችን ማድረቅና ማቃጠል

የሸክላ ቁሶች ተሰርተው ካለቁ በኋላ በፀሐይ ደርቀው በእሳት ይቃጠላሉ። እንደ መረጃ ሰጪዎች ገለጻ ምንም እንኳን በየደረጃው ያሉ የሸክላ ስራ ሂደቶች ጥንቃቄን የሚፈልጉ ቢሆንም ተሰርተው ያበቁ የሸክላ ቁሶችን ማድረቅና ማቃጠል ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ድካም ያለበትና ብርቱ ጥናቃቄን የሚፈልግ የሸክላ ስራ ደረጃ ነው።

ማድረቅ ከማቃጠል ይቀድማል። ሆኖም ዕቃዎችን በማድረቅም ሆነ በማቃጠል ሂደት ለዕቃዎች የሚሰጠው ሙቀት ቀስ በቀስ ከፍ እያለ የሚሄድ ነው። በመሆኑም ቁሶች ተሰርተው እንዳበቁ ጠፈፍ እንዲሉ ነፋስ ላይ ይቀመጣሉ። ነገር ግን ቀጥተኛ ንፋስ ሊያገኛቸው ስለማይገባ (ካገኛቸው ሲቃጠሉ ይሰነጠቃሉ) ነፋስ ከሚነፍስበት

አቅጣጫ በተቃራኒው ወይም ነፋሱን ሊከላከል የሚችል ነገር ባለበት ከአጥር ወይም ከቤት ጀርባ ይቀመጣሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ነፋስ ሲያደርቅ የሚችለውን ያህል ካደረቃቸው በኋላ በእሳት ከሚቃጠሉበት አንድ ቀን ቀደም ብሎ እስካለው ቀን ድረስ በፀሐይ እንዲደርቁ ይደረጋል፡፡ ከሚቃጠልበት ቀድሞ ባለው አንድ ቀን ደግሞ ከፀሐይ ተከልክለው ነፋስ ላይ ይሆናሉ፡፡

በዚህ መሠረት ሸክላ ሰሪዎች የሸክላ ቁሶችን ለማቃጠል ወደ እሳት ከማስገባታቸው በፊት በሸክላው ውስጥ ያለው እርጥበት ሙሉ በሙሉ እስኪጠፋ ድረስ የሸክላ ቁሶችን በነፋስና በፀሐይ ያደርቋቸዋል፡፡ ቁሶች ለመድረቅ የሚፈጅባቸው ጊዜ በወቅቱና (ክረምትና በጋ) በዕቃው መጠን ይወሰናል፡፡ በበጋ ወቅት ትንንሽ ዕቃዎች በሁለት ቀናት ውስጥ ሲደርቁ ትልልቅ ዕቃዎች ደግሞ በሦስትና አራት ቀናት ውስጥ ይደርቃሉ፡፡ በክረምት ወቅት ደግሞ የማድረቁ ስራ ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ሲሆን እንደ ባለሙያዎች ገለጻ ከሁለት ሳምንት በላይ ይፈጃል፡፡ በአንድ ጊዜ የሚቃጠሉት ዕቃዎች ቁጥርም ከበጋው ያነሰ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የክረምት ዕቃዎች ከበጋ ዕቃዎች ይልቅ ሲቃጠሉ ይሰነጠቃሉ፡፡

የሆነው ሆኖ በየትኛውም ወቅት የሚቃጠሉ የሸክላ ዕቃዎች በቅድሚያ በውስጣቸው ያለው እርጥበት ጨርሶ መጥፋት አለበት፡፡ ይህ መሆኑን ደግሞ ባለሙያዎች ራሳቸው ከረጅም ጊዜ የስራ ልምዳቸው የተነሳ ያውቁታል፡፡ ዕቃው ለመቃጠል መድረሱን በምን ታውቃላችሁ ሲባሉ ግን «ይታወቃል መልኩ ሸሮ ዱቄት/አመድ ይመስላል» ይላሉ፡፡ በመሆኑም ቁሶች ለመቃጠል ዝግጁ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ማቃጠሉን ለመጀመር እሳት ያነድዳሉ፡፡ ማገዶዎች ኩበትና እንጨት ናቸው፡፡ ባለሙያዎች የሸክላ ቁሶችን የሚያቃጥሉበት ቦታ የተወሰነ ነው፡፡ በየጊዜው አይቀያየሩም፡፡ በዚህ ስፍራ ምግብ ነክ ነገሮች አይቀርቡም በመሆኑም በፀሐይ የደረቁ ቁሶችን ለማቃጠል በፈለጉ ጊዜ በዚህ ቦታ እሳት ያነድዱና ቁሶችን ያቀርባሉ፡፡

ቁሶች በእሳት ሲቃጠሉ ቀስ በቀስ ነው ሙቀቱን እንዲለምዱት የሚደረገው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ይሰነጠቃሉ፡፡ በመሆኑም የተሰሩት ቁሶች ሁሉ በነደደው እሳት ዙሪያ ተደርድረው የእሳቱ ሙቀት እንዲያገኛቸው ይደረጋል፡፡ ከዚህ በኋላ ኩበቱ በደንብ ሲቀጣጠል እሳቱ እየተጫረ ቁሶቹ ውስጥ ይደረጋል፡፡ በዚህም ሁኔታ እሳቱ እንዳይጠፋ እንጨትና ኩበት እየተጨመረ ዕቃዎች ለአንድ ሰዓት ያህል ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ድስቶች ከሌሎች ዕቃዎች በተለየመልኩ ወደእሳቱ ከመቅረባቸው በፊት ውስጣቸው በወፍራሙ በተቦካ ቀይ አፈር ይቀባሉ፡፡ይህም ተቃጥለው ካበቁ በኋላ ወጥ ሲሰራባቸው ወጡን (እንዳያዳፍቁት) እንዳያበላሹት ነው ብላኛለች ይህንን ስታደርግ ያገኘኋት ወ/ሮ ውዴ ሙጨ የተባለች የ30 ዓመት የሸክላ ስራ ባለሙያ፡፡

በዚህ ሁኔታ ቁሶች ቀስ በቀስ በእሳቱ ሲቃጠሉ ባለሙያዎች ከጎን ቀጫጭን እንጨቶችን አመቻችተው በመደርደር የእንጨት መደብ ይሰራሉ። በኋላም ለአንድ ሰዓት ያህል ከእሳት አጠገብ ተቀምጠው በላያቸው ላይ ፍም ተቀምጦባቸው የነበሩትን የሸክላ ዕቃዎች አንድ በአንድ እያመጡ «መደቡ» ላይ እያመቻቹና ማዲጋዎችን (እንስራዎችን) አንገት ለአንገት እያደጋገፉ ያስቀምጧቸዋል። ትልልቅ ዕቃዎች ከታች ትንንሾች ደግሞ ከትልልቆቹ ላይ ተደራርበው ይቀመጣሉ። በዕቃዎች አቀማመጥ ምክንያት የተፈጠረ ክፍት ቦታ ሁሉ በትንንሽ ዕቃዎች ይሸፈናል። ከዚያ በዕቃዎች ዙሪያ ከታች ካለው እንጨት ጋር እንዲያያዝ ሆኖ እሳት ይነድዳል። ከዚያ በኋላ ዕቃዎች ተመቻችተው መቀመጣቸውና ሁሉም እሳት በአግባቡ እንደሚደርሳቸው ሲረጋገጥ በሳር ይሸፈናሉ። ይህም «ማዳፈን» ይባላል። ሳሩ ከታች በሚነሳው እሳት ይያያዝና ዕቃዎች ከታችም ከላይም እሳት ያገኛቸዋል። በዚህ ሁኔታ ለአንድ ሰዓት ያህል እሳቱ ይነድድና ሳሩ ይገለጣል ዕቃዎችም እስኪቀዘቅዙ ድረስ በተቃጠሉበት ቦታ ይቆያሉ።

ወቅት፣ የእንጨት መኖርና አለመኖር፣ እንዲሁም ገበያ በአንድ ጊዜ ሊቃጠል የሚገባውን የሸክላ ዕቃ ቁጥር ይወስኑታል። ከነዚህ ጉዳዮች አንጻር አንድ ሸክላ ሰሪ በአንድ ጊዜ ከ10-20 የሚደርሱ የሸክላ ዕቃዎችን ታቃጥላለች።

በምዕራፍ አራት የባህረ ሰላጤዋ ዳራ ሲገለጥ እንደተጠቆመው የሰላጤዋ አጎራባች በሆኑ ገጠሮች ለምሳሌ ወንጀጣ፣ ሰቀለጥ፣ ይጎዲ - - - (የሰላጤዋን ካርታ ይመልከቱ) የሚኖሩ ሰዎችና ራሳቸው ዘገኞች የሚገበያዩበት ገበያ በሳምንት ሁለት ቀን ማክሰኞና ቅዳሜ ይውላል። በመሆኑም ሸክላ ሰሪዎች እንደገበያው ሁኔታ በሳምንት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ የሸክላ ዕቃዎችን ሊያቃጥሉ ይችላሉ። ለምሳሌ በመጀመሪያው ማክሰኞ ሁሉንም (በአብዛኛው) እቃዎች ተሸጨው ከሆነ ለቅዳሜ ገበያ ሲባል አርብ የግድ ሌሎች የሚቃጠሉ ይኖራሉ። ማክሰኞ አልተሸጡ ከሆነ ግን ቅዳሜ ቀደም ሲል የተቃጠሉት እስኪሸጡ ድረስ ሌሎች አይቃጠሉም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በሳምንት ሁለት ጊዜ ላለማቃጠል ሲባል እሁድ ለሁለቱም ቀናት ገበያ የሚበቁ ዕቃዎች ሊቃጠሉ ይችላሉ።

እንደባለሙያዎች ገለጻ ሸክላዎች በእሳት ውስጥ በመግባታቸው፣ ከመግባታቸው በፊት የነበራቸውን ጥቁር ቀለም ለውጠው ቀይ ቀለም ይዘው ይወጣሉ። ከቀለማቸው ባሻገር ግን በመቃጠላቸው ምክንያት ጠንካራ ይሆናሉ። የተለመደ ተግባራቸውንም (ውሃ መቅዳት፣ ጠላ ማስቀመጥ፣ በእሳት መጣድ ወዘተ)፣ «በቀላሉ» ሳይሰበሩ እንዲወጡ ይረዳቸዋል።

በአጠቃላይ በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሸክላ ቁሶች አሠራር፤ አፈር መቆፈርና ቁሶችን ለመስራት ማዘጋጀት፣ የሸክላ ቁሶችን ቅርጽ እንዲይዙ ማድረግ፣ ቁሶችን ማስጌጥ፣ ቁሶችን ማድረቅና ማቃጠል የሚባሉ ጥንቃቄን የሚጠይቁ ሂደቶች አሉት።

## 6.4 የሸክላ ስራ ባለሙያዎች

እንደ Graves (1991) ና Rice (1987) ያሉ ምሁራን በየትኛውም ቦታ ያሉ የሸክላ ስራ ባለሙያዎች ሙያውን የለመዱበት ሁኔታና ያለመዳቸው ሰው በሚሰሯቸው የሸክላ ቁሶች ላይ የሚፈጥረው ልዩነት አለ ሲሉ ሃሳባቸውን ይሰነዝራሉ። ከዚህ አንጻር በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚኖሩ ባለሙያዎችንና ሙያውን የለመዱበትን መንገድ ለማወቅ ባደረግሁት አሰሳ በሰላጤው ውስጥ አፋፍ 01 ቀበሌ፣ ጋሚና፣ ሰጎዳ በተባሉ ቦታዎች በጠቅላው 14 የሸክላ ስራ ባለሙያዎች እንዳሉና ዋሻ በሚባል የሰላጤው ጎጥ ውስጥ ደግሞ ከዚህ በፊት ሸክላ ሰሪዎች እንደነበሩ አሁን ግን ብዙዎቹ ሃገር ለቅቀው እንደሄዱ ጥቂቶቹ ደግሞ ስራውን እንደተውት አረጋግጫለሁ።

የሙያውን ለመዳ በተመለከተ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው የሸክላ ባለሙያዎች የልምምድ መንገድ ሁለት አይነት መሆኑን ነው። በሰላጤዋ ውስጥ ከሚገኙት 14 የሸክላ ስራ ባለሙያዎች ሰባቱ ሙያውን ከጎረቤቶቻቸው የተማሩት ሲሆን ሦስቱ ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የተቀበሉት፤ አራቱ ደግሞ እናቶቻቸው ከጎረቤት ተምረው ያስተማሯቸው ናቸው። በአጠቃላይ በሰላጤዋ የሸክላ ባለሙያዎች የሙያ ለመዳ ሦስት መልክ ያለው ነው።

ሙያው ከቀደምት አያቶቻቸው ሲወርድ መጥቶ እነሱ ጋር የደረሰው ባለሙያዎች በአካባቢው ነዋሪዎችና በሌሎች ሸክላ ሰሪዎች ዘንድ የሙያው ባላባት ተደርገው ይቆጠራሉ። እነዚህ ሰዎች እስራኤላዊ ዘር ያላቸው ናቸው። እንደሚናገሩት መቼ እንደሆነ ባያውቁም እናቶቻቸው[10] ጎንደር አካባቢ ከሚኖሩ እስራኤላዊ ዘር ካላቸው ወገኖቻቸው ተለይተው ወደ ዘጌ የገቡ በጋብቻ ምክንያት ነው። ሲመጡም ሙያውን ይዘውት ገብተዋል። ከዚያም ለዘመናት ያህል ሙያው ከልጅ ልጅ እየተወራረሰ እስከ አሁን ድረስ በሰላጤዋ ውስጥ ሊዘልቅ ችሏል። ነገር ግን የሙያውን ህልውና ተጠብቆ ሊኖር የቻለው ሙያውን ከቤተሰብ ከወረሱት ይልቅ ከጎረቤቶቻቸው በተማሩት ሰዎች አማካይነት ነው። ምክንያቱም ዛሬ ዛሬ በሰላጤዋ ውስጥ ካሉት ሸክላ ሰሪዎች ውስጥ ቁጥራቸው ብዙ የሆኑት ሙያውን ከጎረቤቶቻቸው የተማሩት ናቸው። ይህም የሆነበት

---

10 «በዚህ ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ፈላሻዎች በኢትዮጵያ መኖራቸውና. . . . እነዚህም በአብዛኛው በሰሜን ምዕራብ የጐንደር ክ/ሀገር ተበታትነው ይኖሩ እንደነበረ ይታወቃል» (እምሩ፣ 1984:113)።

ምክንያት በሰላጤው ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ብዙ (ሁሉም ማለት ይቻላል) እስራኤላዊ ደም ያላቸው ሰዎች እስራኤል በምታደርገው «በየቦታው የተበተኑ ህዝቦቿን የመሰብሰብ ተግባር» ወደ እስራኤል ሄደው አልቀዋል(በሰላጤው ውስጥ ያሉ እስራኤላውያን ሸክላ ሰሪዎች ብቻ ናቸው)። ያሉትም ቢሆኑ 1ኛ.ዕድሜያቸው ስለገፋ 2ኛ. የሄዱ ዘመዶቻቸው የገንዘብ ድጋፍ ስለሚያደርጉላቸው ስራውን አቁመዋል። በዚህ ምክንያት አሁን በሰላጤው ውስጥ የሚገኙ ሙያውን በዘር ለምደው የሚሰሩ ሰዎች ሦስት ብቻ ናቸው። እነሱም ዕድሜያቸው ከ50 ዓመት በላይ ነው። እነዚህ ሰዎች ሙያውን እንዴት ለመዳችሁት ተብለው ሲጠየቁ ሙያውን ለመልመድ ብለው ሳይሆን የለመዱት ሲሰራ እያዩ በማደጋቸው ምክንያት እንደለመዱት ይናገራሉ። መቼ እንደተማሩት አያውቁም ነገር ግን እናቶቻቸው ሲሰሩ በማየት ዕቃዎችን በማቀራረብና የአፈር ሸክሙን በማገዝ በስራው ላይ ሲሳተፉ እንደቆዩና ከሆነ ጊዜ በኋላ ራሳቸውን የሸክላ ስራ ባለሙያ ሆነው እንዳገኙት ይገልጻሉ። ለምሳሌ ወ/ሮ ፈንታ ገነት እንዴት ስራውን እንደለመዱት ሲናገሩ፡-

> የእናቴ እናትም፣ እናቴም ሸክላ ሰሪ ነበሩ። እኔ ሸክላ መስራት የለመድኩት ኩታራ[11] ሆኜ ነው። ሁል ጊዜ ከእህቶቼ ጋር ሆኜ ለእናቴ አፈር አመጣላት ነበር፣ እንጨት አለቅምላት ነበር። በኋላ ግን ቀስ በቀስ መስራት ተማርኩ። መጀመሪያ እሳቱን እየፈራሁ የምታቃጥልልኝ እናቴ ነበረች በኋላ ሁሉንም ለምጄ መስራት ቻልኩ። እስከአሁን ድረስም እሱን እየሰራሁ እንጀራ እበላለሁ ብለዋል ( 17-02-2000) ።

ሌሎች ስራተኞችም በዚህ መልክ ስራዬ ብለው ሳይማሩ የሙያው ባለቤት እንደሆኑ የሚናገሩ ሲሆን ሌሎች ሙያውን ከጎረቤት የለመዱት ደግሞ በተቃራኒው መተዳደሪያ ይሆነናል ብለው አስበው ስራዬ ብለው እንደለመዱት ይናገራሉ። ያም ሆኖ ግን ስራውን ስራዬ ብሎ ለመማርና እርሱንም መተዳደሪያ አድርጎ ለመቀጠል ያስቻላቸው ምክንያት አለ። ይኸውም ሁኔታውን ከመንግስት የተፈቀደ አድርጎ ከማሰብ ጋር የተያያዘ ነው። ይህም በ1969ዓ.ም የጎጆ ኢንዱስትሪን በተመለከተ ከወጣው አዋጅና ከተግባራዊነቱ ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው (Tolistykh,1988) ። እንደ ባለሙያዎቹ ገለጻ ይህ አዋጅ ለብዙ ሰዎች የሸክላ ስራ መልመድ ምክንያት ሆኗል። ምንም እንኳ ብዙ ሰዎች የሸክላ ስራውን ከጎረቤቶቻው ለምደው ቁሶችን በመሸጥ የቡና ምርት መመናመን ያደረሰባቸውን ድህነት ቢያንስ የዕለት ችግራቸውን መቅረፍ እንደሚችሉ ቢያውቁም ማህበረሰቡ ለሸክላ ሰሪዎች ያለው አመለካት የሚፈቅድላቸው ስላልሆነ ሙያውን ሊማሩት ተምረውም ሊሞክሩት አልደፈሩም። በኋላ ግን አዋጁ ሁሉንም ነገር እንደቀየረው ይናገራሉ። በሰላጤዋ ውስጥ በጋሚ ጎጥ የሸክላ ስራ ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ በተሐ ካሳ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልጹ፡-

---

[11]. ኩታራ- በጉጃም ዘዬ ትንሽ ልጅ የሚል ትርጉም አለው።

> መንግስቱ ኃ/ማርያም ሁሉም ስራ እኩል ነው:: የሚናቅ ስራ የለም ካለ በኋላ ሽክላ የሚሰራው ሽክላ፣ ጣውላ የሚሰራው ጣውላ፣ ሽማቃ የሚሰራው ሽማቃውን በይፋ መስራት ጀመረ:: እኔ ሙያውን የለመድኩት በዘርዋ ሽክላ ሰሪ ከሆነች ጎረቤቴ ነው:: በእርግጥ መንግስት ይህንን ስራ ስሩ ሙያ ክቡር ሲል እንድንሰለጥን ባህርዳር ጎማጣ (ጎልማሶች ማሰልጠኛ ጣቢያ) ብዙ ሴቶች ወስዶ ነበር:: ነገር ግን እኔ ባህርዳር እንደደረስኩ ስላመመኝ ሁሉንም ነገር ትቼ ተመለስኩ በኋላ ግን ጥንት ከዘሮቿ ሙያውን ከለመደች ጎረቤቴ ለመድኩት:: እንዲያውም ከሰለጠኑት ሴቶች ተመልሶ መጥቶ ሽክላ ሰሪ የሆነ የለም:: እዚህ ያለነው ብዙዎቻችን ግን ከጎረቤቶቻችን እያየን መስራት ተማርን:: መንግስት ሙያ ክቡር ነው ማለቱ ሙያ ኖሮን እንጀራ እንድንበላ አድርጎናል ይላሉ (28-8-1999 ዓ.ም) ::

ይሁን እንጂ ሽክላ ስራን ከቤተሰብ የተቀበሉትም ሆኑ ከጎረቤቶቻቸው የተማሩት ሰዎች ሙያውን ለልጆቻቸው ማስተላለፍ እንዳልቻሉ ነው የሚናገሩት:: ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ሽክላ ስራ እጅግ አድካሚ በመሆኑ ልጆች በእርሱ ከሚንገላቱ ይልቅ ዘመናዊ ትምህርት ቢማሩ እንደሚሻል ስለመረጡ ነው:: በዚህ ምክንያት ልጆች በራሳቸው ጊዜ ሙያውን ካልለመዱት በስተቀር ፈቅዳ ሙያውን ለልጆቿ የምታስተላልፍ እናት የለችም::

ይህ ሁኔታ የስራውን ህልውና የሚፈታተነው ሲሆን አልፎ አልፎ ግን የራሳቸው ገንዘብ እንዲኖራቸው የሚፈልጉ የተወሰኑ ወጣቶች በስራው ላለ ተሰማርተዋል:: የእነሱ መጨመር ነው በሰላጤዋ የሚኖሩ የሽክላ ስራ ባለሙያዎችን ቁጥር 14 ያደረሰው:: ለምሳሌ ወ/ሮ ውዴ ሙጬ የ30 ዓመት ወይዘሮና የሽክላ ስራ ባለሙያ ናት:: ሙያውን የለመደችው ከእናቷ ነው:: እናቷ ግን ይህንን ስራ ለማስተማር አትፈልግም ነበር፤ እንዳትሰሪ ስትልም ረግማታለች:: እሷ ደግሞ ስራውን መተው አትፈልግም:: ምክንያቱም ከባሏ ሁሉን ወጪ መቀበል አትፈልግም:: እሷ ግን ለሁለት ሴት ልጆቿ ሙያውን ማስተማር አትፈልግም የሽክላ ስራ «ቀለም ያጠፋል» (ውበት ያጠፋል) በዚህ ላይ እንዲህ ተሰቃይተሽ የምትሸጪበት ዋጋ በጣም ትንሽ ነው ትላለች:: እኔ እንዲህ ሆኜ እነሱም መሆን የለባቸውም ባይሆን ጠንክሬ አስተምራቸዋለሁ ትላለች:: ዳሩ ግን ልጆቹን እንዳየኋቸው የተሰሩ እቃዎችን በማቀራረብ፣ እሷ ስትሰራ አጠገቧ ሆነው የሚያስፈልጋትን በማገዝ ከስራው አካባቢ የማይጠፉ በመሆኑ ሙያውን ጨርሶ አይለምዱትም ማለት ይከብዳል::

ሽክላ ሰሪዎች የሚሰሯቸውን ቁሶች አስመልክቶ ከተጠቃሚዎች የተገኘው መረጃ ሙያውን ከቤተሰብ ካገኙት ይልቅ ተምረው የሰሩት ሰዎች ጥራት ያላቸውና ጌጣቸው ያማረ የሽክላ ቁሶችን እንደሚሰሩ ይገለጻል:: የዚህም ምክንያቱ ሙያውን ከጎረቤት የተማሩ ሰዎች መተዳደሪያ ይሁነኝ ብለው ነው የተማሩት በመሆኑም መተዳደሪያ እንደመሆኑ መጠን የተሻለ ገቢ ለማግኘት ጥሩ ዕቃ መስራት አስፈላጊ ነው የሚል መረጃ ነው ከባለሙያዎችም ሆነ ከተጠቃሚዎች የተገኘው::

በሰላጤዋ ውስጥ ሸክላ ስራ ሙሉ በሙሉ የሴቶች ስራ ነው:: አንድም ወንድ የሸክላ ስራ ሲሰራ አላየሁም (በአፈር ማምጣቱ ግን ወንድ ልጆች ይሳተፋሉ):: ወንዶች አይሰሩምወይ ብዬ ላቀረብኩት ጥያቄ ከባለሙያዎችም ሆነ ከተጠቃሚዎች ያገኘሁት መልስ «ምነው ያስ አባት!?»የሚል አግራሞት የተቀላቀለበት መልስ ነው:: የአግራሞታቸውን ምክንያት አስመልክቶ መልስ ያገኘሁት ከሁለት ወገን ነው:: አንዱ ሙያውን በልምድ ካገኙትና ከተጠቃሚዎች ሲሆን እነሱ «ሸክላ ስራ ለሴት ብቻ ያበጀለት» (እግዚአብሔር ለሴቶች የሰጣቸው ስራ) ነው ይላሉ:: ሁለተኛው ወገን ግን ግልፅ ባልሆነ መንገድ ሙያውን ከዘራቸው ከወረሱና ማህበረሰቡ ፈላሻ ብሎ ከሚጠራቸው ወገኖች የሰማሁትና በኋላ እውቀቱ ይኖራቸዋል ብዬ ከጠየኳቸው ሰዎች ያገኘሁት ነው::

ይህ ቡድን ሸክላ ስራ የእስራኤላውያን ሃብት መሆኑን አምኖ ነው ሙያው ለምን የሴቶች ብቻ እንደሆነ የሚገልፀው:: እስራኤላውያን በግብፅ ምድር በነበሩ ጊዜ የግብፅ ህዝቦች ጡብና ጭቃ በማሰራት በፅኑ ያሰቃዩአቸው ነበር:: በዚህ ጊዜ ግን ወንድ ልጅ የተወለደ እንደሆነ ህዝቡን ነፃ ያወጣዋል ብሎ ስለፈራ የግብፅ ንጉስ (ፈርኦን) ወንድ የተወለደ እንደሁ ይገደል:: ሴት ከሆነች ግን ትኑር ብሎ አዋጅ አወጣ[12] :: እናም ያኔ በህይወት የመኖር መብት የነበራቸው ሴቶች ስለነበሩ የሸክላ ስራው ይሰራ የነበረው በሴቶች ብቻ ነበር:: ያም ሙያውን የሴቶች እንዲሆን አደረገ ልምዱም በዛው ቀጠለና ኢትዮጵያ ውስጥ የመጡ እስራኤላውያንም በልማዳቸው መሰረት ሙያውን ለሴት ልጆቻቸው ሲያስተላልፉ ኖሩ:: ከጐረቤቶቻቸው የተማሩትም ቢሆኑ ሙያውን ብቻ ሳይሆን ልሙዱንም «ከባለቤቶች» ተቀብለው ዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ ሸክላ ስራ አሁን ድረስ የሴቶች ብቻ ሙያ ነው::

በአጠቃላይ በዘጌ ባህረ ሰላጤ በጠቅላላው 14 ሸክላ ሰሪዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ሦስቱ ሙያውን በቤተሰብ ደረጃ ቀሪዎቹ ደግሞ ከጎረቤት የተማሩ ናቸው:: የሚሰሩ የሸክላ ቁሶችን ጥራት አስመልክቶም ሙያውን ከጎረቤት የተማሩ ሰዎች ከቤተሰብ ካገኙት በተሻለ ጥራት ይሰራሉ::

## 6.5 የሸክላ ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃ

Silverman (1999) እና Freeman and Alula (2001) ስለ ኢትዮጵያ የእጅ ስራ ባለሙያዎች ሁኔታ ሲገልጹ ቁሶችን የሚያመርቱ ሰዎች ማህበራዊ ደረጃቸው ከባህል ባህል የሚለያዩ ቢሆንም በአብዛኛው ግን ቡድኖቹ የራሳቸውን መንደር መስርተው እስከሚኖሩ ድረስ በሌላው ማህበረሰብ የተገለሉ ናቸው:: ለዚህም ምክንያቱ ሌላው

[12] ሙሉ ታሪኩን በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፀአት ምዕ1 ቁ.1-22ን ይመለከቷል::

ማህበረሰብ «ባለሙያዎች ልዕለ ሰው ተፈጥሮ ያላቸው ናቸው» ብሎ ስለሚያስብ እንደሆነ ይገልጻሉ።

እንደዚሁ ሁሉ ወደ ዘጌ ባህረ ሰላጤ የሸክላ ስራ ባለሙያዎች ሲመጣ ከዚሁ ሃሳብ ጋር የሚመሳሰል ሁኔታ ነው የሚታየው። በእርግጥ ማህበረሰቡ እነዚህን ባለሙያዎች በዘር ሸክላ ሰሪ የሆኑና የተማሩ ሲል በሁለት ከፍሎ ነው የሚያያቸው።

ከዚህ ክፍፍል አንጻርም ሙያውን በዘር ከወረሱት ይልቅ የተማሩት ሰዎች የተሻለ ክብር አላቸው። ከሌላው ማህበረሰብ ጋር አብሮ የመብላት፣ የመጠጣትና አበልጅ የማንሳት ዕድል ያለው ይሄኛው ክፍል ነው።

ሙያውን በዘር ወደወረሱት ሰዎች ስንመጣ ግን ይህኛው ቡድን በሌላው ማህበረሰብ እጅግ የተገለለ ሆኖ ነው የሚገኘው እንዲያውም ማህበረሰቡ ለእነዚህ ወገኖች «ቡዳ» የሚል ስያሜ ሰጥቷቸዋል። የፈለጉትን ሰው የማሳመም ብሎም የመግደል ኃይል እንዳላቸው ይገለጻል። እንዲያውም ይህን አመለካከት የሚያጠናክር እምነት አላቸው። (እምነቱ፣ ወደ ኋላ «ማህበረሰቡ ስለሸክላ ሰሪዎች ያለው አመለካከትና እምነት» በሚል ርዕስ ይገለፃል) ከዚህም የተነሳ ማህበረሰቡ ከነዚህ ወገኖች ጋር አብሮ መብላት መጠጣት አበልጅ ማንሳትና ጋብቻ መፈጸም አይፈልግም። ጋብቻ የፈጸመ እንኳን ቢገኝ ይወገዛል።

ሌላው ይቅርና የማህበረሰቡ አባላት የሸክላ ዕቃዎችን እንኳን በዘር ከወረሱት ይልቅ ከተማሩት ነው መግዛት የሚያዘወትር። ለዚህም ምክንያቱ «ቡዳዎች ሰውን የሚጎዱት በዓይናቸው በመሆኑ ላለመታየት ሲሉ ነው» በሌላ በኩል ደግሞ በዘር ሙያውን ከወረሱት ይልቅ በትምህርት ያገኙት ባለሙያዎች በቅርጽና በጥንካሬ የተሻሉ የሸክላ ዕቃዎችን የሚሰሩ መሆኑ የገበያው ሁኔታ ወደ ተማሩት እንዲያዘነብል አድርጎታል።

የባለሙያዎችን ክፍፍል በተመለከተ ማህበረሰቡ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ባለሙያዎቹም ትኩረት ይሰጣሉ። በዚህ መሠረት ሙያውን ከጎረቤቴ ተማርሁት የሚሉት ወ/ሮ በተሃ ካሳ እኔ ሙያውን የተማርሁት እንጂ ከዘር የመጣ ባለመሆኑ አላፍርበትም። በእርግጥ በዘር የተወረሰ ቢሆን ሰው ስለማያስጠጋ ሊሳፍር ይችላል ይላሉ (28-8-1999)።

እነዚህ ባለሙያዎች (ከቤተሰብ የወረሱትም ሆነ ከጎረቤት የተማሩት) የሸክላ ስራው እንጀራቸው ነውና ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ያስተዳድሩበታል፣ ልጆቻቸውን አስተምረው ራሳቸውን አስችለውበታል አሁንም እየሰሩና እያስተማሩበት ነው በመሆኑም ስራውን አክብረው እየሰሩት ይገኛሉ። ነገር ግን ወደ ልጆቻቸው ሲመጣ ልጆች ለሙያው ያላቸው አመለካከት በሙያው ህልውናና ቀጣይነት አስጊ ሁኔታ እየፈጠረበት እንደሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው። በእርግጥ አንዳንድ ልጆች የሸክላ አፈሩን

በመቆፈር፣ ተሸክሞ ወደ ቤት በማምጣት ወላጆቻቸውን ያግዛሉ:: ነገር ግን ብዙዎች ወላጆቻውን በስራ ማገዝ ይቅርና ወላጆቻቸው ሸክላ ሰሪዎች መሆናቸው በሌሎች ሰዎች ዘንድ እንዲታወቅ አይፈልጉም:: ይህንን ሁኔታ በተመለከተ ያነጋገርኳቸው አንዳንድ ልጆች እንደገለጹልኝ በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ በሰፈር ቤቶቻችን የሸክላ ስራ ባለሙያዎች መሆናቸው ከታወቀ በዘርም እንኳን ባይኖርብን «የፈላሻ ልጅ» የሚባል ስድብ ከጓደኞቻችን ይመጣብናል:: ጓደኞቻችንም ሊቀርቡን አይፈልጉም:: ስለዚህ ወላጆቻችን ሸክላ ሰሪዎች መሆናቸውን ለማንም አንገልጽም ብለዋል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ በገበያ ውስጥ የሸክላ ዕቃዎችን ሲሸጡ ያገኘኋቸው አንዲት ወ/ሮ፣ ሴት ልጃቸው ስለ እሳቸው ሙያ ያላትን አመለካከት እንደሚከተለው ገልጸዋል:-

> ልጄ የ18 ዓመት ወጣት ናት፣ በምንም ተአምር ከእኔ አጠገብ ቆማ ሸክላ መሸጥ አትፈልግም:: ምክንያቱም ይህንን ካደረገች የክፍል ጓደኞቿና መምህሮቿ የሸክላ ሰሪ ልጅ መሆኗን አውቀው እንዳይንቋት ትፈራለች:: እንዲያውም አንድ ቀን ገበያ ውስጥ ከአጠገቤ ቆማ መምህሯ ሰላያት የምትገባበት ጠፍቷት «መሬት ተከፍታ ብትውጣት በወደደች» ይህንን ሀሳቧን ግን በፍጹም ማስቀየር አልቻልኩም አሁን ከእኔ ጋር ዝምድና ያላት መሆኑ እንዳይታወቅ ስትል ከእኔ ርቃ ሸንኩርትና ድንች ትሸጣለች (ወ/ሮ በተሃ ካሣ:23-02-2000) ::

ከዚህ በተረፈ ደግሞ ብዙ ባይሆኑም የሸክላ ስራውን አስመልክቶ ከማህበረሰቡም ሆነ ከራሳቸው ከባለሙያዎች የሚባሉት ጥቂት ቃል ግጥሞች ሙያውም ሆነ ባለሙያዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ዝቅተኛ ደረጃ የሚያሳዩ ናቸው:: ቀጥሎ ምሳሌ የሚሆኑ 6 ቃል ግጥሞች ቀርበዋል:: የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ማህበረሰቡ የሚላቸው ቀጣዮቹ ሶስት ደግሞ ባለሙያዎች የሚሏቸው ቃል ግጥሞች ናቸው::

ቢኖራት ነው እንጅ አንዳች ብልሃት
አፈር አቅም ኑሮት የሚቆምላት

ይህ ቃልግጥም ሸክላ ዕቃዎች ከአፈር የሚሰሩ መሆኑን ይገልፃል:: ሆኖም ገጣሚው የአፈር ወደ ዕቃነት መቀየር አስገርሞታል:: አፈሩ እንዴት ቆመ ብሎ ሲያስብ ግን ሰሪዋ ከሌላው ሰው የተለየ ችሎታ ስላላት ነው የሚል መልስ ለራሱ ሰጥቷል:: ይህንን ችሎታም «ብልሃት» ሲል ይጠራዋል:: ነገር ግን ይህንን ችሎታ ጥበብ ነው፣ ጉብዝና ነው ሲል አይደለም የሚያደንቀው ሌላው ሰው ማድረግ የማይችለውን ነገር ያስደረጋት አንዳች እኩይ ነገር በውስጧ አለ ሲል ስለ ባለሙያዋ ችሎታ ያለውን እምነት ይገልፃል:: ቀጣዩ ስነቃልም ባለ ሙያዎችን የሚሰድብ ነው::

የአንበሳ ልጅ ሞቶ የጅብ ልጅ ገነነ
አላስቀምጥ አለ ጠጉሩ እየበነነ

ይህ ቃል ግጥም ደግሞ አንበሳና ጅብን እያወዳደረ የአንዱን መድከም የሌላውን ደግሞ ሃያል መሆን ይናገራል:: ማህበረሰቡ እንደሚስማማበት አንበሳ ሃያል ነው:: አሁን

ግን እሱ ስለሞተ ጅብ ሃያል ነኝ ብሎ እንዳሰበና ከዚህ በላይ ደግሞ ሌላውን ጤና እንደነሳ ግጥሙ ይናገራል:: ይሁን እንጂ እዚህ ላይ አንበሳና ጅብ ተምሳሌቶች ናቸው:: ማህበረሰቡ ሸክላ ሰሪዎችን ቡዳዎች ናቸው ሌሊት ሌሊት ጅብ ይጋልባሉ ይላቸዋል:: ይህ ግጥም ደግሞ በደርግ መንግስት «መሬት ላራሹ» ሲታወጅ ባላባቶች መሬታቸውን ተነጥቀው ለሁሉም እኩል ከተከፋፈለ በኋላ የእነሱን አንገት መድፋት፣ እንዲሁም ስራ ክቡር ነው በሚል ሁሉም ሰው የእጅ ስራ መልመድ ሲጀምር ሸክላ ሰሪዎችም ከተናቁበት ራሳቸውን ቀና ቀና ማድረግ መጀመራቸው ተከትሎ የተገጠመ ነው:: በመሆኑም የአንበሳ ልጅ ሲል ባለሃብቶችን ያሞካሸና እነሱ ዝቅ ሲሉ «የጅብ ልጅ» ሲል የሚጠራቸውን ሸክላ ሰሪዎች «ቀን ወጣላቸው» ይላል:: በመሆኑም እነዚህ ወገኖች «ማንነታቸውን» አውቀው እንዲቀመጡ በቀጣዩ ቃል ግጥምም ይነገራቸዋል::

ፋቂ ደበል አንሣ አፈር አላቂጭ
አለሁ አለሁ አትበይ አርፈሽ ተቀመጭ

ይህ ግጥም የተገጠመበት ጊዜ የላይኛው ግጥም በተገጠመበት ወቅት እንደሆን የቃል መረጃዎች ይገልፃሉ:: ግጥሙ የእጅ ስራ ባለሙያዎችን ሁሉ መቅለል አድርጎ ጠርቶ ራሳቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ ይናገራል:: ይህም መንግስት ሁሉም ስራ እኩል ነው የሚል መመሪያ አውጥቶ ባለሙያዎች በሙያቸው መኩራት ሲጀምሩ ማኅበረሰቡ ግን አይሆንም አርፋችሁ ተቀመጡ ሲል ሞራላቸውን ያኮላሸበት ነው::

ማህበረሰቡ በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ ቃል ግጥሞች ለባለሙያዎች ያለውን አመለካከት ሲገልፅ ባለሙያዎችም ቢሆኑ የሚሉት ቃል ግጥሞች አሉና ቀጥለን እንያቸው:-

እብን አንሳ ማለት ዕውቀቱ ጠፍቷቸው
ደበል አንሳ አሉኝ እግዚሔር ያንሳቸው::

ማህበረሰቡ ባለሙያዎችን በተለይም ቆዳ ሰራተኞችን «ደበል አንሳ» ሲል ይጠራቸዋል:: ባለሙያዎች ግን «ይህ ስያሜ ከእውቀት ማነስ የተሰጠን ነው:: ሰው ዕውቀት ስለሌለው ነው እንጅ እኛ እብን አንሳ ነን፤ እብን ማለት ድንጋይ ማለት ነው:: ድንጋይ ደግሞ ምንም የማያውቅ ነው:: እኛ ምንም ዕውቀት ለሌላቸው ድንጋዮች ዕቃ ሰርተን እየሰጠናቸው እኛ በሰራነው ዕቃ ይበላሉ ይጠጣሉ እነሱ ግን ይህንን ማድረግ አይችሉም:: ስለዚህ ዕውቀት የላቸውምና ቢሞቱ ይሻላል» ይላሉ::(ወ/ሮ ታሪክ ገነት:4-02-2000) እነዚህን «ዕውቀት የሌላቸውን ሰዎችም» ስለሚንቁ አቻ ካቻ እንግባባ በሚል የጣዩ ቃል ግጥም በሸክላ ስራ ባለሙያዎች ተገጥሟል::

አንተ ብረት ቀጥቅጥ እኔ ሸክላ ልስራ
ምን ያዳርቅሃል ከደንቆሮ ጋራ

ግጥሙ የስራ ክፍፍልን ያሳያል፡፡ ሸክላ ሰሪዋ የብረት ሰራተኛውን አንተም ሙያ አለህ እኔም የራሴ ሙያ አለኝ፡፡ ስለዚህ አንተ እና እኔ ሁለት ባለሙያዎች አብረን እንኑር እንጂ ምንም ዕውቀት ከሌላት ሴት ጋር መኖር የለብህም ትለዋለች፡፡ ሸክላ ሰሪዎች ስራ (ሙያ) የለውም የሚሉትን ማህበረሰብ «ደንቆሮ» ሲሉ ይጠሩታል፡፡ በመሆኑም ከደንቆሮ ጋር መኖር መድረቅ ነው እኔ ባለሙያዋ የኑሮ አጋርህ ልሁን ስትል የብረት ስራ ባለሙያውን ለትዳር ትጋብዘዋለች ፡፡ በቀጣዩ ቃል ግጥምም እሷ የሸክላ ስራ ሙያ ከሌላት ሴት የተሻለች እንደሆነች ትነግራታለች፡፡

መሳደቡን ትተሽ አዙረሽ እንድታይ

ደሞ እንደ ማዲጋው አንገት ልስራልሽ ወይ

የሸክላ ባለሙያዋ የሸክላ ባለሙያ ያልሆነችውን ሴት አታስተውይም ብታስተውይ ኑሮ እኔ በሰራሁት የሸክላ ዕቃ እንደምትገለገይ ስለምታውቂ አትሳደቢም ነበር፡፡ ስለዚህ እኔ ሙያውና ችሎታው አለኝና አዙረሽ የምታይበት አንገት ልስራልሽ ወይ ትላታላች፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደገለፁት በሰላጤው አዙሮ የማያይን ሰው ለመሳደብ «አንገት የለሽ» ይባላል፡፡

በአጠቃላይ በሰላጤው ውስጥ ከማህበረሰቡም ይሆን ከሸክላ ሰሪዎች አንጻር የተገኙት የተወሰኑ የቃል ግጥሞች ማህበረሰቡ ባለሙያዎችን የሚያንቋሽሽባቸው ሲሆኑ ሸክላ ሰሪዎች ደግሞ በተራቸው መልስ የሚሰጡባቸው ናቸው፡፡ ሆኖም ሁሉም ወገኖች የሚያጋጥሟቸው ቃል ግጥሞች በጠቅላላው ማህበረሰቡ ለሸክላ ስራ ያለውን ዝቅተኛ አመለካከት የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

## 6.6 ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ አውዶች

አንድ የፎክሎር ጥናት፣ፎክሎሩ የሚከወንበትን ማህበራዊ፣ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ አውድ በሚገባ መግለፅ አለበት ( ብርሃኑ: 1995፣ Dorson: 1983፣ Glassie;1999) ፡፡ በመሆኑም በዚህ ርዕስ በዘጌ ባህረሰላጤ የሚገኙ የሸክላ ቁሶች በማህበራዊ ፣በባህላዊና ኢኮኖሚያዊ አውዶች ያላቸውን መልክ የተቃኘ ሲሆን በንዑሳን ርዕሶች ደግሞ በማህበራዊ አውዶች፣ የባለሙያዎችና የተጠቃሚዎች ማንነት (ዘር፣ሃይማኖት፣ስራ ወዘተ)፣በመካከላቸው ያለው ተራክቦ፣አደረጃጀታቸው፣ማህበራዊ ተቋሞቻቸው፣በባህላዊ አውድ፣ የፎክሎሩ ባለቤቶች ፎክሎሩን የተረዱበት መንገድ፣በፎክሎሩ የተገለፀው የህይወታቸው ክፍል፣አገራዊ ዕውቀቶች የሚነሱ በኢኮኖሚያዊ አውድ ደግሞ የጥሬ ዕቃዎችና ያለቀላቸው ዕቃዎች ዋጋ፣የገዢዎች የኢኮኖሚ አቅም ወዘተ ሊጠኑ የሚገባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡

### 6.6.1 በማህበረ ባህላዊ አውዶች

Alula and Freeman (2001) እንደፃፉት የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ያላቸው ማህበራዊ ደረጃ ከቦታ ቦታ ይለያያል:: ያም ሆኖ በአብዛኛው ማህበረሰቡ ዝቅ አድርጐ የሚመለከታቸው ናቸው::

በዘጌ ባህረሰላጤ ማህበረሰቡ ለሸክላ ሰሪ ባለሙያዎች ያለው አመለካከት ከላይኛው ሃሳብ ጋር የሚመሳሰል ነው:: በግልፅ እንደሚታየው የሸክላ ቁሶች ለማህበረሰቡ የእለት ከእለትም ሆነ ለተለየ ጊዜ (ለበዓል፣ ለእምነት ወዘተ) እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: ይሁን እንጂ ማህበረሰቡ ለቁሶች የሚሰጠውን ክብር ግማሽ እንኳን ለባለሙያዎች መስጠት ይቸግረዋል:: በእርግጥ ይህ ሁኔታ በደርግ ዘመን ትንሽ መሻሻል እየታየበት የመጣ ጉዳይ ሆኖ ነበር:: ይህም መንግስት ለእደጥበብ ውጤቶችና ለሰሪዎች አድርጐ ከነበረው ትኩረት ጋር የተያየዘ ነው:: ብዙ ሰዎች ከጐረቤቶቻቸውና ከጓደኞቻቸው ሙያውን ለመማር በቅትዋል:: አሁንም ድረስ ይሰራሉ:: ዳሩ ግን እነዚህ ሰዎች «ሙያ ክቡር ነው» የሚለውን መርህም ሆነ ራሱን ሙያውን ለልጆቻቸው ለማመውረስ ከፍተኛ ችግር ገጥሟቸዋል:: ለዚህም ምክንያቱ ማህበረሰቡ ለሙያተኞች ያለው ዝቅተኛ አመለካከት ነው:: ማህበረሰቡ ሸክላ ሰሪዎችን ብቻ ሳይሆን እንደ ብረትና ቆዳ ሰራ ያሉ ባለሙዎችንም ዝቅ አድርጐ ይመለክታል:: ይህ አመለካከቱ ደግሞ በባለሙያዎች የጋብቻ ህይወት ላይ አንዳች ባህል ፈጥሯል::

በሰላጤው የሸክላ ስራ ሙሉ በሙሉ የሴቶች ተግባር ነው:: ሴቶች ጥሬ ዕቃ ከመሰብሰብ (አፈርን ከመቆፈር) ጀምሮ ዕቃዎች ገበያ ወስዶ እስከመሸጥ ያሉ ተግባራትን ሁሉ ያከናውናሉ:: በእርግጥ አልፎ አልፎ ለመሰሪያ የሚሆነውን አፈር ተሸክሞ ወደ ቤት በመምጣትና ለማቃጠያ የሚሆን እንጨት በመልቀም ወንድ ልጆቻቸው ሊረዷቸው ይችላሉ:: በተረፈ ግን ስራው የሴቶች ነው:: ታዲያ ለዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ልማድ መሰረት እነዚህን ሸክላ ሰሪዎች የሚያገቧቸው ወንዶች የብረት ስሪ ባለሙያዎች ወይም ከዚህ ውጭ ማህበረሰቡ አሳንሶ በሚያያቸው እንደ ቆዳ ስራ ባለሙያዎች የተሰማሩ ወንዶች ብቻ ናቸው:: ምክንያቱም ማህበረሰቡ ለእነዚህ ባለሙያዎች የሰጠው ደረጃ ባለሙያዎች እርስ በእርሳቸው ካልሆነ ከሌላው የማህበረሰብ አባል ጋር እንዳይጋቡ ያግዳቸዋል:: በባለሙያዎች መካከል ግን (በብረት ስሪ በሸክላ ስሪና በቆዳ ስሪ) መካከል የደረጃ ልዩነት የለም:: ይህም በመሆኑ እርስ በእርስ ይከባበራሉ፣ ጋብቻ ይፈፅማሉ፣ ሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶችንም ያለገደብ ያደርጋሉ::

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ተደጋግሞ እንደተገለፀው ማህበረሰቡ ሰሪዎችን እንጂ ቁሶችን አይንቅም:: በመሆኑም ከእለት እለት መገልገያነት ባሻገር በዓላትን በመሰሉ ልዩ ቀናት እንኳን ይጠቀምባቸዋል:: ለምሳሌ ዘገኞች በማህበራዊ ኑሮ ሳቢያ ለሚፈጠሩ እንደ

በዓላት፣ የወለደችን ሴት መጠየቅና በመሳሰሉት ማህበራዊ ግንኙነቶች በገንቦ ጠላ በስጦታነት መውሰድ ባህላቸው ነው። ነገር ግን ወደሚያከብሩትና ወደሚወዱት ሰው ሲሄዱ ጠላ የሚወሰዱባቸው ገንቦዎች ከማንኛውም ቤት የሚወስዷቸው አይነቶች አይደሉም። ጌጣቸውና መጠናቸው (ትልቅ ነው) ከሌላው ይለያቸዋል። ገንቦ ለሰዓት መለኪያም ያገለግላል። ሰዎች ለግብግ ቤታቸው የሚጠሩትን ሰው «የገንቦ ጠላ እንጠጣ» ካሉት «ተሎ ና» /እንዳትቆይ ማለታቸው ነው። የሸክላ ቁሶች ላዲስ ጎጆ ወጪም በስጦታነት ይበረከታሉ። ተቀባዮችም ቁሶች ከሚሰጡት ጥቅም የተነሳ ስጦታው እጅግ ያስደስታቸዋል። ከዚህ በተፈረ የሸክላ ቁሶች ማህበራዊ ደረጃንም ይገልፃሉ። ለምሳሌ ትልልቅ የሸክላ ቁሶች ያሏቸው ጥሩ ኑሮ ያላቸው ሰዎች ናቸው። በሰርግና በተዝካር «ይህንን ያህል ጋን ጠላ ሾመ/ አቀረበ» መባልም የደረጃ መገለጫ ነው። ከዚህ ሌላም ሰው ሞቶ ሬሳው ሲቀበር ከቤት ሲወጣ ሰውየውን የገደለውን ርኩስ መንፈስ ለማስደንገጥና ሌላ ሰው ለመግደል ተመልሶ እንዳይመጣ የሸክላ ዕቃ ይሰበራል።

በአጠቃላይ ሸክላ ቁሶች በማህበራዊና በባህላዊ አውዶች ያላቸው ሚና የሰሪዎቻቸውንና የተጠቃሚዎችንና ማህበራዊ ደረጃ ማሳየት፣ በእለት እለትና «ለሴርሞኒ» ተግባራት ማገልገልና የማህበረሰቡን እምነትና ፍልስፍና ማንፀባርቅ ነው።

## 6.6.2 የሸክላ ቁሶች በኢኮኖሚያዊ አውድ

ትናንትም ይሁን ዛሬ የሸክላ ቁሶችን መስራት ለሸክላ ሰሪዎች የገቢ ምንጭ ነው። በእርግጥ የትናንቶችም ሆኑ የዛሬዎች ሸክላ ሰሪዎች ከሸክላ ስራ ሌላ ገቢ የሚያስገኝላቸው የቡና መሬት ሊኖራቸው ይችላል ወይም ባሎቻቸው የቆዳ ስራ ወይም የብረት ስራ ሰርተው ሊረዷቸው ይችላሉ። ሆኖም ግን ሸክላ ሰሪዎች የሸክላ ቁሶችን ሰርተው ጥቅም ማግኘታቸው የስራው ህልውና እስካሁን እንዲቆይ ዋና ምክንያት ነው።

ቀደም ያሉት ሸክላ ሰሪዎች የሰሯቸውን የሸክላ ቁሶች በገንዘብ አይሸጧቸውም። በቡና ይለውጧቸው ነበር እንጂ ። ምክንያቱም ቀደም ሲል የሰላጤዋ የመገበያያ መንገድ ለውጥ ነበር። ቡናን በሌላ ነገር መለወጥ።

አሁን ግን ሸክላ ሰሪዎች የሰሯቸውን የሸክላ ቁሶች በገንዘብ ይሸጣሉ። የሚያሰሯቸውን የሸክላ ቁሶች ለዘገኞችና ላታ፣ አታንጐሳ ፣ ይጐዲ ፡ ሰቀለጥ፣ ደህና ማርያም ወዘተ በሚባሉ የሰላጤዋ ጐረቤት ገጠሮች ውስጥ ለሚኖሩ አርሶ አደሮች ይሸጣሉ። ሆኖም በሰላጤዋ ውስጥ የሚሰሩትን የሸክላ ቁሶቁሶች ዋጋ የሚወሰኑ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የዕቃዎች መጠንና ወቅት (ክረምትና በጋ) ናቸው።

ሁሉም ሸክላ ሰሪዎች የሚሰሯቸው የሸክላ ቁሶች ውስጥ መጠናቸው ትልቅ የሆኑት መጠናቸው ትንሽ ከሆነው ይልቅ ዋጋቸው ውድ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ዕቃዎች ሲሰሩ ከሚፈጁት ጭቃና ለማቃጠል ከሚያስፈልጋቸው እንጨት፣ ለመድረቅ ከሚያስፈልጋቸው ጊዜ ብዛት የተነሳና ባለሙያዎችም ትልልቅ ዕቃዎችን ለመስራት የሚያጠፉት ጉልበት ከትንንሾች የበለጠ ስለሚሆን ነው፡፡ ሸክላ ሰሪዎች ትንንሽ እቃዎችን ሲሰሩ እነሱ አንድ ቦታ ተቀምጠው ዕቃውን እያሽከረከሩ ነው ትልልቅ ዕቃዎችን ሲሰሩ ግን እነሱ ናቸው የሚዟዟሩ፡፡ ይህ ደግሞ የሚጠይቀው ጉልበት አለ፡፡ ነገር ግን ሸክላ ሰሪዎች ትልልቅ ዕቃዎችን ከመስራት ይልቅ ትንንሽ እቃዎችን መስራት ይመርጣሉ፡፡ ምክንያቱም አሁን አሁን ግለሰባዊነት እየተለመደ ከመምጣቱ የተነሳ በገበያ ላይ ተፈላጊ እነሱ እየሆኑ የመጡ ትንንሽ እቃዎች ናቸውና ቶሎ ቶሎ የሚሸጡ እነሱ ናቸው፡፡ ሽያጫቸውም ጥሩ ትርፍ ያስገኛል፡፡ በመሆኑም ትልልቅ ዕቃዎችን ከመስራት ይልቅ ትንንሽ ዕቃዎችን መስራት ተመራጭ እየሆነ መጥቷል፡፡

ወቅትም በቁሶች ዋጋ ላይ ከፍተኛ ሚና ያለው ጉዳይ ነው፡፡ እንደ የሸክላ ቁስ ወቅቶች ክረምትና በጋ በመሆናቸው የተነሳ የተለያዩ ዋጋዎች ይኖሩታል፡፡ ባለሙያዎች እንዲሁም ተጠቃሚዎች እንደገለፁልኝ የሸክላ ዕቃዎች ዋጋ ከበጋ ይልቅ በክረምት ይቀንሳል፡፡

ሸክላ ሰሪዎች እንደገለፁት በእርግጥ በክረምት የሸክላ ስራን መስራት ከባድ ነው፡፡ ጭቃውን መቆፈር የተቆፈረው ጭቃ ደግሞ ክብደት ስለሚኖረው መሸከሙ እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ የሚወቀጠውን ጭቃ እንዲሁም የተሰሩትን ዕቃዎች ማድረቁ ረጅም ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ለማቃጠያ የሚሆን እንጨት ማግኘትም በጣም ፈታኝ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ምክንያት በክረምት አዲስ የሸክላ ዕቃዎች ከሳምንት በፊት አይቃጠሉም፡፡ ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ሸክላ ሰሪዎች በእነዚህ ችግሮች አልፈው ቁሶችን ቢሰሩ የቁሶች ዋጋ በክረምት ይቀንሳል፡፡ ይህም ከተጠቃሚዎች አቅም አንፃር መሆኑን ነው መረጃ ሰጪዎች የሚገልፁት ፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የሸክላ ዕቃዎች ለሽያጭ የሚቀርቡት ለዘገኞችና በዘጌ ዙሪያ በሚገኙ ገጠሮች ለሚኖሩ አርሶ አደሮች ነው፡፡ ከዘገኞች ደግሞ አርሶ አደር ደንበኞች (ገዥዎች) ቁጥራቸው ይበልጣል፡፡ ታዲያ እነዚህ ተጠቃሚዎች አርሶ አደሮች እንደመሆናቸው በክረምት ወቅት ምንም የእርሻ ውጤት የላቸውም፣ ይቸገራሉ፡፡ ስለዚህ የሸክላ ዕቃዎችን አይገዙም፡፡ በአንፃሩ በበጋ በተለይም ከታህሳስ ጀምሮ ምርት ስለሚኖራቸው ቀጥለው ባሉት ወራትም በድግስ የሚከበሩ እንደ ልደት፣ጥምቀትና ፋሲካ የመሳሰሉ በዓላቶች እንዲሁም ሰርጎች ስለሚኖሩባቸው ለጠላ መጥመቂያና ለአረቄ ማውጫ የሚሆኗቸውን የሸክላ ዕቃዎች ይገዛሉ፡፡ ማለትም በአንድ በኩል በዓላቱ ሲያስገድዷቸው በሌላ በኩል ደግሞ የምርት ውጤቶች የኗቸው መሆኑ የመግዛት አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡ ዘገኞችም ቢሆኑ የቡና ምርት የሚደርስላቸው

በየካቲት ወር በመሆኑ በክረምት የሸክላ ቁሶችን አይገዙም:: በግንቦት ወርም በተለይ የቶፋዎች ዋጋ እንደሚጨምር ነው መረጃ ሰጪዎች የሚናገሩት:: እንደ እነሱ ገለፃ ይህ የሆነው በዚህ ወር ለሚከበረው የግንቦት ልደታ በዓል (ግንቦት 1) በየሰፈሩ ንፍሮ የሚቀቀለው በቶፋ በመሆኑ ነው:: በአጠቃላይ ግን በክረምት ዕቃዎችን የመግዛት አቅም ብቻ ሳይሆን ገዝቶ ወደ ቤት ማድረሱም ቢሆን በአየሩ ሁኔታ የተነሳ አስቸጋሪ መሆኑ ሰዉን የሸክላ ቁስ ከመግዛት ይልቅ አለመግዛትን ያስመርጠዋል:: በዚህም ምክንያት የዕቃዎች ዋጋ ይቀንሳል:: በሰሪዎች ረገድም ቢሆን ዕቃዎች በክረምት ወቅት የሚያወጡት ዋጋ ከድካሙ አንፃር ሊወዳደር ይቅርና የማይታሰብ ስለሚሆንባቸው ስራውን አቋርጠውት እስከመስከረም ይደርሳሉ:: ይህም ገበያ በእቃዎች ስራ ላይ ተፅዕኖ ያለው መሆኑን ያሳያል::

በአጠቃላይ ገበያ በሸክላ ስራ ላይ ተፅዕኖ ያለው ጉዳይ ሲሆን የዕቃዎች ዋጋ በዕቃዎች መጠንና በወቅት (ክረምትና በጋ) ይወሰናል::

## 6.7 ከሸክላ ስራና ስራተኞች ጋር የተያያዙ እምነቶችና አመለካከቶች

ሸክላ ሰሪዎች በሰላጤው ውስጥ ከሚኖረው ማህበረሰብ ውስጥ አንድ ቡድን ናቸው:: እነዚህ ቡድኖች ለማህበረሰቡ የሚያስፈልጉትን ቁሶች እየሰሩ ያቀርቡለታል:ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ በቁሶች እየተገለገለና አብዛኞቹ የቤቱ ዕቃዎች ከሸክላ የተሰሩ ሆኖ ሳለ ለሸክላ ስራ ባለሙያዎች ያለው አመለካከት ዝቅ ያለ ነው::ጋብቻን የመሳሰሉ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ከእነሱ ጋር አይፈፅምም:: ይህንን እንዳያደርግ የሚከለክሉ ዕምነቶች አሉት:: በእርግጥ ባለሙያዎችም ቢሆን ለሸክላ ስራ የራሳቸው የሆነ እምነት አላቸው ::የሁለቱንም ወገኖች እምነቶች የሚያሳዩ ምሳሌዎች ቀጥለው ይቀርባሉ:-

### 6.7.1 ማህበረሰቡ ስለሸክላ ሰሪዎች ያለው አመለካከትና እምነት

ማህበረሰቡ ሸክላ ሰሪዎችን እንደሌላው ማህበረሰብ ሰዎች፣ ባደረጉት የግብረስጋ ተራክቦ የተወለዱ አይደሉም ብሎ ያምናል:: እናታቸው ሰው አባታቸው ደግሞሰይጣን ነው ተብሎ ነው የሚታመነው:: በዚህ የተነሳ ከሌላው ሰው የተለየ ሃይል አላቸው «ቡዳ» ናቸው:: ሰውን የመግደል ወደ ሸክላነት የመቀየር ሃይል አላቸው ሲል ያምናል:: በዚህም የተነሳ ሌላው ማህበረሰብ በጋብቻና በመሰል ግንኙነቶች አግልሏቸው ይኖራል:: መገለሉም ስር የሰደደ እንዲሆን የሚያደርገው አንዳች እምነት አለ :: ዘገኞች ሸክላ ሰሪዎች አንድን ሰው በልተው (በአይናቸው ሃይል (power) ጉድተው ከገደሉት በኋላ ዘመዶቹ ሞቷል ብለው ሲቀብሩት እነሱ ከመቃብር አውጥተው ወደ ቤታቸው ይወስዱታል:: ከዚያም ቀን ቀን የሸክላ ዕቃ ማታ ማታ ደግሞ ሰው እንዲሆን እያደረጉ

የቤት ስራ ያስሩታል ሲሉ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ከእነሱ ጋር መጋባት እንደማያስፈልግ ለልጆቻቸው ያስተምራሉ፡፡ ይህ እምነት ምንም እንኳን ሙያውን ከቤተሰቦቻቸው ለወረሱት ባለሙያዎች የሚባል ቢሆንም ሙያውን ከአካባቢያቸው ያገኙትም ቢሆኑ ከሙያው ጋር« ሌላውን ነገርም» ይማሩታል በሚል መገለሉ አልቀረላቸውም፡፡

ከባለሙያዎች በተጨማሪም አልፎ አልፎ ስለሸክላ ዕቃዎች የሚታመን ነገር አለ፡፡ ማህበረሰቡ «ያልተሟሸ» (አዲስና አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ) ቁስ ቤት ውስጥ መቀመጥ የለበትም ይላል፡፡ ይህ ከሆነ ግን አንድ ሰው ቡዳ ቢበላው «አይለፈልፍም» (ማን እንደበላው አይናገርም)[13] ፡፡ ሸክላው ያለበት ቤት ንግድ ቤት የሆነ እንደሆነ ደግሞ ገበያ ይዘጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ነገር አጋጥሞኛል፡፡ ልጅቱ ምንትዋብ ትባላለች፡፡ በአፋፍ 01 ቀበሌ ጠላ በመሸጥ የምትተዳደር የ28 ዓመት ወጣት ናት፡፡ በጠላዋ ቀን (ቅዳሜ እለት ነው) አንድ የገጠር ሰው ሌሎችን ነገሮች ገዝቶ እስኪመጣ ድረስ ቀድሞ የገዛውን ማዲጋ (እንስራ) አደራ እንድታስቀምጥለት ሲሰጣት አልቀበልም ማለት ስለከበዳት ከተቀበለችው በኋላ ሸክላውን በገለባ(ሳር) ለብልባ(አቃጥላ) ወደቤቷ አስገባችው፡፡ ይህንን ያደረገችው ያልተሟሸው (አዲሱ) ሸክላ ገበያዋን እንዳይዘጋባት መሆኑን ገልፃልኛለች፡፡በአጠቃላይ ምንም እንኳ ማህበረሰቡ የሸክላ ዕቃዎች እስካሁን ድረስ የቤት ውስጥ መገልገያዎቹ ቢሆኑ ስለባለሙያዎች ያለው አመለካከት ግን ጥሩ ያልሆነ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሙያው ለዘመናት መሻሻል ሳይታይበት ኖሯል፡፡ እንዲያውም አሁን አሁን የሰራተኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በእርግጥ የራሳቸው የባለሙያዎች እምነትም ቢሆን ሙያውን በርካታ ሰው እንዳይማረው የሚያደርግ ነው፡፡ ለምሳሌ ቀጣዮች ምሳሌዎች ይህንን ያሳያሉ፡፡

### 6.7.2 የባለሙያዎች እምነት

<u>«ሸክላ አይን ይፈራል»</u>፡-

ሸክላ ሰሪዎች ሸክላ «አይን ይፈራል» ብለው ስለሚያምኑ በሚሰሩበት ጊዜ ሰው እንዲያያቸው አይፈልጉም፡፡ የሚሰራውን ሸክላ ሰው ካየው ይፈርሳል፡፡ በእሳት ሲቃጠል ይሰነጠቃል ብለው ያምናሉ፡፡ ይህም በመሆኑ ዕቃዎችን እየሰሩ ምናልባት ሰው ወደ እነሱ ቢሄድ ሰውየው (ሴትየዋ) ከአጠገባቸው ከመድረሱ /ሷ/ በፊት እነሱ መስራቱን አቁመሙ ወደሰውየው ይሄዳሉ፡፡

ዕቃዎች የሚያቃጥሉበትን እሳትም አያስጭሩም፡፡ ስለዚህ ከሙያው ውጭ የሆነ ሰው ዕቃዎች እየተሰሩ በምንም አጋጣሚ ሲያያቸው አይችልም፡፡ ይህም የሙያውን

---

[13] ሰው ቡዳ ሲበላው በመድሃኒት ማን እንደበላው የት እንደበላውና ሌሎች መረጃዎችን ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

ተስተላልፎ የተገደበ እንዲሆን አድርጎታል::በዚህ መንገድ ሰዎች ሙያውን በቤተሰብ ብቻ የተወሰነ አድርገውት የቆዩ ሲሆን ከቤተሰብ ውጭ ሙያውን የቻሉት ሰዎች ከባለሙያዎች ጋር የተለየ ቅርበት የነበራቸው ጎረቤቶች ብቻ ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪም ባለሙያዎች «ሸክላ ንፅህና ይወዳል» ብለው ያምናሉ:: በመሆኑም የሸክላ አፈር በሚቦካበት በሚጠፈጠፍበትና በሚቃጠልበት ቦታ ሁሉ ምግብና ምግብ ነክ ነገሮች አይደርሱም :: መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት ዛሬ ዛሬ ቀረ እንጂ አንዲት ባለሙያ የወር አባባዋ ከመጣና የግብረ ስጋ ግንኙነት ካደረገች ወደ ሸክላ ስራው አትቀርብም:: ይህንን ካደረገች ግን «ጥላ ስለሚሆንበት» የሚሰራው ሸክላ እሽ ብሎ አይቆምም ይሰበራል:: ስለዚህ የግድ አንዲት ሴት ንፁህ ሆና ነው መስራት ያለባት ይባላል::

በአጠቃላይ ባለሙያዎችም ሆኑ ማህበረሰቡ ስለሙያው ያላቸው አመለካከት በአብዛኛው ሲታይ የሙያውን እድገትና ተስተላልፎ የሚገድብ ነው::

## 6.8 በሸክላ ቁሶችና በሸክላ ስራ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች

በሸክላ ስራ ላይና በሸክላ ቁሶች ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ ነገሮች ይኖሩ ይሆን የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ስል በሰላጤው ውስጥ የሚኖሩ ሸክላ ሰሪዎችን ጠይቄ ለማረጋገጥ እንደሞከርኩት በሰላጤው ውስጥ በሸክላ ስራ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚከፈሉ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ:: እነሱም የሚከተሉት ናቸው::

### 6.8.1 የተፈጥሮ ሃብት መመናመን

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሦስት «የዘጌ ሰላጤ የተፈጥሮ ሃብቶች» በሚል ርዕስ ስር እንደተገለፀው ዘጌ በደን ሃብቷ እጅግ የበለፀገች ሃገር የነበረች ቢሆንም አሁን አሁን ግን የማህበረሰቡ መተዳደሪያ የነበረው የቡና ምርት በተደጋጋሚ በደረሰበት የበረዶ ጭፍጨፋና ድርቅ ማክንያት ህዝቧ ፊቱን ወደ እንጨት ሽያጭ አዞሯል:: በዚህም ምክንያት የሰላጤዋ ደን እየተጨፈጨፈ መጥቷል:: ይህ ሁኔታ ደግሞ በሸክላ ስራው ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ መጥቷል:: አስቀድሜ እንደገለፅኩት ሸክላ ሰሪዎች ለሸክላ ስራ የሚገለገሉበትን ዋልካ አፈር የሚያገኙት ከተወሰነ (አንድ ቦታ) ነው:: ይህ ማለት ደግሞ በተወሰነ ቦታ ላይ ተደጋጋሚ ቁፋሮ ስለሚካሄድ ቀስ በቀስ የሸክላ ስራውን ጥሬ ዕቃ ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል ማለት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ሸክላ ስራ ሁለት ጊዜ በእሳት የማቃጠል ተግባራት ይከናወኑበታል:: አንደኛው ገና ቁስ ከመስራቱ በፊት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቁሱ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ እነዚህ ተግባራት

ደግሞ በርካታ የማገዶ እንጨት አገልግሎት ላይ የሚውልባቸው ናቸው። ዳሩ ግን የደን ሃብት መቀነስ የእንጨት ግዥውን ዋጋ ከፍ ሲያደርገው ለቀማውንም ቢሆን አድካሚ ያደርገዋል። ታዲያ በዚህ ሁሉ ድካምና ወጪ መካከል ተሰርቶ ለገበያ የሚቀርበው የሸክላ ቁስ ደግሞ የሚሸጥበት ዋጋ ድካሙንና ወጪውን የሚያካክስ አይደለም። ባለሙያዎችም ቢሆኑ ዘጌ ውስጥ ገበያው ቅርብ ስለሆነ ብቻ እንጂ ሌላ ቦታ ቢሄዱ በውድ ዋጋ መሸጥ እንደሚችሉ ነው የሚናገሩት። ይህም በመሆኑ ሸክላ ሰሪዎች የተሻለ ስራ ፍለጋ ማሰባቸው አልቀረም ። ይህም ደሞ በበኩሉ ለሙያው ቀጣይነት እንቅፋት መሆኑን ነው መገንዘብ የሚቻለው። በዚህ ሁሉ ችግር መካከል አልፈው ቁሶች ገበያ የሚያቀርቡትን ባለሙያዎች ማህበረሰቡ የሚመለከትበት ዓይንም በሙያው ህልውና ላይ የተደነቀረ ሌላው ችግር ነው።

## 6.8.2 የማህበረሰቡ አመለካከት

የዘጌ ባህረሰላጤ ማህበረሰብ ሙያውን ከቤተሰብ ላገኙትም ሆነ ከጎረቤት ለተማሩት የሸክላ ስራ ባለሙያዎች ያለው አመለካከት ባለሙያዎችን ዝቅ የሚያደርግ ነው ። ቀደም ሲል «የሸክላ ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃ » በሚለው የጥናቱ አንድ ርዕስ እንደተገለፀው ሸክላ ሰሪዎችን ቤተሰቦቻቸው በተለይም ወጣት ልጆች በትምህርት ቤትና በጨዋታ ቦታዎች ሁሉ በጓደኞቻቸው የሚደርስባቸው ንቀትና መገለል አለ። ሸክላ ሰሪዎች በመንደር እንዲሁም በገበያ ቦታ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ይሰደባሉ። ነገር ግን ሸክላ ስራ ለእነዚህ ሰዎች «እንጀራቸው በመሆኑ ስድቡን ችለው፣ መገለሉንም ተቋቁመው ለዘመናት ባለበት እየረገጠም ቢሆን ሙያውን እሁን ድረስ ህልውናው ሳይቋረጥ እንዲቀጥል አድርገዋል። ነገር ግን አሁን ማህበረሰቡ በእነሱም ሆነ በወላጆቻቸው ላይ መገለል ያደረሰባቸው ወጣት ልጆች ሙያውን ለመቀበል እያቅማሙ ነው። አንዳንዶችም በግልፅ አሻፈረን ብለዋል። ይህ ሁኔታም የሙያውን ህልውና አደጋ ላይ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ቀጣዩ ጉዳይም ሌላው በሸክላ ቁሶች ህልውና ላይ ተፅዕኖ እያደረሰ ያለ ጉዳይ ነው።

## 6.8.3 የፋብሪካ ዕቃዎች በፍጥነት ወደ ሰላጤዋ መግባት

Dorson (1972) ዛሬ የኢንዱስትሪው አብዮት በሃገረሰባዊ እጅ ስራዎች ላይ በጠቅላላው ተፅዕኖ እያሳደረ መጥቷል ። የፋብሪካ ዕቃዎች ወደ ገጠሩ ክፍል መጉረፍ መጀመራቸው የእጅ ስራ ባለሙያዎችን ጎድቷል። ከእደ ጥበብ ውጤቶች ይልቅ የፋብሪካ ዕቃዎች ዋጋቸው ርካሽ በመሆኑ ብዙ ሰዎች የፋብሪካ ዕቃዎችን መግዛት

በመጀመራቸው የባህላዊ የእጅ ስራ ባለሙያዎች ስራቸውን እንዲያቆሙ እየተገደዱ ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

በዘጌ ባህረሰላጤ የሚታየውም ከዚህ እውነት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ አሁን አሁን በሰላጤው ውስጥ የፋብሪካ ዕቃዎች ገበያውን አጥለቅልቀውታል፡፡ የእያንዳንዱን አባወራ ቤትም አዳርሰውታል፡፡ እነዚህ ዕቃዎች ከገበያ ውስጥ ከመገኘታቸው ባሻገር በሸክላ ዕቃዎች ዋጋና ተፈላጊነት ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡

የሰላጤዋ ነዋሪዎች ለአያያዝ አመችነትና ለእድሜው ረጅምነት ሲሉ ከሸክላ ዕቃዎች ይልቅ የላስቲክ ዕቃዎችን ይመርጣሉ፡፡ በዚህም መሰረት በሰላጤው ውስጥ በሚገኙ በርካታ ቤቶች ባደረግሁት ምልከታ የሸክላ ስሪዎችን ጨምሮ ሁሉም ቤቶች ውስጥ ማለት ይቻላል የሸክላ ዕቃዎች ይሰጧቸው የነበሩ አገልግሎቶች በፋብሪካ ዕቃዎች ተተከተዋል፡፡ ለምሳሌ ማዲጋ (እንስራ) በጀሪካል፣ በጎማና በብረት በርሚል፤የሸክላ ድስት ፣በብረት ድስት፤ገንቦ በጆግ፤ ጀበና በብረት ማንቆርቆሪያ ፣ ምድጃ በፈርሜሎ (ከብረት የተሰራ የከሰል ማንደጃ) ተተክተዋል፡፡

በአጠቃላይ በዘጌ ባህረሰላጤ የሚገኘው የሸክላ ስራ ምንም እንኳን አሁን ድረስ ህልውናው ጨርሶ ያልጠፋ ቢሆንም ነገ ከነገ ወዲያ ግን ህልውናው አስጊ ሁኔታ ላይ ነው ያለው፡፡ ምክንያቱም ከገበያና ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ እነዚህ ከላይ የተገለፁት የደን ሃብት መመናመን ፣ የማህበረሰቡ አመለካከትና የፋብሪካ ዕቃዎች ወደ ሰላጤዋ በፍጥነት መግባት በስራው ላይ ተፅዕኖ እያሳደሩ ያሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 6.9 የሸክላ ቁሶችን እንዴት ለበለጠ ጥቅም ማዋል ይቻላል?

በዘጌ ባህረሰላጤ መቼ እንደተጀመረ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ሙያው በሰላጤዋ ውስጥ ረጅም ዘመናትን ያሳለፈ መሆኑ በበርካታ የሰላጤዋ ነዋሪዎች የሚገለፅ መረጃ ነው ፡፡ ሆኖም በዚህ ሁሉ ዘመን መካከል በሙያው ላይ የታየ ይሄ ነው የሚባል መሻሻል የለም ፡፡

የሸክላ ስራ ባለሙያዎችም ሆኑ ተጠቃሚዎች እንደሚገልፁት ዛሬ የሚሰሩት የሸክላ እቃዎች ጥንት ሲሰሩ የነበሩት ናቸው፡፡ በመስሪያ ቁሶችም ሆነ በአሰራር ሂደቱ ላይ ምንም የእድገት ለውጥ የለም፡፡ እንዲያውም ዛሬ ዛሬ የባለሙያዎች ቁጥር ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሙያውም አስጊ ሁኔታ ላይ ወድቋል፡፡ ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሱት ምክንያቶች የማህበረሰቡ አመለካከት፣የተፈጥሮ ሃብት መመናመን፣የፋብሪካ ምርቶች በፍጥነት ወደ ሰላጤዋ መግባት ናቸው፡፡

ዳሩ ግን ሙያው እነዚህን «ችግሮች» ተቋቁሞ ህልውናው ሊጠበቅ እንደሚገባና የሚሰሩት የሸክላ እቃዎችም አሁን ከሚሰጡት የበለጠ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው ዘገኞች ያምናሉ:: ቀጣዮቹ ንግግሮችም ይህንን የሚጠቁሙ ናቸው::

> ሸክላ ብዙ ጥቅም አለው:: ማዲጋ ውሃ ያቀዘቅዛል፣ ድስት ወጥ ያጥማል::ዛሬ ግን ሸክላ ሰሪው ስራውን እየተወው ነው:: እንዲያውም ተማሪው ባይቀጥለው ኑሮ ባላባቱ ተሰደብነ ብሎ መስራቱን ስለተወው ጨርሶ ሸክላ የሚባል ዘጌ ላይ አይሰራም ነበር:: ስለዚህ ሸክላ ስራ ካገር እንዳይጠፋ መድሃኒቱ እየተማሩ መስራት ነው :: አለዚያ ትንሽ ቆይቶ ጭራሽ ይጠፋል (ወ/ሮ እናት ትሁን ተባባል፣4-9-1999 ) ::

ወ/ሮ በተሃ ካሳ የተባሉ የሸክላ ስራ ባለሙያ ደግሞ «ልጅ ልጁም ስራውን ጠልቶታል:: ሰው ሰደበነ እያለ ስንሰራ እንኳን አያይም:: ግና ከቡድነትና ከስርቆት በቀር ሁሉም ትምህርት ጥሩ ነበር:: ቢማረው ለሱም ማደሪያ ይሆነው ነበር ሙያውንም ይጠብቀው ነበር:: ታልሆነ ደግሞ መንግስት እንደድሮው ልጅ ልጁን ሰብስቦ ቢሰለጥነው ጥሩ ነበር » ( 23-2-2000 ) ይላሉ:: ሌላይቱ ወ/ሮ አንጓች አንባዬ የተባሉ የሸክላ ስራ ባለሙያ ደግሞ « ሰውም ስድቡን ቢተው፣ መንግስት ደግሞ አዋቂውንም ልጁንም በደንብ ቢያስተምረው፣ ልጅ ልጁም ስራን ቢያከብር ሁልጊዜ ተመሳሳይ እቃ መስራቱ ቀርቶ በሰው አገር እንደምናየው የተሻሻለ እቃ መስራት ይቻል ነበር (30-8-1999 ) ብለዋል ::

በአጠቃላይ ከመረጃ ሰጪዎች ሃሳብ በተለይም ማህበረሰቡ ለሙያው ሙያተኞች ያለውን ዝቅተኛ አመለካከት መረዳት የሚቻል ሲሆን መረጃ ሰጪዎች እንደሚጠቁሙት የአመለካከት ለውጥ ይመጣ ዘንድ በተለይ መንግስት ጠንክሮ መስራት የሚገባው መሆኑን ማስተዋል ይቻላል ::

# 7. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 7.1. ማጠቃለያና መደምደሚያ

ይህ ጥናት የተሰራው በአማራ ክልል በምዕራብ ጐጃም ዞን በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ከባህርዳር ከተማ በስተሰሜን አቅጣጫ በየብስ 30 በባህር ትራንስፖርት ደግሞ 11 ኪ.ሜ ርቃ በምትገኝ ዘጌ በተባለች ባህረሰላጤ (peninsula) ውስጥ በሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ላይ ነበር።

ጥናቱ ትኩረቱን በቁሳዊ ባህል ላይ እንዲያደርግ ያደረገው የአጥኚዋ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ውስጥ ያለውን የቁሳዊ ባህል ጥናት ክፍተት የመሙላት ፍላጐት ሲሆን በተለይ በዘጌ ባህረሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ላይ የተተኮረበት ምክንያት ደግሞ የሰላጤዋ እድሜ ጠገብ ባህላዊ ቤቶችም ሆኑ የሸክላ ቁሶች ህልውና አስጊ ደረጃ ላይ መሆን ነው። ይህን ሁኔታም ያወቅሁት ዘጌ የቱሪስት መስህብ የሆነች ቦታ ከመሆኗ በተያያዘ ለጉብኝት ሄጄ ካገኘሁት ኢመደበኛ መረጃ ነው።

በመሆኑም ጥናቱ በሰላጤዋ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችንና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በሳይንሳዊ አጠናን መንገድ መግለፅ፣ መቅረስና መሰነድ እንዲሁም እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ህልውናቸው ፈፅሞ ከመጥፋት ተቆጥቦ ለማህበረሰቡ አንዳች ጠቃሜታ የሚያበረክቱበትን መንገድ መጠቆም የሚል ዋና አላማ በመያዝ በዚህ ዋና ዓላማ ስር ደግሞ ስምንት ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ይቻል ዘንድ መረጃዎች ከቤተመፃህፍት፣ ከመረጃ መረብ (internet) ና ከመስክ ተሰብስበዋል። በተለያዩ የፎክሎር ባለሙያዎች የተባሉ ትውራዊ ዳራዎችና ከዚህ ጥናት ርዕስ ጋር የሚዛመዱ ሌሎች ጥናቶች ተመርጠው ተዳስሰዋል።እንዲሁም ጥናቱ ስለሚደረግበት ቦታ በቂ ግንዛቤ ለመጨበጥ ቱሪዝም፣ግብርናና የአካባቢ ጥበቃን ከመሳሰሉ ቢሮዎች መረጃዎች ተወስደዋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ ስለ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ጥልቅ ዕውቀት ለማግኘት በመስክ ስራ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚህ ጊዜም ምልከታና ቃለመጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት አገልግለዋል። ምልከታና ቃለመጠይቅ ሲደረግም የፎቶና የቪዲዮ ካሜራ፣ ቴፕሪከርደርና የማስታወሻ ደብተር የመረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎች ነበሩ። በመሆኑም ጥናቱ ቀዳማይና ካልአይ መረጃዎችን (primary and secondary datas) በማሰባሰብ፣ በመሰነድና በመተንተን ወደ ግቡ ለመድረስ ጥረት አድርጓል።

በዚህ ጥረትም ያልተዛባና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ሲባል በዚያው በዘጌ ባህረሰላጤ በመገኘት በምልከታው በሰላጤዋ ውስጥ ይገኛሉ ተብለው በመረጃ ሰጪዎች

ከሚገመቱ 80 ቤቶች ውስጥ 40 ያህሉ ተቃኝተዋል:: በቃለመጠይቁ ቤት ሰሪዎች ፣ የቤት ባለቤቶች፣ ሸክላ ሰሪዎችና ተጠቃሚዎች የሆኑ 30 ሰዎች ቃለመጠይቅ ተደርጐላቸዋል:: ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ 13ቱ ወንዶች 17ቱ ደግሞ ሴቶች ሲሆኑ አብዛኞች ከ30 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው፣ በስፍራው ተወልደው ያደጉና አሁንም በቦታው ላይ ኑሯቸውን የሚገፉ ናቸው::የሸክላ ባለሙያዎች ግን ቁጥራቸው በጠቅላላው 14 ሲሆኑ ሁሉም መረጃ በመስጠት ተባብረዋል::

በመሆኑም በዚህ መልኩ በምልከታና በቃለመጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በሚገባ ከተመረመረ በኋላBen Amos(1982), Kenneth (1978) ,Glassie (1991) ን የመሳሰሉ የተለያዩ ባለሙያዎች የቁሳዊ ባህል ዘርፎች ማዋገኛ ሲሉ ከገለፁዋቸው መንገዶች ውስጥ ባህላዊ ቤቶችን ማህበረሰቡ ራሱ ቅርፅን መሰረት አድርጎ በመደባቸው መሰረት፣ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ደግሞ በተግባራቸው ከተዋገኑ በኋላ ጥሬ መረጃዎች በምዕራፍ ሦስት ከቀረቡ ትውራዊ ዳራዎች ጋር እየተገናዘቡ በአይነታዊ የመተንተኛ ስልት ተተንትነዋል:: ከትነተናውም:-

- በዘጌ ባህረሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶች እሳተ ከላ፣ደርብና ምድር፣ጎጆ ቤት ይባላሉ፤ የሁሉም ተግባር ደግሞ ለሰዎች መጠለያነት ነው::
- የዘጌ ባህላዊ ቤቶች አሰራር ደረጃና ሂደቶች ያሉት ሲሆን ሂደቶችም ለመስሪያ የሚሆኑ ቁሶችን መሰብሰብ፣ የድግስ ዝግጅት ማድረግ፣ቁሶችን ለግንባታ ማመቻቸት፣ ግድግዳ መገንባት (ማቆም) ፣ጣራ ማዋቀር ፣ሳር መክደን፣ግድግዳ መምረግና ቤቶችን ማስዋብና ቤት ማሰናዳት ናቸው::
- በዘጌ ባህረሰላጤ የቤት ስራ በወንዶች የሚሰራ የማህበር ተግባር በመሆኑ እከሌ የተባለ ቤተ ሰሪ የለም :: በቤት ስራ የሚሳተፉት ወግኖችም ከቤት ሰሪነታቸው አንፃር በህብረተሰቡ የተሰጣቸው የተለየ ደረጃ የለም::
- የዘጌ ባህረሰላጤ የማህበረሰቡን ሃይማኖት (religion) መሰረት አድርገው የተሰሩ ሲሆን አሰራራቸው ሙሉ በሙሉ ትብብርን (ማህበራዊነትን) የሚያንፀባርቁ፣ የቤቶች መጠንና ቅርፅ ደግሞ የባለቤቱን ማህበራዊ ደረጃ የሚገልፁ ናቸው:: እሳተ ከላና ደርብና ምድር ቤት የሃብታሞች ብዙ የቡና መሬት ያላቸው ፣ጎጆ ቤት ደግሞ ክፍክፍ ከሆነ መካከለኛ ኑሮ ያለው አልባሶ ከሆነ ግን ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን ሰዎች ያመለክታሉ::
- ከባህላዊ ቤቶች ጋር የተያያዙ እምነቶች ብዙ ባይባሉም አሉ:: በቤቶች ህልውና ላይ ያላቸው እንድምታ ግን አሉታዊ ነው:: ስነ ቃሎች ግን የሉም::
- የአየር ንብረት ለውጥ (የደን ሃብት መመናመን) ቤቶች ከማህበረሰቡ ባህላዊ እምነት ጋር ያላቸው ትስስር፣ የነዋሪዎች ለተሻለ ኑሮ ወደ ሌላ ቦታ መሰደድ

(የተሻለ ኑሮ ፍለጋ) በቤቶች ህልውና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳረፉ ጉዳዮች ናቸው:: እንዲሁም:-

- በዘጌ ባህረሰላጤ የሚገኙ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ጋን፣ ማዲጋ፣ትዝቢ፣ ሸንክላ፣ ቶፋ፣ ገንቦ፣ ድስት፣ በገፊጅ፣ ጀበና ፣ወጪት፣ምጣድ፣ ማጨሻ ምድጃና ጎራሽ ናቸው:: ከእነዚህ ቁሶች ውስጥ ወጪትና ምጣድ በሰላጤዋ ውስጥ አይሰሩም::
- የሸክላ ቁሶች ስራ ደረጃና ሂደቶች አሉት :: ሂደቶችም የሸክላ አፈር ማዘጋጀት፣ ዕቃዎች ቅርፅ እንዲይዙ ማድረግ፣ የሸክላ ቁሶችን ማስጌጥ፣ በፀሃይ ማድረቅና ማቃጠል ናቸው::
- በዘጌ ባህረሰላጤ ሸክላ ስራ የሴቶች ስራ ሲሆን ሰዎች ሙያውን አንድም ከቤተሰቦቻቸው አለዚያ ደግሞ ከአካባቢያቸው ይማሩታል::
- የሸክላ ባለሙያዎች ማህበረሰቡ የሚያገልላቸውና በማህበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ደረጃ የሚሰጣቸው ናቸው::
- የሸክላ ዕቃዎች መጠን የተጠቃሚዎችን ማህበራዊ ደረጃ ያሳያል:: «ሃብታሞች» በመጠናቸው ትልልቅ የሆኑ የሸክላ ዕቃዎች ሲኖሯቸው «ደሃዎች» የሚኖራቸው ዕቃዎች ግን መጠናቸው ትንንሽ ነው::
- ከሸክላ ዕቃዎችና ከሙያው ጋር የተያያዙ ጥቂት እምነቶችና ቃል ግጥሞች አሉ:: ነገር ግን የእምነቶችና የቃል ግጥሞች እንድምታ በሙያው ህልውና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ነው::
- ማህበረሰቡ ለሸክላ ስራ ባለሙያዎች ያለው አመለካከት፣ የተፈጥሮ ሃብት መመናመን፣ የፋብሪካ ዕቃዎች በፍጥነት ወደ ሰላጤዋ መግባት ከሸክላ በተሰሩ የቤት ዕቃዎች ህልውና እንዲሁም በሙያው ቀጣይነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደሩ ጉዳዮች ናቸው የሚሉ ማጠቃለያዎችን አግኝቷል::

ከእነዚህ ማጠቃለያዎች በመነሳትም ጥናቱ የዘጌ ባህረሰላጤ ማህበረሰብ በባህላዊ ቤቶቹና ከሸክላበተሰሩ የቤት ቁሶች አማካይነት ኪነቱን፣ዕውቀቱን፣አስተሳሰቡን፣ እምነቱንና ፍልስፍናውን ሲገልፅ የቆየ ቢሆንም አሁን ግን እነዚህ ቁሳዊ ሃብቶቹ በማህበረሰቡ አመለካከትና ሃገረሰባዊ እምነት፣ በደን ሃብት መጨፍጨፍና በኢንዱስትሪ አብዮት(የፋብሪካ እቃዎች በፍጥነት መግባት) የተነሳ ህልውናቸው በመውደም ላይ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል:: ከመደምደሚያው በመነሳት ቀጥለው የቀረቡት አስተያየቶች ተሰጥተዋል::

## 7.2 አስተያየት

ዘጌ ነዋሪዎቿ ባደረጓቸው ማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮች የተነሳ ፈጥረው የተገለገሉባቸው በርካታ ቁሳዊ ባህሎች ያሏት ባህረሰላጤ ናት፡፡ ከእነዚህ ቁሳዊ ሃብቶቿ ውስጥ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ይገኙበታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ቁሶች ምንም እንኳን የማህበረሰቡ ኪነት፣ እውቀት፣ አስተሳሰብ፣ እምነትና ፍልስፍና የተላለፈባቸው አሁንም እየተላለፈባቸው ያሉ ቢሆንም አሁን አሁን የማህበረሰቡ ሃገረሰባዊ እምነት፣ ማህበረሰቡ ለባለሙያዎች ያለው አመለካከት የደን ሃብት መጨፍጨፍና የኢንዱስትሪ አብዮትን የመሳሰሉ ጉዳዮችየቁሳዊ ሃብቶችን ህልውና ሊያወድሙት በመታገል ላይ ናቸው፡፡ ነገር ግን ይህ ከመሆኑ በፊት አቅምና ችሎታው ያለው ሁሉ የቁሶችን ህልውና ከመጥፋት ሊታደግ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ሊደረጉ ይገባቸዋል ያልኳቸውን ጥረቶች እንደሚከተለው ጠቁሚያለሁ፡፡

አንድን ማህበረሰብ ካለበት ችግር ለማላቀቅም ሆነ ኑሮውን ለማሻሻል የተለያዩ ክፍሎች ትብብር አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የዘጌ ባህረሰላጤ ነዋሪዎች ባህላዊ ቤቶቻቸውና ከሸክላ የሚሰሩ የቤት ቁሶች ህልውናቸው ከመጥፋት ተጠብቆ አሁን ከሚያገኙት የተሻለ ገቢ እንዲያገኙና ኑሯቸው እንዲሻሻል ፡-

- የክልሉ (የአማራ ክልል) መንግስት፣ ማህበረሰቡ በራሱ ባህል እንዲኮራና በራስ ባህል የመኩራት ስሜትን ይፈጥር ዘንድ ስልጠና የሚሰጡ ባለሙያዎችን አሰልጥኖ ቢያዘጋጅ፤
- የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ ማህበረሰቡ የተፈጥሮ ሃብቶቹና እንዲጠብቅ ጥልቅና ተከታታይ ትምህርት ቢሰጥ፤
- ነዋሪዎች በባህላዊ ቤቶችና የቤት ቁሶች የበለጠ ለመጠቀምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስልጠና በቱሪዝም ቢሮ ቢሰጣቸው፤
- የቅርስና ባህል ጥበቃ ቢሮ ቤቶችን በኪራይ ወይም በግዢ ከሰዎች ላይ ተረክቦ የሚታደሱትን በማደስ ህልውናቸውን የመጠበቅ ሃላፊነትን ቢወስድ፤
- ቤቶች ባሉበት ሁኔታ ወደ ሙዚየምነት ቢቀየሩ፤
- የቤቶች ባለቤቶች የቤቶችን ንፅህና በመጠበቅ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ባህላዊ አልጋዎችን አዘጋጅተው ለቱሪስት ማደሪያ በማድረግ ገቢ የሚያገኙበትን መንገድ ቢቀይሱ፤
- ወጣቱ ለባህላዊ አርቲስቶች (ለቤትና የሸክላ ሰሪዎች) ክብር ቢሰጥና የባህላዊ ቤቶች ስራ ቤቶችንና የሸክላ ቁሶችን አሰራር ተምሮ የተቋረጠውን የባህላዊ ቤቶች ስራ

ቢቀጥል፣ ከዚያም ቤቶች ለቱሪስት ማረፊያ የሚሆኑበትን መንገድ ቢፈልግ እንዲሁም የሸክላ ስራውን ህልውና በተሻሻለ መንገድ ቢጠብቀው ፤

- የተማሩ ልጆች ወላጆቻቸውን ወደ ከተማ (የተሻለ ቦታ) ከመውሰድ ይልቅ ባሉበት ቦታ እየረዷቸው ቤቶች ተፈጥሯዊ መልካቸው ሳይጠፋ ቢያድሱላቸው፤ ማህበረሰቡ አሁን እየገባበት ካለው ችግር ውስጥ ለመውጣት መንገድ ያገኛል የሚል እምነት አለኝ።

## ዋቢዎች

ሄለን አላምረው፤« ባህላዊ ሸመናና የቆዳ ስራ በደምበጫና አካባቢዋ»፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍል፣የኤም.ኤ .ቴሲስ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም፡፡( ያልታተመ)

መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም፡፡

ሙሉጌታ መስፍን ፤ «የዘጌ አመሰራረትና ባህላዊ ሁኔታ»፣ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ወጣቶች ባህልና ስፖርት ጽ/ቤት፣ባህር ዳር ፣1996 (ያልታተመ)

ምስጌ ቢራራ፣ «የወይጦ ነገድ አጭር ታሪክና ባህል»፣ ባህር ዳር፣ 1979 ዓ.ም፡፡ (ያልታተመ)

ብርሃነ ትንሳኤ ወልደ ሰንበት ፤«የሸማኔና የማዕድ ቤት ዕቃዎች»፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ዕሁፍ ክፍል፣የአርትስ ባችለር ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1963 ዓ.ም፡፡ ( ያልታተመ)

ብርሃኑ ገበየሁ፤« የስነቃል ምንነት፣ዘውጎችና አተናተን»፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ዕሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1995 ዓ.ም፡፡ (ያልታተመ)

ተሾመ ፎርሲዶ፣ «ባህላዊ የቤት ዕቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ በሐድያ ብሔረሰብ»፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ዕሁፍ ክፍል፣የአርትስ ባችለር ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993 ዓ.ም፡፡( ያልታተመ)

አስገደች አወቀ ፤ « በሲሙ ቢልቢሎ ወረዳ የሚገኙ ባህላዊ የቤት ዕቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች መዘርዝር ከነአገልግሎታቸው»፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ዕሁፍ ክፍል፣የአርትስ ባችለር ማሟያ ጽሑፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1986 ዓ.ም፡፡ (ያልታተመ)

አባ ጎርጎርዮስ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣(ማተሚያ ቤት የለውም)፣ አዲስ አበባ ፣1991 ዓ.ም

አካባቢ ጥበቃ ጥናት ፖሊሲና ቁጥጥር መምሪያ፣ «በዘጌ ሰላጤ በተፈጥሮ ደን ላይ እየተፈጠረ ያለውን ችግር የሚዳስሱ እና መወሰድ ስለሚገባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ያስቀመጠ የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት»፣ ባህር ዳር ፣1996 ያልታተመ

እምሩ ወርቁ (ተርጓሚ)፤ ሞሳድ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት ፣ 1984 ዓ.ም

የአማራ ክልል ቱሪስት መስህብ ሃብቶች (አጭር ቅኝት)፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ ባህርዳር፣ 1991 ዓ.ም. ፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1993 ዓ.ም፡

ገበየሁ ወጋየሁ፤ «የዘጌ ሰላጤ (Pensula) የመጀመሪያ ደረጃ ታሪክ»፣ ለምዕራብ ጐጃም ባህልና ስፖርት መምሪያ የተዘጋጀ፣ ባህር ዳር ፣1996 ዓ.ም። (ያልታተመ)

ፈቃደ አዘዘ ፤ <u>የስነቃል መምሪያ።</u> አ.አ.ዩ የመፅሐፍት ማዕከል፣ አዲስ አበባ፣ 1991 ዓ.ም.።

Atkinss Harry. <u>A Geography of Ethiopia</u>. Sim Printing Press, Addis Ababa, 1970.

Beals , Ralph and Hojjer, L (8th ed ) . <u>Introduction to Anthropology.</u> New York. Loss Angeles. University of California. The Macmillan Company Ltd. 1959

Ben Amos Dan. <u>Folklore in Context</u>. South Asian publishers, New Delhi Madras, 1982.

Dorson ,Richard M. <u>Folklore and Folk life: An Introduction.</u> Chicago , London, The university of Chicago press. 1972

______________ .<u>Hand Book of American Folklore .</u> Bloomington . Indiana University press,1983.

Elisabeth Dorothea Hecht. " The City of Harer and traditional Harer houses". <u>Jornal of Ethiopian Studies.</u> Vol, 15,pp.57-78, 1982.

Fekadu Gedamu. "The Gurage House: Its Construction and Socio-Economic Significance". <u>In Proceedings of the 6th International Conference on the History of Ethiopian Art</u>. Addis Abeba: Addis Ababa University 2003.

Fletcher, H. <u>Techniques of the world's Great Masters of Pottery and Ceramic</u>. Oxford: Quarto Publishing Limited. 1984.

Foster I.LL. and L.Alcock(ed).<u>Culture and Environment</u>.Routledge and Kegan Paul,London,1963.

Freeman, Dena and pankhurst Alula. <u>Living on the edge Marginalized Minorities of Craft Workers and Hunters in Southern Ethiopia.</u> Department of Social and Social Administration. Addis Ababa University. 2001

Girma Kidane, "The traditional ways of building houses with in Wolayta society". <u>In papers the 12th international conference of Ethiopian studies</u>. The Red Sea Press inc: Michigan state University, 1994.

Glassie,Henry . <u>Material culture.</u> Bloomington , Indiana University Press, 1991.

Graves, M.W. "Pottery Production and Distribution among the kalaing: and differentiation" in w.a. longacred, <u>In ceramic Ethino archaeology Tucson</u>: the University of Orizona Press. 1991.

Hallpike C.R. "The Statues of the crafts men". The Konso of Ethiopia a study of values of Cushtic People. Oxford, at the Clarendon press,1972.

Hodges, H. Artifacts an Introduction to early Materials and Technology. London. Gerald duck worth and co.ltd. 1989.http:// www. En. Wikipedia. Org / wiki / "culture". 2007.

Jones, Michael Owen. (ed). putting Folklore to use. The university press of Kentucky. 1994.

------------------- "Concepts and Perspectives in folk art and material culture" Hand book of American folklore. Bloomington . Indiana University press. 1972

Judith Olmsteade. "The Dorze house: a Bamboo Basket". Jornal of Ethiopian Studies. Vol. 10,N° 2, pp 27-36,1972.

Kenneth, L. Ames. " Meaning in Artifacts: Hall Furnishings in Victorian America." In Journal of Intrdisciplinary Histroy. Vol. ix; No.1,pp.19-46.1978.

Macdonald, Donald A. "Field work: collecting oral literature" in Richard Dorsen (ed.) folklore and folklife: An introduction. Chicago and London: the university of Chicago press. 1972.

Makonnen W. Amlak "Influence of climate and tradition on building materials and methods in Ethiopia." Rilem. N° 24. September. Pp 109-113. 1964.

Muluneh Woldtsadik. "Introduction to climate: Reference material." AAU. Bahir Dar teachers Collage. 1986. (Unpublished ).

Oring, Elliott. Folk Genrs and folkore Genres: An Introduction. utah state University press, logan utah.1986.

Rahel Mesfin Leikun. " Zege and it's coffee local livelihoods and natural resource utilization in north west Ethiopia: the case of Zege pensula." Department of anthropology, MA Thesis . Addis Ababa University. 1999.(unpublished)

Rice, M. Pottery analysis: Book .Chicago University of Chicago press. 1975.

Richard and Rita pankhurst . "History and the Art published in Ethiopia and Britain". Ethiopian observer (journal of independent opinion. economic. History and the art. Published in Ethiopia , Vol. VIII, N° 3. 1964.

Silverman A. Raymond. Ethiopian Tradition of Creativity . University of Washington press. Michigan state university Museum. 1999.

Somajee Sultan .Material Culture of Kenya. East African Educational Publishers,Nairobi. 1993.

Susan W. fair "glossary" http:// www.elearn . 2002.

The Encyclopedia of Americana. International edition "culture" vo,12 Groler incorporated, International head quarters Danbury, pp. 315,1983.

Tolstykh v.e. "The policy of the state of Ethiopia in the spare of industrial development". Proceeding of the 9th international congress of of Ethiopian studies. Moscow: Nauka publisher. 1988.

Williamis, t.r., Field methods in the study of culture. USA. Holt,Rinehart and Winston inc, 1967

## አባሪ 1

## ከመስክ ስራ በፊት ተዘጋጅተው ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ

## ጥያቄዎች

1. ዘጌ እንዴት ስሟን አገኘች ?
2. በሰላጤዋ ውስጥ ምን ምን የሚባሉ ባህላዊ ቤቶች አሉ ?
3. ባህላዊ ቤቶች ከመቼ ጀምሮ መሰራት ጀመሩ?
4.የባህላዊ ቤቶች አሰራር ምን ቅደም ተከተል አለው ?
5. ባህላዊ ቤቶችን የሚሰራ ማን ነው?
6. የባህላዊ ቤተ ሰሪዎች ቤት ለሰሩበት ምንይከፈላቸዋል?ደረጃቸውስ ምን ያህል ነው?
7.ከቤቶች ጋር የተያያዙ ባህላዊ ድርጊያዎች፣ልማዶች፣እምነቶች፣ስነቃሎች አሉ?
8.ዛሬ ባህላዊ ቤቶች ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል?
9.ከባህላዊ ቤቶች የተሻለ ጥቅም ለማግኘት ምን ቢደረግ ይሻላል?
10.በሰላጤዋ ውስጥ ምን ምን የሚባሉ የሸክላ እቃዎች አሉ?
11.የሸክላ ስራ መቼ ወደ ሰላጤዋ ገባ ?
12.የሸክላ ስራ ምን ቅደም ተከተል አለው ?
13. ሸክላ የሚሰራ ማን ነው?
14. ሸክላ ሰሪዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የተለየ ደረጃ አላቸው?
15. ከሸክላ ስራ ጋር የተያያዙ ልማዶች፣እምነቶች፣ስነቃሎች አሉ?
16. ዛሬ የሸክላ ቁሶችና የሸክላ ስራ ሙያ ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል ?
17.የሸክላ ስራ አሁን ካለበት የተላቀ ጥቅም እንዲሰጥ ምን ቢደረግ ይሻላል ?

አባሪ 2

መረጃ አቀባዮችና ዝርዝር መግለጫ

| የአቀባይ ሁኔታ መረጃ | | | | | | | የመረጃው አይነትና አሰባሰብ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | የት/ደረጃ | አድራሻ | ስራ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | ርዕሰ ጉዳይ | መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ | መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ |
| 1 | ቄስ ገበዝ ይሄይስ እንግዳዉ | ወ | 70 | የቤተክህነት ት/ት | ጋሚ | ጡረተኛ | 25--8-1999ዓ.ም 3-2-2000ዓ.ም | ስለአሳተከላ ቤት አሰራር | ቴፐ ሪከርደር | በአረቂ ቤትና በመኖሪያ ቤት |
| 2 | መርጌታ ወርቁ ደበበ | ወ | 68 | የቤተክህነት ት/ት የመፅሐፍ መምህር | መሃልዘጌ በትረ ማርያም | የበትረ ማርያም ቤ/ክ የመፅሐፍ መምህር | 25-9-1999ዓ.ም 26-9-1999ዓ.ም | ስለአሳተከላደርብና ምድርቤት አገልግሎት፣ተምሳሌታዊ ትርጉምናስለህላዊየቤ ዕቃዎችታሪክ | ቴፐ ሪከርደር | በመኖሪያ ቤት |
| 3 | ወ/ሮ ሰገነት አሸተ | ሴ | 75 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | መሃል ዘጌ | የቤት እመቤት | 26-9-1999ዓ.ም | ስለአሳተከላ:ደርብና ምድርቤት ክፍሎች አገልግሎት | ቴፐ ሪከርደር | በመኖሪያ ቤት |


| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | አቶ ጀመረ ክብረት | ወ | 60 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | መሃል ዘጌ | አሳ አስጋሪ | 27-9-1999ዓ.ም | ስለባህላዊ ቤቶች አሰራር፣ እድሜናየወደፊት ዕጣፈንታ | ቴፕ ሪከርደር | በመኖሪያ ቤት |
| 5 | ወ/ሮ ስንታየሁ እድሜነዉ | ሴ | 60 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | አፋፍ | ነጋዴ | 7-9-1999ዓ.ም | ስለ አልባሶ የሳር ቤት | ማስታወሻ ደብተር / ቪዲዮ/ፎቶ | በመኖሪያ ቤት |
| 6 | አቶ ዋሴ እንየዉ | ወ | 38 | በቀድሞው የትምህርት ፖሊሲ 9ኛ ክፍል | ኡራ | አስጎብኝ | 26-8-1999ዓ.ም | ስለ እሳተከላና ደርብና ምድር ቤት አሰራርና እድሜ | ቴፕ ሪከርደር | በስራ ቦታ |
| 7 | አቶ ወርቂ ተባባል | ወ | 42 | በቀድሞዉ የትምህርት ስርዓት 9ኛ ክፍል | ጋሜ | አናፂ | 27-8-1999 ዓ.ም | ስለ ጎጆ ቤት አሰራር ሂደት፣የድግስ አስፈላጊነት | ቴፕ ሪከርደር | በሻይ ቤት በመኖሪያ ቤት |
| 8 | አቶ አለሙ ታዬ | ወ | 55 | 12⁺²(ዲፕሎማ) | ይጋንዳ | የዘጌ ማዘጋጃ ቤት ኃላፊ | 27-8-1999ዓ.ም | ስለቤትስራማህበራዊነት፣ ስለሸክላ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ | ቴፕ ሪከርደር | በስራ ቦታ |
| 9 | አቶ ግርማ ይታየዉ | ወ | 42 | የቤተክህነት ትምህርት ተምረዋል | አፋፍ | የቀን ስራተኛ | 28-8-1999ዓ.ም 29-8-1999ዓ.ም 17-2-2000ዓ.ም | ስለአልባሶና ክፍክፍ ቤትአሰራር | ቴፕ ሪከርደር ቪዲዮ/ፎቶ | በስራ ቦታ |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | አቶ በለጠ ወርቁ | ወ | 65 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | አፋፍ | ቤት መራጊ | 28-9-1999ዓ.ም | ስለ ቤት መምረግ | ማስታወሻ ደብተር | በጠላ ቤት |
| 11 | እሙሀይ ወለላ | ሴ | 80 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | ጋሜ | የቤት እመቤት | 5-9-1999ዓ.ም | ከቤቶች ጋር ስለተያያዙ ሃገረሰባዊ እምነቶች | ቪዲዮ | በመኖሪያ ቤት |
| 12 | አቶ ይህአለም ታደሰ | ወ | 42 | በቀድሞዉ ስርዓተ ትምህርት 12ኛ ክፈል | አፋፍ | ወፍጮ ቤት ሰራተኛ | 29-9-1999ዓ.ም | ስለባህላዊ ቤቶ አይነቶች | ማስታወሻ ደብተር | በመኖሪያ ቤት |
| 13 | አቶ ጉዳይ ሙጪ | ወ | 68 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | አፋፍ | ልብስ ሰፊ | 25-2-2000ዓ.ም | ከሸክላ ስራ ጋር የተያያዙ ስነቃሎች | ማስታወሻ ደብተር | በስራ ቦታ |
| 14 | ሊቀረድ ፅጌ ገነት | ወ | 70 | የቤተክህነት ትምህርት | ኡራ | ጡረተኛ | 30-9-1999ዓ.ም | ስለደርብና ምድርቤት | ማስታወሻ ደብተር/ፎቶ | በመኖሪያ ቤት |
| 15 | ወ/ሮ አንጓች አንባዬ | ሴ | 50 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | አፋፍ | ሸክላ ሰሪ | 30-8-1999ዓ.ም | ስለ ሸክላ ስራሂደት ፣ስለሸክላስራባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ | ፎቶ/ቴፕ ሪከር ደር /ማስተወሻ ደብተር /ቪዲዮ | በስራ ቦታ |
| 16 | ወ/ሮ ጨዶ ሙጨ | ሴ | 30 | በቀድሞዉ ስርዓተ ትምህርት 12ኛ ክፍል | ሰጎዳ | ሸክላ ሰሪ | 10-2-2000ዓ.ም | ስለ ሸክላ ስራሂደትና ስመዳ | ቪዲዮ/ፎቶ | በስራ ቦታ |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | ወ/ሮ አናት ብርሃኑ | ሴ | 55 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | ሰጎዳ | ሸክላ ሰሪ | 17-2-2000ዓ.ም | ስለ ሸክላ ስራሂደትና ስመዳ | ማስታወሻ ደብተር /ፎቶ | በስራ ቦታ |
| 18 | ወ/ሮ ታሪክ ገነት | ሴ | 60 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | ጋሚ | ሸክላ ሰሪ | 10-2-2000ዓ.ም | ስለ ሸክላ ስራሂደት፣ ስለሸክላ ስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ | ማስታወሻ ደብተር | በስራ ቦታ |
| 19 | ወ/ሮ ፈንታ ገነት | ሴ | 58 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | ጋሚ | ሸክላ ሰሪ | 17-2-2000ዓ.ም | ስለ ሸክላ ስራሂደትና ስመዳ | ማስታወሻ ደብተር | በስራ ቦታ |
| 20 | ወ/ሮ በተሃ ካሣ | ሴ | 50 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | ጋሚ | ሸክላ ሰሪ | 28-8-1999ዓ.ም 23-2-2000ዓ.ም | ስለ ሸክላ ስራሂደትና ስመዳ | ቪዲዮ/ቴፕሪከርደር /ፎቶ | በስራ ቦታ |
| 21 | ወ/ሮ ምንትዋብ እንተሁን | ሴ | 28 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | አፉፍ | ጠላ ንግድ | 5-2-2000ዓ.ም | ስለ ሸክላ ስራሂደትና ስመዳ | ማስታወሻ ደብተር | በስራ ቦታ |
| 22 | ወ/ሮ ማሬፊያየ ወርቂ | ሴ | 55 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | ሰጎዳ | ሸክላ ሰሪ | 27-1-2000ዓ.ም | ከሸክላ ስራ ጋር የተያያዙ እምነቶች | ቴፕ ሪከርደር/ፎቶ | ገበያ/በስራ ቦታ |
| 23 | ወ/ሮ መሰረት ገብሬ | ሴ | 25 | ፭ኛ ክፍል | ሰጎዳ | ሸክላ ሰሪ | 6-2-2000ዓ.ም | ከሸክላ ስራ ጋር የተያያዙ ስነቃሎችና የሸክላስራ ሂደት | ማስታወሻ ደብተር /ፎቶ | በስራ ቦታ |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 24 | ወ/ሮ መሰረት ጓዴ | ሴ | 23 | 5ኛክፍል | ሰጎዳ | ሸክላ ሰሪ | 5-2-2000ዓ.ም | የሸክላስራ ሂደት | ማስታወሻ ደብተር | በስራ ቦታ |
| 25 | ወ/ሮ ዘርትሁት አስማረ | ሴ | 46 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | ሰጎዳ | የቤት እመቤት | 3-9-1999ዓ.ም | ስለባህላዊ ቤቶች ምን ያህልነት ስለክፍሎቻቸው መጠንና ተግባር | ቴፕ ሪከርደር | በስራ ቦታ |
| 26 | ወ/ሮ እናትትሁን ተባባል | ሴ | 38 | በቀድሞዉ ስርዓተትምህ ርት 9 ክፍል | ጋሚ | ነጋዴ | 4-9-1999ዓ.ም<br>2-2-2000ዓ.ም | ስለሸክላስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ ፣ከሸክላ ስራ ጋር የተያያዙ እምነቶች | ቴፕ ሪከርደር | በመኖሪያ ቤት |
| 27 | ወ/ሮ ይታይሽ ሁነኛዉ | ሴ | 40 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | ጋሚ | ነጋዴ | 3-2-2000ዓ.ም | ከሸክላ ስራ ጋር የተያያዙ እምነቶች | ማስታወሻ ደብተር | በመኖሪያ ቤት |
| 28 | ወ/ሮ ትሁን ብርሃኑ | ሴ | 55 | ማንበብና መፃፍ አይችሉም | አፋፍ | ሸክላ ሰሪ | 4-2-2000ዓ.ም | ስለሸክላስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ፣ ከሸክላ ስራ ጋር የተያያዙ እምነቶች | ማስታወሻ ደብተር | በመኖሪያ ቤት |
| 29 | አቶ ጌጤ በርሄ | ወ | 60 | የቤተክህነት ትምህርት ተምረዋል | መሃል ዘጌ | አሣ አስጋሪ | 24-9-1999ዓ.ም | ስለባህላዊ ቤቶች አሰራር፣ከባህላዊ ቤቶች ጋር የተያያዙ እምነቶች | ማስታወሻ ደብተር | በመኖሪያ ቤት |
| 30 | ምስለኔ ተመስገን አለሙ | ወ | 70 | የቤተክህነት ትምህርት ተምረዋል | መሃል ዘጌ | ጡረተኛ | 23-9-1999ዓ.ም | ስለባህላዊ ቤቶች አሰራር፣ከባህላዊቤቶች ጋር የተያያዙ እምነቶች | ማስታወሻ ደብተር | በመኖሪያ ቤት |


# አባሪ 3




1.የጎጆ ቤት ጣሪያና ግድግዳ



2..ለሳር መክደኛ የሚያገለግል እንጨት ሲቆረጥ



3. ክፍክፍ ቤት ሲከደን




4. የእሳተ ከላ ቤት በር





6. የፈረስ እሳተ ከላ ቤት




7. የሸክላ ቁስ(ጀበና) ሲሰራ




8. የሸክላ ቁሶች ለመቃጠል እየተዘጋጁ




9.የሸክላ ቁሶች ወዲያውኑ ተቃጥለው እንዳበቁ




10.ማዲጋ ወደ ገበያ እየተወሰደ




11. የሸክላ ቁሶች(ጀበና) በገበያ ላይ

<u>መግለጫ</u>

ይህ ቴሲስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ) የእኔ ወጥ ስራ (Original work) ሲሆን፣ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የድግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም:: ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ::

እለቴፍ ሙላ

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የካቲት፣2000 ዓ.ም